
# የብርሃን እናት

2ተኛ ዕትም



ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

በአብ፡ ስም፡ አምኜ፡ አብን፡ ወላዲ፡ ብዬ፡ በወልድ፡ ስም፡ አምኜ፡ ወልድን፡ ተወላዲ፡ ብዬ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ አምኜ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ሠራፂ፡ ብዬ ምንም፡ ለአጠይቆ፡ አካላት፡ ሦስት፡ ብል፡ በባሕርይ፡ በህልውና፡ አንድ፡ አምላክ፡ ብዬ፡ አምኜ፡ ረድኤተ፡ እግዚአብሔርን፡ አጋዥ፡ በማድረግ የመድኃኔ ዓለምን፡ የእናቱን፡ ነገር፡ የሚናገርን፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡ መጻፍ፡ እጀምራለሁ፡ ፡

# የብርሃን እናት

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

፳፻፲፬ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ISBN 978-99944-3-518-0

<u>የአዘጋጁ ቀደምት መጻሕፍት</u>

ክብረ ክህነት (ጥር 1999 ዓ.ም) ፡ ቅዱስ ገብርኤል (ጥር 2000 ዓ.ም) ፡ ታቦት በሐዲስ ኪዳን (ነሐሴ 2001 ዓ.ም) ፡ ቅዱስ ሐቢብ ጊዮርጊስ /ትርጉም/ (ነሐሴ 2003 ዓ.ም) ፡ ተግባራዊ ክርስትና /ትርጉም/ (ኅዳር 2004 ዓ.ም) ፡ መንፈሳዊ አገልግሎት ፤ በመማርና ማስተማር (የካቲት 2005 ዓ.ም) ፡ ከሞት ባሻገር (ጥር 2008 ዓ.ም) ቃና ዘገሊላ (ጥር 2007 ዓ.ም) ፡ የግዮን ወንዝ (ዐቢይ ጾም 2014 ዓ.ም.)

yebirhanenat@gmail.com

እናቱን መርጦ ለተወለደው ድንቅ ሕፃን ፣ መቅደሱን መርቶ ለገባው ኃያል አምላክ ፣ ፍጡር ሆኖ ፈጣሪዋን እንድትወልድ ላበቃት ክህሎ ፣ በምሴተ ሐሙስ የሐዋርያትን እግር ላሰጠጋውና በዕለተ ዐርብ ያቀፈውን የሐንስ እቅፍ ላላደገችው አደራ ለሰጠው ፣ የእናትነት ቃሏዋን ሰምቶ የታናውን ውኃ ወደ ወይን ፣ የእኛን ሞት ወደ ሕይወት ለለወጠው የሚናገር በግ ፣ በግርፋቱ ከአጋንንት ግርፋት ላዳነን ፣ ነፍሱን እስከመሥዋዕት ለወደደን ከኃጢአታችን በደሙ ላጠበን ሊቀ ካህናት ፣ በሚያልፍ ወርቅ ሳይሆን በክቡር ደሙ ለገዛን ባለጸጋ ፣ በጎኑ ውኃ ተጠምቀን ፣ ክቡር ሥጋውን በልተን ፣ ቅዱስ ደሙን ጠጥተን ለምንኖርበት የሕይወት እንጀራችን ፣ ለምንገነባበት መንገዳችን ፣ ለምንቀመጥበት መርከባችን ፣ ለምናርፍበት ወደባችን ፣ ለምናይበት ብርሃናችን ፣ ሁሉ በእርሱ ፣ ከእርሱ ፣ ለእርሱ ለሆነ

ለአማልክት አምላክ ለጌቶች ጌታ ለነገሥታት ንጉሥ

ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁንልኝ።



'በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን በሰማይ አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ' ብሎ የገባውን ቃልኪዳን አምኜ እኔን ኃጢአተኛውን ባሪያውን (ተክለ ማርያምን) ዳግም ሲፈርድ ሲመጣ በመንግሥቱ እንዲያስበኝ በቀኙ እንዲያቆመኝ ፣ የወንጌት ያቴታል በተባለው ቀን በኃጢአት የወጋሁት እኔ ባሪያውን እንዲምረኝ ብዬ ተስፋ ስላደረግሁት ይህችን መጽሐፍ ራሴን ከምወድደው በላይ ለሚወድደኝ ፣ ታውን መግቦ ፣ በመልአኩ አስጠብቆ ፣ ይቅርታውን አልብሶ ላሳደገኝ ፣ በቁስሉ ቁስሌን ለፈወሰ ደሜን በደሙ ላነጻ ፣ ድካሜን አይቶ የእናቱን ፍቅር ላሳደረብኝ ለመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ አድርጌያታለሁ:: ነገሥታት ዘውዳቸውን የሚጥሉልህ ፣ ወታደሮች ትጥቃቸውን የሚፈቱልህ ፣ መነኮሳት በፍቅርህ የመነኑልህ ፣ ሰማዕታት ስምህን እየጠሩ የተሠዉልህ ፣ የዘወትር ቅዳሴያችን የሆንህ ጌታ ሆይ የፍቅርህን መዓዛ አሽትተው ነፍሳት ሁሉ ወደ አንተ ይመለሱ:: የማያውቁህ ሁሉ አንተን ወደማወቅ ይድረሱ::

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ወሕይወት ኮሉ ዓለም
እመሰ አነ እትጋገል ለምንት ተወለድከ እግርያም ቅድስት ድንግል ወተሰብእከ በእንቲኣየ።
ስምህ የጣፈጠ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እኔ የምጠፋ ከሆነ ከቅድስት ድንግል ማርያም
ለምን ተወለድህ ስለምንስ በሥጋችን አደግህ?

ረቂቁን አንብበው ያረቁ ሊቃውንትና መምህራን

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መልአከ
መ/ጌ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማኅሩ
ቀሲስ ታምራት ውቤ
ዲያቆን አቤል ካሣሁን

የለቀማ ንባብ (Proof reading)
ዲያቆን ደጀኔ ኮርሳ /ሳቢቴን/
ዲያቆን ዳዊት ከበደ /ዶ/ር/
ዲያቆን ኤልያስ ግዛሌ

የሽፋን ዲጂታል አርትና ዲዛይን
ማራኪ ገርማ

የርእስ ፎንት ዲዛይን
ለዓለም እሸቱ

የብራና ሥዕልና ሐረግ ስኬች
ቤተእብ ዓለሙ


ምስጋና

በሕይወታቸው ላልተለዩኝ ገዳማውያን አበው እና ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ትውልድ ልጆች ሁሉ
እንዲሁም ከራሴ በላይ ለሚጨነቁልኝ ለውድ ጓደኞቼ
ማኪዳ ደገረው ፤ አቤል ገብረ ጻድቅ ፤ ሽዊት የማነ ፤ ሰሎሞን ኃይለ መለኮት ፤
ቢዛዊት ታጠት ፤ ዶ/ር ዳዊትና ዶ/ር ቶማስ ፤ ለሣምራዊትና ዶ/ር ቢቲ ፤ ለሬሽን ድሬ ፤
ሶልያናና ምሕረት ፤ ዛቲ መታፈሪያ ፡

# የፊት ገጽ ሥዕል ማብራሪያ

የሐሳቡ መነሻዎች ፡-

ስለ ሰው ልጅ ድቀትና ትንሣኤ (fall and restoration) ሔዋንና ድንግል ማርያምን በማነፃፀር ያስተማረው የሰማዕቱ ዮስጦስ ትምህርት ፣ ኤልሳቤጥና ድንግል ማርያም የተገናኙበት በዓይነ ከርም የሚገኘው እመቤቶችን ዐንሳ የተመቸበት የግድግዳ ሥዕል ፣ Mary and Eve የተሰኘው የSr. Grace Remington የሥዕል ሥራ ፣ The Tree of Life Icon mentioned in Jordan Peterson's lecture

## የሥዕሉ አሳብ

በሥዕሉ ላይ የሚታየው አረንጓዴ ሥፍራ የሰው ልጅ ይኖርበት ዘንድ የተሠጠውን ዔድን ገነትን የሚያሳይ ሲሆን በስተ ግራ በኩል ያለው ዛፍ የዕፀ በለስ ዛፍ ነው:: በዛፉ አጠገብ ቆማ የምትታየው ኀዘንተኛ ሔዋን ስትሆን ከዛፉ ፍሬ ቀጥፋ በልታ በእጇዋ ይዛ ትታያለች:: ኀዘንዋ ከውድቀት በኋላ ያለችበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ዕርቃንዋን በበለስ ቅጠል መሸፈንዋ ደግሞ በዛፉ ፍሬ ምክንያት የሰው ልጅ ጸጋ መገፈፉን የሚያሳይ ነው:: በሔዋን እግር ሥር የተጠመጠመው ዕባብ ደግሞ የሰይጣን አንደበት ሆኖ ያሳታት ዕባብ ሲሆን በእርሱ ክፉ ምክር ተጠልፋ መውደቅዋን የሚገልጽ ነው:: ከሴቲቱ እግር ሥር ያለው አጽም ደግሞ ከውድቀት ውጤት አንዱ የሆነው ሞት በሰው ልጅ ላይ መምጣቱን የሚያሳይ ነው።

በስተቀኝ በኩል ቆማ የምትታየው ሁለተኛይቱ ሔዋን የብርሃን እናት ድንግል ማርያም ስትሆን በሔዋን ላይ በዛፍ ፍሬ ምክንያት የተፈረደውን ፍርድ በማሕፀንዋ ፍሬ እንዳስወገደች የሔዋንን እጅ ወደ ፀነሰችው ብርሃን እየሳበች ስታጽናናት የሚያሳይ ነው:: በእግርዋም የዕባቡን ራስ በመርገጥ 'በእባቡና በዘርዋ' መካከል ጠላትነት መሆኑንና ልጅዋ የእባቡን ራስ መቀጥቀጡን የሚያሳይ ነው። በድንግል ማርያም በኩል ያለው የስንዴ ዛላና የወይን ዛፍ ደግሞ በዕፀ በለስ ፈንታ ከእርስዋ የተገኘውን ዕፀ ሕይወት የተባለ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሚወክል ነው።

ልዩ ምስጋና ፦ ሥዕሉን ከአራት ወራት በላይ እንደ አየሩ የሚቀያየሩ ሃሳቦቼንና እርማቶቼን ታግሦ ደጋግሞ ደጋግሞ ለሠራልኝ ዲጂታል አርቲስት ማራኪ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

መታሰቢያና ምስጋና (3-4)
የመጽሐፉ የፊት ሽፋን ሥዕል መግለጫ (5)
ግውጫ (6-7)

## ምዕራፍ አንድ

## የገነት ስደተኞች


- የሚጎዳ ማሰሪያ (8)
- የእግዚአብሔር እንግዳ (15)
- የነፃነት እስረኞች (26)
- የሰማዩ ይሁዳ (46)
- ወዳቂና ተነሽ (60)
- ከበለስ በታች አየሁህ (70)
- ስምን አዳም ያወጣዋል (95)
- የሔዋን መድኃኒት (109)


## ምዕራፍ ሁለት

## የምሕረት አዋጅ


- ፍርድ ወይንስ ፍትር (121)
- የአርያም ንስር (137)
- ደስ ይበልሽ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበልሽ (153)
- ጸጋን የተሞላሽ ሆይ (173)
- መልስ አልባ ጥያቄ (187)
- የአብርሃም ድንኳን (208)
- የፍጥረት ናፍቆት (232)

ምዕራፍ ሦስት

## ከፀሐይ አጠገብ የነበረው ኮከብ (257)

ምዕራፍ አራት

## የጻድቃን ቀጠሮ

- ፈጥና ወጣች (286)
- ያልተወለደው ባለ ቅኔ (296)
- መዝሙረ ድንግል (308)
- ያመነች ብፅዕት (325)
- ብፅዕትና ብሁዓን (340)
- ነቢይት ማርያም (347)
- የዝምተኛዋ ንግግሮች (365)
    - ነፍሲ እግዚአብሔርን ታላቅ ታደርገዋለች (369)
    - መንፈሲም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል (375)
    - የባሪያይቱን መዋረድ አይቶአልና (378)
    - ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል (380)
    - ታላቅ ሥራን ለእኔ አድርጎአል (394)
    - ስሙ ቅዱስ ፤ ምሕረቱ ለልጅ ልጅ (396)
    - ኃይልን በክንዱ አደረገ (399)
    - ለአብርሃምና ለዘሩ (405)

ስለ የብርሃን እናት የተሠጡ የመምህራን ቤተ ክርስቲያን አሳቦች (412)

ለመጻፍ የተነበቡ መጻሕፍት (423)

፩

# የገነት ስደተኞች

## • የሚጎዳ ማሠሪያ

የኦሪት ዘፍጥረትን ሦስተኛ ምዕራፍ ያህል በሰው ልጅ ላይ ትልቅ ጠባሳ የጣለ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የለም፡፡ ሔዋን በዕባብ ተንኮል የሳተችበትና የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ በልታ ለባልዋ ያበላችበት ታሪክ የሰው ልጅን ታሪክ ሙሉ በሙሉ የለወጠና ከዚያ በኋላ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይዘት የወሰነ የዕዳ ደብዳቤ ነው፡፡ ያ ምዕራፍ ብዙ ብዕረኞች ሴት ልጅን ከሰይጣን በጥቂቱ ብቻ የምትሻል አድርገው እንዲስሏትና ሁሉም የቻለውን ያህል ለክፍለ ዘመናት የዘለቀ የወቀሳ ቅኔ እንዲቀኙባት መንገድ የጠረገ ታሪክ ነው፡፡

በእርግጥ ሔዋንን መሆን ምንኛ ከባድ ነው? አንድ ቀን ቀጥፋ በበላችው ዕፀ ምክንያት ብዙ ነፍሳት በሞት እንደሚቀጠፉ ማሰብስ ለሔዋን ምንኛ አስጨናቂ ነው? እነዚያ ነፍሳት ከእርስዋ የተወለዱ እናቴ የሚሏት ልጆችዋ መሆናቸውን ማሰብስ ምንኛ ያስታያት ይሆን? ምናልባት ሔዋን ዕፀ በለስን በበላችበት ቀን አጣጥማው ጣፍጦአትም ላይሆን ይችላል፡፡ ግን በዚያች ዕፀ ምክንያት ለልጆችዋ መራራ ሞትን እንዳጎረሰች ማሰብ ለሔዋን እስከ ዕለተ ሞትዋ ድረስ የመረር ጉዞንዋና የዕንባዋ ምንጭ ነበር፡፡[1]

የሔዋን ጭንቀትና የጥፋተኝነት ስሜት ከሞተች በኋላም የምትገላገለው ነገር አይደለም፡፡ ወደ ሲኦል ከወረደችም በኋላ ባለጠጋው ነዌ አብርሃምንና አልዓዛርን ባየበት ዓይን በአፀደ ነፍስ ሆና የምታየው ነገርም ለእርስዋ ማንም ሰው ላይ ከደረሰው በላይ ቅጣት ነው፡፡ ሉቃ. ፲፮፥፳፫ ከእርስዋ ቀድሞ በግፍ ተገድሎ የሞተው ንጹሕ ልጅዋ አቤል ብቻውን ወደ ሲኦል የወረደው እርስዋ በበላችው ዕፀ ምክንያት ነበር፡፡ ሔዋን በሞተችበት ዕለት ወደ ሲኦል ወርዳ አቤልን ስታገኘው ምን

[1] 'አዳም ወሔዋን ይበክዩ በእንተ ሰብአ ዓለም እስመ ውሉዶሙ እሙንቱ' እንዲል ገድለ ክርስቶስ ሠምራ ዘታኅሣሥ ቁ. ፳

ተሰምቶአት ይሆን? ንጹሕ ልጅዋ አሟሟቱ ሳያንሰው በእርስዋ ምክንያት ሲኦል መገኘቱን ማየት በራሱ ለሔዋን ሌላ ሲኦልዋ ነው፡፡

'እግዚአብሔር በደይን ለጣላት ሔዋን የሚጎዳ ማሠሪያዋ' ከሲኦል መውረድዋ በላይ ብዙ ንጹሐን ሰዎች በእርስዋ ጥፋት ወደ ሲኦል ሲወርዱ ማየትዋ ነበር፡፡ እንኳንስ ሲኦል ቀርቶ ምድራዊ እስር ቤት ውስጥም ቢሆን በእኛ ጥፋት ሰዎች እየታሰሩ ሲገቡ ማየት እጅግ ያስጨንቃል፡፡ ሔዋን ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በሲኦል ሆና የልጅ ልጆችዋ ሁሉ ወደ ሲኦል ሲመጡ እያየች ተሠቃይታለች፡፡

ያ ጨካኝ ባለጠጋ ስንኳ ላልሞቱ ወንድሞቹ ራርቶ 'ወደዚህ የሥቃይ ሥፍራ እንዳይመጡ' ብሎ ከተጨነቀ ሔዋን ስለ ገዛ ልጆችዋ ምንኛ ትረበሽ ይሆን? ሉቃ. ፲፮፥፳፰ ቅዱሳን ሆነው የኖሩት ያለጥፋታቸው ወደ ሲኦል ሲመጡ ፤ በእርስዋ ምክንያት በኀሰቀለው ባሕርያቸው ኃጢአት የሠሩ ልጆችዋም ወደዚያ 'የሥቃይ ሥፍራ'[2] ሲወርዱ በመመልከትዋ 'ይህ ሁሉ እኮ በአንቺ ምክንያት ነው' የሚለው የሕሊና ወቀሳ ከሲኦል መውረድዋ በላይ የሚጎዳት ማሠሪያዋ ነው፡፡

---

[2] "እርሱም፦ እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰድደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ' ሉቃ. ፲፮፥፳፰

በምድር ያለን ልጆችዋስ ብንሆን ሔዋንን መቼ ተውናት? 'ሔዋን ሆይ ምን አደረግንሽ? በሰማያውያን አምሳል እንኖር እንዳልነበርን እነሆ ሥጋችን በኃጢአት ምክንያት ጠቆረ' 'ኦ፡ሔዋን፡ምንተኑ፡ረሰይናኪ፡ናሁ፡ጸልመ፡ሥጋነ፡በብዝኃ፡ኃጣውእ፡ዘእምነበርነ፡በአርአያ፡ሰማያውያን'፡ እያልን በቅዳሴያችን እናዜም የለምን?

ሴቶችንም ወክለን እንዲህ እናማርራታለን፡-

'ሔዋን ሆይ ምን አደረግንሽ? አንቺ በገነት ያለችውን ዕፀ እንዳደማሻት ዛሬ ሴት ልጆችሽ ይደማሉ። በሕማምና በምጥ ሲወልዱም ሴት ልጆችሽ ሁሉ ያለቅሳሉ"፡'ኦ፡ሔዋን፡ምንተኑ፡ረሰይናኪ፡ናሁ፡ይበክያ፡ኵሉን፡አዋልድኪ፡ሶበ፡ይወልዳ፡በፃዕር፡ወሕማም፡ወደዲሆሞዋ፡በከመ፡እድመውኪያ፡አንቲ፡ለእንትኩ፡ዕፀ፡ዘውስተ፡ገነት'[3]

ሔዋንን ለመውቀስ በሕይወት የሚገጥሙን ክፉ ገጠመኞች ሁሉ መነሻዎቻችን ናቸው፡፡ 'በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ' በሚለው የሔዋን እርግማን ምክንያት ሴቶች በወሊድ ምጥ ሲሠቃዩ በእርስዋ ጥፋት የመጣ ምጥና ሥቃይ መሆኑን አስታውሰው ይወቅሷታል፡፡

[3] ቅዳሴ አትናቴዎስ ፪፡፳፱

በየወሩ ደም በፈሰሳቸው ጊዜ በሚሰማቸው አካላዊ ሕመምና ሥነ ልቡናዊ ምቾት ማጣት ውስጥ ሆነው ሁሉም ያስታውሷታል::[4] የሚወድዷት ሰው በሞት የተለያቸው ሁሉ በመቃብሩ ዙሪያ ሆነው እያለቀሱና ደረታቸውን እየደቁ ስለ ሞት አመጣጥ ሲያስቡም ከአዳም መረገም ጋር የሚያስቧት የፈረደባት ሔዋንን ነው::

ሔዋን ሆይ አንቺ እንደ አምላክ እኖራለሁ ብለሽ እንደ ሰው መኖርን ያሳጣሽን ምን አደረግንሽ? እንደ እግዚአብሔር መሆን ያማረሽስ ምን ያህል ዘመን ሰው ሆነሽ ኖረሽ ታክቶሽ ነው? ሰው መሆንን

[4] የሚያጠቡ እንስሳት ሁሉ የወር ዑደት ያላቸው ሲሆን ይህ ዑደት ለመውለድ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ዑደት እንደመሆኑ የሴት ልጅ የወር አበባ ከሔዋን መረገምስ በፊት አልነበረምን? ከድቀት በፊት ይህ ዑደት ከሌለስ 'ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት' የተባለውን እንዴት ሊፈጽሙ ይችላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ:: የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት የሔዋን ወርኃዊ ዑደትን ምድርን ከሚያረሰርሰው ውኃ ጋር በማነፃፀር የሚያስቀምጡ ሲሆን ሔዋን ከእርግማን በፊትም የወር ዑደት እንደነበራትና ሆኖም በሰውነትዋ ውስጥ ብቻ የሚካሔድ እንጂ ውጪያዊ የደም መፍሰስ እንዳልነበራት ፡ በቤተ መቅደስ በምትመሰለው ገነት ውስጥ ሴቲቱ ምንም እድፍ እንዳልነበረባት ያስረዳሉ:: የወር አበባን ከእርግማን ጋር ያገናኘው 'በፀነስሽ ጊዜ ምጥሽን አበዛዋለሁ በጎዘን ትወልጂያለሽ' የሚለው ቃል ሲሆን ከእርግዝና ፡ ከወሊድ ጋር የተያያዙ ሕመሞችን ብቻ ሳይሆን ለሴት ልጅ መውለድ ወሳኝ ምልክት በሆነው በወር ዑደት ወቅትም የሚፈጠረውን አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ሕመም የሚያካትት ስለሆነ ነው:: (መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ፤ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፤ A Brief Theology of Periods, Rachel Jones) የሴትን ሕማም ያስወግድ ዘንድ 'የሕማም ሰው' ክርስቶስ ከተገለጠ በኋላ እንዴት ይህ ሥቃይ አልቆመም? ለሚለው ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ 'ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለን' ሮሜ ፰፥፳፪ እንዳለ የምንኖረው በወደቀ ዓለም እንደመሆኑ የእርሱ መምጣት ከዘለዓለማዊው ሞት ሊያድነን እንጂ በጊዜያዊነት የምንኖርባትን ድንኳን ምድር ወደ ገነትነት ሊለውጥ ስላልሆነ ነው::

እንድትሰለቺና የበለጠ ነገር እንድትፈልጊ የሚያደርግስ ከአዳም በቀር ያን ጊዜ ምን ያህል ሰው በገነት ውስጥ ነበረ?

አምላክነትን የሚያስመኝ ነገር ሆኖሽ በተፈጠርሽበት ዓለም የጎደለብሽስ ምን ነገር ነበረ? ገነት ውስጥ እየኖርሽ 'የምኖርበት ኑሮዬ ይበቃኛል' ማለትን እንዴት አልቻልሽም? የሰው ልጆች ሁሉ እናት የመሆን ክብር ተሠጥቶሽ ሳለ ለልጅ ልጆችሽ ሕመምና ሞትን ያወረስሽን ለምንድርን ነው? ገነትን ከምታህል ርስት ወጥተሽ በተረገመች ምድር የወለድሽንስ ለምንድርን ነው? የሚል የብዙ ትውልድ ጩኸት በሕሊናዋ ውስጥ የሚጮኽባት ሔዋን ብቻ ነበረች፡፡ ፩ ጢሞ. ፮፡፮

ሔዋን ከውድቀት በፊት የሰው ልጅ የነበረውን ጸጋ ጠንቅቃ የምታውቅ እንደመሆንዋ የሰው ልጆችን ምን እንዳሳጣችንም ከእኛ በላይ እርስዋ ታውቃለችና እኛ ከምንወቅሳት በላይ ልብዋ የሚቆስል ኀዘንተኛ ናት፡፡ ነፍስዋን የማያሳርፍ የነቢያት ልቅሶ ይረብሻታል፡-

> 'ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፡ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው ፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፡ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል' ፡ 'ሰማያትን ቀድደህ ምነው ብትወርድ' ፡ 'እጅህን ከአርያም ላክ' 'የእስረኞች ጩኸት ወደ ፊትህ ይግባ' የሚሉት የነቢያት

ጨኸቶች ከማንም ፍጡር በላይ ሔዋንን ያሳቅቃሉ፡፡

ኢሳ. ፳፯፥፩ ፤ኢሳ. ፳፯፥፯ ፤ መዝ. ፻፬፥፯ ፤መዝ. ፸፬፥፲፬

በዓለም ላይ የብዙ ሺህ ሰው ነፍስ ያጠፉና ያም ባይሆን ለብዙ ሰው መጥፋት ምክንያት የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ የሔዋንን ያህል ግን ለሞት መፈጠርና ለብዙዎች ነፍስ ጥፋት ተጠያቂነት የሚሰማው ሰው የለም፡፡ ለአቤል ሞት ምክንያት የሆነው ቃየን እንደዚያ ከተረበሸ ለአዳም ዘር ሞት መነሻ የሆነችው ሔዋን ምንኛ ትጨነቅ ይሆን? ለመሆኑ ለሔዋን የሺህ ዓመታት ጭንቀት ፤ ለሰው ልጆች የዘመናት ምሬት ምክንያት የሆነው የዘፍጥረት ሦስተኛ ምዕራፍ ታሪክ ምንድር ነው?

በእርግጥ የአንድን ዛፍ ፍሬ ቀጥፎ መብላት ይኼንን ያህል ዋጋ ማስከፈል ነበረበት? እግዚአብሔርስ ዛፉን ለምን ፈጠረው? ዛፉ መልካምና ክፉን እንድናውቅ የሚያደርግ ከሆነ እግዚአብሔር ክፉና ደግ እንዳንለይ ይፈልጋል ማለት ነው? ዛፉን ከበሉ በኋላ ዓይኖቻቸው ተከፈቱ 'መልካምና ክፉን በማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆኑ' ይላል፡፡ ታዲያ የዕባብ ምክር ልክ ነበር ማለት ነው? ሔዋንስ ምንም አላጠፋችም ማለት ነው? በቀጣዮቹ ገጾች እነዚህን የነፍስ ጥያቄዎች አብረን እንቃኛለን፡፡

## • የእግዚአብሔር እንግዳ

ንጉሥ ዳዊት

'ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ ጨረቃና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ታስበው ዘንድ ሰው ምንድርን ነው? ትጎበኘውስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?' 'አቤቱ፥ እርሱን ታውቀው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ታስብለት ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?' ይላል፡

፡ መዝ. ፰፥፫ ፤ ፻፵፬፥፫

ንጉሥ ዳዊት የሰማይን ርዝመት ፡ የፀሐይን ርኅቀት ፡ የጨረቃና ከዋክብት ውበትና ብዛት ሲያይ ቁመቱ ከሁለት ሜትር የማያልፈውን ደቃቁን የሰው ልጅ እግዚአብሔር ማስታወሱ ራሱ ደነቀው፡፡ እውነትም እኛ ካለንበት ጋላክሲ ውጪ ያሉትን እጅግ ብዙ ዓለማትና ድንቃ ድንቅ ፍጥረታት አስተውለን በተረዳን ጊዜ እግዚአብሔር ሥፍር ቁጥር ከሌለው ድንቅ ፍጥረቱ ሁሉ ለይቶ እኛን ያስታውሰን ዘንድ እኛ ምንድርን ነን? እንላለን፡፡

እኛን ሊጎበኝ እስከ አሳባችን ድረስ ሊመረምረን መፍቀዱስ የሰው ልጆች ምን ስለሆንን ነው? ጻድቁ ኢዮብ 'ታከብረው ዘንድ ልብህንስ ትጥልበት ዘንድ ሰው ምንድርን ነው?' እንዳለው እግዚአብሔር እኛን

ማወቁ ብቻ ራሱ እኛ የሰው ልጆች ምን ስለሆንን ነው ያሰኛል፡፡ የራሳችንን ጠጉር ሳይቀር በቁጥር ያውቀን ዘንድ እኛ ምንድር ነን? ክፉ ደግ መሥራታችንን በቀንና ሌሊት የሚከታተለንስ ምን ስለሆንን ነው? 'ማለዳ ማለዳስ ትጐበኘው ዘንድ፣ ሁልጊዜስ ትፈታተነው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?' ኢዮ. ፯፥፲፰

እጅግ ውስብስብና ግዙፉን የሆኑ የእልፍ አእላፋት ከዋክብትና የብዙ ሺህ ፀሐዮች ባለቤት ፣ እኛ የማናውቃቸው የብዙ ፕላኔቶች ፈጣሪ ባለ አጭር ቁመት ባለ ጠባብ ደረቶቹን እኛን ማየቱ ለምን ይሆን? በመጠንዋ ከሌሎች ብዙ ፕላኔቶች ከምታንሰው መሬት ላይ አፈር ዘግኖ የፈጠረውን ደካማ ፍጥረት ለቅጽበት እንኳን ዓይኑን ሳይነቅል መመልከቱ የሰው ልጅ ምን ስለሆነ ነው? ጻድቁ ኢዮብ እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል ፡- የማትተወኝ እስከ መቼ ነው? ምራቁንስ እስክውጥ ድረስ የማትለቅቀኝ እስከ መቼ ነው? ሰውን የምትጠብቅ ሆይ፣ በድዬስ እንደ ሆነ ምን ላድርግልህ? ስለ ምን እኔን ለአንተ ዓላማ አደረግኸኝ? ስለ ምን እኔ ሸክም ሆንሁብህ?" ኢዮ. ፯፥፲፰-፳

በዚህ ደረጃ ከንቱና ታናሽ የሆነው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር የትኩረት ማዕከል የሆነበት ምክንያት በአሪት ዘፍጥረት ላይ እንዲህ

በአጭሩ ተጽፎ እናገኘዋለን፡፡ 'እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈ
አበጀው' ዘፍ. ፪፥፯

ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል

'እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጀው' ከሚለው ቃል ውስጥ የሰው ልጅ ኢምንት መሆኑንም ታላቅ መሆኑንም እረዳለሁ። የተፈጠረበትን አፈር ብቻ ካየህ የሰው ልጅ ኢምንት ነው። የተፈጠረበትን ክብር ካየህ ግን የሰው ልጅ ታላቅ ነው''

በእርግጥም እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ጨረቃንና
ከዋክብትን የፈጠረበት መንገድ ሰውን ከፈጠረበት ሁኔታ ጋር ሲተያይ
የሰው ልጅ ከሁሉም ታላቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከብርሃን ጀምሮ
በምድርና ሰማይ ያሉ አካላትን የፈጠረው 'ለይኩን' 'ይሁን' በሚለ
ይሁንታዎች በቃሉ ተናግሮ ነበር፡፡ ብርሃን ይሁን ሲል ብርሃን ሆነ ፤
ጠፈር ይሁን ሲል ጠፈር ሆነ ፤ የብስ ይገለጥ አለ የብስ ሆነ ፤ ምድር
ዘርን ታብቅል አለ በቀለ ፤ ብርሃናት በሰማይ ይሁኑ አለ ብርሃናት ሆኑ ፤
ውኃ ተንቀሳቃሾችን ታስገኝ አለ ተገኙ ፤ ምድር እንስሳትን ታስገኝ አለ
ተገኙ፡፡

ባሕርን ዓሦችን እንድታወጣ ፣ ምድርን ዕፅዋትን እንድታበቅል በቃሉ ያዘዘው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከአፈር ሲፈጥረው ግን 'ምድር ሰውን ታብቅል' አላለም፡፡ ከመፍጠሩ በፊት እስካሁን ካደረገው በተለየ ከራሱ ጋር ተነጋገረ 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር' በሚል ልዩ የሆነች ምክረ፡ሥላሴ እግዚአብሔር ከራሱ ተማክሮ ሰውን ሊፈጥር ወደደ፡፡ መላእክቱን በአሳቡ ፣ ሌላውን ፍጥረት በቃሉ የፈጠረው ሁሉን ቻይ አምላክ ሰውን ግን በግብር ሊፈጥር ወድዶ 'ለአክብርተ ሰብእ ጭቃ ይዞ ታየ'፡፡

ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል :-

> 'ከእኛ በላይ የተዘረጋው ታላቁ ሰማይ የተፈጠረው በእግዚአብሔር ቃል ነው።
>
> እንደ ትልቅ የምንቆጥራቸውና ዓይኖቻችንን እንጋጥጠን የምናደንቃቸው ፀሐይ ፣ ጨረቃና ከዋክብትም በቃሉ ብቻ የተፈጠሩ ናቸው። ባሕርና የብስ ፣ እንስሳትም ሁሉ በቃሉ የተፈጠሩ ናቸው። ከብርሃን በላይ ፣ ከሰማይም በላይ ፣ ከጠፈርም በላይ ፣ ከብርሃናትም በላይ ግን የሰው ልጅ አፈጣጠር የከበረ ነው።

የእኛ ሰውነትን ሙሉ በሙሉ በእጆቹ ያበጃጀው ዘንድ የተገባ ሆነ። አንዱን መልአክ እንዲያበጃጀን አላዘዘውም። ምድር ራስዋ እንደ በራሪ ነፍሳት አላበቀለችንም። የመላእክትን አለቆችም ይህን አድርጉ ያንን ሥሩ ብሎ አላዘዛቸውም። እንደ ሠዓሊና ቀራጺ በአምላካዊ እጆቹ አፈርን አነሣ። የተሠራበትን መንገድ ስታይ ሰው ክቡር ነው ፤ የተፈጠረበትን አፈር ስታይ ሰው ከንቱ ነው''[5]

ነቢዩ ዳዊት የፀሐይን የጨረቃንና የከዋክብትን ታላቅነትና ውስብስብ ተፈጥሮ አይቶ ከሰው ታናሽነት ጋር አነጻጽሮ 'ታስበው ዘንድ ሰው ምንድርን ነው?' አለ እንጂ ከተፈጠርንበት ክብር አንጻር ስናየው 'በእጆችህ የፈጠርከውን የሰውን ልጅ ባየሁ ጊዜ ታስባት ዘንድ ፀሐይ ምንድር ናት? ትጎበኛቸውስ ዘንድ ጨረቃና ከዋክብት ምንድር ናቸው?' የሚያሰኝ ክብር ለሰው ልጅ ተሠጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ከዋክብትን ቢፈጥርም አንዳቸውም ምንም እውቀት የላቸውም፡፡ ፀሐይ ምን ብትገዝፍ ከትልቅ የእሳት ኳስነት ያለፈ ሕያውነት የላትም፡፡ ከሩቅ አምራ ተውባ ለብዙኃን ብታበራም ማን እንደሆነች ፡ ለማን እንደምታበራ እንኳን አታውቅም፡፡

---

[5] St. Basil the Great, On The Human Condition, Second Homily 3

እግዚአብሔር ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትን ለምን እንደፈጠራቸው ሲገልጥ ለምድር ከማብራት ጋር 'ለምልክቶች ለዘመናት ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ' ብሎ ለጊዜ መቁጠሪያ እንዲሆኑ ነው:: ስለዚህ እነዚህ ግዙፍ ፍጥረታት ለሰው ተፈጠሩ እንጂ ሰው ለእነርሱ አልተፈጠረም::

ሊቁ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ እንዳለው ፀሐይን ፤ ጨረቃና ከዋክብትን ጣዖት አድርገው እስከማምለክ የሚደርሱ ሰዎችም ሞኞች ሆነው የምናገኛቸው ድርጊታቸው በአሁን ዘመን ቋንቋ ሰው የቤቱን ውስጥ አምፖል ፤ የእጁን ሰዓትና የቀን መቁጠሪያውን አምላኬ ብሎ ቢያመልክ የሚሳቅበትን ያህል ተመሳሳይ ድርጊት ስለፈጸሙ ነው::[6]

ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ብቻ ሳይሆኑ ፍጥረታት ሁሉ ለሰው የተፈጠሩ ናቸው:: ፍጥረታት ለሰው ሊታዘዙና ሰውን ሊያገለግሉ ተፈጥረዋል:: ሰው ከፈጣሪው ባይጣላ ኖሮ ፍጥረታትን እንደ ፈለገ ያዝዛቸው ነበር:: ይህን እውነታም ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ቅዱሳን ሰዎች ተፈጥሮን አዝዘው አሳይተውናል:: ባሕር ለሙሴ ተከፈለ ፤ ፀሐይ ለኢያሱ ቆመች ፤ ቁራ ኤልያስን መገበ ፤ እሳት ለሠለስቱ ደቂቅ

[6] St Theophlus of Antioch I, Autolycus, 6 in B V.5 P. 15

በረደ ፤ አንበሶች ለዳንኤል ትራስ ሆኑ ፤ ዓሣ አንበሪ ለዮናስ ቤት ሆነ፡፡ በዚህም ሁሉም ለሰው የተፈጠሩ መሆናቸውን ነገሩን፡፡

'ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል' ፍጥረታት ሌላው ሥራቸው የፈጣሪን ክብር መናገር ነው፡፡ መዝ. ፲፱፥፩ በሦስቱ ወጣቶች መዝሙር ላይ እንደተገለጸው እንደበት ባይኖራቸውም እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በመኖራቸው ብቻ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጡ መዘምራን ናቸው፡፡ ከኃያልዋ ፀሐይ እስከ ትንሹ ጉንዳን ድረስ ለፈጣሪያቸው ይዘምራሉ፡፡ ከዘማሪዋ ወፍ እስከሚያንቋርረው እንቁራሪት ድረስ ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ማሕሌታውያን ፍጥረታት የመዘምራን አለቃቸው የሰው ልጅ ነበረ፡፡

ከእነዚያ ሁሉ ድንቃ ድንቅ ፍጥረታት የበለጠው ፍጥረት በፈጣሪው አምሳል አዋቂ ነገርና ሕያው ሆኖ የተፈጠረው የሰው ልጅ ነው፡፡ እግዚአብሔር 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር' ሲል ሰምተው ቅዱሳን መላእክት 'እግዚአብሔርን የሚመስል ፍጥረት እንዴት ያለ ነው?' ብለው ሊያዩት የጓጉለት ግሩምና ድንቅ ፍጥረት ሰው ነው፡፡ ሰው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ (masterpiece) ፤ መላውን

ህዋ ጠቅልሎ የያዘ ንዑስ ዓለም (microcosm)[7] ፣ ከመላው የከዋክብት ሥርዓት በላይ የተወሳሰበ አእምሮ ያለው ጠቢብ ፣ ሊኖር እንጂ ሊሞት ያልተፈጠረ ንጉሥ ፡ 'በእጆችህ ሥራ ሁሉ ላይ ሾምከው' እንደሚል እግዚአብሔር በፍጥረታቱ ላይ የሾመው ገገር ነው፡፡ መዝ. ፰፥፮

ሰውን እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሳሉ መፍጠሩን ራሱ በቃሉ 'እንፍጠር' ብሎ መስከሮ መናገሩ የሰው ልጅን ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ከፍ ያለ ያደርገዋል፡፡ 'ምንትኑ፡ይከብር፡እምዝንቱ፡መዓርግ፡፡ ወይ፡ምክሕ፡ዘየዐቢ፡እምዝንቱ፡ትምክህት' 'ከዚህ ክብር የሚበልጥ ምን ክብር አለ? ከዚህ ትምክህት የበለጠስ ምን የሚያስመካ ነገር አለ?' እንዳለ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ[8]

እግዚአብሔር ሰውን ከፍጥረታት ሁሉ በኋላ መጨረሻ መፍጠሩም የክብር እንግዳ ቦታ እንደሠጠው የሚያሳይ ነው፡፡ እንግዳ ከመምጣቱ በፊት ሁሉ ነገር እንደሚዘጋጅ እግዚአብሔር ሰማዩን በከዋክብት አስጊጦ ፣ ምድርን በአበባ አስውቦ ያቆየው በመላእክት አሳጅቦ የተቀበለው 'የእግዜር እንግዳ' የሰው ልጅ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እግዚአብሔር ለፍጥረታቱ ሁሉ የደፋላቸው ዘውድ አክሊለ ፍጥረታት

[7] 'The Whole world in miniature' Othrodox Teachings, On the creation of man, Knowing God, Antony Coniaris,

[8] ሃይማኖተ አበው ፣ ዘጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፴፮፥፲፪

አዳምን ነው ይላል፡፡[9] ንጉሥ ሁሉን ልብሱን ለብሶ ከተዘጋጀ በኋላ በመጨረሻ ላይ ዘውዱን እንደሚደፋው እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ከተፈጸሙ በኋላ በላያቸው ላይ አዳም የተባለ ዘውድን ጫነላቸው፡፡

አዳም የሚለው ስም ከጎኑ ያለችውን ሔዋንንም የሚጨምር ስም ነው ፡-

> ‘ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፤ ባረካቸውም።
> ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው’
> እንዲል፡፡ ዘፍ. ፭፥፪

አዳም የፍጥረታት አክሊል ከሆነ ደግሞ ሔዋን አዳም ከተፈጠረ በኋላ ከጎኑ ወጥታ የተሠራች የመጨረሻዋ ፍጥረት መሆንዋ በፍጥረታት አክሊል በአዳም ላይ በክብር የተቀመጠች እንደ ዕንቊ የምታበራ ጌጥ ያደርጋታል፡፡

አዳም ከፍጥረታት መጨረሻ መፈጠሩ ከክብሩ ባሻገር ከትዕቢት ጾር የሚጠብቀው ከለላውም ነበር፡፡ አዳም ሁሉንም ፍጥረታት ባየ ጊዜ በመኖር ከእርሱ የሚቀድሙ መሆናቸውን ሲያስብ ገዥ ሆኖ በእነርሱ ላይ በመሾሙ ምክንያት ፍጥረታትን ሁሉ እንዳይንቅ ይረዳዋል -

[9] St. John Chrysostom, On Genesis , Homily 8.2

የቢታችንም መናት ትዕቢት ነውና፡፡ ቀድመውት መፈጠራቸውን ሲያይ ግን በራሪዋ ትንኝ እንኳን በዕድሜ እንደምትቀድመው አስቦ ራሱን ይገሥጻል፡፡[10]

እግዚአብሔር ስም እውጣላቸው ብሎ በሠጠው ክብር አዳም በእንስሳት ላይ ንጉሥ ነበረ፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለው 'እስራኤል ከክብሩ የተነሣ የሙሴን ፊት ለማየት እንዳልተቻላቸው[11] እንስሳት አዳም ስም ባወጣላቸው ጊዜ የፊቱን ክብር ማየት ተስኖአቸው አተርትረው ይሔዱ ነበር'[12] ለዚህም ምክንያቱ ቀሌምንጦስ እንዳለ:-

> 'የአዳም ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ የሚበልጥ ሥጋውም እንደ ጠዋት ኮከብ የሚያበራ ስለነበረ ነው' (ወይፈደፍድ፡ ብርሃኑ፡ ለአዳም፡ እምብርሃነ፡ ፀሐይ፡ ወይበርህ፡ሥጋሁ፡ከመ፡ኮከበ፡ጽባሕ)

ወዳጄ ይህን ስትሰማ 'ሰው እንዴት እንደ ፀሐይ ሊደምቅ እንደ ከዋክብት ሊያበራ ይችላል? ብለህ ለማመን ከተቸገርክ አዳምም የበደለው

---

[10] The Legends of the Jews, Vol. 1 From Generations to Jacob, II, Louis Ginzberg, 1913

[11] የአይሁድ መተርጉማን ደግሞ በሲና ተራራ የሙሴ ፊት በበራ ጊዜ የሰው ጥንተ ተፈጥሮ ወደ ቦታው ተመልሶ የነበረ ቢሆንም አዳም በሌለበት ሐዋንን ያሳተ ዲያቢሎስ ሙሴ በሌለበት ሕዝቡን አስቶ ተጃ ሠርተው እንደ ሐዋን አምላክ ላይ እንዲያምጹ አገብሯቸው የሙሴን ብርሃን መጎናጸፍ ሳይችሉ ቀሩ ብለው ያምናሉ፡፡ /Tehillim – Psalms, Commentary from Taludic, Midrashic and Rabbinic sources, Shabbos 146 a/

[12] St. Ephraim the Syrian, Commentary on Genesis 1

እሁን እኔና እንተ ያለንበትን ሳይደምቁ ሳያበሩ መኖር እንዳለ ማመን ስላልቻለ ነበር፡፡

> 'አዳምና ሔዋን አለመታዘዛቸው የሚያመጣውን ጥፋት ለመገመት አልቻሉም ነበር። እኛም የእነርሱን ካለመታዘዝ በፊት የነበራቸውን ጥፋት የሌለበት የበረከት ሕይወት ለመገመት አይቻለንም' ብሏል ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ[13]

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም አዳም በገነት ሳለ ለብሶት የነበረውን የክብር ብርሃን በታቦር ተራራ ከተገለጠው ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ካሳየው ብርሃን ጋር አንድ ነው ይላል፡፡[14] እንስሳት ብርሃን የለበሰውን አዳምን ሲያዩ እንደ ታቦር ደቀ መዛሙርት በፍርሃት ከመውደቅ በቀር ምንም ማድረግ አይችሉም ነበር፡፡ በዚህ ደረጃ የሚያከብሩትን ፍጥረታት አዳም ቀድሞአቸው ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ኋላ የገጠመው ፈተና ቀድሞ መጥቶ ፈጣሪያችሁ ነኝ እንዳያሰኘው ጠበቀው፡፡

---

[13] St. Gregory of Nyssa, On the beatitudes, Homily 3, pg 44

[14] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤መጽሐፈ ምሥጢር ፴፤፳፱

## • የነፃነት እስረኞች

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በነፍሱ በአርአያው ነባቢ ለባዊ ሕያው አድርጎ ከፈጠረው በኋላ ፍጹም ፈጣሪውን ወደ መምሰል ክብር ከፍ ይል ዘንድ የሚያስችለውን ነፃ ፈቃድ (ግእዛን) አብሮ ሠጠው፡፡ እግዚአብሔር ያለ አንዳች ግፊት አንዳች ሳያስፈልገው ፍጥረታትን በፈቃዱ ፈጥሮአል፡፡

እርሱ በመፍጠሩ አንዳች የማያገኝ 'አንዳች የማይጎድለው በሰው እጅ የማይገለገል' ፤ በራሱ ጊዜ ብዑዕና ብቻውን የሆነ ገገር' ነው፡፡ እንድናመሰግነው ፈልጎ ፈጠረን እንዳንል በባሕርይው 'ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ዘንድ በነበረ ክብር በራሱ ዘንድ የከበረ' ነው፡፡ እንድናምነው ብሎ ፈጠረን እንዳንል 'ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል ፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና" ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው አንዳች ፈልጎ ሳይሆን በፈቃዱ ነበር፡፡ ሐዋ. ፲፯፥፳፭ ፤ ፩ጢሞ. ፮፥፲፭ ፤ ዮሐ. ፲፯፥፭ ፤ ፪ጢሞ. ፪፥፲፫

ሰውን በዘፈቀደ (በፈቀደው) በራሱ አርአያ የፈጠረው እግዚአብሔር ለሰው ልጅም ይህን ነፃ ፈቃድ አብሮ ሊሠጠው ወደደ፡፡ ሁሉን አዘጋጅቶ በፍጹም ፍቅሩ ሰውን ከፈጠረው በኋላ ሰው ደግሞ

በተራው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር እንዲያሳይ ዕድልን ሊሠጠው ወደደ፡፡ የመምረጥ ነፃነት እስከሌለህ ድረስ ፍቅርህን ልታሳይ አትችልምና እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እግዚአብሔርን እስካለመውደድ ድረስ እንዲመርጥ ነፃነትን ሠጠው፡፡ የሰው ልጅ ያለ ነፃ ፈቃድ ቢፈጠር ኖሮ ከማምረቻ ማሽን ያለፈ ዋጋ አይኖረውምና 'ክፉን ለመጥላት መልካሙን ለመምረጥ' እንዲችል ነፃ ሆኖ ተፈጠረ፡፡ ነፃነት ሳይኖረው መልካም ሥራ ቢሠራ እንኳን በግዴታ እስከሆነ ድረስ ዋጋ ቢስ ነው፡፡ 'በግድ የሚሠራ መልካም ነገር መልካም አይደለም' ይላል ቅዱስ ባስልዮስ፡፡[15]

ይህን በማድረጉ የሰው ልጅ አምላኩን ላይመርጥም ይችላልና ነፃ ፈቃድን ለሰው በመሥጠቱ ሁሉን ቻዩ አምላክ ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍል አምላካዊ ውሳኔን ወሰነ፡፡ የቅዱስ ሄሬኔዎስን 'ጥንታዊው የሰው ግእዛን ሕግ' የተሰኘ አገላለጥ መነሻ በማድረግ አንድ ግሪካዊ ጸሐፊ እንዲህ ይላል

> 'ለፍቅሩ በነፃነት ምላሽ ሊሠጡ የሚችሉ ሰዎች ያሉበትን ዓለም በመፍጠር እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል ባሕርይውን ሊገድብ ፈቀደ።

[15] St. Basil the great, On the Human Condition 7 pg 31

ሰዎችን ከፈጠረ በኋላ ከፍጥረታቱ ራሱን በመሰወር ፍጥረታቱ መርጠው ለመውደድ የሚችሉበትን ሁኔታ ሠጣቸው ይህን በማድረጉ የሰው ልጅ ፈጣሪውን ላይመርጥ ስለሚችል አደገኛ ውሳኔ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ይህን ባያደርግ ኖሮ ዓለም ያለ ፍቅር ትቀር ነበር'[16]

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ነፃ ፈቃዱን እንዲጠቀምበትና በመታዘዝ ወደ መጨረሻው ፍጹምነት እንዲሻገር ያስቀመጠለት መሻገሪያ በገነት መካከል ከነበረው ዕፀ በለስ እንዳይበላ መከልከልን ነበር፡፡ ዕፀ በለስ የሰው ልጅ የነፃ ፈቃዱን እና የመታዘዙን አክሊል የሚያገኝበት መንገድ ነበር፡፡

'እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" ዘፍ. ፪፡ ፲፮-፲፯

ወንጌላዊው 'ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና! ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም' እንዳለው 'ሸክሙ ቀሊል ቀንበሩ

[16] Inner kingdom Vol. 1, The Collected works of Kallistos Ware, SVS press, NY 2000

ልዝብ' የሆነው እግዚአብሔር ለአዳም ነፃ ፈቃድ መገለጫና ለፈጣሪው የሚታዘዝ መሆኑን ለማሳየት የሠጠው ትእዛዝ እጅግ በጣም ቀላል ትእዛዝ ነበር፡፡ ፩ኛ ዮሐ. ፭፥፫ ፤ ማቴ. ፲፩፥፴

ዕፀ በለስን አለመብላት የሰው ልጅን ወደ ፍጹምነትና ሱታፌ አምላካዊ የሚያበቃ የመታዘዝ ፈተና ቢሆንም ለመፈጸም ግን እጅግ በጣም ቀላል ትእዛዝ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለአዳም አየር ወደ ውስጥህ አትሳብ አትተንፍስ ፤ ዓይንህን ጨፍነህ አትግለጥ ፤ ከአንድ ቦታ እንዳትላወስ ዓይነት አስጨናቂ ትእዛዝ አላዘዘውም፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዛፎችን ፍሬ እንዲበላ ፈቅዶ አንዲትን ዛፍ ብቻ ባለመብላት መታዘዙን እንዲፈጽም ነገረው፡፡ ልብ አድርጉ አዳም በዚያ ጊዜ የስስት ረሃብ አልነበረበትም፡፡[17] ስለዚህ እንኳንስ አንድ ዛፍ ከሁሉም ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ ቢከለክለው እንኳን የማይከብደው ትእዛዝ ነበረ፡፡

ዕፀ በለስ በራሱ ክፋትን ያዘለ መርዛማ ዛፍ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር 'ከፍሬው አትብሉ' ያለው ዛፍ ስለነበረ ግን ዛፉ መታዘዝንና አለመታዘዝን ለመምረጥ የተዘጋጀ መሣሪያ ሆነ፡፡ አዳምና ሔዋን ከፍሬው ካልቀጠፉ 'የመታዘዝ ዛፍ' ይሆናል ፤ ቀጥፈው ከበሉ ግን 'ያለመታዘዝ ዛፍ' ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ዕፀ በለስን የፈጠረው የሰው

[17] St. Ephraim the Syrian, Commentary On Genesis 3

ልጅ ነፃ ፈቃዱን ተጠቅሞ በሚወስነው ውሳኔ ወደ ዘለዓለማዊነት እንዲሸጋገር ምልክት እንዲሆንና የመታዘዝ ሕይወት መለማመጃ እንዲሆነው ብቻ ነው:: 'ይህ ትእዛዝ ኢመዋቲነትን ለመሸለም ቃል የሚገባ የሕይወት መመሪያ ነበረ'[18] ስለዚህ ጉዳይ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ 'ዕፀ በለስ ገና ሲበትል ክፉ ሆኖ የበቀለ ዛፍ አይደለም' ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም 'ዕፀ በለስ በተፈጥሮው በውስጡ ክፋትን አልያዘም ፤ መታዘዝንና አለመታዘዝን ግን ይዞአል' ብሏል::[19]

ዛፉ የተለየ ምትሐታዊ ዛፍ ሆኖ አይደለም:: እግዚአብሔር ለአዳም ትእዛዝ ሊሠጥ ሲል ለብቻው ጠቅሶ አነሣው እንጂ የተፈጠረው በዕለተ ማክሰኞ ከሌሎች ዛፎች ጋር ነበር::[20] ዕፀ በለስ መሆኑ ቀርቶ ዛፉ የሾላም የዝግባም የዘንባባም ዛፍ ቢሆን አትቅጠፉት ተብሎ ከታዘዘ ያ ዛፍ ክፉትና መልካምነትን ለመምረጥ የተዘጋጀ ፤ በፈጣሪና በፍጡር ፤ በገገርና በተገገር መካከል ምልክት የሚሆን ዛፍ መሆኑ አይቀርም:: በአጭሩ በዘመናችን ቋንቋ ዕፀ በለስ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ከማምለክና ካለማምለክ አንዱን እንዲመርጥ የቀረበለት የምርጫ ድምፅ

[18] St. Gregory of Nyssa, On Song of Songs, Homily 12

[19] St. Gregory of Nazanzus, 2nd Oration on Easter 8 St. John Chrysostom, On Genesis, Hom.16.6

[20] መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ አሪት ዘፍጥረት አንድምታ ትርጓሜ ገጽ ፳፫ አዲስ አበባ ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

መሥዋዕ ሣጥን ሲሆን ዕፀ በለስን ለሰው ውድቀት እንደ ምክንያት አድርጎ ማንሣትም መራጩን የሰው ልጅ ትቶ የድምፅ መሥዋዕ ሳጥኑን እንደ ጥፋተኛ መቁጠር ነው፡፡

አዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር በነፃ ፈቃዳቸው ተጠቅመው እግዚአብሔርን መውደዳቸውንና ለእርሱ መታዘዛቸውን ሊያሳዩ የሚችሉበት መንገድ ለኑሮአቸው ብዙም አስፈላጊ ያልሆነውን ዕፀ በለስን ባለመብላት ብቻ ነበር፡፡ ያንን ማድረግ ከቻሉ እግዚአብሔርን የመምሰልን የመጨረሻ ክብር አግኝተው ወደ ዘለዓለማዊነት ያድጉ ነበር፡፡ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እንዳለ 'ዛፏ የተቀመጠው ሰው ቀስ በቀስ ወደ ሕያውነት እንዲመጣና በሕጉ ሕይወትነት ሕያው እንዲሆን ነበር'[21] አዳምና ሔዋን የተሠጣቸውን ነፃነት ተጠቅመው ሕይወትን መምረጥ ባለመቻላቸውና ከዛፉ ፍሬ በመብላታቸው የገዛ ነፃነታቸው እስረኞች ፤ የነፃ ፈቃዳቸው ሰለባዎች ሆኑ፡፡

የተጻፉ ትእዛዛት በሌሉበት በዚያ ጊዜ ለእነርሱ የተሠጠች ብቸኛ ሕግ ከዚያች ዛፍ ፍሬ እንዲጾሙ ነበር፡፡ አታመንዝር በሐሰት አትመስክር ወላጆችን አክብር የሚለው ሕግ አልተሠጣቸውም፡፡ ሆኖም

[21] St. Gregory of Nyssa, On the Song of Songs, Homily 12, pg 44m

በገነት ሳሉ የነበረችውን እንዲትም ሕግ እርስዋም ሕግጋትን ሁሉ ፍጹም የምታደርግ የፍቅር ሕግን ጥሰው ክብራቸውን አጡ፡፡

እንዳንድ ሰው አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ከመብላታቸው በፊት ምንም ነገር የማያውቁ ሆነው ቆይተው በዛፉ ፍሬ ዕውቀትን እንዳገኙና ዛፉም ጥበብን የሚሠጥ እንደሆነ ያስባል፡፡ የዕባብን ቃል ይዞም እግዚአብሔር አላዋቂ ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ ፈልጎ ዛፉን እንደከለከላቸው አድርጎ ይደመድማል፡፡[22] እውነት ለመናገር እግዚአብሔር ዓላማው ከአዳምና ሔዋን ዛፉን መከልከል ከሆነ ስለዛፉ ባለመንገር ብቻ ዛፉን ሳይበሉ እንዲኖሩ ማድረግ ይችላል፡፡ ጨርሶም ዛፉን ባለመፍጠር ደግሞ ዘግይተውም ቢሆን እንዳያገኙት ማድረግ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ዓላማው ሰው ለፈጣሪው በግድ የሚገዛና የሚነዳ ባሪያ እንዳይሆንና ወድዶና መርጦ በነፃ ፈቃዱ አምላኩን ማምለክ እንዲችል ማድረግ ነው፡፡

ከዚያ ውጪ ግን አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ከመብላታቸው አስቀድሞ አዋቂዎች ነበሩ፡፡ የሰው ልጅ ሲፈጠር 'ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው' ተብሎ እንደተጻፈ አዋቂ ሆኖ የተፈጠረ ፍጥረት ነበር፡ ፡ ጠቢቡ ሲራክም ስለሰው ተፈጥሮ ሲገልጽ 'በምሳሌው ፈጠራቸው

[22]St. Gregory of Nazanzus, 2nd Oration on Easter 8

ፍጥረቱ ሁሉ ይፈሯቸው ዘንድ አደረገ ... ጥበብንና ማወቅንም አጠገባቸው ክፉና በጎንም አሳያቸው' ብሏል፡፡ አዳምና ሔዋን ማሰብ የማይችሉና ምንም ዕውቀት የሌላቸው ቢሆኑ ኖሮ እግዚአብሔር ለማያስብ ፍጡር ትእዛዝን አይሠጥም ነበር፡፡ ማሰብ ለማይችል አዳምም ለእንስሳት ስም አውጣላቸው ፤ ገዥ ሁናቸው ብሎም አያዝዝም ነበረ፡፡ መዝ. ፰፥፰ ፤ ሲራ. ፲፯፥፫-፯

ይህ ከሆነ ዕፀ በለስ ክፉና ደግን የሚያሳውቅ ዛፍ ለምን ተባለ? አዳምና ሔዋንስ ከዛፉ ፍሬ ከበሉ በኋላ ዓይናቸው ተከፈተ ለምን ተባለ? 'ከዚያ በፊት ዓይኖች ከሌሏቸው ሔዋን ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ በምን አወቀች? ማየትስ ካልቻለች ወደሚያስጎመጀው የዛፉ ፍሬ ለምን እንጋጠጠች?' ይላል አባ ጊዮርጊስም፡፡ እግዚአብሔር 'መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና' ብሎ ለአዳም አዝዞታል፡፡ ስለዚህ ዛፉ መልካምና ክፉን ያሳውቅ ከሆነ ሰው ቢያውቅ እግዚአብሔር ምን ገዶት ነው የከለከለው? ዕባብ ያለው ልክ ነው ማለት ነው? የሰው ልጅ ከዚያ በፊት ዕውቀት ነበረው ካልን እግዚአብሔር እየከለከለው ያለው ዕውቀት ምንድርን ነው?

ይህን ለመመለስ አንድ ምሳሌ ልጠቀም፡-

አንድ አባት ለልጁ 'ይህ የሚሽከረከር መሣሪያ ውስጥ እጅህን እንዳታስገባ ፤ እጅህን ካስገባህ እጅህን ይቆርጥሃል' ብሎ አስጠንቅቀው እንበል። አባት ይህን ካለው በኋላ አንድ ተንኮለኛ ሰው መጥቶ 'እጅህን እዚህ መሣሪያ ውስጥ አስገባ' ብሎ መከረው። ልጁም 'አይሆንም ፤ አባቴ እጅህን እንዳታስገባ ፤ ካስገባህ እጅህን ይቆርጥሃል ብሎኛል' አለው፡ ፡ ተንኮለኛውም መልሶ 'አባትህ ይህን ያለህ እጅህን ስለምትቆረጥ ሳይሆን እጅን ወደ ተሽከርካሪው መሣሪያ ማስገባት ምን እንደሆነ እንዳታውቅ ብሎ ነው' አለው።

ልጁም ይህን ምክር ይዞ እጁን ወደ መሣሪያው ከተተ ፤ እጁም ተቆረጠ። ያን ጊዜ ዓይኑ ተከፈተ ፤ አባቱ የከለከለው መሣሪያ ውስጥ እጅ ማስገባት ምን እንደሆነ አወቀ። እጁንም አጣ። ተደብቆ ሲያለቅስ አባት 'ልጄ ሆይ ወዴት ነህ?' ብሎ ጠራው። ልጅም 'እጄን ስለተቆረጥሁ ፈራሁህ ተደበቅሁም' አለው። አባትም 'እጅህን እንዴት ተቆረጥህ? እጅህን ወደሚሽከረከረው መሣሪያ አስገባህን?' አለው። እያለ ይቀጥላል።

ዕፀ በለስ ከፉና ደግን ያሳውቃልን? አዎ ያሳውቃል፡፡ የመታዘዝን ጸጋ ባለመታዘዝም የሚመጣውን ውርደት ያሳውቃል፡፡

አዳምና ሔዋን ከዛፉ ፍሬ በፊት የነበራቸውን ክብር ያውቃሉ:: ዛፉን በልተው ደግሞ ከክብር መዋረድ ምን እንደሆነ አወቁ:: ዓይናቸው ተከፍቶ ያወቁት የመጀመሪያው ዕውቀት ራቁታቸውን እንደሆኑ ነው:: መልካሙን ተነጥቀው ክፉውን ተሸክመው አወቁት:: የሰው ልጅ ዕፀ በለስን በመብላቱ የበለጠ ክብር አገኛለሁ ሲል የነበረውንም ክብር አጣ:: የቆጡን አምላክነት አገኝ ብሎ የብብቱን ሰው መሆን አጣ:: ከዛፉ ፍሬ ከበላ በኋላ አዳም እንኳን ከአምላክ ጋር እኩል ሊሆን ከመብላቱ በፊት ራሱ ከነበረበት ክብሩም ጋር መተካከል አልቻለም:: 'ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፡ ፍጻሜዋ ግን ሞት ነው' የሚለው ቃል የተሻለ ክብር አገኛለሁ ብሎ ወደ ሞት ለተጓዘው አዳም የተስማማ ሆነ:: ምሳ. ፲፬፡፲፪

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይገልጻዋል :-

'የሰው ልጅ የበለጠ ክብርና ዕውቀት አገኛለሁ ብሎ የነበረውን ጣለ። ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አለመሆን ብቻ ሳይሆን ወደ ባሰ ወጥመድም ተጣለ። ዛፉን በመብላቱ ምንም አለማግኘቱ ሳያንስ የተሻለ ዕውቀት አገኛለሁ ብሎ የነበረውንም ዕውቀት አጣ'[23]

[23] St. John Chrysostom, Commentary on the Gospel of John Homily 7

በዕፀ በለስ የተገኘው ጥበብ 'ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ' (ወእንዘ፡ ይፈቅዱ፡ ይጥብቡ፡ አብዱ) የተባለው ዓይነት የኃጢአት እውቀትና ውርደት ነበር፡፡ ሮሜ ፩፡፳፪ የሰው ልጅ ዕርቃኑን መሆኑን ለማወቅ ብሎ እግዚአብሔርን የማወቅ ጸጋ አጣ፡፡ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ለጻድቁ ሄኖክ የዕፀ በለስን ዛፍ ባሳየው ጊዜ የተናገረው ይህን እውነታ የበለጠ ያጎላዋል፡፡

> 'ይህ ዛፍ ምንድርን ነው አልሁት። ቅዱስ ሩፋኤልም መለሰልኝ ፡ የቀደሙህ ሽማግሌው አባትህና ባልቴቲቱ እናትህ ከእርሱ የበሉ የጥበብ ዛፍ ይህ ነው። ጥበብንም አወቁት። ዓይኖቻቸውም ተገለጡ። ዕራቁታቸውንም እንዳሉ ዐወቁ ከገነትም ተሰደዱ' ሄኖ. ፰፡፳፫-፳፰

'የአንድ ዛፍን ፍሬ መብላት የሰውን ዘር ይህን ያህል ዋጋ ማስከፈል ነበረበትን?' ብሎ የዕፀ በለስን ጉዳይ የአንድ ፍሬ ጉዳይ አድርጎ የሚረዳ ሰው ካለ የዋህ ነው፡፡ አዳምና ሔዋንን የጣላቸው ፍሬው ሳይሆን ፍሬውን የበሉበት ምክንያት ነው፡፡ ዕፀ በለስን የበሉት የሕባብን ቃል ሰምተው ፤ አምላክ ለመሆን ፈልገው ነው፡፡ የፍሬውን ቅርፊት በጥርሳቸው ሲፈነቅሉም መፈንቅለ አምላክ እያካሔዱ ነበር እንጂ

ረሃባቸውን እያስታገሡ አልነበረም:: ስለዚህ ጉዳዩ አምላክነትን የመሻት ፡ ያለመታዘዝና በነፃ ፈቃድ ማመፅ ነው:: ለዚህም ነው ቅዱስ ኤፍሬም ዕፀ በለስን መብላትን 'ሔዋን እንጨት በልታ ያደረገችው አመፅ' ብሎ የሚጠራው::[24]

ዕርቃንን ማወቅ ዕውቀት ከሆነ አዳምና ሔዋን ቢቀርባቸው ይሻላቸው ነበር:: ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል:-

> 'ዕርቃናቸውን አለማወቅ ይሻላቸው ነበር ፤ በማወቃቸው ምክንያት የሰው ልጅ ሕሊና ተራ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ወደ መጨነት ወረደ። ለራሱ ልብስን ለማዘጋጀትና ዕርቃኑን ለመሸፈን ተጋ። በዚህ ምክንያት ወደ ፈጣሪ ብቻ ከማየት አቋርጦ ልቡ ወደ ሌላ ነገር ተከፈለ'[25]

የብርሃን ልብስን የለበሰው ንጉሥ የሰው ልጅ ዕርቃኑን ለመሸፈን ቅጠል አገለደመ:: ፈጣሪውም በኋላ የቁርበት ልብስን አልብሶ ከገነት አስወጣው:: የእንስሳት ገገር የፍጥረታት አክሊል አዳም የእንስሳ ቆዳ ለብሶ ከገነት ሲወጣ ከማየት በላይ ምን የሚያሳዝን ነገር አለ? እንስሳት ቀና ብለው የማያዩት ንጉሥ የእንስሳትን የተፈጥሮ ልብስ ተውሶ የዕርቃኑ መሸፈኛ አድርጎ እንስሳ መስሎ ሲታይ ምንኛ ያሳዝናል:: 'ሰውስ ክቡር

---

[24] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ፤ ውዳሴ ማርያም ፤ ዘሐሙስ ፤

[25] St. Basil the Great, On the Human Condition

ሆና ሳለ አላወቀም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ' የሚለው የዳዊት መዝሙር ለዚያች ዕለት የተስማማ ነበረ፡፡ መዝ. ፵፱፥፲፪

በዚያን ጊዜ የገነቱን ስደተኛ አዳምን ልጁን ያዕቆብን እንደ ዳሰሰው እንደ ዓይነ ሥውሩ ይስሐቅ በዳበሳ የሚነካው ሰው ቢኖር ኖሮ 'ይህ ድምፅ የአዳም ድምፅ ነው ፤ ልብስህ ግን የእንስሳ ነው' ባለው ነበር፡፡ መዝ. ፵፱፥፲፪ ፤ ዘፍ. ፳፯፥፳፪ የሰው ልጅ መዋረድ በቁርበት ልብሱ እንስሳትን በመምሰል አላበቃም፡፡ በክብር የተፈጠረው የሰው ልጅ ማክሰኞ ከተፈጠሩ ዕፅዋት ጋርም በረጋፊነቱ ተመሳስሎ 'ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው' እየተባለ መዘመር ተጀመረ፡፡ መዝ. ፻፫፥፲፭

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ሲል ይተነትነዋል፡-

> 'ሰው ንጉሥ ሲሆን አላወቀም ራሱን በፈቃዱ አዋረደ ፤ ባሪያም ሆነ። ጌቶች ያልሆኑም ገዙት። ሰው ባለጸጋ ሲሆን አላወቀም ፤ ራሱን በፈቃዱ አደኸየ ፤ ሆዱን አስራብ ነፍሱንም አስጠማ ፤ ሰው የብርሃንን ልብስ የለበሰ ሲሆን አላወቀም ፤ የቁርበትን ልብስ ለበሰ ፤ ሰውስ ከጌታ በታች ገዢ ሲሆን አላወቀም ካልተፈቀደለት ዕፀ ሰርቆ በላ'[26]

[26] ቅዳሴ አትናቴዎስ ፩፥፪

አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን በልተው የዕርቃንን እውቀት ተጎናጽፈው ከገነት ከተባረሩ በኋላ ልብስና ምግብ የሰው ልጅ የሕይወት ዘመን ጥያቄ ሆኖ ቀረ፡፡ የሰው ልጅ የወደቀው በመብላት ሲሆን የተዳረገውም ለዕርቃንነት በመሆኑ ለታላቅ ክብር የተፈጠረው የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚቆያትን እጅግ አጭርና መራራ ዘመን አብዛኛውን ምግብና ልብስ ለማሟላት ሲኳትን ይጨርሰዋል፡፡ የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ ፍለጋ ሲሯሯጥ ዕድሜውን እንደዋዛ ይጨርሳል፡፡ እግዚአብሔር በአዳም ላይ የተናገረው የእርግማን ቃል ላይም ሦስት ጊዜ 'ትበላለህ' የሚለውን ቃል መናገሩ የሰው ልጅ ጥፋቱም ቅጣቱም ምግብ እንደሆነ ያሳያል፡፡ '... በድካም ከእርሰዋ ትበላለህ ... የምድርን ቡቃያ ትበላለህ ... በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ ... ዘፍ. ፫፡፲፯-፲፱

የተከለከልከውን ፍሬ ለመብላት ከወሰንህ መብላት የሕይወት ግብህ እንዲሆን መርጠሃል፡፡ ዕርቃን መሆንህን ለማወቅም ከወሰንክ ልብስ የዕድሜ ልክ ራስ ምታትህ እንዲሆን ፈቅደሃል፡፡ በዚህ ምክንያት የሰው ልጅ እግዚአብሔር 'ስለምትበሉትና ስለምትለብሱት አትጨነቁ' እስኪለው ድረስ ለምግቡና ለልብሱ የሚጨነቅ ፍጡር ሆኖ አረፈው፡፡ ማቴ. ፮፡፳፭

ልብስና ምግብም ከሰው አገልጋይነት ወደ ሰው መለኪያነት ከፍ ብለው 'ሰውና ጀንያ ያለ እህል አይቶምም' 'የእንጀራ ጉዳይ' 'እህል ውኃ ነው' 'አንተ የበላኸውን ነህ' 'ምን ለብሼ ልውጣ' 'ልብሴን ልቀይር' የሚሉ ቃላት ከአፉ የማይጠፉ ሕይወቱና ማኅበራዊ ግንኙነቱ ፣ ክብሩና ውርደቱ ሳይቀር ከምግብና ከልብስ ጋር የተሳሰረ ሆኖ ቀረ፡፡ የሰው ልጅ በውስን እድሜው ያለ ምግብ ከአንድ ሳምንት በላይ የማይቆይ የምግብና መጠጥ ጥገኛ ሆነ፡፡ በአሁኑ ዘመን ሳይበሉ መኖር ምን ማለት እንደሆነ ማሰብ እንኳን የሚከብደን ለዚህ ነው፡፡

መብላትና መልበስም በሰው ልጅ ሥነ ልቡና ላይ ትልቅ ጠባሳ የጣለና የሰው ልጆችን ማኅበራዊ ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ሥነ መንግሥታዊ ሥርዓት ሳይቀር የሚወስን ከመሆኑ ባሻገር እኩል ሆኖ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የሰው ልጅ ጌታና ሎሌ ፣ ደሃና ሀብታም ፣ ታናሽና ታላቅ በሚል መደብ ከፋፍሎ ምድርን አንደኛ ሁለተኛ ሦስተኛ ዓለም በሚል መደብ እስከ መከፋፈል የደረሰ ሆነ፡፡

በዚህ ምክንያት ሰው በምድር ላይ ከሚኖርበት አጭር ዕድሜ ላይ ከእንቅልፍ የተረፈውን ግማሽ ዘመን የሚበላውን በማዘጋጀት ፣ ቁጭ ብሎ በመብላት ፣ የበላበትን ገበታ በማንሣት ፣ ልብሱን በማጠብ ፣ ልብሱን በመልበስ ፣ ልብሱን በማውለቅ የሚያባክነው ሆነ፡፡ በበላ

በሰዓታት ልዩነት ውስጥ ምግብ የሚያስፈልገው ፡ ካልለበሰም ለሕመም የሚዳረግ የምግብና ልብስ ጥገኛ ሆኖ ቀረ፡፡ የቀረውን ዘመኑንም የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ በሚሠራው ሥራ ላይ ተወጥሮ በወዙ እየበላ መኖር ሥራው የሆነ ፍጡር ሆነ፡፡

ከምግብ ባሻገር የሰው ልጅ ማወቅ ፈልጎ ከፈጣሪ የተጣላ በመሆኑ የተፈጥሮ እውቀቱን ስላጣ እውቀትን ለማግኘት መማር ማንበብ አስፈልጎት ከምግብና ልብስ ውጪም ትምህርት ሌላው የሰው ልጅ ዕድሜ ፈጅ አድካሚ ዳገትና የሰው ደረጃ መለኪያ መሥፈርት ሆነ፡፡ እንደ መላእክት ሳይማሩ የማወቅን ጸጋ ተጎናጽፎ የተፈጠረው የሰው ልጅ አንዱ ከአንዱ እግር ሥር ቁጭ ብሎ የሚማር ፡ የተማረውም በቀላሉ የማይገባው ፡ የገባውም የሚዘነጋው ደካማ ፍጡር ሆነ፡፡ ያውም ዘርፎች መርጦ ለማወቅ እንጂ በሁሉም ነገር ላይ ለማወቅ ዕድሜውም የማይፈቅድለት ሲሆን ይህቺም እውቀት ሆና አንዱ በሌላው ላይ እየተኮፈሰ የሚመካበት ጉዳይ ሆኖ አረፈው፡፡

ልብ አድርጉ ምግብ መብላት የተጀመረው ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ ነው እያልን አይደለም፡፡ 'ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ' እንደሚል ከዕፀ በለስ ውጪ ያለው የተፈቀደላቸው የዛፍ ፍሬ በሙሉ ይህን ያሳያል፡፡ ዘፍ. ፪፥፲፮ አዳምና ሔዋን በገነትም ሳሉ ምግብ ይበሉ ነበር፡፡

ሆናም ምግብን የሚበሉት ረሃብ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ኖሮት በሚያስገድድ ፍላጎት ተገፍተው ፡ የህልውና ጥያቄ ሆኖባቸው አልነበረም:: ልብስንም መልበስ የማያስፈልጋቸው በብርሃን ልብስ ያጌጡ ነበሩ:: ምድርን አነሳቁለው የሚያስታግሱት ረሃብና ስግብግብነት አልነበረባቸውም::

ከእርግማን ወዲህ ግን ምድርም ስለተረገመች ሰው የፈለገውን ምግብ በደስታ የማታቀርብና የአዳምን የድካም ላብና ወዝ ካልጠጣች የማታፈራ ሆነች:: የሰው ልጅ በደረሰበት የምግብ ምርኮኝነት ምክንያትም ጠባዩ ተለውጦ ፡ ምድርን የሚያነሳቁል ፡ እንደ ልጅ ስም ያወጣላቸውን እንስሳት ሳይቀር አሳድጎ አርዶ የሚበላ ሆነ:: ከእነርሱም ኃይለኞቹ አራዊት ገዢያቸውን የሰው ልጅ ካገኙ የማይምሩ ሆነው ተለያዩ::

አዳም ወደ ነበረበት ምግብን ያልተመረኮዘ ኑሮ ምን እንደሚመስል ለማየት የምትፈልግ ከሆነ ብቸኛው መንገድ ጾም ነው:: አብዝቶ የሚጾም ሰው ከምግብ ምርኮኛነት ወጥቶ የጥንተ ተፈጥሮ ማንነቱን ለማግኘት የሚታገል ሰው ሲሆን በዚህም ብዙዎች ተጠቅመው በሕይወት ሳሉ የገነትን ኑሮ ምንነት ተረድተዋል:: እንደነ አባ እንጦንስ ያሉትን ጾመኞች ሰይጣን 'ከመጀመሪያው ሰው አዳም ወዲህ እንዲህ ያለ

ሰው አልገጠመኝም' ብሎ የተደነቀባቸው ለዚህ ነው:: ጾም እያስፈልግም እያለ የሚከራከር ሰው ደግሞ 'እርግማኑን አትንኩብኝ ምግብን እንደተደገፍኩ ልኑር' የሚል ይመስላል:: በቅዱስ ጳውሎስ 'ሆዳቸው አምላካቸው' ከተባሉት ወገን ነው:: ፊልጵ. ፫፡፲፱

የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነትንም የምናየው እዚህ ላይ ነው:: የሰውን ልጅ 'ትበላለህ' ብሎ የምግብ ባሪያ እንዲሆን የፈረደበት አምላክ የሰው ልጅን መዳንም በምግብ አድርጎ በወደቀበት እንዲነሣ ዕድል ሠጥቶታል:: ይህም ራሱን ምግብ አድርጎ የሠጠበት 'ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው' የሚለው የሐዲስ ኪዳን ጸጋ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መብላት ነው:: ዮሐ. ፮፡፶፬ የሚያሳዝነው አትብላ የተባለውን በልቶ የወደቀው የሰው ልጅ አሁን ደግሞ 'እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው' ተብሎ የተሠጠውን የሕይወት ምግብ ደግሞ ባለመብላት ፈጣሪውን አልሰማ ማለቱና ከእግዚአብሔር መንገድ በተቃርኖ መቆምን መምረጡ ነው:: ማቴ. ፳፮፡፳፮

ከአዳምና ሔዋን ድቀት በኋላ ልብስም የሰውን ልጅ ላይ የወረደ ሌላ ትልቅ ጠባሳ ሆነ:: ሰው ሰውነቱ ብቻ የሚያስከብረው ፍጡር እንዳልነበረ ልብሱን በማየት መለካት ፡ አለባበሱን አይቶ ማክበር ፡ ልብሱን አይቶ መናቅ የዓለም ሕይወት መመሪያዋ ሆነ:: ለዘለዓለማዊነት

የተፈጠረው የሰው ልጅም ከገነት ሲባረር ከለበሰው የቅጠልና የቆዳ ልብስ በተጨማሪ ልብስ ለመቀያየር ብዙ ድካም የሚደከም ሆነ፡፡ ልብስን ዕርቃን ለመሸፈን ከመልበስ አልፎ ዛሬ የለበሰውን ነገ መድገም በሰው ፊት የሚያስንቀው ነገር ሆነ፡፡ ስለዚህ በአብዛኛው የሰው ልጅ ዘንድ ልብስ የምግብ ያህል ሁልጊዜ የሚያስፈልግ የኑሮ ጥያቄ ነው፡፡ ምን አለፋችሁ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን የምግብና ልብስ ምርኮኞች አድርገውን ሔዱ፡፡ እነርሱስ ብዙ ሰው ባልነበረበት ዘመን ስለኖሩ ያገኙትን በልተው በአንድ ልብስ ብቻ ቢኖሩ የሰው አፍ አያስፈራቸውም ነበር፡፡ እኛ ግን ምን እንደበላን ምን እንደለበስን አይቶ በሚመዝን እልፍ ማኅበረሰብ ውስጥ ተጥለን የበለጠ ተሠቃየን፡፡

ሴት ልጅ ላይ ትንሽ ጨከን ያለ ብዕር ያለው ሊቁ ጠርጠሉስ 'ሔዋኖች ሆይ ወደ ልብስ ገበያ ከተታችሁን!' እያለ እንዲህ ሲል ያማርራል፡-

'የተከለከለውን ዛፍ የቀጠፈችው ሴት ነበረች ፤ የአምላክ የመጀመሪያ ሕግ ተላላፊ ሴት ናት። ዲያብሎስ እንኳን ያልቻለውን አዳም ድል የነሣችው ሴት ናት። ሴቶች ሆይ እናንተ የሰይጣን መግቢያ በር ሆናችሁ ፤ የእግዚአብሔር አምሳል የሆነን የሰው ልጅ በተላሉ አፈረሳችሁት። እናንተ

ባመጣችሁት አስመታዘዝ ሞት በዓለም ላይ መጣ።
የእግዚአብሔር ልጅ እንኳን ሊሞት ግድ ሆነበት።
አሁንም ሰው ከገነት ሲወጣ እንደነበረው በቆዳ ልብሶች
ራሳችሁን ስለማስጌጥ ታስባላችሁ። በእናንተ ምክንያት
ከዓለም መጀመሪያ ሚሊሲያኖች በግ ሸለቱ ፡ ሶርያውያን
ጥጥን ፈተሉ ፡ ጢርሳዊያን አቀለሙት ፡ ቱርካውያን
በመርፌ ሰፉት ፡ ባቢሎናውያን በዕንቁ አንቆጠቆጡት ፡
በከበሩ ድንጋዮችም እንዲያብረቀርቅ አደረጉት ፡ ወርቅም
ለልብስ መግዣነት ተሠጠ። መስታወት የመዋሸት ፈቃድ
ቢኖረው ብዙ ሴቶች ደስ ባላቸው ነበር። የሔዋን ዘር
ከገነት ተባርራም ይህን ጌጥ ትመኛለች። እነዚህ ምኞቶች
የሴት ልጅ ሸክሞች ናቸው' ይላል፡፡[27]

ሊቁ ጠርጠሉስ ድምዳሚው ላይ ትንሽ ያበዛው ቢመስልም ሴት ልጅ በቀጠፈችው ዕፅ የሰው ልጅ ታሪክ መበላሸቱ ግን የማይታበል እውነታ ነው፡፡ እውነት ግን ሔዋን ያጠፋችው ምን ነበር? አዳምስ ንጹሕ ነበረ? እባብስ ድርሻው ምንድርን ነው? በእባብ ያደረው ሰይጣንስ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ቢጣላ የሚጠቀመው ምንድርን ነው? እግዚአብሔርስ ሰይጣንን ለምን ፈጠረው? እርሱ ባይፈጠር ይኼ ሁሉ

[27] Tertullian, On the Apparel of women, Book 1 Chapter 1

ችግር መች ይፈጠር ነበር? በቀጣይ ገጾች የሴት ልጅ ዕዳ ጽሕፈት የሆነውን የዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት የበለጠ ከፍተን እንቃኘዋለን፡፡

## • የሰማዩ ይሁዳ

'ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ' ሔዋንን ያሳታት እጅግ በሚያስፈራ አውሬ ውስጥ ሆኖ አልነበረም፡፡ ራእይ ፲፪፥፱ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እንዳለው :-

> 'ሰይጣን መልአክ መስሎ አልመጣም ወይንም
> እንደ ገዳመ ቆርንቶስ ሰው ሆኖ አልተገለጠም።
> እጅግ ግዙፍ በሆኑት በብሔሞትና ሌዋታን
> አምሳልም ወደ እነርሱ አልመጣም'[28]

በሾለ ጥርስ በሚያስፈራ ገጽ ወደ እርስዋ የመጣ ልዩ አውሬም አልነበረም፡፡ ለነገሩ እጅግ የሚያስፈራ አውሬም ሆኖ ቢሆን አዳምና ሔዋን ከውድቀት በፊት ፍርሃት አልነበረባቸውም፡፡ በጥንተ ተፈጥሮ አራዊት አዳምን ይፈሩ ነበር እንጂ 'የትኛውም አውሬ አዳምና ሔዋንን አያስፈራቸውም ነበር'[29]

---

[28] St. Ephrem the Syrian, Commentary on Genesis,
[29] St. John Chrysostom, On Genesis, Homily 16

ሰው ወደ አዳማዊ ቅድስናው ሲመለስም ከአራዊት ጋር አብሮ መሆን እንደሚቀልለው የብዙ ቅዱሳን ሕይወት ምስክር ነው፡፡

'ትሑትና ቅዱስ ሰው በዓተኛ አውሬዎችን ሲቀርባቸው ሲመለከቱት አውሬነታቸው ይገራል። እንደ ጌታቸውም ያዩታል። በፊቱ አጎንብሰው እግሩን ይልሳሉ። አዳም በገነት ሳለ ስም ሲያወጣላቸው የነበረውን መዓዛ ከእርሱ ሲወጣ ያሸትታሉ' ይላል ይስሐቅ ዘነነዌ [30]

ሰዎች ከእንስሳት ጋር በቃል እስከመነጋገር በሚደርሱበት በዚያ የፍጹምነት ዓለም ውስጥ ሰይጣን ወደ ሔዋን የቀረበው የሰው ልጅ አሁን ውሻን በሚያቀርብበት የታማኝነት ልክ ለአዳምና ሔዋን ቅርብ በሆነው ዕባብ ነበር፡፡

'የዛሬውን እባብ አታስቡ ፤ ዛሬ ከእባብ እንዴት እንደምንሸሽና እንደምንጸየፈው አድርጋችሁ አታስቡት። ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም። እባብ የሰውን ልጅ ቀርበው ከሚያገለግሉ እንስሳት አንዱ ነበረ። ከሰው ጋር ያለው ጠላትነት የመጣውም ከእርግማን በኋላ ነው' ይላል አፈወርቅ፡፡

አባ ዮሐንስ ዘደማስቆም ፡-

[30] Isaac of Nineveh, Ascetical Homilies 77

'ዕባብ ከእራዊት ሁሉ ለሰው የቀረበ ነበረ። ባማረ አካሔዱ ቀርቦ ሰውን ያነጋግረው ነበር ፤ በአታላይነቱም ለሰው የባሰውን ክፋት አስተዋወቀ'[31]

ምዕራፉ ሲጀምር 'እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ' ብሎ ይጀምራል፡፡ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ በተኩላዎች መካከል እንደ በግ ሲልካቸው 'እንደ ርግብ የዋህ ፤ እንደ እባብ ብልሆች ሁኑ' ብሎ ከየእንስሳቱ አንድ አንድ ምሳሌነትን ሲጠቅስ እባብን በብልህነት አንሥቶታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም 'ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ' በማለት የእባብን ተንኮለኛነት ገልጾአል፡፡ ከተንኮል ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ እባብን የተሳለ አንደበት የነበረው መሆኑን 'ምላሳቸውን እንደ እባብ ሳሉ' በማለት በንፅፅር ይናገራል፡፡ በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እባብ ሲናገርም ፤ እባብን ሲራገምም በአብዛኛው በእባብ ሥጋ ተሰውሮ የሰውን ልጅ ከገነት ያስወጣውን ዲያብሎስን በእባብ በኩል እየወከለም ጭምር ነው፡፡ ማቴ. ፲፥፲፮ ፤ ፪ኛ ቆሮ. ፲፩፥፫ ፤ መዝ. ፻፵፥፫

[31] St. John of Damascus Exposition about Paradise 11,25

ሆኖም አባብ ተንኮለኛና ብልህ ነው ሲባል የአባብ ተንኮለኛነትና ብልህነት 'ከምድር አውሬ ሁሉ' ብቻ መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡ አባብ በጥበብ የሚበልጠው ማሰብ የማይችሉትን እንስሳት ነው እንጂ ከጠቢቡ የሰው ልጅ ጋር የሚደራረስ አይደለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ 'ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚብሔር ሞኝነት ይጠበባል' እንዳለው ከእንስሳት ጥበብም ይልቅ የሰው ልጅ ሞኝነት ይጠበባል፡፡ ከሰው መካከል ሞኝ የሚባለው ሰውዩ እንኳን ከእንስሳት ሁሉ ጠቢብ ከሆነው እንስሳ በላይ ጠቢብ ነው፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ 'የአባብ ተንኮለኝነት ከአዳምና ሔዋን ጥበብ ጋር ሲነጻጸር ሞኝነት ነበረ' እንዳለው ነው፡፡[32]

አባብ ከሔዋን ጋር ያደረጉት ምክክር ወደ ዝርዝር ይዘቱ ሳንገባ ውይይቱ በራሱ ስሕተት ነበረ፡፡ ሐዋርያው 'አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል' እንዳለው ሔዋን ከአባብ ጋር እንደ ባልንጀራ አፍ ለአፍ መግጠምዋና ከዚያም አልፎ ከአባብ ምክር መቀበልዋ ብቻ በራሱ አሳፋሪ ስሕተት ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፲፭፥፴፫

ሔዋን ልትፈጠር ስትል እንደ ምክንያት የተነገረውን ቃል አስታውሱ፡፡ አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም ካወጣላቸው በኋላ 'ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር' ይላል፡፡ ለአዳም

[32] St. Epraim the Syrian, Commentry on Genesis, 3

እንደ እርሱ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ረዳት ከፍጡራን ሁሉ ስላልነበረው ለእርሱ ረዳት ልትሆን የምትችለዋን ሔዋን ከጎኑ አጥንትን ወስዶ አበጃጅቶ ወደ እርሱ አመጣለት፡፡ በዚህም ለሰው ልጅ ረዳትና የአሳቡ ተካፋይ መሆን የሚችለው እንደርሱ ያለ ረዳቱ የሰው ልጅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከአዳም ጋር ረዳቱ ልትሆን የተፈጠረችው ሔዋን ግን እንስሳውን እባብ ረዳትዋና አማካሪዋ አድርጋ ራስዋን አዋረደች፡፡ ዘፍ. ፪፡፳

ቅዱስ ኤፍሬም ይህን ሲገልጽ ፡-

> 'የሚያነጋግራት እባብ የእርስዋ የተፈጥሮ ወገን ነበረን? አልነበረም። እባብ ለእርስዋ ተገዢ ከሆኑት እንስሳት ወገን ነበረ። ሔዋን ግን የእባቡን ቃል አመነች። የእርሱም ምክር ከፈጣሪዋ የበለጠ ነው ብላ ተቀበለች። ይቅር ሊባል በማይችል መታለል ተታልላ ነበር' ይላል፡፡[33]

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ደግሞ ፡-

> 'ሴት አገልጋይ እመቤትዋን እንደምትመክር ለእርስዋ እንደሚቀና ሆኖ እባብ መከራት። ካሳታት በኋላ ግን የልጆችዋን እግር ለመንከስ የሚጠባበቅ ጠላት

[33] St. Epraim the Syrian, Commentary on Genesis 3

ሆናት' ሲል የሔዋንና የእባብን ወዳጅነት ከእመቤትና ደንገጡር ቅርበት ጋር አነጻጽሮታል፡፡

ሔዋን ከእባብ ጋር በነበራት ቆይታ የከበረውን የእግዚአብሔር ቃል ዘርዝራ ለእባብ አስረድታለች፡፡ ከዚህ ብሉ የሚል ትእዛዙንና ከዚህ አትብሉ የሚለውን ሕጉን በረድፍ በረድፍ አድርጋ እያስቀመጠች አምላክ ላከበረው ፍጡሩ ለአዳም የነገረውን ምሥጢር ለተናቀው እንስሳ ስታብራራ ዋለች፡፡ ከፍ ብለን ባየነው በአባ ጊዮርጊስ አገላለጥ መነጽር እንኳን ብናየው አንድ የንጉሥ ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ንጉሡ የነገረውን ዜጎችን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አደገኛ የሞት ሽረት ምሥጢር ሁሉ ዘርዝሮ ለቤቱ አገልጋይ አያወራም፡፡ ሔዋን ግን የሰው ልጅን የዘለዓለማዊነትና መዋቲነት ዕጣ ፈንታ የሚወስነውን መላውን ዓለም አደጋ ላይ የሚጥል ምሥጢርና አምላካዊ ሕግ ለእባብ መተንተን ጀመረች፡፡

በወንጌል :-

'በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ' ተብሎ ተጽፎአል፡፡ ማቴ. ፯፥፮

'ሔዋን ግን መለኮታዊውን ምሥጢር በእባብና ዲያብሎስ ፊት ጣለች' እባብም የእግዚአብሔርን ትሞታላችሁ የሚል ቃል በእግሩ እንደ ሐሰት ረገጠው:: 'እርስዋንም ባልዋንም ተመልሶ ነከሳቸው' ይላል አፈወርቅ:: [34]

ለመሆኑ ከእባብ ጀርባ ተደብቆ የሚልከሰከሰው ማን ነው? እንዲህ በእባብ ውስጥ ተደብቆ ለሰው ልጅ ክፉ ምክር የሚመክረው እርሱ ማን ነው? እንደበት ካልተዋሰ ማውራት የማይችለው በእባብ የጀመረውን ክፋት በየዘመናቱ በየፍጡራኑ እየገባ ክፋትን የሚዘራው ጠላት እርሱ ማነው?[35] ሰይጣን አይደለምን?[36] በእርግጥ ሰይጣንን እንዲህ ያከፋው ምንድርን ነው? በሰው ልጅስ ላይ ያነሣሣው ምንድርን ነው?

---

[34] St. John Chrysostom, Commentary on Genesis, Homily 16

[35] ዲያቢሎስ የወደቀ ረቂቅ መንፈሳዊ መልአክ እንደመሆኑ በወደደው ነገር ላይ ገብቶ የማደር ችሎታ አለው:: በዚህ ምክንያት በሰው ልጅ ላይ አድሮ የሰዎችን አንደበት ቀምቶ መለፍለፍ ፤ በእንስሳትም ላይ በእባብ ፤ በአሳማ ወዘተ እያደረ የደመ ነፍስ እውቀታቸውንም ቢሆን መቆጣጠር ፤ ሌላው ቀርቶ በድንጋዩ ፤ በእንጨት ፤ በዛፉ እያደረ ጣዖት ማስመለክን ይወድዳል:: በተቃራኒው ቅዱሳን መላእክት ይህን ማድረግ ቢቻላቸውም እንኳንስ በእንስሳ በሰው ልጅም ላይ አድረው አንደበቱን ልቆጣጠር አይሉም:: ይህን ማድረግና የእግዚአብሔር ማደሪያ በሆነው በሰው ልጅ ላይ ማደር የእግዚአብሔርን ዙፋን መጋፋት ስለሆነ ቅዱሳን መላእክት የሰውን ልጅ ሰውነት አክብረው ይጠብቃሉ እንጂ አያድሩበትም:: /ርቱዐ ሃይማኖት ምዕራፍ ፪/

[36] መጽሐፈ ሄኖክ በእባብ ተሰውሮ ሔዋንን ስላሳተው ጋኔን ሲናገር 'ስሙ ጋርድኤል ነው ... ሔዋንን ያሳተው እርሱ ነው' ይላል:: ሄኖ [illegible]

አንዳንድ ሰዎች 'እግዚአብሔር ሰይጣንን ባይፈጥረው ኖሮ እኮ ይኼ ሁሉ ችግር አይፈጠርም ነበር' ብለው በራሳቸው ድምዳሜ ይተክዛሉ፡፡ ሰይጣንን የፈጠረው ግን እግዚአብሔር አይደለም፡፡ 'ሆይ ጉድ ታዲያ ማን ፈጠረው ልትል ነው?' ካልከኝ ሰይጣንን የፈጠረውማ ራሱ ሰይጣን ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረው ሰማልያል ወይም ሳጥናኤል የተባለ እጅግ የተዋበ ሊጋርድ የተቀባ ኪሩብ ፤ ብሩህመጋ የአጥቢያ ኮከብ የሆነ መልአክን ነበር፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረው በዔድን ገነት የነበረ ፤ የከበረ ዕንቁ ልብሱ የሆነለት ፤ በእግዚአብሔር ተራራ የሚኖር አለቃን ነበረ፡፡ 'ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ' ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር የፈጠረው እጅግ የተዋበ በቅድስና የተሸለመ መልአክን እንጂ ሰይጣንን አልነበረም፡፡[37] ሕዝ. ፳፰፥፲፭

እናት ልጅ ወልዳ በኋላ ልጅዋ አድጎ ሌባ ቢሆን እርስዋ ልጅን እንጂ ሌባ ወለደች ልትባል እንደማይገባ እግዚአብሔርም ፍጹም መልአክን ፈጠረ እንጂ ራሱን ወደ ረከሰ የፍጥረት ከሳሽነት በነፃ ፈቃዱ የለወጠው ራሱ ሰይጣን ነው፡፡ ቅዱስ ሆኖ ተፈጥሮ የረከሰው ፤ ክቡር ሆኖ ተፈጥሮ የተዋረደው እርሱ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ሳጥናኤልን

[37] St. Basil the Great, On How God is not the cause of the evil, 8 pg 31, 608

እንጂ ሰይጣንን አልፈጠረም፡፡ የሚያብከነክነው ካለ መጽሐፍ ቅዱስ ሞትንም የፈጠረው እግዚአብሔር አይደለም ይላል፡፡ ታዲያ ማን ፈጠረው? ካልከኝ ጠቢቡ ሰሎሞን ይመልስልሀ :-

> እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና ነዋሪ ይሆን ዘንድ ሰውን ፈጥሯልና ... እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በቃል ጠሩት ፤ ባልንጀራም አደረጉት ፤ በእርሱም ጠፉ" ጥበብ ፩፡፲፫-፲፮

ሰማልያል የተባለው መልአክ ስለምን ወደቀ? በአጭሩ 'በልዑል እመሰላለሁ' ስላለ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሥፍራ ሊሆን አምላክነትን ፈልጎ መላእክቱንም ሊያስታቸው ስለሞከረ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ለዚህ አሳዛኝ መልአክ እንዲህ ሲል ሙሾ ያወርድለታል፡-

> አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንደት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ! አንተን በልብህ። ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ፤ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ' ኢሳ. ፲፬፡፲፪-፲፬

ሌላው ዐቢይ ነቢይ ሕዝቅኤልም እንዲህ ሲል ስለ ሳጥናኤልና ተከታዮቹ ጽፎአል :-

'በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ በምድር ላይ ጣልሁህ ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ። በበደልህ ብዛት በንግድህም ኃጢአት መቅደስህን አረከስህ ስለዚህ እሳትን ከውስጥህ አውጥቻለሁ እርስዋም በልታሃለች፤ በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ አድርጌሃለሁ'' ሕዝ. ፳፰፥፲፯-፲፰

ሰይጣን በትዕቢቱ የወደቀው ለብቻው አልነበረም:: ልብ አድርጉ ትዕቢት መልአኩን ሰይጣን ያደርጋል ፤ ትሕትና ደግሞ ሰይጣናዊ ሕይወት ያለውን ሰው መልአካዊ ያደርጋል:: ሰይጣን የወደቀው በዝሙት አይደለም:: በስካር በጥጋብም አይደለም:: ከተፈጠረ እስካሁን በአፉ እህል ያልዞረ ጾመኛ ነው:: እርሱን የጣለው ትዕቢት ነው:: ያለ ትሕትና ድንግልናን የሚጠብቅ ሰው ከሰይጣን አይሻልም ፤ ትዕቢተኛ ጾመኛም የሱ ቢጤ ነው:: ለአባ ሙሴ ጸሊም እንደተነገረው 'አንተ ትጾማለህ ፤ ሰይጣንም አይበላም። አንተ ትተጋለህ ፤ ሰይጣንም እንቅልፍ አያውቅም። ሰይጣንን ድል ልትነሣበት የምትችለው በእርሱ ዘንድ የሌለ ነገር ትሕትና ብቻ ነው'

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ይላል:-

> 'ሰይጣን ከሰማይ የወደቀው በዝሙት ፣ በስርቆት ወይም በማመንዘር አይደለም።[38] በትዕቢቱ ነው።
> 'ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ ፤ ዙፋኔንም ከመላእክት በላይ አደርጋለሁ ፤ በልዑልም እመስላለሁ' ስላለ ነው'[39]

ነፃ ፈቃድ (ግእዛን) ከሰው ልጅ በፊት ለመላእክት የተሠጠ ጸጋ ነበር፡፡ እግዚአብሔር እንደፈጠራቸው ከመላእክቱ ራሱን የሰወረውም የተሠጣቸውን ነፃነት ተጠቅመው ፈጣሪያቸውን እንዲያውቁና መርጠው እንዲያምኑበት ነበር፡፡ ሳጥናኤል አስቀድሞ እውነት ባለበት ሥፍራ ላይ ቢፈጠርም እርሱ ግን በተፈጠረበት የእውነት ሥፍራ ላይ ጸንቶ መቆም አልቻለምና በነፃ ፈቃዱ ከነበረበት ቦታ ወጣ፡፡ ጌታችን ይህን ሲገልጽ 'እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም' ብሏል፡፡ ዮሐ. ፰፥፵፬

ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል ፦

> 'ሰው በምን ምክንያት ክፉ ይሆናል? በነፃ ፈቃዱ ምክንያት ነው። ሰይጣንስ ለምን ክፉ ሆነ? እርሱም በነፃ

---

[38] በእርግጥ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አገላለጽ ዲያቢሎስ ያልተሠጠውን መመኘቱም ዝሙት ተብሎ ይጠራል፡፡ እምላክነትን መሻትም ሆነ ሌላ አምላክን ማምለክን መጽሐፍ ቅዱስ ማመንዘር ብሎ ይጠራዋል፡፡ 'የአባቶቻቸውንም አምላክ በደሉ፥ እግዚአብሔርም ከፊታቸው ባጠፋቸው በምድሩ አሕዛብ አማልክት አመነዘሩ' 'በግልሙትናዋም በመቅለልዋም ምድሪቱ ረከሰች እርስዋም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች' የሚሉት ቃላት ስለ ጣዖት አምልኮ የተነገሩ ናቸው፡፡ ፩ዜና ፭፥፳፭ ፤ ኤር. ፫፥፱

[39] St. Athanasius the Great, About Virginity, 5 pg 28

ፈቃዱ ምክንያት ነው። ገብርኤል መልአክ ነው ፤ ከእግዚአብሔር ፊት መቆምን መረጠ። ሰይጣንም መልአክ ነው ከተሠጠው ቦታ ለዘላለም ወደቀ። ነፃ ፈቃድ አንደኛውን በሥፍራው አስቀመጠው ፤ ሌላኛውን ግን በነፃ ፈቃዱ የመረጠው ምርጫ ወደ ምድር ጣለው'[40]

ሰይጣን አሁንም የትዕቢት ጉዞውን ትቶ ቢጸጸት እግዚአብሔር ይቅር ይለው ዘንድ የታመነ አምላክ ነው፡፡ አሁንም ድረስ የቅዱሳን መላእክትም የሠራዊተ አጋንንትም ነፃ ፈቃዳቸው እንዳለ ነው፡፡

'ወመላእክትኒ፡ እመ፡ ፈቀዱ፡ ከመ፡ የአብሉ፡ መባሕት፡ ሉሆሙ፡፡ ለሰይጣናትኒ፡ እመ፡ አፍቀሩ፡ ከመ፡ ይነስሑ፡ ብውህ፡ሉሆሙ፡ከመ፡ይኩን፡ኮነኔ፡በድሉወተ'

'መላእክትም ሊበድሉ ቢወዱ ሥልጣን አላቸው ፤ ሰይጣናትም ንስሓ ሊገቡ ቢወዱ ተሠጥቷቸዋል ፤ ይህም ፍርድ በሚገባ ይሆን ዘንድ ነው'[41]

ችግሩ አጋንንት ንስሓ ይገቡ ዘንድ ትዕቢታቸው አይፈቅድላቸውም፡፡ ደግነቱም ቅዱሳን መላእክትም ይበድሉ ዘንድ ትሕትናቸው አይፈቅድላቸውም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው የማያቋርጥ የምስጋና አንድነት ለኃጢአት አሳብ ፋታ አይሠጣቸውም፡፡

[40] St. Basil the Great, on the human condition, Homily 3, SVS 2005

[41] ትርጓሜ አሪት ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ግእዝ ብራና

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ሰይጣንን ለምን ይቅር አይለውም፣ ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ሰይጣን አልተቀበለም እንጂ ኢትዮጵያዊትዋ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራም ለብዙ ክፋት ምንጭ የሆነውን 'ሰይጣንን ማርልኝ' ብላም ጸልያለች፡፡ እግዚአብሔር ምሕረቱ ለሁሉም ቢሆንም ሰይጣን ራሱ በነፃ ፈቃዱ 'ማረኝ' እስካላለ ድረስ አስገድዶ ምሕረትን አይሠጠውም፡፡ 'ምሕረት የሌለው ጠላት' ተብሎ የሚጠራው ሰይጣን ምሕረት የሌለው ለራሱም ጭምር ነውና የጸጸት ምልክትን አሳይቶ አያውቅም፡፡ ስለዚህ ጥያቄው መሆን ያለበት 'እግዚአብሔር ሰይጣንን ለምን ይቅር አይለውም?' ሳይሆን 'ሰይጣን ለምን እግዚአብሔርን ይቅር በለኝ አይለውም?' ነው፡፡

ዲያብሎስ በሰው ልጅ ላይ ሲቀልድ ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል ራሱን እንደተበዳይ መሳልና የሰው ልጆች የእርሱ ተቆርቋሪ እንዲሆኑ ማድረግ በመሆኑ ሰይጣን እንዲያው ዝም ብሎ የሚያሳዝናቸው አንዳንድ ሰዎች ተፈጥረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ራሱን ከማዕረጉ እንደተሻረ የመላእክት ሠራዊት አባል ሳይሆን ከእግዚአብሔር በተቃራኒ የቆመ ሌላ አምላክ አድርጎ ራሱን በማግዘፍ በብዙ ሰው ልብ የውሸት የምንታዌ (dualism) ምስል ተክሎአል፡፡ ሰይጣን የእግዚአብሔር አቻ ተገዳዳሪ ኃይል ሳይሆን ከመላእክት ሠራዊት መካከል የነበረ ከክብሩ

የተዋረደ መልአክ ብቻ ነው፡፡ ሲአልም የሰይጣን እስር ቤቱ እንጂ ግዛቱ አይደለም፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ 'እግዚአብሔር ለምን ጨርሶ ሰይጣንን አያጠፋውም? እርሱ ከጠፋ ሁሉም ችግር አብሮ ይጠፋ የለምን?' ብለው ይጠይቃሉ፡፡ እግዚአብሔር ይህን ማድረግ የሚቻለው ቢሆንም የማያደርግባቸው አምላካዊ ምክንያቶች አሉት፡፡ እግዚአብሔር የተቃወሙትን ሁሉ ከመኖር ወደ አለመኖር ብን ትንን አድርጎ የሚያጠፋቸው ቢሆን ኖሮ እርሱን ማምለክ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ይሆናል፡፡ የቀሩት መላእክትም እግዚአብሔርን በማመን የሚጸኑት በፍላጎታቸው ሳይሆን እንደ ሰይጣን ጨርሶ ላለመጥፋት ፈርተውም በሆነ ነበር፡፡

ከዚያ ውጪ ሰይጣንና አጋንንቱ ፍርድ የሚጠብቁ 'ኃጢአት ያደረጉ መላእክት' ናቸው፡፡ ፪ጴጥ. ፪፡፬ ኃጢአትን ያደረጉትን ሁሉ ወዲያው እልም አድርጎ ሊያጠፋ ፈቃዱ ከሆነ ይህ አሠራር 'ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን' የምንል የሰው ልጆችንም ሳይነካን አይተወንም፡፡ እግዚአብሔር በምድር ያሉ በደለኞችንና የካዱትን ሁሉ ጨርሶ ላጥፋቸው እንደማይል ሁሉ በሰማይ የበደሉትን አጋንንት

ከክብራቸው አዋርዶ 'እስከ ታላቁ ፍርድ ቀን ድረስ ጠብቆአቸዋል' እንጂ ጨርሶ ህልውናቸውን ላጥፋ አይልም፡፡ ይሁ. ፩፥፮

## ● ወዳቂና ተነሽ

'እንደ መብረት ከሰማይ የወደቀው'[42] ዕሩቅ፡ውዱቅ (የተራቆተ ፡ የወደቀ) የሆነው ዲያብሎስ እርሱና ሠራዊቱ 'በቀደመው ወራት ያልተሠጣቸውን ሽተው በድለው'[43] ከየነገዳቸው ከክብራቸው ተዋርደው ጾጋቸው ተገፍፎ ወደቁ፡፡[44] እነርሱ ከሰማይ ወደ ምድር በወደቁበትና በተዋረዱበት ወቅት ጨርሶ ከመላእክት ወገን ያልሆነ ሌላ እጅግ ያማረ የተዋበ ፍጥረት በፍጥነት ወደ ፍጹምነት ክብር ሲገሰግስ ሰይጣን ተመለከተ፡፡ ወዳቂው ዲያቢሎስ ተነሺውን አዳም በክብር ከፍ ከፍ ሲል ተመለከተው ፤ በቅንዓት እሳትም ተንገበገበ፡፡

---

[42] ሉቃ. ፲፥፲፰

[43] ተአምረ ማርያም መቅድም

[44] አጋንንት የወደቁት ከተለያየ ነገድ ነው፡፡ ኪሩብ ከነበረው ከሳጥናኤል ጀምሮ ከመናብርት ፤ ከኃይላት ፡ ከሊቃናት ወዘተ የወደቁ አሉ፡፡ቆላ. ፪፥፲፭ ፤ ይሁ. ፩፥፮ እንደየወደቁበት መዓርግ ክፋታቸውም የዚያን ያህል ይለያያል፡፡ 'ከእርሱ የከፉትን ሌሎችን ሰባት አጋንንት ከእርሱ ጋር ይይዛል' 'ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ጦም በቀር አይወጣም' የሚለው ስለእነርሱ ነው፡፡ ሉቃ. ፲፩፥፳፮ ፤ ማቴ. ፲፯፥፳፩

በአምላኩ አርአያና አምሳል የተፈጠረ ፡ ከምድር አፈር ተገኝቶ ከመላእክት እጅግ በጥቂት የሚያንስ ፡ ታናሽ ሲሆን ታላቅ የሆን ግሩምና ድንቅ ፍጥረት ሲያይ የወደቀው መልአክ ተቆጣ፡፡ 'በሰው መፈጠርም ቀና'[45] 'የሰው ልጅ ከመላእክት በሚያንስ ደካማ ሥጋ ተፈጥሮ ታላቅ ክብርን ሲጎናጸፍ ሲያየው በቅናት ተሸነፈ'[46] ሊገዳደረው በማይችለው በፈጣሪው ላይ እንኳን ለመቅናት ድፍረት የነበረው ዲያብሎስ አዳምን ሲያይ ለአንተማ አላንስም በሚል ትዕቢት በቅናት ተነሣ፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን በጥበብ ፪፥፳፬ ላይ ፦ 'በዲያብሎስ ትንዓት ሞት መጣ ወደዚህ ዓለምም ገባ' እንዳለው 'እርሱ ከመላእክት መካከል ተወርውሮ መጣሉን እያየ ምድራዊው አዳም ቀስ በቀስ ወደ መላእክት ኅብረት ሲወጣ ማየትን መቋቋም አልቻለም' [47]

በሰው ክብር የቀናው ዲያብሎስ እርሱ እንደወደቀ የሰውን ልጅን ሊጥል በቁጣ ተነሣ፡፡ ወደ ሔዋን መጥቶ አሳቢ መስሎ ሲያታልል 'እንደ እግዚአብሔር እንድትሆኑ' ብሎ ዋሸ እንጂ ሰይጣንስ የፈለገው የሰው ልጆች እንደ እግዚአብሔር እንድንሆን ሳይሆን እንደ እርሱ እንድንሆን ነበር፡፡ እርሱ አምላክ መሆን እንደሻተ እንድንሻ ፡ እርሱ

[45] St. Irenaeus, Against Heresies, Book V, Ch.40.3
[46] St. John Chrysostom, On Genesis, Homily 22.2
[47] St. Basil the Great, On the Human Condition.

እንደተዋረደ እንድንዋረድ ፤ እርሱ ከሥፍራው እንደተባረረ እንድንባረር ፤ እርሱ እንደተራቆተ እንድንራቆት አስቦና አቅዶ ነበር ፤ ይህንም አሳክቶአል፡፡

'ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ' ሲል አምነን ተቀብለነው እንጂ እርሱስ እየሸነገለን ነበር፡፡ እውነት ከአፉ አይወጣም እንጂ እርግጡን ቢናገር ኖሮ ትክክለኛው አሳቡ 'እንደ እግዚአብሔር እንድትሆኑ ከዛፉ ፍሬ ብሉ' ሳይሆን 'እንደ እኔ እንድትሆኑ ከዛፉ ፍሬ ብሉ' ነበር፡፡ ሊመክረን የመጣውም ወድዶን ሳይሆን ጠልቶን ነበር፡፡

'በመዓ፡ ወጽአት፡ እመዐዛግብቲሃ' ያለው ጻድቁ ሄኖክ ይህን አብራርቷል፡፡ 'ኃጢአት ከማደሪያዎችዋ ከአጋንንት ተገኘች ፤ ያልወደደችው የሔዋንንና የአዳምን ልቡና አገኘች ፤ ዝናም በምድረ በዳ ጠል በተጠማች ምድር እንዲያድር እርስዋም በእነርሱ አደረች' 'ኃጢአት ከማደሪያዎችዋ ከአጋንንት ተገኘች' የሚለው ቃል ሰይጣን በራሱ ኃጢአትን የፈጠረ ኃጢአተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ድንጋይ ከድንጋይ ሲጋጭ እሳት እንደሚፈጠር ሰይጣን ኃጢአትን ከራሱ አመነጨ እንጂ እርሱን ያሳተው ሌላ ሰይጣን አልነበረም፡፡'ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል' ይላል ወንጌል፡፡ ሄኖክ ፲፪፥፫ ፤ ዮሐ. ፰፥፵

ሰይጣን ወደ ሔዋን ለማሳት ሲመጣ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ ነበር ፤ ይደንቃል! መጽሐፍ ቅዱስን አስተውሎ ያነበበ ሰው ሰይጣንን እንዲሁ ሲሽሎከለክ ፤ የሌሎችን አንደበት እየዞረ ሲዋስና ራሱን ሲደብቅ ያገኘዋል፡፡ በባቢሎን ንጉሥ ውስጥ ሲሸሸግ ፤ በጢሮስ ንጉሥ ውስጥ ሲያድር ፤ በፋርስ መንግሥት አለቃ ተመስሎ ገብርኤልን ሲቋቋም ፤ በምድረ በዳ ነፋስ ተመስሎ የኢዮብን ቤት ሲመታና በብዙዎችና ሌዋታን ተመስሎ የኢዮብን ሥጋ ከአጥንቱ በፍርሃት ሲያላቅቅ ...

... በሐዲስ ኪዳንም አንድ ጊዜ በጴጥሮስ አድሮ 'አይሁንብህ' ሲል ፤ አንድ ጊዜ በይሁዳ አድሮ ጌታን ሲያሻሽጥ ፤ በአይሁድ አድሮ ሲያስጨክንና ሲያስገርፍ ፤ በብርሃን መልአክ ተመስሎ ራሱን ሲለውጥ ፤ በሐናንያ ልብ ገብቶ መንፈስ ቅዱስን ሲያታልል ሲሞክር ፤ ጳውሎስን ከአገልግሎቱ ሲያዘገይ ፤ ለጳውሎስ የሥጋ መውጊያ ሆኖ ጎኑን ሲወጋ ፤ የጢሞቴዎስን ሆድ ሲቆርጥ ፤ በማይታዘዙት ልጆች ላይ ተቀምጦ ሲሠራ እንዲሁ እንደተወነና ዘመኑን ፈጀ፡፡[48]

የሚገርመው እኛ አልነቃ አልን እንጂ ሰይጣን ለመጣ ለሔደው ትውልድ ለፈተና የሚቀርብበት መንገድ ብዙም ያልተራራቀና ሔዋንን

[48] ኢሳ. ፲፬፥፲፪ ፤ ሕዝ. ፳፰፥፲፪ ፤ ዳን. ፲፥፲፫ ፤ ኢዮ. ፩፥፲፱ ፤ ማቴ. ፲፮፥፳፪ ፤ ዮሐ. ፲፫፥፳፯ ፤ ፪ቆሮ. ፲፩፥፲፬ ፤ ሐዋ. ፭፥፫ ፤ ፩ተሰ. ፪፥፲፰ ፤ ፪ቆሮ. ፲፪፥፯ ፤ ፩ጢሞ. ፭፥፳፫ ፤ ኤፌ. ፪፥፪

ካሳተበት የፈተና ቅርፅ ብዙም ያልተለየ ነው። በሐዲስ ኪዳን እንኳን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ገና እርግጠኛ ሆኖ ባላወቀበት ጊዜ በምድረ በዳ ሲፈትነው ያቀረባቸው የፈተና ዘዴዎች ሔዋንን ከፈተነበት መንገድ ጋር በጣም ተመሳሳይ መሆኑ ለሰው ልጅ ካለው ንቀት የተነሣ ለፈጠራ ችሎታው ብዙም እንደማይጨነቅና ተጫዋቾቹን እንጂ ጨዋታውን እንደማይቀይር ያሳያል።

ሔዋንን 'ከዛፉ ፍሬ ብሉ' አላት ፤ ክርስቶስንም 'ድንጋዩን ዳቦ አድርገህ ብላ' አለው። ሔዋንን 'ሞትን አትሞቱም' ብሎ አበረታታት ፤ ክርስቶስንም 'ወደ ታች ራስህን ወርውር' መላእክቱን ስለሚያዝዝልህ ሞትን አትሞትም አለው ፤ ሔዋንን የምልሽን ምክር ከሰማሽ 'እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ' አላት ፤ ክርስቶስንም 'ወድቀህ ብትሰግድልኝ የዓለም መንግሥታትን ሁሉ እሠጥሃለሁ' አለው። ሔዋን ድል ተነሣች ፤ ክርስቶስ ግን አሳፍሮ መለሰው። ማቴ. ፬፥፩-፲

ወዳጄ አንተስ ጋር ሰይጣን እባብ ሆኖ መጥቶ አያውቅም? የግድ እባብ ላይሆን ይችላል ፤ ብቻ በሌላ መልክ መጥቶ አነጋግሮህ አያውቅም? ከፈጣሪ በላይ ለአንተ አሳቢ ተቆርቋሪ መስሎ ሆድ የሚያስብስህ ሁሉ እመነኝ እባብ ነው። በሕይወትህ ውስጥ እግዚአብሔር ከሠጠህ ብዙ ዛፎች ይልቅ የከለከለህን ዕፅ ነግሮህ

አያውቅም? በተሠጠህ ብዙ ነገር ከማመስገን ይልቅ የተከለከልከውን ትንሽ ነገር አሳይቶ ሕይወትህን መራራ አድርገህ ከፈጣሪ እንድትጣላ ያደረገህ ሁኔታ ካለ የገነቱ እባብ አንተም ጋር መጥቶአል ማለት ነው:: በተለይ ኑሮህ ገንታዊ ከሆነና ከተደላደልክ እባብ ወደ አንተ እንደሚመጣ ጠብቅ:: የምስጋና ሕይወትህን ሊነጥቅህና ያጣኸውን ብቻ የሚያሳይ መነፅር ሊያጠልቅልህ ወደ አንተ ይመጣል::

ለአንተስ የጋበዘህ ዕፀ በለስ ምንድርን ነው? አንድ ጊዜ ቀምሰኸው ዕድሜ ልክ የምታለቅስበት ነገር የለም? አትብላ ከተባልከው ነገር ውስጥ መጥቶ እያሳየ ያስመኘህ ፣ እንደ ሔዋን ያስጎመጀህ ነገር የለም? ለመብላት የሚያሳሳህ የተከለከለ ፍሬ ባንተ ሕይወት ውስጥ የለም? ካልጠፉ ዛፍ እያየህ በጉጉት የጎመጀህበት ነገር የለም? የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንድትጠራጠርና አስፈላጊነቱ ላይ ጥያቄ እንድታነሣ ያደረገህ ፈተና የለም? የሰው ሚስት ፣ የሰው ባል ፣ የሰው ቤትና ንብረት ፣ የሰው እውቀትና ስኬት እያሳየ ያንተ ያልሆነውን እንድትመኝ የሚያደርግህ ፈተና በአንተ ሕይወት ከመጣ እመነኝ የቀደመው እባብ ወደ አንተም ጎራ ብሎአል::

አንዳንድ ጊዜ 'ብትበሉ ሞትን አትሞቱም መልካምና ክፉውን እንዲታውቁ ብሎ ነው' የሚለውን ምክር እየሰማን እንኳን የሚያናግረን

ሰይጣን ሊሆን እንደሚችል አንጠረጥርም:: ለምሳሌ በድንግልና ለሚኖር ወጣት 'ለምን ከጋብቻ በፊት ሩካቤ አትፈጽምም?' ብሎ ይጠይቀዋል ፤ 'እስካሁን ድረስ ምንም አታውቅም? እንዲያው ምንም ምንም?' ብሎ ያሾማቅቀዋል:: ባልበላት አንዲት ፍሬ ምክንያት እህል ቀምሶ እንደማያውቅ እንዲሰማው ያደርገዋል:: 'እግዚአብሔር እኮ ከዝሙት ሽሹ ዝሙት የሰውነትን መቅደስ ያፈርሳል ብሎአል' ብሎ ወጣቱ ይመልሳል::

እባቡ ይቀጥላል ፤ 'መቅደሱ ስለሚፈርስ አይደለም ፤ ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ማድረግ ምን እንደሆነ እንዳታውቅ ብሎ ነው' ይላል:: ባለትዳሮቹንም 'እስከ ዛሬ ከባልሽ ውጪ ከማንም ጋር ሔደሽ አታውቂም?' እያለ የማመንዘርን ዕፀ በለስ ይጋብዛል:: 'በአንቺ አልተጀመረም' ፤ 'እንደት ይኼንን ሕይወት እስከዛሬ አልተመሰሽውም?' እያለ ያሾማቅቃቸዋል:: ከዚያም ሌላ ቀን ኃጢአት ነው ብለው የተከለከሉትን ፍሬ ጎምዥተው እንዲቀጥፉና ወደ ኋላ መመለስ በማይችሉበት ትዳራቸውን እንዲያበላሹ አድርጓል::

'እስከዛሬ ካልተመሰከው እንደት ታውቀዋለህ። ምኑን ኖርከው ታዲያ ፤ ምን ችግር አለ ብታየው እኮ ዓለም ነው ፤ አንድ ጊዜ ብታደርገው አትሞት!' ይልሃል ፤ በንግግሩ እንኳን እባብ መሆኑን

ካልጠረጠርህ ምክሩን ሰምተህ የዘሙትን ፍሬ ትበላለህ ፤ እንደ አዳምና ሔዋን ራቁትህን መሆንህን ትረዳለህ ፤ ትሸማቀቃለህ። ከዚያ ሲጫወትብህ ይኖራል።

ብዙ ታዳጊ ወጣቶችን በዚህ መንገድ ወደ ሰካርና ሱስ ፤ ወደ አደንዛዥ ዕፅ ባርነት የከተተው ሔዋንን ባናገረበት መንገድ እያናገረ ነው። ሰው ለማወቅ ያለውን ጉጉት በሔዋን የተረዳው ዲያብሎስ ወጣቶችን የገዛ ጓደኞቻቸውን እንደ እባብ እየተጠቀመ ያግባባቸዋል። 'እንዲህ የሚባለውን ጭፈራ ቤት እስከ ዛሬ አታውቀውም? ይህን መጠጥ እስከዛሬ አልሞከርከውም? ይህን ዕፅ እስከዛሬ አልወሰድከም? ታዲያ አንተ ምኑን ኖርከው? ወጣት አይደለህ እንዴ? 'ባክህ እግዚአብሔር ከልክሎአል ፤ ኃጢአት ነው የሚባል ነገር የለም ፤ ሞትን እንደሆነ አትሞትም ፤ እስቲ አንድ ጊዜ እየው ከዛ በኋላ እስከዛሬ መቆየትህም ይቆጭሃል' ብሎ ብዙ የዋሃን ወጣቶችን በማይሽከሙት የመንፈስ ውድቀት ውስጥ ከትቶአቸዋል። በመጠጥና በሌላ ነገሮች ሱስ ዛፍ ውስጥ ራሳቸውን ደብቀው 'አዳም ሆይ ወዴት ነህ?' ብሎ ፈጣሪ ሲጠራቸው 'ራቁቴን ስለሆንሁ ፈራሁ ተሸሸግሁም' የሚሉ የእባቡ መርዝ ምስኪን ሰለባዎች ብዙ ናቸው።

እግዚአብሔር ግን ወደ አዳም እንደመጣ የእባብን ምክር ሰምተው ወደጠፉ ልጆቹ ሁሉ በፍቅር ፍለጋ ይመጣል፡፡ ወደ አዳም ሲመጣ የመጣው የሰው የእግር ዳና እያሰማ ነበር፡፡ ነጎድጓድ እያስጮኸ ፤ መብረቅ እየወረወረ ፤ ዛፎቹን እየገነደሰ በታላቅ ቁጣ ቃል እያስፈራራው አልነበረም፡፡[49] 'በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ' ያለው አምላክ አዳም ወደ እርሱ እንዳልመጣ ሲያይ በማታ እርሱ ሊፈልገው መጣ፡፡ በመለኮታዊ ክብር ምድርን እያንቀጠቀጠ ሳይሆን በሰው የእግር ኮቴ ድምፅ ወደ እርሱ መጥቶ ጠራው፡፡ ኤፌ. ፬፥፳፮

ወዳጄ ይህን መጽሐፍ ማንበብህን ቆም አድርገህ የአንተን እባብ ፤ የአንተን ዕፀ በለስ ለይተህ አስብ፡፡ 'በፍጹም! በየትኛውም መንገድ እባብ በእኔ ሕይወት መጥቶ በጭራሽ አያውቅም' ካልከኝ ደግሞ ትንሽ ዞር ዞር ብለን አንተነትህን ከዚሁ ታሪክ ውስጥ አብረን እንፈልገው፡፡ አንተን ለኃጢአት የገፋፋህ እባብ ባይገጥምህም ምናልባት አንተ በምክርህ እባብ የሆንክበት ሰውስ የለም? እባቡ አንተ ሆነህስ ቢሆን? ያም ባይሆን ሔዋንን ሆነህ ፍሬ ቀጥፈህ ያበላኸው የኃጢአት ተጋባዥ የለህም? ወይም ፍሬ ሰጥታህ ሳትጠይቅ እንደ አዳም የተቀበልካት ሔዋን ፤ የተቀበልሽው አዳም የለ ይሆን?

[49] ልጆቻችንን እንዴት እናሳድግ? ክፍል ፩ ፤ አቤል ሰሎሞን ፤ 2005 ዓ.ም. አዲስ አበባ

እባብንም ሔዋንንም አዳምንም ሆኜ አላውቅም ካልከኝ ግን ያንተን ቦታ ለመጨረሻ ጊዜ ልናገር፡፡ ምናልባት ዕፀ በለስ ሆነህ ይሆን ብዬ እፈራለሁ፡፡ አንተን ለማግኘት ብለው የተማከሩና ከፈጣሪ የተጣሉ ፡ በአንተ ተሰናክለው የወደቁ ፤ በአንተ ተሰናክለው አምላክን ያጡና የሚማረሩብህ ሰዎች በአንተ ሕይወት ካሉ እመነኝ ዕፀ በለስ ነህ ማለት ነው፡፡ ሰዎች አንጋጠው እያዩ ሊቀጥፉህ የሚሹ የኃጢአት ዛፍ ላይ የተጠንጠለጠልህ ፍሬ አንተ ነህ ማለት ነው፡፡ ጌታ በኢያሪኮ ከዛፍ ላይ በፍቅሩ እንደ ቀጠፈው ቁመተ አጭር ፍሬ እንደ ዘኬዎስ ከዛፉ ውረድ ብሎ ለቤትህ መዳን ያድርግልህ እንጂ ሌላ ምን እልሃለሁ?

ምናልባት እንደ እኔ ሁሉም ጋር ራስህን አግኝተኸው ይሆን? ሰኞ እባብ ፡ ማክሰኞ በለስ ፤ ረቡዕ አዳም ፤ ሐሙስ ሔዋን እየሆንህ ትኖር ከሆነም እመነኝ ከአዳምና ሔዋን የበለጠ ምሕረትን የምንሻው እኔና አንተ ነን፡፡ ኃጢአት ሠርተን ብንሸሽግም ከፈጣሪ ዓይን ግን አንሰወርም፡፡ ምክንያቱም የትም ብትደበቅ ፤ በምንም ዓይነት ቅጠል ብትሸፈን እግዚአብሔር ያይሃል፡፡

እርሱ እንደሆን የቱንም ያህል ብትሸሸውም ይከተልሃል፡፡ በአዳም ታሪክ የሆነውን ተመልከት ሰው ከእግዚአብሔር እመልጣለሁ ብሎ ሲሸሽ በመጨረሻ እግዚአብሔር ራሱ ሰው ሆነ፡፡ አንተ ከእርሱ

ስትሸሽ እንተን ሆኖ የሚቀርብህ ጌታን ተመልከተው፡፡ ከራሳችን መሸሽ መቼም እንችልምና አምላካችን ለእኛ ከእኛ የሚቀርብ አምላክ ነው፡፡

በገነት ዛፎች መካከል እንደነበረው አዳም ዕርቃንህን መሆንህንም አስታውስ፡፡ ዕርቃኔንስ አልቀረሁም ካልህ ደግሞ ፡-

> ‘ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህ መሆንህን ስለማታውቅ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ’... ‘እንግዲህ ከወደት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሓም ግባ’
>
> ራእ. ፫፥፲፯ ፤ ፫፥፲፰

## • ከበለስ ሥር አየሁህ[50]

እባብ ወደ ሔዋን ቀርቦ ፡- ‘በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት’ ጌታችን ‘የሐሰት አባት’ ብሎ የጠራው

[50] ይህ ቃል ጌታችን ናትናኤልን ባገኘው ጊዜ የተናገረው ቃል ሲሆን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ የሰው ልጅን የሚመለከት ቃል ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ከበለስ ሥር አየሁህ ማለቱ ዕፀ በለስን በልቶ ጸጋው የተገፈፈው የሰው ልጅ የበለስን ቅጠል ለራሱ ግልድም ማድረጉን ለመግለጽ ሲሆን ‘ኃጢአት ለፍናብህ አየሁ’ ማለትም ነው፡፡ /ትርጓሜ ወንጌል አርባዕቱ ፤ ዘዮሐንስ ፩፥፵፱ ፤ St. Augstine, sermon 174.4/

ዲያብሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈው የመጀመሪያው ንግግሩም ሐሰት ነበረ፡፡ እግዚአብሔር 'ከገነት ዛፍ ሁሉ አትብሉ' አላለም፡፡ እንደ አላዋቂ ሆኖ መቅረብ ሰይጣናዊ ስልት ነውና ጨዋታውን እንዳላወቀ ሆኖ ጀመረ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል መለወጥ ፣ የተናገረው ላይ መጨመር ፣ መቀነስ ፣ ተጠራጥሮ ማጠራጠር ያን ጊዜ የተጀመረ መንገዱ ነው፡፡ እግዚአብሔርንም 'ሁሉን ነገር ከልክሎ ፍጥረቱን መተንፈሻ የሚያሣጣ' ጨቋኝ አድርጎ መሳል የዲያብሎስ አካሔድ ነው፡፡ ዮሐ. ፰፥፵፬

ሔዋን መለሰች 'በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን ፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም'

ሔዋን ለእባብ የእግዚአብሔርን ሕግ ዘርዝራ ተናገረች፡፡ ዕፀ በለስ የተከለከለ ዕፅ መሆኑን ፣ ዕፀ በለስን መብላትም የሚያመጣው ቅጣት ምን እንደሆነ ተናገረች፡፡ ስለዚህ ሔዋን የበደለችው ባለማወቅ አልነበረም፡፡ ሕጉን ጠንቅቃ ታውቃለች ፤ ሕጉን መተላለፍ የሚያመጣውንም ቅጣት ታውቃለች፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኃጢአት መሆኑን እያወቅን የምንሠራው ኃጢአት አለ፡፡ ስለ እግዚአብሔር ቃል ያለን እውቀት ፍላጎታችንን መግታት አቅቶት ሕጉን እየተነተንን ፣ በጥቅሱ

ላይ እየተወያየን እንበድላለን፡፡ 'ሔዋን ሕጉን አልረሳችውም ፤ የበደለችው ስለ ሕጉ እየተወራና ከእባብ ጋር ስለ እግዚአብሔር እየተነጋገሩ ነው' ይላል የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ[51]

ሔዋን ስለ ሕጉ ለእባብ በሠጠችው ማብራሪያ ላይ እግዚአብሔር ከተናገረው ላይ አንድ ቃል ጨምራለች፡፡ እንደሚታወቀው እግዚአብሔር ከዛፉ ፍሬ አትብሉ ብሎ ሕግ ሲሠጥ ሔዋን ገና በአዳም ጎን ውስጥ ነበረች እንጂ ሰው ሆና አልተሠራችም ነበር፡፡

> 'እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። እግዚአብሔር አምላክም አለ፡ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት' ዘፍ. ፪፡፲፮-፲፰

ሔዋን የእግዚአብሔርን ሕግ የሰማችው ከባልዋ ከአዳም ነበረ፡፡ ለእባብ በተናገረች ጊዜ ግን 'አትንኩት አለን' የሚል ቃል ጨምራለች፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ 'ማንም አንዳች ቢጨምር ወይንም ቢያጎድል እግዚአብሔር ከሕይወት ዛፍ ዕድሉን ያጎድልበታል' የሚለው ቃል

ከሕይወት ዛፍ በተባረረችው በሔዋን ተፈጸመ ይላሉ አንዳንድ ተቺዎች፡ ፡ ራእ. ፳፪፡፲፰

ቅዱስ እምብሮስ 'ብዙዎች ትእዛዙ ሲነገር ሔዋን ገና አልተፈጠረችምና የአዳም ጥፋት ነው ይላሉ ምክንያቱም ለሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የነገራት አዳም ነው' ይላል፡፡[52] የአይሁድ ረበናት ደግሞ በትርጓሚያቸው 'ሕጉን እንዳትተላለፍ ካለው ትጋት የተነሣ አዳም ለሔዋን 'አትንኩት አለን' ብሎ ነግሯት ነው ፤ የአዳም የግነት ንግግር ለአባብም መንገድ ከፈተ' በማለት ተወቃሽዋ ሔዋን ሳትሆን አዳም ነው ይላሉ፡፡[53] በእርግጥ 'አትንኩት' የሚለው ቃል እርቆ የማጠር ያህል የሚጠቅም እንጂ ያን ያህል ጎጂ ቃል አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በእጅ እያገላበጡ እያዩ እየዳሰሱ አለመብላት የበለጠ አሳሳችና ሳያስቡትም ሊበሉት እንዲችሉ የሚያደርግ ሁኔታ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ሔዋን ስለ እግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ለአባብ ዘርዝራ ተናገረች፡፡ ስለ ሕጉ ስትናገር 'ከፍሬው የማንበላው ከበላን ስለምንሞት ነው' ብላ ሕጉን የሕይወት መመሪያዋ አድርጋው አልነበረም፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚጠብቁትን ይጠቅማል እንጂ

---

[52] St. Ambrose, Hexameron, Paradise, Cain & Abel, The Fathers of the Church Series Vol. 42

[53] The Legends of the Jews, Vol. 1, Louis Ginzberg, JPSA, 1913, page 71

ለእግዚአብሔር ብለው የሚከፍሉት ዕዳ አይደለም:: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ 'ባሪያህ ደግሞ ይጠብቀዋል በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል' የሚለውን አሳብ ሔዋን አልተረዳችምና 'ሕግጋቱን የምንጠብቀው እኛ አይደለንም ፤ ይልቁንስ ሕግጋቱ እኛን ይጠብቁናል ፤ ለመጠበቅና ለመጠጊያነት ይሆኑናል እንጂ' 'እኮ፡ ንህነ፡ ዘነዓቅቦሙ፡ ለሕግጋት፡ አላ፡ እማንቱ፡ ሕግጋት፡ የዓቅቡነ፡ ለዐቂብ፡ ወለተጸውኖ' ብላ ማስረዳት አልቻለችም:: መዝ. ፲፱፡፲፩

እርስዋ ግን ፈጣሪ ለእኛ ብሎ ከዛፉ ፍሬ ከለከለን በማለት ፈንታ እኛ ለፈጣሪ ብለን ተከለከልን አለች:: 'እንበላ ነበር ምን ዋጋ አለው አትብሉ አለን እንጂ ፤ ለፈጣሪ ብለን ተውነው እንጂ ብንበላስ አንጠላም ነበር' የሚል ድምፀት ባለው ቃል ፈጣሪዋን ለእባብ አማች:: ለፈጣሪ ብዬ ተከለከልሁ ማለትም በራሱ በደስታ ሳይሆን በቅሬታ የመታዘዝ አንዱ ማሳያ ነው:: ጠቢቡ ሲራክ 'ስለ እግዚአብሔር ብዬ ተከለከልሁ አትበል ፤ እርሱ የሚጠላውንም አታድርግ' የሚለው ይህን ነው:: ሲራክ ፲፭፡፲፩

ይህን ማብራሪያ ተከትሎ

'እባብም ለሴቲቱ አላት። ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ

እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ' አላት፡፡

ሔዋን ከእባብ ጋር ንግግርዋን በቁጣ ማቋረጥ የነበረባት ይህን መልስ ስትሰማ ነበር፡፡ እባብ ደፍሮ ከብር ይግባውና የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር የተናገራችሁ ነገር 'ሐሰት ነው' እያላት ነው፡፡ ከአዳም ጎን አጥንት ወስዶ የሠራሽ ፣ በገነት ውስጥ በተድላ ያኖረሽ እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነው ብሎ አንድ እንስሳ ሲናገር ሔዋን ስምታ ዝም ማለትዋ ምንኛ ያሳዝናል?

ሔዋን ሆይ ለምን ዝም ትያለሽ? መልስ እያለሽ መልስ እንደሌላት ለምን ትሆኛለሽ? እንዴት ብትደፍረኝ ነው ፈጣሪዬን በእኔ ፊት የምታማው አትይውምን? የፈጣሪን ቃል ንቂ ትቼ የአንተን የእንስሳውን ቃል እንዴት ልቀበል እችላለሁ? ለፈጠረህ አምላክ ያልታመንክ አንተ ላልፈጠርኩህ ለእኔ እንዴት አሳቢ ልትሆን ትችላለህ? አንተ እንስሳ ሆነህ እኛ ገዢዎችህ ያላወቅነውን ነገር ከየት አምጥተህ አወቅህ? ብትይው አትችይም ነበር?

ሔዋን ለእባቡ 'በዛፍ ፍሬ የባሕርይ አምላክ መሆን የሚገኝ ነገር ከሆነ አንተ በልተኸው አምላክ አትሆንምን? ብትለውም መልስ ነበረ፡፡[54]

[54] መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ ዘፍጥረት ንባቡና ትርጓሜው

እባቡ ከዛፉ ፍሬ እንድትበላ ሲጋብዛት 'እሰቲ አንተ ዓይኖችህ ይከፈቱ ዘንድ ቀድመህ ና ብላ' ልትለው በተገባት ነበር። (ወዓዲ፡ከመ፡ትበሉ፡ እምደለዋ፡ነዓ፡ብላዕ፡ከመ፡ይትከሠታ፡አዕይንቲከ)[55]

ቅዱስ ኤፍሬምም 'ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ' ለሚለው የእባብ ምክር ሔዋን ምን ልትመልስለት ትችል እንደነበረ ሲገልጽ እንዲህ ይላል :-

> ማየት የማልችል ከሆንሁ አሁን የማየውን ሁሉ እንደት ላየው ቻልሁ? በክፋና በደግ መካከል ያለውን ልዩነት የማላውት ከሆንሁ የአንተስ ምክር ክፉ ይሁን ደግ በምን ላውት እችላለሁ? አምላክነት ጥሩ እንደሆነና ዓይን መከፈት መልካም መሆኑን በምን አውቃለሁ? ይህን መረዳት ከቻልሁስ ወደ እኔ መምጣትህ ለምንድርን ነው? ልትለው ትችል ነበር'[56]

እባብ 'እንደ እግዚአብሔር እንድትሆኑ' ብሎ ለሰው ልጅ የአምላክነትን ቦታ እንዲመኙ አቀረበ። በእባብ ውስጥ የተሰወረው ዲያብሎስ እርሱ በወደቀበት ፈተና የሰውን ልጅ ለመጣል ወጥመዱን

---

[55] ትርጓሜ ወንጌል ግእዝ ብራና ዘመርጡለ ማርያም

[56] St. Ephrem the Syrian, Hymns on P[illegible]

ዘረጋ፡፡ ፍጡራንን ማምለክም ያን ጊዜ ተጀምሮ ጣዖት አምልኮ ተስበከ፡፡ ከአዳምና ሔዋን የተወለዱ እነዜውስ እነ አርጤምስ በሚልዮን በሚቆጠሩ ሰዎች እንደ አማልክት ተቆጥረው ታጥኖላቸዋል፡፡ ሰይጣን 'እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ብሎ ብዙ አማልክትን ለዓለም ማስተዋወቁን ጀመረ' ይላል ቅዱስ ቴዎፍሎስ[57] የሰውን ልጅ አምላክ ትሆናለህ ብሎ ከፈጣሪ ያጣላው ሰይጣን ሰውን ከክብሩ አሳንሶ እንስሳውን ፡ ዛፉን ፣ ድንጋዩን እስከማምለክ ድረስ እንዲዋረድ አደረገው፡፡

ሔዋን ግን የእባብን ምክር ያለ ምንም ጥያቄ ሰማች፡፡ በተሠጣት ሰብአዊ እውቀት የእንስሳውን ተንኮል ከመመርመር ይልቅ ዓይንዋ የዛፉ ፍሬ ላይ ተተክሎ ቀረ፡፡ 'ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፣ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች' ለሰባት ዓመታት ስታየው ከምንም ያልቆጠረችው ዛፍ አሁን ግን ያማረ መስሎ ታያት፡፡[58] የሰይጣንን ምክር የሰማህ ዕለት እንደ ሔዋን ሌላ ቀን

---

[57] መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ ፤ ኦሪት ዘፍጥረት ንባቡና ትርጓሜው ገጽ ፬ ፤ St. Theophilos to Autolychus, ANF 1885, Vol. 2, p. 105

[58] በቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜ መሠረት አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ሳይበሉ ትእዛዙን ጠብቀው የቆዩበት ዘመን ሰባት ዓመታት ሲሆኑ በሰይጣን ተፈትነው የወደቁት ከሰባተኛው ዓመት በኋላ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከኃጢአት ፈተና ይከለከል ዘንድ አንድ ሕፃን ሰባት ሲሞላው መጾም እንዲጀምር ታዝዛለች፡፡ ክርስቶስ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ቤተ መቅደስ ከመምህራን እግር ሥር መገኘቱን ለማሰብ ደግሞ አንድ ሕፃን በዐሥራ ሁለት ዓመቱ መምህረ

የናቅኸው ነገር ሁሉ ያስጎመጅሃል፡፡ በጆሮህ የእባብ ቃል አይንቆርቆር እንጂ ዓይንህ በምኞት ይሸነፋል፡፡ ሔዋን የዛፉን ፍሬ ገና ስታየው አማራት ፤ ምግብ መቼስ ሲያዩት ያላማረ ከሆነ ሲበሉት ያቅራል ይባላል፡፡ ሔዋን ግን ስታየው ያማራት ፍሬ ስትበላው አቃራት፡፡

'ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች' የሚለው ቃል ምንኛ ይደንቃል? አንድን ዛፍ መልኩን በማየት ብቻ ከተበላ በኋላ ስለሚያመጣው ውጤት እንዴት ሊታወቅ ይችላል? ጆሮህን ለእባብ ከሠጠህ የምትሰማውን ከማመን ወጥተህ የምታምነውን ብቻ ወደ ማየት ትደርሳለህ፡፡ ሔዋን የእባቡን ቃል በልብዋ ማመን ስትጀምር የዛፉ ፍሬን በማየት ብቻ ሊታወቅ የማይችለው ነገር ሳይቀር እውነት መስሎ ይታያት ጀመር፡፡

'ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ' ሌላ ምግብ ቢሆን ሔዋን የበላሁት ለባሌም አይቅርበት ብላ ለባልዋ በመሥጠትዋ እናመሰግናት ነበር፡፡ አሁን ግን የሠጠችው ከመርዝ የከፋ የነፍስን ሞት የሚያመጣ ፍሬ ነው፡፡ ረዳት ትሁንህ ተብላ ለአዳም የተሠጠችው ሔዋን ረዳቱ በመሆን ፈንታ የሞቱ

ምክንያት ሆነች፡፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ እንዳለ 'አኮ፡ዘኮነቶ፡ረዳኢተ፡ አላ፡ኮነቶ፡ቀታሊተ' 'ረዳትስ የሆነችው አይደለም ፤ ገዳዩ ሆነች እንጂ'[59]

ሔዋን ይህን በማድረግዋ ራስዋን በፈታኝ ቦታ አስቀመጠች፡፡ እርስዋ ለመውደቅዋ እባብን አሳሳችዋ እንዳደረገች እርስዋም ለአዳም የአሳሳችነት ሚናን ተጫወተች፡፡ ሔዋን በሰይጣን ተፈትና ወደቀች ፡ አዳም ደግሞ በሔዋን ተፈትኖ ወደቀ እንደማለት ነው፡፡ በዚህም ሔዋን ራስዋን በኃጢአት ፈተና ሥፍራ አስቀመጠች፡፡ ጠቢቡ ሲራክ 'ጥንቱን ኃጢአት ከሴት ተገኘች ፤ ስለ እርስዋ ሁላችን እንሞታለን' ብሎ ሔዋንን የኃጢአት መገኛ አደረጋት፡፡ ሲራ. ፳፭፥፳፬

እግዚአብሔርም በአሪት ዘፍጥረት ላይ ስለ ሔዋን የተናገረውን ነገር ቆይቶ ስለ ኃጢአት ሲደግመው እናገኛለን፡፡ በዘፍ. ፫፥፲፮ ላይ እግዚአብሔር ሔዋንን በረገማት ጊዜ 'ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል እርሱም ገዢሽ ይሆናል' ብሎ ነበር፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ ላይ ደግሞ ለቃየን ስለ ኃጢአት ፈተና ሲነግረው 'ፈቃድዋ ወደ አንተ ነው ፤ በእርስዋ ንገሥባት' ብሎ የሔዋንን ሥፍራ በሰው ልጅ ደጅ በምታደባ ኃጢአት ተክቶ ተናግሯል፡፡ ዘፍ. ፬፥፯

---

[59] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፣ ኆኀተ ብርሃን ዘዕለተ ቀዳሚት ፲

አይሁዳዊው የእስክንድርያው ፈላስፋ ፊሎም አዳምን በሰው ልጅ አእምሮ ፤ ሔዋንን በሰው ልጅ ስሜታዊ ደመ ነፍስ ፤ ዕባብን ደግሞ በፍትወት ይመስላቸውና፦ ስሜት አስፈላጊ ነገር ቢሆንም ለሕሊና መገዛት ያስፈልገዋል ፤ አለዚያ ፍትወት ያሸንፈዋል' በማለት ሔዋንን በሰው አእምሮ ላይ ከሚመጣ ስሜታዊ ፈተና ጋር አነጻጽሮአታል፡፡[60] ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ሥፍራ 'ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ' ብሎ አዳምን ሲወቅስ በሌላ ሥፍራ ደግሞ 'የተታለለ አዳም አይደለም ፤ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች' ብሎ ሔዋንን ይወቅሳል፡፡ የሐዲስ ኪዳን ሰው ነውና በሌላ ሥፍራ ደግሞ 'ሴት የለም ወንድ የለም ሁሉ በክርስቶስ አንድ ነው' ብሎ ያጽናናታል፡፡ ፩ቆሮ. ፲፭፡፳፩ ፤ ፩ጢሞ. ፪፡፲፫ ፤ ገላ. ፫፡፳፰

ያም ሆነ ይህ እንደ ሔዋን ለባልዋ ምግብ አቅርባ የተወቀሰችና የራስዋንም ሕይወት ያበላሸች ሴት የለችም፡፡ መርዝ በጥብጠው ባሎቻቸውን ያጠጡ ጨካኝ ሴቶች ዜና እንኳን አንድ ሰሞን ጉድ ተብሎ ዝም ይባላል፡፡ ሔዋን ግን ለክፍለ ዘመናት ባልዋን ባበላችው ፍሬ የወቀሳ ዝናም ይወርድባታል፡፡ ምክንያቱም ያንን ዕፀ ራስዋ በልታ ለባልዋ ስታበላ በእርግማን ያደፈረሰችው የሰው ዘርን ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ምንጩ ከተበከለ ውኃው የቱን ያህል ኪሎ ሜትር ቢፈስስ መርዛማነቱ

ሊጠፉ እንደማይችል ሔዋን በዚያን ቀን ሥራዋ በተረገመችው እርግማን ያመጣችው የዘረ ሔዋንን ሕመም ፡ የዘረ አዳምን ድካም ነበረና 'ሔዋን ሆይ ምን አደረግንሽ' እያልን ማዜማችንን እንደሆን እንተውም፡፡

ሔዋን ቀድማ እንደመብላትዋ ቀድማ ዕርቃንዋን እንዴት አልሆነችም? በሚለው ላይ ሊቃውንት የተለያዩ ሃሳቦችን ሠጥተዋል፡፡ መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት 'ሔዋን እኩል አምላክነትን እንዲያገኙ ብላ እኩል እንዲበሉ አድርጋለች ፤ ሰይጣንም ስትበሉ እኩል ብሉ ብሎ መክሯታል' ሲል ሔዋንን ከባልዋ ጋር መንገሥ የምትሻ አሳቢ ሚስት አድርጎ ያያታል፡፡[61]

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ 'ሔዋን ራስዋ በሆነው አዳም ላይ ራስ መሆንን ፈለገች። ሰው በመሆን ታላትዋ ለሆነው አዳም አምላክ በመሆን ታላቁ ልትሆን ቸኮለችና በላች… ሔዋን ከዛፉ ፍሬ እንደበላች እንዳች ነገር ብትሆን ኖሮ አዳም በእርስዋ የደረሰውን አይቶ ይከለክል ነበርና ትጣቱ የሆነው ሁለቱም ከበሉ በኋላ ነው' ይላል፡፡[62] ቅዱስ አምብሮስ ደግሞ 'ሔዋን ዛፉን እንደበላች ዕርቃን መሆንዋን አያየች ለባልዋ መሥጠትዋ ሁለተኛው ኃጢአትዋ ነው ፤ ምናልባት ከገነት ለብቻዋ

እንዳትባረር ፈርታ ሊሆን ይችላል' ይላል ፤ አዳም አላየም ወይ ቢያስኘም፡፡[63] የቅዱስ አምብሮስ ተማሪ የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ ደግሞ 'መጽሐፍ ሔዋን ለአዳም ዕፁን ስትሠጠው ለማሳመን ተናገራ እንደሆነ አልተጻፈም። ሙሴ የተወው ለአንባቢ ነው። ምናልባት እንደበላች አለመሞትዋን ሲያይ ተደፋፍሮ ሊበላ ወስና ይሆናል' ብሏል፡፡[64] ሊቃውንቱ በዝርዝሩ ላይ ቢለያዩም ተቀዳድመውም ሆነ እኩል ሆነው አዳምና ሔዋን ጸጋቸው መገፈፉ ግን እርግጥ ነው፡፡

እግዚአብሔር አስቀድሞ ሕጉን ሲሠጥ 'በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ' ብሎ ነበር፡፡ ሆኖም አዳምና ሔዋን በበሉ ቀን ዕርቃናቸውን ሆኑ እንጂ እዚያው ፍግም ብለው ወድቀው አልሞቱም፡፡ ይልቁንም ዕፀ በለስን ከበሉ በኋላ ለብዙ መቶ ዓመታት ኖረዋል፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር 'በበላችሁ ቀን ትሞታላችሁ' ያለው ለማስፈራራት ብቻ ነበር? ያሰኛል፡፡

በተለምዶ እኛ ሞት ብለን የምንጠራው የነፍስን ከሥጋ መለየት ነው፡፡ ይህ ሞት ግን የመንፈሳዊው ሞት ውጤት ነው፡፡ መንፈሳዊው ሞት ነፍስ ከነፍስዋ ስትለይ ነው ፤ የነፍሳችን ሕይወትዋም እግዚአብሔር ነው፡፡ 'እስመ፡ሞታ፡ለነፍስ፡ርኂቅ፡እም፡እግዚአብሔር' 'የነፍስ

---

[63] St. Ambrose, On Paradise, Chapter 6

[64] St. Augistine of Hippo, Litral meaning of Genesis, Book XI, Chapter 30

ሞትዋ ከእግዚአብሔር መለየትዋ ነው' እንዲል፡፡ ቅዱስ መቃርዮስ ይህን ሞት 'ይህ እውነተኛ ሞት ሲሆን በልብ ውስጥ የተሸሸገ ውስጣዊ ሞት ነው' ብሎ ይገልጸዋል፡፡[65] አዳምና ሔዋን በበሉ ቀን የሞቱት ይህን መንፈሳዊ ሞት ነበር፡፡ ስለዚህ አዳም በበላበት ቀን በነፍሱ ሞተ ፤ ከዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመታት በኋላ ደግሞ በሥጋው ሞተ፡፡

ሔዋን ላይ ወቀሳው በረታ እንጂ አዳምም ከደሙ ንጹሕ አልነበረም፡፡ ነገሩን አስተውለን ያየነው እንደሆን አዳምንም ከሔዋን በላይ የሚያስወቅስ ብዙ ነገር እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔር አዳምን 'አትብላ ካልኩህ ዛፍ በላህን?' ብሎ ሲጠይቀው የሠጠው መልስ 'ረዳት ትሁንህ ብለህ የሠጠኸኝ ሴት ከዛፉ ሠጠችኝና በላሁ' ነበረ፡፡

ከጥበብና ማስተዋል ጋር የተፈጠረው ታላቁ ፍጥረት አዳም እንደ አላዋቂ ሕፃን 'ሠጠችኝና በላሁ' ሲል ተመልከቱ! አዳም ሆይ የተሠጠህን ሁሉ እንዴት ትበላለህ? ርቦህ ነበረ እንዳንል ከውድቀት በፊት እንደማትራብ እናውቃለን፡፡ በዕድሜ ከአንተ የምታንስህ ፤ ከጎንህ በመገኘትዋ ልጅህ ከምትባለው ሔዋን የተሻለ ልታስተውል አይገባህም ነበርን? 'አልትሳ ስለለመነችኝ ፤ ስላባበለችኝ በላሁ' እንኳን አላልህም፡፡ 'ሠጠችኝና በላሁ' ማለት ከአዋቂ የማይጠበቅ ተራ መልስ ነው፡፡

---

[65] St. Macarius of Egypt, On Guarding the Heart 2,15-16

ቅዱስ ባስልዮስ 'አዳም ክፋትን የሠራው በሚያስገድድ ፍላጎት ሳይሆን ካለማሰብ ነበረ'[66] እንዳለው አዳም ሔዋን እጁ ላይ ያስቀመጠችውን ፍሬ ወደ አፉ ለመስደድ ቆይ ጥቂት ላስብበት እንኳን አላለም:: ሔዋን ከእባብ እንደሰማችው ዓይነት ብዙ ማብራሪያም አልጠየቀም ፤ የሠጠችውን ተቀብሎ በላ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ :- 'አዳም ለሔዋን በቀላሉ እጅ እንደሠጠበት መንገድ ከሆነ ያለ ሰይጣንም ቢሆን መበደሉ የማይቀር ይመስላል' ይላል::[67] ቅዱስ ኤፍሬምም በዘፍጥረት ትርጓሜው 'እባብ ባይመጣ ኖሮ አዳም ባልወደቀ ነበር የሚሉ ሰዎች አሉ። ነገር ግን አዳም እባብ ባይመጣ ኖሮ በኤሊ ይሸነፍ ነበር' ብሎ ችግሩ የአሳሳቹ ማንነት ሳይሆን የአዳምና ሔዋን ስኍታንነት መሆኑን ያስረዳል::

የአዳም በደል ከሔዋን የሚከፋበት ብዙ መንገድም አለ:: እንደሚታወቀው የእግዚአብሔርን ከዛፉ ፍሬ አትብሉ የሚል ትእዛዝ ቀድሞ የሰማው አዳም ነበረ:: አዳም ያንን ትእዛዝ በሰማበት ወቅት ሔዋን አልነበረችም:: ስለ ትእዛዙ የሰማችው ከአዳም ነበር:: ልብ አድርጉ ትእዛዙ አዳም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሰማው ሲሆን ሔዋን

[66] St. Basil the Great, On the Human Condition, Homily on Explaining that God is not the Cause of Evil, page 75
[67] St. John Chrysostom, To Stageiron 1.5 page 47

ግን በተዘዋዋሪ የሰማችው ነው:: ስለዚህ ሔዋን ብትበድል በሰው ተሰብካ ነው ፤ አዳም ግን በቀጥታ የተነገረው ሲሆን ለሔዋን የሕግ መምህርዋም ነበረ:: 'የጌታውን ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል ... ብዙ ከተሠጠው ብዙ ይሹበታል' እንዲል ከሔዋን በላይ ከአዳም ብዙ ይጠበቅ ነበር:: ሉቃ. ፲፪፥፵፯

የሚደንቀው በፈተና ጊዜም ሕጉን አስታውሳ የጠቀሰችው ሔዋን ብቻ ነበረች:: 'ሞትን እንዳትሞቱ አትብሉ አትንኩትም አለን' ብላ እባብን ትንሽም ቢሆን ተከራክራለች:: አዳም ግን ስለ ሕጉ እንደ ሔዋን አስታውሶ 'ለምን ቀጠፍሽው? አትብሉ ተብለን የለም እንዴ?' አላላትም:: በራሱ አንደበት የሆነውን ሲናገር 'ሠጠችኝና በላሁ' ነው ያለው:: ምንም እንኳን መጨረሻ ላይ ብትስትም በዚህስ ሔዋን ከአዳም ተሽላ ተገኝታለች::

የአዳም ሌላ ጥፋት ከዛፉ ፍሬ ለምን እንደበላ ለመግለፅ ምክንያት ያቀረበበት አገላለጽ ነው:: 'ረዳት ትሁንህ ብለህ የሠጠኸኝ ሴት ከዛፉ ሠጠችኝና በላሁ' አለ:: 'አጥንትሽ ከአጥንቴ ፤ ሥጋሽ ከሥጋዬ ፤ አንድ ሥጋዬ አካሌ' ብሎ በፍቅር ቃል እንዳልተናገረላት አሁን 'አጥንቴና ሥጋዬ አካሌ ሠጠችኝ' አላለም:: ከእርሱ እንዳልተገኘች ፣ እንዳያት እንዳልወደዳት ሁሉ አሁን ግን ባዕድ አድርጎ

'የሠጠኸኝ ሴት' ብሎ ለፈጣሪ መለሳት:: የሰው ልጅ አመስግኖ የተቀበለውን ነገር አልሆን ሲለው ተሳድቦ እንደሚመልስ በዚህ ታወቀ::

አዳም 'የሠጠኸኝ ሴት' በሚል ንግግሩ የከሰሰው ሔዋንን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ነበር:: አንተ እርስዋን አምጥተህ ባትሠጠኝ ኖሮ እርስዋም አትሠጠኝም እኔም አልበላም ነበር ማለቱ ነው:: እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሲናገር 'እንደ አዳም ቃልኪዳንን ተላልፈዋል በዚያም ላይ ወንጅለውኛል' ያለው አዳም መበደሉ ሳያንስ ፈጣሪውን ስለወነጀለ ነው:: ሆሴዕ ፮፥፯

> 'አዳም 'የሰጠኸኝ ሴት' ማለቱ ዛሬም ድረስ የሰው ልጆች በትዕቢት በሽታ እንዴት እንደሚሰቃዩና ስለ ኃጢአታቸው ፈጣሪያቸውን ተጠያቂ እያደረጉ በጎ ሥራቸውን ደግሞ ለራሳቸው እንደሚሠጡ ያሳያል'' ይላል የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ::[68]

አዳም ሔዋንን 'ሠጠችኝና በላሁ' ብሎ በከሰሰ ጊዜ እግዚአብሔር ሔዋንን 'ለምን ከዛፉ ፍሬ ሠጠሽው?' ብሎ አልጠየቃትም:: እግዚአብሔር የአዳምን ቃል ሰምቶ በሔዋን ላይ የሚፈርድ አምላክ

[68] St. Augstine, Litral meaning of Genesis XI Ch. 35

አይደለም:: ይልቁንስ 'ያደረግሽው ምንድርን ነው?' ብሎ ሔዋንን እንደ አዲስ ጠየቃት:: እያንዳንዱ ሰው የራሱን ታሪክ እንዲተርክ ዕድል የሚሠጥ እንጂ በአንዱ ወሬ ሌላው ላይ የሚፈርድ አምላክ አይደለም:: ስለዚህ 'ያደረግሽውን ሁሉ አዳም ነግሮኛል' ብሎ ሔዋንን ከመገሠጽ ይልቅ ፍትሐዊው ዳኛ ለተከሳሽዋ እንድትናገር ለብቻዋ ዕድል ሠጣት::

ሔዋን ለእግዚአብሔር 'እባብ አሳተኝና በላሁ' አለች:: ይህ ንግግርዋ ከአዳም ንግግር በብዙ እጥፍ የተሻለ ነው:: 'የሠጠኸኝ ሴት' የሚለው የአዳም ንግግር እግዚአብሔርን ከተከሳሾች ቁጥር የሚጨምር ሲሆን 'እባብ አሳተኝ' የሚለው ቃል ግን ፈጣሪን ከመወንጀል የጸዳ ነው:: 'ለሰው ልጆች ተገዢ ይሁን ብለህ የፈጠርከው እባብ አሳተኝና በላሁ' ብትል ኖሮ አዳምን በመሰለች ነበር:: እርስዋ ግን ከእባብ ጀመረች እንጂ 'ያው አንተ የፈጠርከው እባብ' አላለችም::

'አሳተኝና በላሁ' የሚለው ንግግርዋም ከአዳም 'ሰጠችኝና በላሁ' የሚል ንግግር እጅግ በጣም የተሻለ ነው:: ሰጠችኝና በላሁ ሲል ሙሉ በሙሉ ጥፋቱን ወደ ሔዋን የደፈደፈ አነጋገር ሲሆን 'አሳተኝና በላሁ' በሚለው ውስጥ ግን 'እኔም ስቻለሁ ፣ ተታልያለሁ' የሚል የራስን

ጥፋት ማመን አለበት፡፡ ቅዱስ አምብሮስ 'ሔዋን ከአዳም ይልቅ መታለልዋን ተድግ እመነች' ያለው ይህን ነው፡፡[69]

እግዚአብሔር በአዳምና ሔዋን መውደቅ ምክንያት የእርግማንን ቃል በተናገረ ጊዜ አስቀድሞ መናገር የጀመረው በሰው ልጅ ላይ ሳይሆን እባብን በመርገም ነበር፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም በዚህ ውስጥም የእግዚአብሔርን ፍቅር ያደበታል :-

ቅዱስ ኤፍሬም 'አዳምና ሔዋን ሰምተው እንዲፈሩና ንስሓ እንዲገቡ ሲል እግዚአብሔር ፍርዱን እባብን በመርገም ጀመረ'[70] እንዳለ እባብ ቀድሞ የተረገመበት ሁኔታ ለአዳምና ሔዋን ለማሰብ ፋታ የሚሠጥ ነበረ፡፡ በዚህም መሠረት የሰይጣን መሣሪያ የሆነው እባብን 'መናገር እንዳይችል አደረገው ፤ በምላሱ ሥር መርዝን አስቀመጠበት ፤ ወደ አዳምና ሔዋን የተራመደበትንም እግሩን ነሣው'፡፡[71] እባብ ሳይንስም ሳይቀር እንደሚያምነው እግር ያለው ቆሞ የሚሔድ እንስሳ እንዳልነበር እየተሳበ የሚሔድ የምድር አውሬ ሆነ፡፡[72]

---

[69] St. Ambrose of Milan, On Paradse 32

[70] St. Ephrem the Syrian, Commentary on Genesis 3, p.332

[71] Josephus Flavious, Jewish Antiquites, Book 1, Chap. 1, 49-51

[72]ሳይንስ የእባብን እግር በተመለከተ ያለው አሳብ እባብ አራት እግሮች የነበሩት እንስሳ የነበረ መሆኑን የተስማማ ሲሆን እግሮቹን ስላጣበት ምክንያት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተቀመጠውን ምክንያት ሳይሆን በዝግመታዊ ሒደት ምክንያት የጠፉ ነው ይላል፡፡ ከዚያ ውጪ ግን ባለ አራት እግር ለመሆኑ አሁንም ድረስ እባብ ቆዳ ላይ የሚታዩ ምልክቶች ያሉ ሲሆን በእንቁላል

'አባብ የልቡን አይቶ እግር ነሣው' እንዲሉ አበው ወደ ሰው ልጅ በክፋት የተራመደበትን እግር ቀማው፡፡ የሴቲቱንና የእባብ ወዳጅነት ያመጣውን ችግር አይቶአልና እግዚአብሔር 'በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል። አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ' ብሎ ወዳጅነታቸውን ወደ ጠላትነት ለወጠው፡፡ ዘፍ. ፫፥፲፭ ሰውና እባብም አፍ ለአፍ ገጥመው በፍቅር እንዳልተማከሩ በኋላ አንዳቸው አንዳችውን ለመቀጥቀጥ በነፍስ የሚፈላለጉ ደመኞች ሆኑ፡፡

በእባብ አድሮ ሰውን ያሳሳተው ሰይጣን ከሆነ እባብ ስለምን ተቀጣ? የሚል ሰው ካለ ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ይመልሳል ፦

'ይህ ቅጣት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው የማይነገር ፍቅር ማሳያ ነው። ልጁን በጣም የሚወድድ አባት የልጁን ገዳይ ሲቀጣ ልጁ የተገደለበትን ቢላዋ ወይንም ሰይፍ ሰባብሮ እንደሚጥል ሰይጣን ሰውን የገደለበትን መሣሪያ እባብንም እግሮቹን ሰባብሮ ወደ ምድር ጣለው'[73]

አዳምና ሔዋን በዚያች ዕለት በበሉት ያለ መታዘዝ ፍሬ ምክንያት ከክብር ተዋረዱ፡፡ 'እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው የሰው ልጅ ትእዛዙን በመተላለፉ ምክንያት ከመኖር ወደ አለመኖር መጓዝ

ውስጥ ያለ የእባብ ፅንስም አራት እግር ያለው ሆኖ ይታያል፡፡ (Cell Press Journal, Vol. 167, Issue 3, October 20, 2016)

[73] St. John Chrysostom, Homilies on Genesis 17. 6, p 146

ጀመረ'[74] እግዚአብሔር 'ገዢዎች ናችሁ የልዑል ልጆች ናችሁ' ብሎ ያከበራቸውን አዳምና ሔዋን 'ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ፤ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ' ብሎ ከአለቆች እንደ አንዱ እንደ ዲያብሎስ ጣላቸው:: መዝ. ፹፫፥፮-፯ ከፍጥረታት በላይ ሆኖ የተፈጠረው አዳም ከአንዲት የዕፀ በለስ ዛፍ በታች ሆነ:: 'ከበለስ በታች አየሁህ' የሚለው ቃለ ክርስቶስ ኃጢአት ሰፍናበት ከዛፍ ሥር ለተዋረደው አዳም የተስማማ ነበረ:: ዮሐ. ፩፥፵፱

ከፈጣሪው ይልቅ መብላትን የመረጠውን የሰው ልጅ የዕድሜ ልክ የምግብ ጥገኛ አድርጎ ቀጣው:: ወደ ሲኦል ከመግባቱ በፊት በሕይወቱ ሳለ ሆድ ወደሚባል ሲኦል ውስጥ ከተተውና የሰው ልጅ ለሆዱ ሲል የሚንከራተት 'በላቡ በወዙ ጥሮ ግሮ የሚበላ' የለፋውን ያህል የማያገኝና ምድር እሾኽ የምታበቅልበት ምስኪን ገበሬ ሆነ:: ሔዋንንም 'ገዢ እሆናለሁ' ብላ ስለጓጓች የባልዋ ተገዢ እንድትሆን ፤ ደስታዋን ከባልዋ የምትሻ ፈቃድዋም ወደ ባልዋ እንዲሆን አደረጋት:: የምትወልዳቸውን ልጆች ለመከራ የምትዳርግ እናት በመሆንዋ እርስዋም መከራውን ቀምሳ በምጥ ተሰቃይታ የምትወልድ ሆነች::

---

[74] St. Athanasius the Great, On the Incarnation, Chapter 1:4

ወዳጄ አዳምና ሔዋንን በዚያች ዛፍ ፍሬ ምክንያት አምላክነትን ሊያገኙ ፈልገው የሰው ልጆችን ላለንበት የመከራ ዓለም ስለዳረጉን እንማረራለን እንጂ እኔና አንተም ከእነርሱ የባስን እንጂ የተሻልን አይደለንም:: እንዲያውም ትክ ብለን ካየነው እነርሱ ፍሬውን ብቻ በሉ እንጂ እኛስ ቅርንጫፉን ፣ ግንዱን ከነሥሩ ገንድሰን ቀርጥፈን የበላን በደለኞች ነን:: እውነት እነርሱ ከሠሩት እኛ ያልሠራነው ምን አለ?

እግዚአብሔር የከለከለውን መብላት ከሆን እንደኛ የሚበላ አለ? እንዲያውም የብዙዎቻችን ተወዳጅ ምግብ የተከለከለ ፍሬ አይደለምን? አድርጉ ያለንን ከማድረግ ይልቅ አታድርጉ ያለው ላይ ስንረባረብ የምንውለው እኛ አይደለን እንዴ? እባብ እስከሚያሳስተን ድረስ የማንጠብቅ በራሳችን ምኞት ተጣድፈን የተከለከልነውን ዛፍ የምንበላ ፣ እባብ ራሱ 'እነዚህስ ለእኔም አይመለሱም' የሚለን የኃጢአት ፍሬ ደንበኞች ፣ ዕፀ በለስን እየገመጥን ፣ ጭማቂውን እየጠጣን የምንኖር በደለኞችስ እኛ ነን::

ዕፀ በለስን ከበላን በኋላም 'አጥፍቻለሁ' ማለት አቅቶን አዳም 'የሠጠኸኝ ሴት ሠጠችኝና በላሁ' እንዳለ ለኃጢአታችን ተጠያቂነትን ላለመቀበል እግዚአብሔር የሠጠንን ነገሮች ለኃጢአታችን ሰበብ አድርገን 'የሠጠኸኝ ሰውነት' ፣ 'የሠጠኸኝ ገንዘብ' ፣ 'የሠጠኸኝ ውበት' 'የሠጠኸኝ

ሥልጣን' 'የሠጠኸኝ ወላጆች' 'የሠጠኸን ጓደኞች' ኃጢአት አሠሩኝ ብለን የምናመካኝ:: ሰይጣንን ምክንያት አድርገን ጥፋታችንን የማናምን ፡ የአዳምና ሔዋንን ታሪክ እያነበብን እንኳን እንደወደቁት የምንወድቅ እኛ አይደለንምን?

ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴያችን እንዲህ እንዳለ፡-

'አዳምና ሔዋን ሆይ እኛስ እናንተን መንቀፍ አይቻለንም ፤ በእርሱ እየተናገሩበት የራስን አንደበት ለመንቀፍ እንደማይቻል እንዲሁም እናንተ እኛን ናችሁ ፤ እኛም እናንተን ነን። አዳምና ሔዋን ሆይ እናንተን እንዳንነቅፋችሁ ይቅር ባይ ጌታ ባመጣባችሁ መከራ ተጸጽታችሁ ንስሓ ገብታችኋል። አዳምና ሔዋን ሆይ እናንተስ ድናችኋል ቤዛ ሆኖ ባዳናችሁ በጌታ ደም ወደቀደመ ርስታችሁ ወደ ገነትም ገብታችኋል... እኛን ልጆቻችሁን ግን ኃጢአት እንደ እሳት አቃጠለችን። ፍትወትም አነደደችን'

አዳምና ሔዋንን ስንወቅስ ምናልባት 'እኛ እኮ ምንም ኃጢአት ብንሠራም አምላክ ለመሆን ግን አልሞከርንም። እነርሱ ግን አምላክ መሆንን ፈልገዋልና ፍርድ ይገባቸዋል' ብለን እንጽናናለን:: ይሁንንና ይህ ንግግር ራሱ አምላክነትን መፈለግ ነው:: 'አዳምና ሔዋን

አምላክነትን ፈልገዋልና ፍርድ ይገባቸዋል ትላለህ። አንተም በእነርሱ ላይ ስትፈርድ አምላክ መሆንን መፈለግህ አይደለምን?' ይላል አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ:: እኛ እንደ ፈጣሪ ሁልጊዜም ንጹሐንና ምንም እንከን የሌለብን የሆንን ይመስል በሌላው ሰው ኃጢአት ላይ በፈራጅነት ለማውራት ከቸኮልን ሌላውን በደስታ የምንኮንን ከሆንን በፍጥረቱ በሚፈርደው በእግዚአብሔር ቦታ ራሳችንን እያስቀመጥን ነው:: 'ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?' ያዕ. ፬፥፲፪

ወዳጄ አምላክ መሆንን መፈለግ ዓይነቱ ብዙ ነው:: በሁሉ ነገር አዋቂ ፣ በሁሉ ነገር ተጠያቂ ፣ በሰዎች ዘንድ ምንም እንከን የሌለበት መስሎ መታየትን የሚፈልግ ሰውም ሳይታወቀው ፍጡርነቱን ክዶ እንደ አምላክ መሆን እየፈለገ ነው:: ከሰው የሰማውን ወይም ተምሮ ያገኘውን እውቀትና ጥበብ ከእናቱ ሆድ ይዞት የወጣ ያህል የሚኮፈስና ሌሎችን የሚንቅም ሰው ፍጡር መሆኑ ከለከለው እንጂ ራሱን የሚያየው በፈጣሪነት ዓይን ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ዓይነቱን ሰው :-

'አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ

የምትመካ ስለ ምንድር ነው?' 'በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን' ይለዋል:: ፩ቆሮ. ፬፡፯ ፤ ምሳ. ፫፡፯

ውሱን መሆንህን ማመን ካቃተህ ፤ ሁሉን ሊያዝ ሁሉን ሊጨብጥ ካልህ እመነኝ ያለ እባብ ምክር አኃዜ ኵሉ የሆነውን የእግዚአብሔርን የአምላክነት ሥፍራ እየተመኘህ ነው:: ከሁሉም ሰው የበላይ የመሆን ፍላጎት ካለህ ፤ በዙሪያህ ያሉ ሰዎች ከአንተ ፈቃድና ፍላጎት ውጪ እንዲሆኑ የማትፈልግ ከሆንህ ፤ በባሕርይው ልዑልና ሁሉም በእርሱ ፈቃድ የሚኖርበትን ገዢ እግዚአብሔርን እየተገዳደርህ ነውና ራስህን ጣዖት አድርገህ ማምለክ በመጀመርህ 'ከእኔ በተር ሌላ አምላክን አታምልክ' ይልሃል:: ዘጸ. ፳፡፫

ይህ ዓይነቱ ራሱን በአምላክ ቦታ የማስቀመጥ ደዌ የያዘው ሰው ክፋቱ ራሱን እንደ እግዚአብሔር ማየቱ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የማያደርጋቸውንም ነገሮች ማድረጉ ነው:: እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ፤ ነገር ግን የሰውን የእውቀት ውሱንነት አውቆ በትሕትና ከሰው ይነጋገራል:: 'እግዚአብሔር ኃያል ነው ፤ ማንንም አይንትም' እንደሚል የባሕርይ አምላክ ሆኖ ሳለ እንኳን ልዕልናው ትሕትናን አያሳጣውም:: ኢዮ. ፴፮፡፭ ሰው ግን ራሱን በአምላክ ዓይን ከፍ አድርጎ ማየት ሲጀምር

ለማንም አይራራም፡፡ ሁሉን ሰው ይንቃል፡፡ ከእኔ በቀር ማንም አይናገር ይላል፡፡

አምላክነትን መፈለግ እየዘቀጠ ሲመጣ ሰው ራሱን አምላክ አድርጎ ከማሰብ ወርዶ ሆዱን አምላክ ፣ ውበቱን አምላክ ፣ እውቀቱን አምላክ ፣ ገንዘቡን አምላክ እያደረገ አዳምና ሔዋን ላይ ከሚነገረው የባሰ የአምላክነት ጥማት ውስጥ ይገባል፡፡ ወደ ሲኦል ሳንገባ ምድርን ሲኦል ያደረግናትም በዚህ ከአዳምና ሔዋን የባሰ የክፋትና ዐመፅ መንገድ ተጉዘን ነው፡፡

'በከመ፡ምሕረትከ፡እምላክነ፡ወአኮ፡በከመ፡አበሳነ'

'አቤቱ እንደቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን'

## • ስምን አዳም ያወጣዋል

አሁን ደግሞ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ፡፡ ስለ ቀደመችዋ እናታችን ፣ ልጆችዋ ወደ ሲኦል ሲወርዱ እያየች ስለምታዝነው ፣ ለሞት ምክንያት ሆንሽ ተብላ በትውልድ ስለምትረገመው ፣ በገነት ዛፎች መካከል አንገትዋን ስለደፋችው ስለሔዋን ወደመናገር እንመለስ፡፡

‘ሔዋን ሆይ ምን አደረግንሽ?’ በሚል የትውልድ ጩኸት የቆሰልሽው ሕመምተኛዋ እናታችን ሆይ አሁን ደግሞ ስለ ሕመምሽ መናገር ትተን ስለመፈወስሽ ልንናገር ነውና ወደ እኛ ነይ፡፡ እናታችን ሆይ እባቡ ከነገረሽ የሚያታልል ቃል ይልቅ ደስ የሚያሰኝ እውነተኛ ቃልን ልንነግርሽ ነውና ወደ እኛ ነይ፡፡ ከዛፉ በላይ ለዓይን ደስ የሚያሰኝ ለጥበብም መልካም የሆነ ዜና ልንነግርሽ ነውና ሔዋን ሆይ እስቲ ወደ እኛ ነይ፡፡ በልተሽ ስለማትሞቺበት የሕይወት ፍሬና ፍሬውን ስላስገኘችው ዛፍ ልንነግርሽ ኀጉተናልና ሔዋን ሆይ ወደ እኛ ነይ፡፡

ለንጉሥነት ተፈጥሮ ራሱን ለባርነት የሸጠውን የሰው ልጅ እግዚአብሔር በአምላካዊ ክንዱ ከወደቀበት ሊያነሣው በወደደ ጊዜ እነሣሡን እንደ አወዳደቁ ሊያደርግለት ፈልጎ ነበር፡፡ ሸክላ ሠሪ ብዙ ደክሞ የሠራው ሸክላ ሲሰነጠቅበት አፍርሶ ድጋሚ እንደሚሠራው ሰውን እንደ ሸክላ ከአፈር የፈጠረው እግዚአብሔርም የተሰበረውን ሥራውን ለመጠገን እንደ አዲስ አፍርሶ ሊሠራው ወደደ፡፡[75] አንድ ሕመም ከሥሩ እንዲነቀል ከተፈለገ የበሽታው መንሣኤ መታወቅና መታከም

[75] ኤር. ፲፰፥፮ ፤ ‘ድኅረ ተሰብረ አጽንዖ ለሰብእናነ ልሕኩት ፤ ለብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት’ ሸክላ (ሰብእናችን) ከተሰበረ በኋላ ሸክላ ሠሪው ክርስቶስ በአዲሲቱ ጥምቀት ውኃ አጸናው (ሠራው) /መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ፤ መጽሐፈ ቅኔ /ዝክረ ሊቃውንት/ ክፍል ፪ ገጽ ፲፩ ፤ ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ፤ መርሐ ልቡና ገጽ 18/

ስላለበት እግዚአብሔር የሰው ልጅን ሕመም ከበሽታው መነሻ አንሥቶ ሊፈውሰው ወደደ፡፡

እግዚአብሔር የሰው ልጅን ያዳነበት መንገድ በዕለተ ዐርብ በመሰቀሉና መከራን በመቀበሉ ብቻ የሚመስለውና ከነገረ መስቀሉ ውጪ ያለው ጉዳይ የሚጠቅም የማይመስለው ሰው ካለ ነገረ ድኅነትን ጨርሶአልተረዳም፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር በድንግል ማርያም ተፀንሶ ተወልዶ ሠላሳ ዓመታትን መቆየት ሳያስፈልገው ልክ የመጀመሪያውን አዳም እንደፈጠረው የሠላሳ ዓመት የሆነ ሥጋንና ነፍስን ለራሱ ፈጥሮ መለኮቱን አዋሕዶ ሰው መሆን ይችል ነበር፡፡ ይህንን ቢያደርግም ሦስት ዓመታት በምድር ላይ አስተምሮ በጊዜው ተሰቅሎ የማዳን ሥራውን መፈጸም ይችል ነበር፡፡

እርሱ ግን ማዳኑን የጀመረው በማሕፀን ከመፀነስ ነበር፡፡ አረጋዊው ስምዖን 'ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል' እንዳለ ማዳኑንም የጀመረው ሕፃን ሆኖ በመታቀፉ ነው፡፡ ሉቃ. ፪፥፴ የጌታ የማዳን ሥራ ወሳኙ ታሪክ ከመስቀሉ ጋር በችንካር የታሰረበት ብቻ ሳይሆን በድንግል ማርያም እቅፍ በፍቅር የታሰረበት ቅፅበትም ነው፡፡ ክርስቶስ ሊያስታውሰው የማይፈልገው የልጅነት ሕይወት ያለው አይደለምና ስለ ክርስቶስ የሚሰብኩም ሁሉ ይህንን ድንቅ የሕፃንነት ጊዜውንና ያደገበትን

ሁኔታ ቸል ሊሉ አይገባም:: ክርስቶስን 'በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ሆኖ' በሰዎች ልቡና እንዲሣል በመጀመሪያ በድንግል ማርያም እቅፍ እንደተወለደ ሆኖ መሣል ይገባዋል:: ልብህ ውስጥ ሳይወለድ የሚሰቀል ክርስቶስ ካለ ለወለደችው እናቱና ለድንቅ ልደቱ ዋጋ ልትሠጥ አትችልም::

መስቀል መሸከሙ ዘልቆ የሚሰማህ በልጅነቱ ያቀፈችውን ድንግል ማየት ስትችል ነው:: ሐሞትና ከርቤ መጠጣቱ የሚያስለቅስህ ድንግልናዊ ወተትን ካጠባችው እናቱ ጋር አብረህ ስትሆን ነው:: አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ላለው ክርስቶስ በምድር ላይ በቆየበት መዋዕለ ሥጋዌው አልፋው ድንግል ማርያም ስትሆን ኦሜጋው መስቀል ነበር:: የተሰቀለ ቀን ብቻ አይተህ ልታውቀው አትችልም:: ሁለተኛ አዳምነቱ ዘልቆ የሚሰማህ ወደ ልደቱ ስትመለስ ነው:: የሰው ልጅ ቁስልም የሻረው ጌታ ሊወለድ ካለበት ቅፅበት ጀምሮ ነው::

በገነት ዛፎች መካከል አንድ የረከሰ መልአክ እና አንዲት ሴት ተነጋግረው ተስማምተው ያበላሹትን የሰው ልጅ ታሪክ ድጋሚ ሊጽፈው የፈቀደው እግዚአብሔር በተቀደሰ መልአክና በአንዲት ሴት መካከል ንግግር አስጀመረ:: ሰይጣን በምድር ከሚርመሰመሱ አራዊት መካከል ተንኮለኛውን እባብን መርጦ ሔዋንን በማሳመን የሰው ልጅ ከገነት

አስወጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ በስግያት ከሚያመሰግኑ ብርሃናዊያን መላእክቱ መካከል ከዋነኞቹ አለቆች አንዱን ቅዱስ ገብርኤልን መርጦ ድንግል ማርያምን እንዲያበሥራት ላከ፡፡[76]

ሁለተኛይቱ ሔዋን ድንግል ማርያም ከመጀመሪያይቱ ሔዋን እጅግ በብዙ ነገሮች ትለያለች፡፡ ሔዋን የተቀደሰው ገነት ውስጥ ተፈጥራ ፈጣሪዋን የበደለች ስትሆን ድንግል ማርያም ግን በእርግማን በረከሰው ምድር ላይ ተፈጥራ የተቀደሰች ናት፡፡[77] የቀደመችው ሔዋን በገነት መካከል ሥራ ፈትታ የምትመላለስና የእባብን ድምፅ ሰምታ አዳምን ለሞት የምትዳርግ ስትሆን አዲሲቱ ሔዋን ግን ራስዋ ምድራዊት ገነት ሆና አዳምን ያስገኘች ናት፡፡ ከዚህች ገነት ተፀንሶ የተወለደው ሁለተኛው አዳም እንደ ቀድሞው አዳም ተባርሮ የወጣ ሳይሆን 'ሙሽራ ከጫጉላው እልፍኝ እንደሚወጣ' ከእርስዋ የወጣ ሙሽራ ነው፡፡

ይህች ሔዋን ከቀደመችዋ የምትበልጥ መድኃኒትዋ ስለመሆንዋና በየዘመናቱ የተነሡ አበው ተባብረው ተናግረዋል፡፡ ነገረ ድኅነትን እንደ ዳግም ተፈጥሮ (The theology of redemption as recaptulation)

[76] ወበእንተዝ ደለዎ ከመ ይጹር ዜናሃ ለማርያም' እንዲል አስቀድሞ ማኅበረ መላእክትን ማረጋጋቱ ለዚህ ክብር አስመርጦታል ይላሉ፡፡
[77] Olga Moss, The Life of Holy Virgin Mary, page 5

አድርጎ በማስተማር የመጀመሪያው የሆነው ቅዱስ ሄሬኔዎስ በዚሁ ጉዳይ ሲናገር :-

> 'መላው ዓለም በአንዲት ድንግል ምክንያት በሞት ሰንሰለት ውስጥ ገባ ከእስር የተፈታውም በድንግል ምክንያት ሆነ። ድንግልናዊ አለመታዘዝ በድንግልናዊ መታዘዝ ተካሰ ፤ የበኵረ ሰብእ አዳም ኃጢአትም በበኵረ አብ ተደመሰሰ' ብሏል፡፡[78]

ለመጀመሪያ ጊዜ ሔዋንና ማርያምን[79] በማነፃፀር ውድቀታችንን ከመዳናችን ጋር አስተያይቶ የጻፈው ሰማዕቱ ዮስጦስ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

> አለመታዘዝ በመነጨበት በኩል ፈራረሰ። ሔዋን ድንግል ሆና ሳለ የእባቡን ቃል በልብዋ ፀንሳ አለመታዘዝንና ሞትን ወልዳ ነበር። ድንግል ማርያም

[78] St. Irenaeus, Adversus Haeresus V ANF, Vol. 1, 547

[79] የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሔዋን-ማርያም ንጽጽር ትምህርት ለመጀመራቸው መነሻው ቅዱስ ጳውሎስ 'ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሠጥ መንፈስ ሆነ' ብሎ ያስቀመጠው የአዳም-ክርስቶስ ንጽጽር ትምህርት ነው፡፡ 'በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና' 'በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ' የሚሉት አዳምን ከክርስቶስ ጋር የሚያነጻጽሩ ትምህርቶች ሔዋንን ከድንግል ማርያም ጋር ለማነፃፀር መነሻ የሆኑ የትርጓሜ ስልት መነሻዎች ናቸው፡፡ ፩ቆሮ. ፲፭፥፵፭ ፤ ሮሜ ፭፥፲፬-፲፱

ግን የገብርኤልን ብሥራት ተቀብላ እውነትንና ደስታን ወለደች''[80] ሲል

ሔዋን ላይ የጨከነው ብዕረኛ ሊቁ ጠርጡለስም 'የሰው ልጅ በወደቀበት ጾታ ዳግም ወደ ድኅነት ተመለሰ። ሔዋን እባብን አመነች ፤ ማርያምም ገብርኤልን አመነች' ብሎ የሔዋንን በልጅ መካስ አጽንቶአል፡፡[81]

ይህችኛይቱ ሔዋን በቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ንግግር :-

'የእናትዋን ሔዋንን ዕዳ የከፈለች ፤ ከመዋትያን መካከል ሆና ሕይወትን የወለደች ሁለተኛ ሔዋን ፤ የወደቀችዋን እርጊት የረዳቻትና በዕባብ ተነድፋ ከወደቀችበት ያነሣቻት አገልጋይዋ። ዕርቃኑን ሆኖ በዛፍ መካከል የተሸሸገ ሽማግሌ አባትዋን ልብሰ ሰፍታ ያለበሰች ሴት ልጅ' ናት፡፡

ይህችኛይቱ ሔዋን የሰው ልጅ ቃልዋን ቢሰማ 'የሔዋንን ቃል ሰምተሃልና የተረገምህ ትሆናለህ' ተብሎ የሚሞትባት ሔዋን አይደለችም፡፡ ይህች ድንግል ቃልዋን ብንሰማ የምንባረክባት ከአንደበትዋ የሚወጣው

[80] Justine the Martyr, Dialogue with Trypo, ANF Vol.1.249
[81] Tirtulian, De Carn Christ 17

ቃል እንደ ሔዋን ካለመታዘዝ ፍሬ እንድንበላ ሳይሆን 'የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ' የሚል የሚያድን ቃል ነው፡፡ ዮሐ. ፪፥፭

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚህ ሲናገር ፦

'የሔዋን ቃል ዕፀ በለስን አሳየ ፤ በዚያም ዕፅ አዳም ከገነት ደስታ ወጣ። ከድንግል የተገኘው ቃል ግን ወንበደው ከአባቱ ከአዳም ጋር ወደ ገነት ደስታ የገባበትን ዕፀ መስቀልን ገለጠ' 'ቃላ፡ለሔዋን፡ከሠተ፡ ዕፀ፡ ወበውእቱ፡ ዕፅ፡ ወጽአ፡ አዳም፡ እምገነተ፡ ተድላ፡፡ ወቃልሰ፡ ዘተወልደ፡ እምድንግል፡ ከሠተ፡ መስቀለ፡፡ ወቦቱ፡ ቦአ፡ ፈያታዊ፡ ውስተ፡ ገነተ፡ ተድላ፡ ዘምስለ፡ አቡሁ፡አዳም'[82] ብሏል፡፡

አባ ጊዮርጊስ 'በከመ፡ ወለደ፡ ብእሲ፡ ብእሲተ፡ ዘእንበለ፡ ብእሲት፡ ከማሁ፡ ብእሲትኒ፡ ወለደት፡ ብእሲ፡ ዘእንበለ፡ ብእሲ' 'ወንድ ሴትን ያለሴት እንደወለደ እንዲሁ ሴት ወንድን ያለ ወንድ ወለደች' እንዳለው የቀደመችው ሔዋን ከወንድ ከብቻው የተገኘች ሴት ስትሆን ይህችኛዋ ሔዋን ደግሞ ወንድን ያስገኘች ሴት ናት፡፡

[82] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፷፮፥፭

'ሔዋን እናት ስለሌላት ሰው በመሆንዋ ላይ አንዳች ነገር እንዳላጎደለባት እንዲሁ ክርስቶስም በሥጋ አባት ስለሌለው ሰው በመሆኑ ላይ አንዳች ነገር አልጎደለበትም': 'ወከመ፡ ከመ፡ ኢሐፃ፡ ለሔዋን፡ አካለ፡ ለብእና፡ በእንተ፡ ዘኢሀሰዋ፡ እም፡ ከማሁ፡ክርስቶስኒ፡ኢሐፆ፡ፍና፡ትሰብእት፡በእንተ፡ ዘኢሀሰዎ፡አብ፡በሥጋ' እንዲል[83]

ያችኛይቱ ሔዋን ከአዳም ተገኝታ የተሠራችና አዳም ወደ እርስዋ እያየ 'ይህች አጥንት ከአጥንቴ ይህች ሥጋ ከሥጋዬ ናት' የሚላት ናት:: ይህችኛይቱ ሔዋን ድንግል ማርያም ግን ከአዳም የተገኘች ሳትሆን አዳምዋ ክርስቶስ ሥጋው በጅራፍ ግርፋት ሲቆስልና አጥንቶቹ ሲቆጠሩ በጭንቀት እያየች 'ይህ አጥንት ከአጥንቴ ነው ፤ ይህ ሥጋም ከሥጋዬ ነው' የምትል ሔዋን ናት::

የቀደመችዋ ሔዋን አዳምዋ በእርስዋ ምክንያት ጠፍቶ 'አዳም ሆይ ወዴት ነህ?' ተብሎ ሲፈለግ በዛፎች መካከል ሆኖ ከአባቱ ከእግዚአብሔር 'ፈርቼ ተሸሸግሁ' የሚል አዳም ሲሆን ሁለተኛይቱ ሔዋን ግን አዳምዋን ፍለጋ የምትጨነቅና ወዴት ነህ? ስትለው አዳምዋ 'በአባቴ ቤት እኖር ዘንድ እንዲገባኝ አታውቁምን' ብሎ የሚመልስላት ከአባቱ

---

[83] ትርጓሜ ወንጌል ፤ ግእዝ በግእዝ ፤ ዘመርጡለ ማርያም

እቅፍ ያልተለየ አዳም እናት ናት፡፡ ለድንግል ማርያም ክርስቶስ ከእርስዋ የተገኘ አዳምዋ ብቻ ሳይሆን በቀናተኞቹ ቃየኖች አይሁድ በግፍ የተገደለባት አቤልዋም ጭምር ነው፡፡ ልዩነቱ የአቤል ደም ወንድሙን የሚከስስ ደም ሲሆን የእርስዋ ልጅ የክርስቶስ ደም ግን 'ከአቤል ደም ይልቅ የሚሻለውን የሚናገር' 'ከኃጢአት ሁሉ የሚያነጻ ደም' ነው፡፡[84]

ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለ:-

'የቀደመችው ሔዋን የወለደችው ነፍሰ ገዳዩን ቃየንን ነበረ ፤ ማርያም ግን ሕይወትን የሚሠጥን ልጅ ወለደች። የቀደመችው ሔዋን የገዛ ወንድሙን ደም የሚያፈስስ ቃየንን ወለደች ፤ ድንግል ማርያም ግን ለወንድሞቹ ደሙን የሚያፈስሰውን ክርስቶስን ወለደች። የመጀመሪያይቱ ሔዋን ልጅዋን ቃየንን በምድር እርግማን ምክንያት ሲፈራና ሲቅበዘበዝ አየችው ፤ ድንግል ማርያም ግን ልጅዋ ክርስቶስ እርግማንን ተሸክሞ ወስዶ በመስቀሉ ሲቸነክረው አየች'[85]

በእርግጥም አዲሲቱ ሔዋን ከመጀመሪያዋ ሔዋን እጅግ ትበልጣለች፡፡ ሐዋርያው 'ሁሉ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆኗል' እንዳለ

[84] ፩ዮሐ. ፩፥፯ ፤ ዕብ. ፲፪፥፳፬ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ አርጋኖን ድንግል ዘሰኑይ
[85] St. Ephrem the Syrian, Commentary on Tatian's Diatessaron II, 2.60-61

እግዚአብሔር ድጋሚ በአዲስ ተፈጥሮ ሲፈጥረን ወድዶአልና ከቀደመችው ሔዋን የተሻለች ሔዋንን ፈጥሮ አዲስ የማድረግ ሥራውን ጀመረ፡፡ ፩ቆሮ. ፲፭፣፵፭

ከገነት ከተባረረች ወዲህ በነቢያት መጻሕፍት ስምዋ እንኳን ያልተነሣው የፍጥረት ክስ ያለባት ሔዋን ከተረገመች በኋላ የተናገረችው ሁለት ቃላትን ብቻ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ቃል ቃየንን በወለደች ጊዜ ስም ስታወጣለት 'ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ' ያለችው ነበር፡፡ ሁለተኛው ንግግርዋ ደግሞ ቃየን በገደለው በአቤል ፋንታ በወለደች ጊዜ 'እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው' የሚለው ነበር፡፡ ከእዚህ በኋላ የሔዋን ድምፅ ተዘግቶአልና በቅዱሱ መጽሐፍ ላይ ሔዋን እንዲህ አለች የሚል ቃል አናገኝም፡፡ የእርስዋ ብቻ ሳይሆን የሴት ልጅ ድምፅም በዚያው ተዘግቶ ሔዋኖች አንገታቸው ተደፍቶ ሊኖሩ ግድ ሆነባቸው፡፡ ዘፍ. ፬፣፩፣፳፭

የሔዋን ብቻ አይደለም ፤ የአዳምም አንደበት ከእርግማን በኋላ ተይዞ ነበር፡፡ ለእንስሳት ሳይቀር ስም ሲሠጥ የነበረው ንግግር አዋቂው አዳም ከገነት ከተባረረ በኋላ 'እንዲህ አለ' ተብሎ በመጽሐፍ የተጻፈለት ቃል በትካዜ ሆኖ የተናገረው ይህ ቃል ነው ፦ 'አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና' ዘፍ.፫፣፳

ከአዳም ንግግር ብንጀምር ፈጣሪው የቁርበት ልብስን አልብሶት ፣ ገነትን የሚያህል ቦታ እግዚአብሔርን የሚያህል ጌታ አጥቶ ፣ የሱራፌ የእሳት ሰይፍ ከጀርባው እየተገለባበጠበት ሲወጣ መጀመሪያ ያደረገው ነገር ግራ የሚያጋባ ነገር ነው:: 'የሠጠኸኝ ሴት ከዛፉ ሠጠችኝና በላሁ' ብሎ ሔዋንን እንዳልከሰሰ ከገነት በእርስዋ ምክንያት ተባርሮ በወጣበት ቅጽበት ግን ለሚስቱ 'ሔዋን' ሕይወት ፣ የሕያዋን እናት ብሎ ስም ማውጣትን የመጀመሪያ ሥራው አደረገ:: በእርስዋ ምክንያት ሞት ተፈርዶበት እየወጣ 'ሞቴ ፣ እንትፋቴ' ብሎ ሊጮኽባት በሚችልበት ቅጽበት ለሚስቱ አስቀድሞ ካወጣላት የተሻለ ከእርስዋ ሁኔታ ጋር ግን ተቃራኒ የሆነ 'የሕያዋን እናት' የሚል ስም ሸለማት::

አዳምና ሔዋን ምንም ከፈጣሪ ቢጣሉም መንፈስ እግዚአብሔር ጨርሶ አልተለያቸውምና የሁለቱም ንግግር ትንቢት ነበረ:: የሔዋን የመጨረሻ ንግግሮች እንደ ባልዋ ሁሉ ከሁኔታዋ ለየት ያሉ ነበሩ:: 'እግዚአብሔር ወንድ ልጅ ሠጥቶኛል' ብላ የጠራችው ቃየን ወንድ ልጅዋን የሚነጥቅ ነፍሰ ገዳይ ሆነ 'ዘር ተክቶልኛል' ያለችው ሴትም አቤልን ከመተካት ያለፈ ለሔዋን የጠቀማት ምንም ነገር አልነበረም:: በሁለቱም ንግግሮችዋ ውስጥ አንዳች የምትናፍቀው ነገር እንዳለ ፣ አንዳች የምትቃትትለት ተስፋ እንዳላት ማየት ይቻላል::

'እግዚአብሔር ወንድ ልጅ ሠጥቶኛል' የሚለው ንግግርዋ ከቃየን ይልቅ 'ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሠጥቶናል' ለተባለለት ነፍስ አድን ልጅዋ ለክርስቶስ የሚገባ ስም ነበር፡፡ 'ሔዋንስ የሞት ምክንያት የሆነ ቃየንን ወለደች ማርያም ግን ሁሉን ወደ ሕይወት የሚመራውን ቃልን ወለደች' 'ሔዋንሰ፡ወለደት፡ቃየልሃ፡ዘውእቱ፡ምክንያተ፡ሞት፡፡ ወማርያምሰ፡ወለደት፡ቃለ፡ዘውእቱ፡መራሒ፡ኲሉ፡ኀበ፡ሕይወት' ይላል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡፡[86]

'እግዚአብሔር ዘር ተክቶልኛል' የሚለው ቃልዋም 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስተርልን ኖሮ፥ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር' ለተባለላት ለሴቲቱ ድንግል ማርያምና ለዘርዋ ክርስቶስ የተገባ ስም ነበር፡፡ ኢሳ. ፩፥፱

አዳም ሔዋንን የጠራበት 'የሕያዋን እናት' የሚል ስም በእርግጥም ለልጆችዋ ሞትን ላወረሰችው ሔዋን የሚስማማ አልነበረም፡፡ እርሱ በተኛበት ሳያያት የተፈጠረችውን ሔዋንን በተሠጠው የትንቢት ጸጋ ከጎኑ መፈጠርዋን አውቆ 'ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት' ያለው አዳም ነቢይ ስለነበረ ነው፡፡[87]

---

[86] ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ፤ ንባቡና ትርጓሜው ፷፯፥፱

[87] St. John Chrysostom, On Genesis. Homily 16,5 PG 53፤ St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, 634

አሁንም 'የሕያዋን እናት' ብሎ ነቢዩ አዳም እየተናገረ ያለው አጠገቡ ስላለችው ሔዋን ሳይሆን 'ትንሣኤና ሕይወት'ን ወልዳ ከሞት ፍርድ ስለምትገላግለው ፤ መድኃኒትን ወልዳ ቁስሉን ስለምትፈውስለት በተስፋ ስለሚጠብቃት በዓይኑ ስላላያት የኋለኛይቱ ሔዋን ስለ ድንግል ማርያም ነበር፡፡ አባ ሕርያቆስ 'ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ' እንዳለ 'አዳም እመቤታችን ማርያም ከእርሱ አብራክ እንድትከፈል ከሔዋንም ማሕፀን እንድትወለድ አውቆ ሔዋንን ሕይወቴ ነሽ ይላት ነበር'[88] የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ እንዳለው 'በእርግጥ ሔዋን ድንግል ማርያምን በዘመን ትቀድማታለች ፤ ሔዋን ማን እንደሆነች ያወቅነው ግን ድንግል ማርያም ስትመጣ ነው'

በእርግጥም 'የምትመቸው ረዳት እንፍጠርለት' በሚለው ቃል ላይ ያለው 'ረዳት' የሚል ስምም እንዲሁ ከሔዋን ይልቅ ለብላቴናዋ ሔዋን ለድንግል ማርያም የተስማማ ስም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሔዋን ለአዳም በተግባር ረዳቱ የሆነች ሳትሆን እንደ ሶምሶን ክብሩን ያጣባት ደሊላው ነበረች፡፡[89]

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንዲህ ይላል :-

---

[88] መቅድመ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ

[89] 'The second Eve cast down the second Adam, that is Samson… Eve expelled Adam from Paradise; Delilah took from Samson his rank of being a Nazirite.' St. Jacob of Sarug, Homily on Samson 395, Gorgias Press p. 52

'ረዳትስ የሆነችው አይደለም ፤ ገዳይ ሆነችው እንጂ።
በእርስዋ ምክር ዕፀን በልቶ ስቶአልና አመፅን አስተማረችው። ሔዋን ረዳት ተብላ የተሰየመችውስ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ነው።

ይህች ድንግል ማርያም ለአባቱ ራሱን የሚናገር መሥዋዕትና ንጹሕ ዕጣን አድርጎ አሳርጎ ለብዙኃን ቤዛ የሞተውን ፤ በደሙ መክፈቻነት የገነትን በር ለጻድቃን ነፍሳት የከፈተውን ፤ ከሱራፊ እጅ የእሳት ጉጠትን ያስወገደውን ፤ ሕይወትን ወልዳለችና ለሰው ወገንም ሕይወት ሆናለችና ረዳት መባል ለድንግል ማርያም ይገባታል'[90]

# • የሔዋን መድኃኒት

አበው 'ወድቀው ይነሡ በእጅ ፤ ዘግይተው ይከብሩ በልጅ' እንደሚሉት የአዳምና ሔዋን ኀዘንና መከራ የተወገደው በኋላ ባገኟት ልጃቸው ነው፡፡ አባ ሕርያቆስ 'ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሚ ኵሉ ፍጥረት' 'የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ በአንቺ ታደሰ' እንዳለው ድንግል ማርያም ወላጆችዋን አዳምና ሔዋንን ዳግም የወለደች ልጃቸው ናት፡፡ አባ

[90] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፥ ኆኅተ ብርሃን ፥ ዘዕለተ ቀዳሚት ፲

ጊዮርጊስ 'አቡሃ፡ለሔዋን፡ተወልደ፡እምወለተ፡ሔዋን'፡'የሔዋን አባት ከሔዋን ልጅ ተወለደ' እንዳለው እርስዋ የአዳምና ሔዋንን ፈጣሪ ወልዳ ለወላጆችዋ አያት መሆን የቻለች ናት፡፡[91]

ለክፍለ ዘመናት የዘለቀ ኀዘን ያደቀቀሽ እናታችን ሔዋን ሆይ በትንሽዋ ልጅሽ ትጽናኚ ዘንድ ነይ ተመልከቺ ፤ እግዚአብሔር በደይን ሲኦል የጣለሽና በአንቺ ምክንያት ወደ ሲኦል የሚወርዱትን እያየሽ የምታለቅሺዋ ሔዋን ሆይ የሴት ልጅሽ የማሕፀንዋ ፍሬ ሲኦል ድረስ መጥቶ አንቺን እስከነ ልጆችሽ እንደሚያወጣችሁ ልንናገር ነውና ወደ እኛ ነዪ፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም 'እነሆ ዛሬ ሔዋን በሲኦል ሆና ደስ ይበላት ! የሴት ልጅዋ ልጅ የእናቱን እናት ሊፈውስ የሕይወት መድኃኒት ሆኖ ወርዶአልና'[92] ብሎ የዘመረልሽ ሔዋን ሆይ ሞት የሚያመጣውን የዕፀ በለስን ፍሬ የታቀፍሽው እናታችን ሆይ ታናሽዋ ልጅሽ በእጆችዋ የሕይወትን ፍሬ ታቅፋ አይተሽ ትጽናኚ ዘንድ ፈጥነሽ ነይ፡፡ 'ንዒ፡ኦ፡ሔዋን፡ከመ፡ትትፈሰሒ፡በሞገሰ፡ወለትኪ፡እስመ፡አምጽአት፡ለኪ፡ሕይወተ'፡'ሔዋን ሆይ ሕይወትን አምጥታልሻለችና በሴት ልጅሽ ሞገስ ደስ ይልሽ ዘንድ ነይ'

---

[91] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፺፮፡፩

[92] St. Eprem the Syrian, The Luminous Eye, page 99

ድንግል ማርያምንም ዘወትር ደስ ይበልሽ ስንላት ሔዋንንም አብረን እናስታውሳታለን፡፡ 'የሔዋን የሚጎዳ ማሠሪያዋ በአንቺ የተቆረጠላት እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ' 'ተፈሥሒ፡ ኦ፡ ማርያም፡እንተ፡ብኪ፡ተበትከ፡ማዕሠረ፡ሔዋን፡ማሕመሚ፡እንተ፡ገጸፋ፡ እግዚአብሔር፡ውስተ፡ደይን'[93]

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ይላል

> 'ሔዋን ያለባት ዕዳ ምንድርን ነው? እስቲ የፍርድዋ ደብዳቤ ይውጣና ይነበብ ፤ ሔዋን የፈረመችበትን ዕዳ የድንግል ማርያም ልጅ አሁን ይከፍለዋል። ዕባብ ሴቲቱን ሔዋንን ነክሷት ነበር ፤ ታናሽ ልጅዋ ማርያም ደግሞ ለፈውስ የሚሆናትን የመድኃኒት ቅጠል ሠጠቻት'[94]

ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት የፈሰሰውን የሔዋንን ዕንባ የጠረገች ፡ በሞት ጥላ ለምትኖር እናትዋ ሕይወትን የወለደች ፡ በጨለማ ለምትመላለስ እናትዋ ብርሃንን አቅፋ የሠጠቻት የብርሃን እናት ድንግል ማርያም ነበረች፡፡

---

[93] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ፤ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፳፰፣፴፮

[94] St. Jacob of Serugh, On the Mother of God, homily 2

ሔዋን በገነት ዛፎች መካከል ቆማ የሠራችውን የጥፋት ታሪክ ድንግል ማርያም በናዝሬት ገሊላ ቆማ አረመችው፡፡ ሔዋን በገነት ሳለች ማድረግ ያልተቻላትን ነገር ሁሉ ታናሽዋ ብላቴና አድርጋ አሳየቻት፡፡ የሰው ልጅን ከገነት ያስወጣው የእባቡና የሔዋን ቃለ ምልልስም ሰውን ወደ ገነት በመለሰው በገብርኤልና በማርያም ቃለ ምልልስ ተተካ፡፡ ሰይጣን በእባብ አድሮ የሠራው ሰውን የማታለሉ የውድቀታችን ታሪክ 'እባብም ለሴቲቱ እንዲህ አላት' ተብሎ በየዕለቱ ሲተረክና የሰው ልጅን እንገት ሲያስደፋ እንዳልኖረ አሁን በተራችን የገብርኤልንና የማርያምን ንግግር 'መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ እንዲህ አላት' እያልን በዘወትር ጸሎታችን ሳይቀር እየደጋገምን የምንጸልየውና የምንዘምረው የክብራችን ማስታወሻ ሆነ፡፡ በሴት ልጅ ይሁንታ ወደ ሞት ፍርድ የወረደውን የሰው ልጅ በሴት ልጅ ይሁንታ ወደ ሕይወት መመለሱን ፤ እየዘመርን የዲያብሎስን ሴራ መክሸፍ እናበሥራለን፡፡

> 'ዛሬ ገብርኤል ይናገራልና እባብ ዝም ይበል ፤ ውሸት ይፈራርሳል ፤ እውነትም ይገለጣል። የቀደሙት ነገሮች ያልፋሉ ፤ ድንግሊቱ ስትወልድ ሁሉም ነገር ዳግም አዲስ ይሆናል' ይላል ማር ያዕቆብ፡፡[95]

[95] Mar Jacob of Serugh, Homily on the Friday of the Passion, 133

መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ቅዱስ ገብርኤል ሲናገር 'በእባቦች ላይ በገነትም ባሉ ጻድቃን ላይ በኪሩቤልም ላይ የተሾመ ከክበሩ መላእክት አንዱ ቅዱስ ገብርኤል ነው' ይላል:: ሄና. ፮፥፯ በእባቦች ላይ ሥልጣን ያለው ገብርኤል በእባብ ምክር የመጣውን ጥፋት ሊለውጥ የሰውን ልጅ ሁሉ ወደ ገነት ጻድቃን ኅብረት ሊደምር እግዚአብሔርን በምትሸከመዋ የሐዲስ ኪዳን ኪሩብ ድንግል ማርያም ፊት ቆመ::

እባብ ሔዋንን ለማሳመን ብዙም አልተቸገረም ነበር:: ቅዱስ ገብርኤል ግን ታናሽዋን ድንግል በቀላሉ አላሳመናትም:: ሔዋን ለእባብ አንድ ጥያቄ እንኳን አልጠየቀችውም:: 'ምንም ቃል ሳትናገር እምና ሞትን ቀመሰች። ከዛፍ አምላክነት እንዴት እንደሚገኝ አልጠየቀችም'[96] ወዲያው ዛፉን ማየትና መጎምዠት ጀመረች:: ቾኩላም በላች:: ታናሽዋ ብላቴና ማርያም ግን የነገሯትን ሁሉ ዝም ብላ የምትቀበል አልነበረችም:: ብርሃናዊ መልአክ ሰላምታ ሲያቀርብላት 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?' ብላ ትመረምራለች:: 'ትፀንሻለሽ' ስትባል 'ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?' ትላለች:: ድንግል ማርያም ለገብርኤል የጠየቀቻቸውን ጥያቄዎች ሔዋን ለእባብ ጠይቃው ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ ከገነት ባልወጣ ነበር::

---

[96] St.Jacob of Serug, Homilies on the Nativity 225. Gorgias Press page 36

የሒዋን ችኮላ ከማርያም ትዕግሥት ጋር እኩል ነበረ፡፡ ልብ አድርጉ ሒዋን እባብ መጥቶ 'ብትበሉ እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ' ብሎ የነገራትን ነገር ከዚያ በፊት ሰምታው የማታውቀው ነገርን ነው፡፡ ገብርኤል ለድንግል ማርያም የነገራት ነገር ግን 'እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች' ብለው ነቢያት በትንቢት የተናገሩለትና ለዘመናት በተስፋ ሲጠበቅ የነበረ ነገርን ነው፡፡ ሒዋን ሰምታ ለማታውቀው ነገር ያሳየችው ችኮላ እና ድንግል ማርያም ለምታውቀው ትንቢት ያሳየችው አለመጓጓት እጅግ አስደናቂ ነው፡፡ ኢሳ. ፯፥፲፬

የግእዝ ትርጓሜ እንዲህ ይላል፡-

> 'ሒዋንስ አስቀድማ እንዲህ ያለ ቃልን አልሰማችም ነበር ፤ መጽሐፍም ይህን አልጻፈም ፤ ነቢይም አልተናገረም። ማርያም ግን በነቢያት መጻሕፍት ያለውን የክርስቶስ ነገር የቃሉን እውነተኛነት ታውቅ ዘንድ በትዕግሥት ሰማች እንጂ አልቸኮለችም'
>
> 'ወሒዋንሰ፡ ኢሰምዓት፡ እም፡ ቀዲሙ፡ ዘከመዝ፡ ቃለ፡ ወመጽሐፍኒ፡ ኢዘከረ፡ ቦቱ፤ወነቢይኒ፡ ኢነበበ፡፡ ወማርያምሰ፡በእንተ፡ዘሀሰወ፡ዝክረ፡ክርስቶስ፡ውእቱ፡ ውስተ፡ መጽሐፈ፡ ነቢያት፡ አጽምአት፡ በትዕግሠት፡ ከመ፡ታእምር፡ጽድቀ፡ቃሉ፡ዘተብህለ፡ወኢጓጕአት'

'ሔዋን የተሞኘችውን ያህል ድንግል ማርያም ተጠበበች ፤ ያቺኛይቱ የገባችውን ዕዳ ሁሉ ይህችኛይቱ ከፈለች። በሔዋን የወደቅን ሁላችን በድንግል ማርያም ተነሣን' ይላል ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፡፡[97] ሔዋን ዕፀ በለስን እያየች ለዓይንዋ ደስ ብሏት ለሰው ልጆች የሞትን ፍሬ ሠጠችን ፤ ማርያም ግን 'መንፈሴ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል' ብላ የማሕፀንዋን ፍሬ መድኃኒታችንን ሠጠችን፡፡

'ዲያብሎስ አምላክ መሆንን ለአዳምና ሔዋን ተስፋ እንደሠጣቸው ገብርኤልም ለማርያም በሥጋዋ አምላክን መውለድን ተስፋ ሠጣት' 'በከመ፡ አሰፈዎሙ፡ ዲያብሎስ፡ ከዊነ፡ አምላክ፡ ለአዳም፡ ወለሔዋን፡ ከማሁ፡ አሰፈዋ፡ ገብርኤል፡ ለማርያም፡ ወሊደ፡ አምላክ፡ በሥጋሃ' የሚያስደንቀው ሔዋን አምላክ መሆንን ፈልጋ ከዛፉ ፍሬ በትዕቢት ቀጠፈች ፤ ማርያም ግን እንኳን አልፋ አምላክ ለመሆን ልትፈልግ 'አምላክን ትወልጃለሽ' ስትባል እንኳን 'የጌታ ባሪያው ነኝ' ብላ በትሕትና ተናገረች፡፡

በእባብ ሥጋ ተሰውሮ ለማታለል ወደ ሔዋን የመጣው ዲያብሎስ ወደ ድንግል ማርያም መጥቶ ተመሳሳይ የማታለል ሙከራ አድርጎ ቢሆን ኖሮ ብለን እናስብ፡፡ ወደ እርስዋ ዲያብሎስ ቢመጣ ኖሮ ብዙው ነገር

[97] St. Jacob of Serugh, On the Virgin, M. Hansbury, 33

ያልጠበቀው ይሆንበት ነበር፡፡ መከበር ፈልጎ 'ወድቀህ ብትሰግድልኝ ዓለምን እሰጥሃለሁ' እስከማለት የሚደርሰው የውዳሴ ናፋቂ ዲያብሎስ ታናሽዋ ብላቴና 'ይህ እንደት ያለ ሰላምታ ነው' እያለች ለመቀበል ስትፈራ ከማየት በላይ ምን ሊያበሳጨው ይችላል? በትዕቢቱ ወደር የሌለው ሰይጣን በትሕትናዋ ወደር በሌላት ፊት እንዴት ይቆም ነበር?

እግዚአብሔር ከፍ ሲያደርገው በውበቱና በክብሩ ብዛት በትዕቢት የወደቀው ሰይጣን እግዚአብሔር ክብርዋን ሲያበዛላት ራስዋን የበለጠ ዝቅ የምታደርገውን ብላቴና ሲያይ ምንኛ ይቃጠል ይሆን? አዳምና ሔዋንን 'ለማወቅ' ብለው ከዛፍ ፍሬ እንዲበሉ ያደረጋቸው ዲያብሎስ የገሊላዋ ድንግል 'ወንድ አላውቅም' ብላ አለማወቅዋን እንደ አቋም ስትናገር ሲሰማት ምን ይሰማው ይሆን?

አምላክነትን እንዲፈልጉ መክሮ አዳምና ሔዋንን ያሳተው ሰይጣን የገሊላዋ ማርያም 'የጌታ ባሪያ ነኝ' ብላ ሥፍራዋን ስትናገር ሲሰማ ምን ይሰማው ይሆን? ሔዋን አምናበት የበላችውን ዛፍ 'እባብ አሳተኝ' ብላ ለሰው ልጅ ሞት ከተጠያቂነት ስትሸሽ ያየው ሰይጣን ድንግል ማርያም 'እነሆኝ አለሁ' ብላ ለሰው ልጅ መዳን የድርሻዋን ልትወስድ ስትቆም ሲያይ ምንኛ ይፈራት ይሆን? በእርግጥም ዲያብሎስ በፊትዋ ቢቆም ኖሮ የገሊላዋን ብላቴና የድንግል ማርያምን ወደር የሌለው ፍጹም

ትሕትናዋን መቋቋም አቅቶት ተንፈራፍሮ ከእባብ ውስጥ 'ዓላማ ይዞ እንደተሰለፈ ሠራዊት የምታስፈራ ይህች ማናት' እያለ እየሰፈሰፈ ፣ እየጮኸ በወጣ ነበር፡፡ አለዚያም በእሳማዎቹ ላይ እንዳደረገው እባብን ይዞት ገደል በገባ ነበር፡፡ መኃ. ፮፡፲ ፤ ሉቃ. ፳፡፴

ምጥ ያሰቃያት ሴት በልጅዋ ምጥዋን እንደምትረሳ እኛ የሰው ልጆችም በሔዋን ምክንያት የደረሰብንን ምጥ ሁሉ ድንግል ማርያምን ከተወደደው ልጅዋ ጋር ስናያት እንረሳዋለን፡፡ አዲሲቱን ሔዋን ድንግል ማርያምን ስናይ የቀድሞዋን እናታችንን ሔዋንን መውቀስ ትተን 'ኸረ እንኳንም ዕፀ በለስን የበላሽ' ወደ ማለት እንደርሳለን፡፡

አባ ጊዮርጊስ እንዳለ :-

> እኔስ ስለ እርስዋ መዳን ፣ ለእኔም ድኅነት ማርያም ትወለድ ዘንድ ሔዋን እንኳንም ከዕፀ በለስ ፍሬ በላች እልሁ። ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቃስ ቢሆን በገነት ፍሬዎች እየተደሰተች ብቻዋን ከባልዋ ጋር በኖረች ነበር። ማርያምም የኃጢአትዋን ፍዳ ለማስቀረት ከልጅ ልጆችዋ ባልተወለደች ነበር። ያሳታት የእባብም

መርዙ በክርስቶስ በመለኮቱ ጨውነት አልጫ

ባልሆነ ነበር'[98]

እግዚአብሔር በሔዋን ላይ ያወረደው እርግማንም በድንግል ማርያም ምክንያት ተለውጧል፡፡ እግዚአብሔር ለሴት ልጅ 'በቁጣዬ ቀሥፌ በፍትሬ ምሬሻለሁ' ያለበት እና ሐዋርያውም ሴት ልጅን 'በመውለድ ትድናለች' ያለበት መንገድ ልጅን መውለድ ከሰው ልጅ እርግማን ማስታወሻነት ወደ ሰው ልጅ መዳን መንገድነት በመለወጡ ነው፡፡ 'ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል ... በምጥ ትወልጃለሽ' የሚለው የሴት ልጅ እርግማንም 'ያለ ወንድ ዘር ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ' በሚል ቃለ ብሥራት ተተካ፡፡ ኢሳ. ፫፥፲ ፤ ፩ኛ ጢሞ. ፪፥፮

ሴቶች በምጥ ተጨንቀው ሲሰቃዩ የሔዋንን መረገም እያሰቡ ይማረሩ ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ያሉ ሴቶች ግን ሔዋንን መውቀስ እርግፍ አድርገው ትተው የመድኃኒትን እናት 'ማርያም ማርያም' እያሉ ይወልዳሉ፡፡ 'የባሪያይቱን [ሔዋንን] መዋረድ አይቶአልና በምጥ ላይ ያሉ ትውልድ ሁሉ 'የተረገመች' ሲሏት እንዳልኖሩ ድንግል ማርያምን 'ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ነሽ' ይሏታል፡፡ በወላዶች ሁሉ ቤት ስምዋ

[98] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፹፪፥፹፩

እየተጠራ ከመወቀስ ሔዋንን ያዳነቻትን ድንግል ማርያም 'የሔዋን መድኃኒት ሆይ ደስ ይበልሽ' እያልን የምናመሰግናት ለዚህ ነው፡፡

> 'የእግዚአብሔር የጥበቡ ሥራ ምን ይደንቅ በምጥ በጋር በልብ ኀዘን ትወልድ ዘንድ የተፈረደባት ማሕፀን የሕይወት መገኛ ሆነች ፤ ከባሕርያችን መርገምን የሚያስወግደውን ያለ ወንድ ዘር ወለደችው' 'ስለ ሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ ዳግመኛም ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን ፤ ከዕፀ ሕይወትም እንበላ ዘንድ አደለን'

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በሌላ ሥፍራ ደግሞ ሔዋንና ድንግል ማርያምን የሰው ልጅ ሁለት ዓይኖች ናቸው ይላል፡-

> 'ማርያምና ሔዋን የአንድ ሰው ሰውነት ላይ ያሉ ዓይኖችን ይመስላሉ። አንደኛው የግራ ዓይን የታወረና የጨለመ ሌላኛው ደግሞ አጥርቶ የሚያይና ለመላው ሰውነት ብርሃን የሆነ ዓይንን ይመስላሉ። ይህ ዓለም ሁለት ዓይኖች ነበሩት። የታወረው የግራ ዓይኑ ሔዋን ስትሆን የምታበራው የቀኝ ዓይን ደግሞ ማርያም ናት። በታወረው ዓይን ምክንያት መላው ዓለም በጨለማ እየዳከረ ነበር።

> የሰው ልጆችም በዳበሳ ይሔዱ ነበርና የሚነኩት ድንጋይ ሁሉ አምላክ ነው ብለው እየተሰናከሉ ሐሰቱን እውነት እያሉ ኖሩ። የቀኝ ዓይን ስትበራ እና ሰማያዊ ብርሃን በእርስዋ መካከል ሲያድር ግን የሰው ልጆች ዳግመኛ ዕርቅን አገኙ። የተደገፉት ሁሉ የሚያጠፋቸው እንደነበረ ተረዱ' ይላል፡፡[99]

በእርግጥም በሔዋን ያላየነውን ያየንባት እናቶች 'ዓይኔ ነሽና ብርሃኔ' እያሉ የሚዘምሩላት የሰው ልጆች ሁሉ የብርሃን ዓይናችን እመቤታችን ናት፡፡

[99] St. Ephrem the Syrian, Hymns on Ecclisia, Sebastian Broock 37:4-7

፲

# የምሕረት አዋጅ

## • ፍርድ ወይንስ ፍቅር

እግዚአብሔር ከፍጥረታቱ ሁሉ አክብሮ የፈጠረው የሰው ልጅ የሰይጣንን ምክር አምኖ ተቀብሎ ትእዛዙን መጣሱ ለሰው ባሕርይ መጎስቆልና ከጸጋዎቹ መራቆት እንዲሁም ለሞት ሞት ምክንያት የሆነ ውድቀት ነበረ። ስለ እስራኤል ቤት 'ለወይኔ ያላደረግሁለት፤ ከዚህ ሌላ አደርግለት ዘንድ የሚገባኝ ምንድር ነው? ወይንን ያፈራል ብዬ ስትማመን ስለ ምን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ?' ብሎ እንደተናገረ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ያላደረገው ከዚያም ሌላ ሊያደርግ የሚገባው ምንም ነገር አልነበረም። ኢሳ. ፭፥፬ የሰው ልጅ ግን

ፈጣሪው እርሱን ባከበረው ልክ እርሱ ፈጣሪውን ሊያዋርድ ሞክሯልና መከራውም ቀድሞ በነበረው ደስታ ልክ ሆነ፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የነሣው ምንም ነገር አልነበረም፡፡ በክብር ካለ መኖር ወደ መኖር ጠርቶ ፣ ምድርን አስጊጦ የተቀበለው የእግዚአብሔር እንግዳ አዳም እንግድነቱን ሳያጣጥም የጠራውን ጌታ ለመተካት አማረው፡፡ ሸክላ ሠሪውን ታገለ ፣ ሥዕል ሠዓሊውን ለመሆን ከተቀደደ ሌላ ሥዕል ከዲያብሎስ ጋር ተመካከረ፡፡

በሁሉ ገዢ የሆነው እግዚአብሔር ሰውን በሁሉም ላይ ገዢ አድርጎ በመሾም ከመለኮታዊ ባሕርይው ተካፋይ አድርጎ ቢፈጥረውም ሰው ግን ገዢነቱን ላካፍልህ ያለውን ጌታ 'የለም የምፈልገው መካፈል ሳይሆን መቀማት ነው' አለ ፣ የተመኘውም የእግዚአብሔርን የአምላክነት ቦታ ለመውሰድ ነበር፡፡ 'ጎልማሳ በሚስቱ ንጉሥ በመንግሥቱ ፈጣሪ በአምልኮቱ ሲመጡበት አይወድም' እንደሚባለው በእባብ አማካሪነት የተታለለው አዳም ሁሉን የሠጠውን አምላክ በሥራው 'እኔ የምፈልገው እንዳንተ ፈጣሪ መሆን ነው' ብሎ አሳዘነ፡፡ 'ግሩምና ድንቅ አድርገህ ስለፈጠርኸኝ አመሰግንሃለሁ' ብሎ ስለተፈጠረበት አፈጣጠርና ከፍጥረታት ሁሉ በላይ አድርጎ መሾሙ አመስግኖ ሳይጨርስ የእግዚአብሔርን ዙፋን ተመኘ፡፡

ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት ለኃጢአት ስትጋብዘው 'እነሆ ጌታዬ በቤቱ ያለውንም ሁሉ ለእኔ አስረክቦኛል ፤ ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም ሚስቱ ስለ ሆንሽ ከአንቺም በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?' ብሎ አሳፍሯት ነበር፡፡ የሰው ልጅ ግን እባብ ለኃጢአት ሲገፋፋው 'እነሆ ጌታዬ በገነት ያለውን ሁሉ ለእኔ አስረክቦኛል ፤ በገነት ከእኔ የሚበልጥ ፍጡር የለም ፤ የባሕርይው ስለሆነ እንጂ ከአምላክነት በቀር ያልሠጠኝ ነገር የለም። እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?' ማለት አልቻለም፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረ የገጠመውን የመጀመሪያውን የእምነት ፈተና ወደቀ፡፡ ዘፍ. ፴፱፥፰

ልዑል እግዚአብሔር ትእዛዙን የጣሱት አዳምና ሔዋን ላይ ብዙ ነገር ሊያደርግ ይችል ነበር፡፡ ቀላሉ ነገር እነዚህን ሁለት ሰዎች ጭራሽ ከመኖር ወዳለመኖር እንዲጠፉ አድርጎ የሰውን ልጅን ድጋሚ መፍጠር ይችል ነበር፡፡ ይህን ቢያደርግ ኖሮ ነገሩ በሁለት ሰዎች ተጀምሮ በሁለት ሰዎች ባበቃ ነበር፡፡ ይህን ቢያደርግ ኖሮም ማንም የሚጠይቀው ፤ ይህን አጠፋህ ፤ ይህን አለማህ ሊለው የሚቻለው ማንም የለም፡፡ እግዚአብሔር ግን ፍትሐዊ ነውና ይህን አላደረገም፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዳለ ፡-

> 'በእርሱ የተፈጠረውን ፍጥረት በዲያብሎስ የማታለል ወጥመድ ምክንያት ወደ አለመኖር ያጠፋው ዘንድ ለእግዚአብሔር መልካምነት የሚገባ ነገር አይደለም። ... ይህን ከማድረግስ ቀድሞውኑ አለመፍጠር ይሻለው ነበር። ምክንያቱም ተፈጥሮ ከመጥፋት ይልቅ አለመፈጠር የተሻለ ነገር ነው። በዚያ ላይ የገዛ ሥራውን በዓይኑ ፊት ሲጠፋ መመልከቱ መልካምነቱን ብቻ ሳይሆን ሁሉን ቻይነቱንም ጥያቄ ውስጥ የሚከትት ይሆናል። እስተድሞም የፈጠረው እርሱ አልነበረምን? ያሰኛል'

በዚያ ላይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ "ሠዓሊ የሣለውን ሥዕሉን ያጠፋልን? የቀደመ መጠበብህን አስብ እንጂ" 'ያጠፍዖኑ፡ ሰሥዕሉ፡ ሠዓሊ፡፡ ኪነተከ፡ዘትካት፡ ሐሊ'[100] እንዳለ እግዚአብሔር በከበረች ምክረ ሥላሴ 'እንፍጠር' ብሎ የሠራውን የሰውን ልጅ ግሩምና ድንቅ አድርጎ ፈጥሮታልና በድንቅ ፍጥረቱ ጨክኖ ሊያጠፋው አልወደደም፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ መለኮታዊው አጣብቂኝ (the divine dilemma) ብሎ የገለጸው ፍቅር ወይንስ ፍርድ የተሰኘ የእግዚአብሔር መንታ መንገድ የመጣው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት

[100] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መልክዐ ሕማማት ፤

የሚታዩት ሁለት ምርጫዎች ነበሩ:: አንደኛው ፍርዱን በይቅርታ ኸር ማንግትና ሰውን ወደነበረበት ክብሩ መመለስ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ አስቀድሞ የተናገረው ፍርዱን ማጽናትና አዳምን ለተፈረደበት ዘለዓለማዊ ፍርድ አሳልፎ መሥጠት ፤ ሁለት ሞትን እንዲሞት ፤ በሥጋም በነፍስም ፤ በምድርም በሲኦልም የተቀጣ ሆኖ እንዲቀር መተው ነው::

እግዚአብሔር የሰው ልጅን ውድቀት የማይሻ አምላክ የመሆኑን ያህል የእውነትና የፍትሕ አምላክም ነው:: አስቀድሞ የዛፉን ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ብሎ በሥጋ ሞት ላይ የነፍስ ሞት እርሱም ወደ መቃብር በመውረድ ላይ ሲኦል መውረድ በሰው ልጅ ላይ እንደሚመጣበት ተናግሯል:: የሰው ልጅ የተነገረውን ቸል ብሎ የዲያብሎስን 'ሞትን አትሞቱም' የሚል ምክር ሰምቶ ከክብሩ ተዋረደ ፤ በሰይጣንን ምክር ሰምቶአልና የአጋንንት መጫወቻ ሆነ:: ከመሐሪው አባት እቅፍ ወጥቶ በጨካኙ ገገር ሥር የወደቀውን አዳምን ማየት ለእግዚአብሔር የምሕረት ዓይን ደስ የሚያሰኝ አልነበረም::

እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ ፍርዱን እንዳያጸና ይህን እንዳያደርግ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለው ጥልቅ ፍቅርና ምሕረት አላሰናበተውም:: 'ምን ቢበድለኝ ፍጠረኝ ሳይለኝ ፈጥሬዋለሁና ልምረው ይገባኛል' የሚል በፈታሒነት ላይ የተጨመረ መሐሪነት በእርሱ ዘንድ

ነበረ፡፡ በዚያ ላይ አዳም ከመጀመሪያው በደለኛ ከዲያብሎስ በተለየ ፍጹም የንስሓ ኀዘንን አዝኖ ነበረ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር መሐሪነት ከአዳም ማረኝ ማለት ጋር አንድ ሆኖ ሳለ በፈረደው ፍርድ መጽናትንና 'ይሙት በቃ' ማለትን እግዚአብሔር አልወደደም፡፡

በሌላ በኩል አምላክ የሰውን ልጅ እንዲሁ ይቅር ቢለውና የአዳምን ኀዘንና ጸጸት ተቀብሎ ቅጣቱን ቢተውለት ይችል ነበር፡፡ ይህን ቢያደርግ ግን አስቀድሞ የተናገረውን 'ትሞታላችሁ' የሚል ቃል ሐሰት የሚያደርግ ሲሆን ዲያብሎስንም 'እኔስ ምን አልሁ? ትሞታላችሁ ያለው እውነት አይደለም ብዬ አልነበር' የሚያሰኝ ነው፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዳለ ፡-

'የእውነት አባት ለሆነው እግዚአብሔር 'ትሞታላችሁ' ብሎ የተናገረውን ቃል ይተውና ወደ ኋላ ይመለስ ዘንድም የማይታሰብ ነገር ነው። ራሱን ሊዋሽ አይችልምና እግዚአብሔር ምን ያድርግ? ንስሓ ቢገቡና ቢቀበላቸው ይሻል ነበርን? የእነርሱ ንስሓ ግን አምላካዊውን እውነተኛነቱን ሊጠብቅለት አይችልም። እንደተናገረው ሞት በሰው ልጅ ላይ ገዥ ካልሆነ እግዚአብሔር የተናገረው እውነት አይደለም ማለት ይሆናል። ንስሓም የሰው ልጆች ከሥራት ክፉ ነገር ሊያነቃቸውና ኃጢአትን ከመሥራት

ሊያቆማቸው ይችላል እንጂ ተፈጥሯቸውን ሊለውጠው አይችልም'[101] 'ሐሰትን እንዲናገር እግዚአብሔር ሰው አይደለም' ዘኁ. ፳፫፥፲፱

የተናገረውን መሻርና አዳምን ወደነበረበት ተፈጥሮ መመለስ እግዚአብሔርን ሐሰተኛ የሚያሰኘው ብቻም አይደለም፡፡ የሰው ልጅ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የሚነግረውን ነገር እውነት ነው ብሎ ማመንና መፍራትን ያቆማል፡፡ እግዚአብሔር አንዳች ቢከለክለው እንኳን እንደ ተራ ማስፈራሪያ እንጂ እንደ እውነት አይቆጥረውም ነበር፡፡ የጉባኤ ኒቅያው አፈ ጉባኤ እንዳለ ፡-

'እግዚአብሔር የፈረደውን ፍርድ እንዲወገድ ቢያደርግ ኖሮ ለእርሱ የሚቻለው ነገር ሲሆን ኃይሉንም የሚገልጥ ነገር ይሆን ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ ከእርሱ ውጪያዊ የሆነ እንጂ ከሰውነቱ ጋር ያልተዋሐደ ጸጋን ተቀብሎ አዳም ከውድቀት በፊት ወደ ነበረበት ሥፍራ ብቻ ይመለሳል፡፡ በውጤቱም የሰው ልጅ ድጋሚ የመውደቅ አደጋ ሊገጥመው የሚችል ሲሆን ሁለተኛ ጊዜው

---

[101] St. Athanasius the Great, On the Incarnation, The Divine Dilemma and it's solation in the Incarnation, Chap. II.8

እንደመሆኑም ከበፊቱ በባሰ መጠን አወዳደቁ የከፋ ይሆናል''[102]

ምናልባት እግዚአብሔር የተናገረውን በምሕረቱ ሲሽር እንደ ነነዌ ሰዎች ባሉ በሌሎች ታሪኮች ላይ ያነበበ ሰው ግራ ሊገባው ይችላል፡፡ ሆኖም የአዳምና ሔዋን በደል እንደ ሌሎች ሰዎች ያለ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለመሆን የተደረገ አመፅ ነበረ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተናገረውን ቅጣት ሊሽር አልወደደም፡፡

ስለዚህ ምን ቢሆን ይሻላል? ለሚለው ጥያቄ እግዚአብሔር ፍርድን በማንሣትና ፍርድን በማጽናት ሁለት ጨርሶ የማይሆኑ ምርጫዎች መካከል ግን ሌላ መንገድን መረጠ፡፡ 'እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ በደለኛውንም። ንጹሕ ነህ አይልም እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው' እንደሚል እርሱ በደለኛውን አዳም ንጹሕ ነህ በማለትና የተናገረውን ቃል በማጠፍ መንገዶች ውስጥ ሳይሔድ የሰው ልጅን ስለመውደዱ ሌላ የራሱ የሆነ እጅግ ጠባብ መንገድን መረጠ፡፡ ናሆ. ፩፥፫

ይህ መንገድ እግዚአብሔር በሰው ላይ የፈረደውን ፍርድ በራሱ ላይ ማድረግና ፍርዱን መቀበል ነበር፡፡ በሰው ልጅ ላይ የተፈረደውን ፍርድ

[102] St. Athanasius the great, Against Arians II 68, in migen p.g. 26,292

በራሱ ለማድረግና ሞትንና ሲኦል መውረድን ለመቀበል ደግሞ እግዚአብሔር ሰው መሆን ነበረበት፡፡ ስለዚህ የሰውን ልጅ ዳግም የእግዚአብሔር ልጅ ለማድረግ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆነ፡፡

ለሰው ልጅ የሚገባውን ቅጣት እግዚአብሔር ተቀበለ ፣ 'የፈጣሪውን ትእዛዝ ተላልፎ ራሱን ገዳይ ሆኖአልና በመከራ ተሰቅሎ መሞትስ ለአዳም በተገባው ነበር' 'እስመ፡ ሞትሰ፡ እምደለዎ፡ ለአዳም፡ ለቀቲለ፡ ዘበኃሣር፡ በእንተ፡ ዘተዓደወ፡ ትእዛዘ፡ ፈጣሪሁ፡ ወኮነ፡ ቀታሌ፡ ርእሱ' ይሁንና እግዚአብሔር 'ለአዳም የሚገባውን ሞት በራሱ ላይ አመጣው ፤ በልዕልናው ፈንታ ተዋረደ ፤ በኃያልነቱም ፈንታ ሞተ' 'አምጽአ፡ሞተ፡ላዕለ፡ርእሱ፡ዘድሉው፡ላዕለ፡አዳም፡፡፡ወተትሕተ፡ህየንተ፡ ልዕልናሁ፡ወሞተ፡ህየንተ፡ኃይሉ'[103]

'ባለመታዘዝ የቆሰለውና የተሰበረው የሰው ልጅ ድል ነሺነትን ለመጎናጸፍና ራሱን ዳግም ለማደስ የማይቻለው ነገር ነበር። በኃጢአት ኃይል ሥር በመሆኑ ራሱን ማዳንም አይችልምና ይህን ሁሉ ነገር የእግዚአብሔር ልጅ ሊያደርግለት ወደደ'[104]

ለሰው ልጅ መነሣት እንደ መውደቁ ቀላል አልሆነለትም፡፡ ክብሩን መመለስም ክብሩን እንደመጣል አልቀለለውም፡፡ የሰው ልጆች

---

[103] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ፤ መቅድመ ወንጌል ጉባኤ ፬

[104] St. Ireanues against heresis, 3. 18

ራሳቸውን ለኃጢአት ባሪያ አድርገው መሸጥ ቢችሉም ድጋሚ ራሳቸውን ከኃጢአት ነፃ ማድረግ ግን አልተቻላቸውም። በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው የኖሩ ነቢያትና ቅዱሳን ሁሉ ምንም ቢቀደሱም ሰውነታቸውና በዕዳ ተይዘው ነበር፡፡ የአዳም በደል ያመጣውን ፍርድ ለማስወገድ የእነርሱ ጽድቅና የሰማዕትነት ደምም አልቻለም ነበር፡፡

'የአዳምና ሔዋን የኃጢአታቸው ሚዛን ከነቢያት የጽድቃቸው ሚዛንና ከልዑል ቅዱሳን ከደማቸው ሚዛን የበለጠ ነው። የአዳምና ሔዋን ከገነት መውጣት ምክንያት አምላክ ለመሆን መሻት ነውና። እግዚአብሔር በአምላካዊ ደም ካልሆነ በቀር አምላክ ለመሆን የመሻትን ዕዳ እንደማይከፍል ዐወቀ። ስለዚህ የሔዋን አባት በሔዋን ሴት ልጅ አደረ። የአዳም አባቱ ዳግማይ አዳም ለመሆን ተጋ'[105] ይላል አባ ጊዮርጊስ፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፍርድ በቃሉ ብቻ ተናግሮ ማስወገድ እየቻለ ሰው መሆን ለምን አስፈለገው?

ቅዱስ ቄርሎስ እንዲህ ይላል፡-

'የእግዚአብሔር ቃል [ሰውን ለማዳን] ሥጋን መልበስ አያስፈልገውም ነበር። በቃሉ ትእዛዝ ብቻ መዳናችንን

[105] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፣ መጽሐፈ ምሥጢር ፫፥፷፩

> ሊፈጽመው ይቻለው ነበር። ሆኖም ከሰው ልጆች ጋር አንድነትን ይመሠርት ዘንድ ከእኛ ጋር ሥጋን መልበስን ለመጋራት ወደደ"[106]

እግዚአብሔር ሰውን ሊያድን በወደደ ጊዜ 'እንፍጠር' ብሎ በቃሉ ተናግሮ በግብር የፈጠረውን ሰው ለማዳን ቃሉን ሥጋ ይሆን ዘንድ ወደደ:: በአበው ብሂል 'የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ' ይባላል:: እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረው ቃል እውነትነት ከሚጠፉ አንድያ ልጁ የሆነው ቃልን ወደ ምድር ሊልክ ወደደ:: የሰው ልጅን ከመከራና የእግዚአብሔርን ቃል ሐሰተኛ ከመባል ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ:: ቅዱስ አትናቴዎስ እንዳለ፡-

> 'ከመጀመሪያው ሁሉን ካለመኖር ካመጣው ከእግዚአብሔር ቃል በቀር የእግዚአብሔርን ቃል ማን ሊያድነው ይችላል። የጎሰቆለውን የሰው ባሕርይ ወደ ነበረበት መመለስና የአብን ቃል እንዳይታጠፍ ማድረግ የአብ ቃል የብቻው ሥራ ነው'[107]

[106] St. Cyril of Alexandria, About the Incarnation of the Word. Ch.18, in Migne P.G 75,1448
[107] St. Athanasius the Great, On the Incarnation, The Divine Dilemma and it's solution in the Incarnation, Chap. II.8

ስለዚህ በቃሉ እንፍጠር ብሎ ተናግሮ በክብር የፈጠረውን የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ 'ያ ቃል ሥጋ ሆነ' ይባል ዘንድ ግድ ሆነ፡፡ ሰውን ለሁለተኛ ጊዜ ሲፈጥረው ግን እንደ መጀመሪያው 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር' በሚል አምላካዊ ምክር ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ራሱ ሰው በመሆን ነበር፡፡ ሰው በአምላክነት ዙፋን ለመውጣት በመፈለግ የሠራውን ስሕተት እግዚአብሔር ወደ ሰውነት በመውረድ አረመው።

ሌላው አስደናቂ ነገር እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የመረጠው መንገድ ዲያብሎስ ሰውን ለማሳሳት የሔደበትን መንገድ የሚያፈራርስና የሰውን የውድቀት ታሪክ ዳግመኛ በድል ታሪክ የሚለውጥ መሆኑ ነው፡፡ ወንጌላዊው 'የዲያቢሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ' እንዳለ አምላክ ሰውን ያዳነበት መንገድ ዲያብሎስን እጅግ የሚያስቆጭና እርሱ ሰውን እንዳታለለ በተራው ሰው በሆነ ጌታ የተታለለበት ነበር፡፡ ፩ዮሐ. ፫፥፰ እግዚአብሔር ዲያቢሎስን ያሸነፈው በአምላክነት ኃይሉ ተጠቅሞ አልነበረም፡፡

'በአሸናፊዋ ኃይሉ አላሸነፈውም ፤ በሁሉን ቻይነቱም ድል አልነሣውም ፤ በትሕትናውና በፍርዱ እውነተኛነት እንጂ ከታላቅነቱም በአንዳች ነገር አልረታውም። በአሸናፊዋ

> ኃይሉ ሰይጣንን ድል ነሥቶት ቢሆን ድንቅ ነገር ባልሆነ ነበር' 'ወኢሞአ፡በኃይሉ፡መዋኢት፡፡ወኢኃየሉ፡በክሂሉቱ፡፡ ወኢበምንትኒ፡ እምዕበዩ፡ አላ፡ በትሕትናሁ፡ ወፍትሐ፡ ጽድቁ፡፡፡ ሶበሰ፡ ኮነ፡ እግዚእነ፡ ሞዖ፡ ለሰይጣን፡ በኃይሉ፡ መዋኢት፡እማኢኮነ፡መንክረ'[108]

ሰይጣን ወደ ሰው ልጅ የመጣው በእባብ ውስጥ እንደነበረ እናስታውሳለን፡፡ በዚያ መንገድ ከገነት የወጣውን የሰው ልጅም እግዚአብሔር በዚያው መንገድ መለሰው :-

> 'ሰይጣን በተንኮል በእባብ ሥጋ ውስጥ እንደተሰወረ ከማስሪያ መዳናችንም እንዲሁ የእግዚአብሔር ቃል በእኛ ሥጋ ውስጥ በመሠወሩ ሆነ' 'ወበከመ፡ኮነ፡እንክ፡ሰይጣን፡ በጉሕሉት፡ ተኃብዓ፡ ውስተ፡ ሥጋ፡ ከይሲ፡ ከማሁ፡ ኮነ፡ ድኅነትነ፡ እማዕሰር፡ በተሰውሮተ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ በዘመድነ' እንዲል፡፡

ሰይጣን በእባብ ውስጥ ሆኖ የሰው ልጅን ግራ ያጋባውን ያህል የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆኖ በተገለጠ ጊዜ ከፅንሰቱ እስከ ስቅለቱ ዲያቢሎስን በግራ መጋባት ማዕበል ውስጥ እንዲላጋ አድርጎት ፤ አወቅሁ ሲል ሲሰወርበት ፤ አየሁ ሲል ሲጋረድበት ቆይቶ ነበር፡፡

---

[108] ወንጌል ቅዱስ ፤ መቅድመ ወንጌል ጉባኤ ፩

ሊቃውንት እንደጻፉ ፡-

'ጌታ ዕንሱን ለዮሴፍ በመታጨትዋ ውስጥ ሰወረበት። መላእክት ዛሬ ተወለደ ሲሉ ግን አወቀ' ይህን አወቅሁ ብሎ ወደ ሕፃኑ ሲያይ ግን 'እናቱ በወለደችውና በጨርቅ በጠቀለለችው በእንስሳት በረት ባኖረችው ጊዜ ዳግመኛ ተሰወረበት' 'ካዕበ፡ ተኀብአ፡ እምኔሁ፡ ዝንቱ፡ ግብር፡ እመ፡ ወለደቶ፡ እሙ፡ ሶበ፡ ጠብለለቶ፡ በአጽርቅት፡ ወአንበረቶ፡ ውስተ፡ ጎለ፡እንስሳ' እንዲል[109]

ጌታችን ሕፃን ሳለ ሰይጣን በሔሮድስ አድሮ ግብጽ ድረስ ባሳደደው ጊዜ መሸሹን ሲያይ አምላክነቱ ተሰወረበት፡፡ እያሳደደ ያለው ሲአል ድረስ የሚያሳድደውን ጌታ እንደነበረ አላወቀም፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለ 'ሰይጣን ሳያውቅ አዳኙን አደነው'[110]

ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ 'የምወድደው ልጄ ይህ ነው' ሲባል አወቀው ሲራብ ሲያየው ግን ተሰወረበት፡፡

'ዲያቢሎስ ይህ አምላክ ቢሆን ኖሮስ ይህን አያደርግም እንዲልና በእርሱ እንዲጠራጠር ጌታችን ራሱን በመብል

---

[109] ዐሥርቱ ተስእሎታት Scritti Teologici Ethiopici, 1960

[110] St. Ephrem the Syrian, Hymn on the Nativity, Hymn 17:3

በመጠጥ ፤ በረሃብና በጥም ፤ በጾምና በጸሎት ፤ በለቅሶ ፤ በእንቅልፍና በድካም ውስጥ ሰወረ። ይህን ማድረግም ሊሰቀል እስካለባት ሌሊት ድረስ አልተወም' 'ወእግዚእነኒ: ኀብአ: ርእሶ: እምኔሁ: በመብልዕ: ወመስቴ: ወረኀብ: ወጽምእ: ወጾም: ወጸሎት: ወብካይ: ወንዋም: ወድካም: ከመ:ይናፍቅ:ቦቱ:ዲያብሉስ:ወይበል:እመሰ:ኮነ:ዝንቱ: እምላክ: እምኢገብረ: ከመዝ: ወኢያዕርግ: ዘንተ: እስከ: ሊሊተ:ሰቅለቱ'[111]

የዲያብሎስ ሥራ የፈረሰው ከሁሉም ነገር በላይ አምላክ ሰው በመሆኑ ምክንያት ሰው አምላክ በመሆኑ ነው፡፡ እርሱ ለተንኮል ብሎ ብትበሉ እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ያለውን ቃል እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ልጅ ለማንሣት በወደደ ጊዜ ፈጸመው፡፡ የሰው ሥጋ ከመለኮት ጋር ተዋሐደ ፡ የመለኮት የሆነም ሁሉ የሥጋ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር አዳም በወደቀ ጊዜ 'አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ' ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ዘፍ. ፫፥፳፪ ሰይጣን ሰውን ለማዋረድ ያቀረበው ምክር እግዚአብሔር መጨረሻ ላይ ሰውን ለማክበር ምክንያት አደረገው፡፡ ሰውን ከፈጣሪ ለማጣላት ያነሣው አሳብ ሰውን ፈጣሪ

[111] ዐሥርቱ ተስእሎታት Scritti Teologici Ethiopici, 1960

አደረገው:: ይብላኝ ለዲያብሎስ እንጂ የእኛ ሥጋስ አምላክነትንም አገኘ:: ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለው

'አዳምን የጣለው የተደመው አባብ ዳግመኛ እስከ ምን ከፍታ ድረስ ፈጣሪ አዳምን እንዳከበረው በዓይኖቹ ተመለከተ'[112]

እግዚአብሔር ፈርዶ ከመቅረትና ፍርድን ከመሻር የፍቅርና የፍርድ አማራጮች ሦስተኛውን መረጠ እልን እንጂ የወሰነው ውሳኔ ግን ፍርዱን ከመሻር የበለጠ ፍቅር ነው:: ተከሳሹን ለማዳን ፍርዱን በራሱ ላይ የሚፈርድ ዳኛ እንዴት ያለ ነው? ወንጀለኛውን ነፃ ለማውጣት ራሱ የሚታሰር ዳኛ ፣ ጥፋተኛውን ለማዳንስ የሚገረፍ ዳኛ እንዴት ያለ ነው? 'ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም' 'ፍቅር ኃያል ወልድን ከዙፋኑ ድረስ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው' ዮሐ. ፲፭፥፲፫

'የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ምድር ይወርድ ዘንድ ፣ ከድንግል ማርያም ሰው ይሆን ዘንድ ፣ በጨርቅ ይጠቀለል ዘንድ ፣ በበረት ውስጥ ይጣል ዘንድ ፣ ከሴት ልጅ ጡቶች ወተትን ይጠጣ ዘንድ ምን አተጋው?

ለእኛ ለጠፋነው አይደለምን?'

---

[112] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity, Hymn 21.25

'ምንትኑ፡እጽሐቆ፡ይረድ፡ስቃለ፡እግዚአብሔር፡ውስተ፡ምድር፡ወይሠገው፡እምቅድስት፡ድንግል፡ወይጠብለሉ፡በአጽርቅት፡ወይትወደይ፡ውስተ፡ጎሬ፡ወይጥቡ፡ሐሊበ፡እምአጥባተ፡ብእሲት፡አኮኑ፡ውእቱ፡በእንቲአነ፡ለእለ፡ማለነ'[113]

## • የአርያም ንጉሥ

ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ በተላከ ጊዜ ሁሉ የመጣበትን ምክንያት ሲያስረዳ ደጋግሞ የሚናገረው አንድ ቃል ፡- 'ትእዛዝ ወጥቶአል' የሚል ነበረ፡፡ ይህ ትእዛዝ እግዚአብሔር ለመልአኩ ወደ አንድ ሰው እንዲሔድና እንዲናገር የሚሠጠው ትእዛዝ ነበር፡፡

> 'ገናም በጸሎት ስናገር አስተድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እየበረረ መጣ። ተናገረኝም እንዲህ አለኝ፡ አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛዝ ወጥቶአል። እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ' ዳን. ፱፡፳፫
>
> 'ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃውና እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል' ዳን.፱፡፳፭-፳፫

[113] ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ዘቅዱስ አለእስክንድርስ ፲፯፡፪

ቅዱስ ገብርኤል ወደ አንድ ሥፍራ ይሔድ ዘንድ ከፈጣሪ ትእዛዝ ይወጣ ከነበረ ወደ ናዝሬት ገሊላዋ ድንግል ማርያም በተላከበት በዚያ እጅግ ወሳኝ ዕለትስ እንዴት ያለ ትእዛዝ ወጥቶ ይሆን? የዳንኤልን ሕልም ለመፍታት ትእዛዝ ከወጣ የሰው ልጆችን የዘመናት ሕልም ለመፍታት የሚወጣው ትእዛዝ የተለየ መሆኑ አይቀርም፡፡ ናቡከደነፆርን 'እውሬ ትሆናለህ' ብሎ ሕልሙን ለመፍታት ቅዱስ ጠባቂ የልዑልን ትእዛዝ ካመጣ አምላክን ሰው ይሆናል ለማለት ምን ዓይነት ትእዛዝ ያመጣ ይሆን? ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ለማውጣት ይህ መልአክ ታዝዞ ከተላከ የአዳምን ዘር ከሲኦል እሳት ለመታደግ ወሳኙን ዜና ይናገር ዘንድ እንዴት ያለ መመሪያን ተቀብሎ ይሆን?

እግዚአብሔር ቅዱስ ገብርኤልን ለመላክ ትእዛዝን ባወጣ ጊዜ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ የሚበልጠውን ዓለምን የሚያድንበትን ጥበብ ምሥጢረ ሥጋዌን ለብቻው ነገረው፡፡ ይህ ምሥጢር 'እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው' የተባለለት ምሥጢር ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት 'የማይታይ ሥውር ጥበብን አስታወቅኸኝ' ብሎ የዘመረለት ፤ 'እግዚአብሔር አስቀድሞ ለክብራችን የወሰነው ተሰውሮም የነበረውን ምሥጢር' ይህ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሥውር ጥበብ

ለቅዱስ ገብርኤል ለብቻው ነገረው፡፡ ፩ጢሞ. ፫፥፲፮ ፤ መዝ. ፶፥፮ ፤ ፩ቆሮ. ፪፥፯

ይህ ምሥጢር በአንድነት እስከዘመሩባት የልደቱ ደስታ ዕለት ድረስ ከቅዱሳን መላእክትም እንኳን ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፡፡ ሊቁም 'በአርያም ካሉ የቃልን የመምጣቱን ምሥጢር ያወቀ ማንም የለም መልአኩም ቃል ሥጋ የሚሆንበትን ዕለት አላወቀም' ወእሬኢ፡ ዘአእመረ፡እምእለ፡ሀለዉ፡ውስተ፡አርያም፡ምሥጢረ፡ምጽአቱ፡ለቃል፡ መልአክኒ፡ኢያእመረ፡ዕለተ፡ትስብእቱ፡ለቃል' ይላል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ 'ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም' እንዳለ የዚህ ዓለም ገዢ የተባለ ዲያብሎስም ስለ አምላክ ሰው መሆንና ከድንግል መፀነስ ተሰውሮበት ነበር፡፡ ፩ቆሮ. ፪፥፰ ዮሐ. ፲፪፥፴፩ 'የማርያም ድንግልና ፤ የዕንስዋ ነገርና የጌታ መሞት ከዚህ ዓለም ገዢ ከዲያብሎስ የተሠወሩ በእግዚአብሔር ዝምታ ውስጥ የተሸሸጉ ምሥጢራት ናቸው'[114] የሚለው ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ የቅዱስ ገብርኤልንም ብሥራት ዲያብሎስ ጨርሶ እንዳላወቀና ጌታም ድንግልናዊ ልደቱን ለዮሴፍ በመታጨትዋ ውስጥ ሰውሮበት እንደነበር ይገልጻል፡፡

[114] St. Ignatius of Antioch, Letter to Ephestians 19.1

በእርግጥም ዲያብሎስ የክርስቶስን አምላክነት መጠራጠር በጀመረበት ጊዜ እንኳን በሔሮድስ አድሮ ሕፃኑን ክርስቶስ ለማግኘት ብዙ ሕፃናትን አስጨፍጭፎ ነበር፡፡ ይህን ያደረገው ጠላት መፅነስዋን ቢያውቅ ኖሮ ደግሞ ብዙ ፅንስን ባጨናገፈ ነበር፡፡ ገብርኤል ወደ አንዷት ድንግል ሔዶ እንደነበረ ቢሰማ ኖሮም ብዙ የእስራኤል ደናግልን ባስገደለ ነበር፡፡ መላእክት ወደገቡበት ወደ ሎጥ ቤት እንዳይገቡ የሰዶምን ሰዎች ዓይን ያሳወረና መግቢያው እንዲጠፋቸው ያደረገው አምላክ ሰይጣንንና ሠራዊቱም ድንግሊቱ ያለችበትንና መልአከ እግዚአብሔር የገባበትን ሥፍራ እንዳያውቁ ዓይናቸውን አሳውሮባቸው ነበር፡፡ ቅዱስ ገብርኤል እንዲያበሥር የተነገረው ዜናም ከመላእክትም ከአጋንንትም የተሰወረ ምሥጢር ነበር፡፡ 'የያዘው ምሥጢር ከልዑል ዘንድ ለእርሱ ብቻ ተነግሮታልና ሊነግራት ወደደ ፤ በጉዞው እንዳይዘገይ በፈጣን ክንፎቹ ወደ እርስዋ በረረ' እንዳለ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ገብርኤል የእግዚአብሔር ምሥጢረኛ ነበር፡፡

ዲያብሎስ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም እንደተላከ ቢያውቅ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? ካልን ይኸው መልአክ በአንድ ወቅት ወደ ነቢዩ ዳንኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመው ክስተት ለዚህ መልስ የሚሆን ነው፡፡

'እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ። የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት' ዳን. ፲፥፲፪-፲፫

ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ታዝዞ ለዳንኤል መልእክትን ሊያደርስ ሲመጣ የፋርስ ሰዎችን ለማያት የሚያስገዳቸው የፋርስ መንግሥት አለቃ ዲያብሎስ ሃያ አንድ ቀን በመንገድ ላይ እየተዋጋ ተቋቁሞ አዘገየው::[115] ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳው ሲመጣ ግን ገብርኤል ወደ ዳንኤል መጣ:: ለዳንኤል መልእክቱን ከተናገረ በኋላም ገብርኤል ስለ ቀጣይ ጉዞው ሲናገር 'አሁንም ከፋርስ አለቃ ጋር እዋጋ ዘንድ እመለሳለሁ' ብሎ ከዲያብሎስ ጋር ውጊያው እንደሚዘልቅ ነግሮታል:: ዳን. ፲፥፳

ልብ አድርጉ! ለነቢዩ ዳንኤል መልእክትን ሊያደርስ የተላከውን ቅዱስ ገብርኤልን ሃያ አንድ ቀናት ተዋግቶ ያዘገየው ዲያብሎስ ይኸው

[115] ዳንኤልና ዐሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት ፤ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ገጽ ፪

መልአኩ ወደ ድንግል ማርያም ዓለምን የሚያድን መልእክትን ያደርስ ዘንድ እንደተላከ ቢያውቅ ኖሮ ስንት ቀን ያዘገየው ይሆን? በእርግጠኝነት መላውን የአጋንንት ሠራዊት ሁሉ ሰብስቦ ቅዱስ ገብርኤልን በከበበው ነበር፡፡ ገብርኤልን ለመርዳትም ሚካኤል ብቻ ሳይሆን ሁሉም መላእክት በመጡና በሰማይ ታላቅ ሰልፍ በሆነና ሚካኤልና ሠራዊቱም ዘንዶውን እንደ ቀድሞው በተዋጉ ነበር፡፡

ሆኖም 'ወሰእለ፡ ይትቃወማ፡ ኀይሉ፡ በኢያእምሮ፡ ሠወሮሙ''የሚቃወሙ አጋንንትን ባለማወቅ ሠወራቸው' እንዲል የፋርስ ብቻ ሳይሆን የዚህ ዓለም ገዢዎች አጋንንት የገብርኤልን ተልዕኮ አላወቁም ነበር፡፡ አንድም 'ወሰእለ፡ ይቀውሙ፡ ኀይሉ፡ በኢያእምሮ፡ ሠወሮሙ' ቢል 'ለምስጋና የሚቆሙ መላእክትንም ባለማወቅ ሠወራቸው'[116] ቅዱስ ገብርኤል ግን ይህን የማዳን ምሥጢር እንዲይዝ የተመረጠ የሠራዊት አምላክ ታማኝ ባለ አደራ ነበረ፡፡

በመጀመሪያው የመልአክ ተልእኮ እግዚአብሔር ድንግሊቱ ከመፅነስዋ በፊት ስለ ፅንስዋ ይነገራት ዘንድ መልእክትን አስቀድሞ ሊልክ ወደደ፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር በሁሉ የሞላ አምላክ ሆኖ ሳለ መልእክተኛን መላክ አያስፈልገውም ነበር፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ

[116] ትምህርተ ኅቡአት ፣ ምዕራፍ ፩፡፲፩

እንዲህ ይጠይቃል፡- 'እርሱ እግዚአብሔር ከኪሩቤልና ሱራፌል ይልቅ አይፈጥንምን? ከመላእክትስ ሁሉ አይፈጥንምን? የእርሱ መነሣት ከመላእክት መብረር የፈጠነ ነው። እርሱ ከብርሃን ይፈጥናል ፤ ነፋስም አይይዘውም። ታዲያ ስለምን መልአኩን ላከ? ስለምንስ እንዲሁ በማሕፀንዋ አላደረም?' ሲቱ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ይመልሳል 'ያለ ጋብቻ ያለ ሩካቤ እንዲሁ እንደፀነሰች አይታ እንዳትታወክ በድንግልና የምትፀንሰው ማንን እንደሆነ ታውቅ ዘንድ አስተድሞ ላከው'[117]

አባ ጊዮርጊስም ያለ ብሥራተ ገብርኤል ብትፀንስ ኖሮ ሊፈጠር የሚችለውን ሁኔታ ሲገልጽ ፡-

> 'ገብርኤል ሳያበሥራት በሥጋ ይወለድ ዘንድ እግዚአብሔር ቢወድድ ኖሮ በቻለ ነበር። ነገር ግን በጥቲቱ ሲያድግ ስለፅንስዋ በልቧ ይህ ስለ ጽኑዕ ደዌ የመጣ ነውን? ወይስ የሰውን ልጅ ከሚተነኳኩሱት ከመናፍስት ይሆንን ብላ እንዳትደነግጥ ለእናቱ አሰበላት'[118] ይላል፡፡

እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ከሰው ጋር ለማድረግ ሲፈልግ የሰው ልጅ ግእዛን (ነፃ ፈቃድ) ያከብራል፡፡ ነቢያቱን ለነቢይነት

---

[117] St. Jacob of Serugh, Homilies on the Nativity 144
[118] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፬፡ ፲፪

ሐዋርያቱን ለሐዋርያነት ሲመርጣቸውም አስገድዶ ሳይሆን ነፃ ፈቃዳቸውን አክብሮ ነበር፡፡ እርሱ ለማዘዝ ኃይልና ሥልጣን ያለው አምላክ ሲሆን ነቢያቱን 'ማንን እልካለሁ ማንስ ይሔድልናል?' የሚል አምላክ ነበረ፡፡ ሕሙማንን ለመፈወስም 'ልትድን ትወዳለህን?' የሚል ጌታ ፤ የሚያምንበትን ሰውም 'ሊከተለኝ የሚወድድ' ብሎ ነፃ ፈቃዱን የሚጠይቅ አምላክ ነው፡፡ ኢሳ. ፮፡፰ ፤ ዮሐ. ፭፡፮ ፤ ማቴ. ፲፮፡፳፬

'እሳትና ውኃን በፊትህ አቀረብሁልህ ፤ ወደ ወደድኸው እጅህን ስደድ' የሚለው ይህ የነፃነት አምላክ እንዲትን የዓሥራ አምስት ዓመት ገሊላዊት ብላቴና ፀንሳ እንድትወልደውና በእርሱ ምክንያት የሕይወት ዘመን ስደትን እና ኀዘንን እንድትቀበል ያለ ነፃ ፈቃድዋ ሊወስንባት አይፈልግም፡፡ 'ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ለአንድያ ልጁ እናትን ያደርግለት ዘንድ ወደደ። ሆኖም እርሱ ስለመረጣት ብቻ እናት እንድትሆን አልወደደም'[119] ስለዚህ እርሱ ለእናትነት እንደመረጣት እርስዋ ደግሞ ልጅዋ እንዲሆን ፈቅዳ ትመርጥ ዘንድ ፈቃድዋን ለመጠየቅ ብርሃናዊ መልአኩን ወደ እርስዋ ላከ፡፡

አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሙሽራ የምትሆነውን ሴት አሳምና እንዲያመጣ ሎሌውን ኢያውብርን ብዙ እጅ መንሻ አስይዞ እንደላከው

[119] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, SVS press, 1998, page 25

እግዚአብሔር አብም ለአንድያ ልጁ ማደሪያ የትሆነውን ድንግል እሺ ያሰኛት ዘንድ ሎሌውን ገብርኤልን የምስጋና እጅ መንሻ አስይዞ ሰደደው፡፡[120] ዘፍ. ፳፰፥፲፪-፲፱ ማገር ያዕቆብ እንዳለው እግዚአብሔር ጸያሒ ፍኖቱ ይሆንለት ዘንድ 'ወደ ምድር ወርዶ ያድር ዘንድ በፊቱ መንገድን ይጠርግለት ዘንድ መልአኩን ከዙፋኑ ወደ እግሩ መርገጫ ላከው'[121]

ድንግሊቱን ለእናትነት የመረጠው አምላክ መልአኩን ሲልከው ይዞአት ወደ ሰማየ ሰማያት እንዲያመጣለት አላዘዘውም፡፡ እንደ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ተጭና ወደ ጽርሐ አርያም ትምጣልኝና ከእርስዋ ሰው ሆኜ ልወለድ አላለም፡፡

> 'በወደዳትና ደም ግባትዋን በወደደ ጊዜም በጽርሐ አርያም እናት ትሆነው ዘንድ ወደ ሰማይ አላሳረጋትም። እርሱ ራሱ ወረደና በጠራቢው በዮሴፍ ቤት አደረ እንጂ። ገብርኤልን ዘጠኝ ወር በማሕፀንዋ ትሸከመኝ ዘንድ ድንግልን ወደ እዚህ አምጣት አላለውም። ራሱ ትሕትናዋን ተሳተፈ እንጂ፡

[120] በቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜ ሦስቱ አርእስተ አበው አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናቸው፡፡ አንድያ ልጁን ሊሠዋ የፈቀደው አብርሃም አንድያ ልጁን እስኪሠዋ ዓለሙን የወደደው የአብ ፤ ለአባቱ ታዝዞ ሊሞት የነበረውና በአባቱ ሕሊና ውስጥ ለሦስት ቀናት የሞተው ይስሐቅ እስከሞት ድረስ የታዘዘውና በመቃብር ለሦስት ቀንና ሌት ያደረው የእግዚአብሔር ወልድ ፤ የ፳ኤል ዘሥጋ አባቶች የሆኑ ፲፪ ልጆች አባት የሆነው ያዕቆብ ደግሞ የ፳ኤል ዘነፍስ አባቶች የሐዋርያት አባታቸው የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናቸው፡፡

[121] St. Jacob of Serugh, Homilies on the Nativity, Gorgias Press 130.

፡ ከገብርኤል ጋር ወረደ ወደ ችግረኛ ቤትም ገባ' ይላል

አባ ጊዮርጊስ፡፡

ድንግል ማርያም ፀንሳ የወለደችው በሰማይ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጆች ዛሬ ያገኘነው ደስታ ባጣን ነበር፡፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ እንዲህ ሲል ይቀጥላል :-

> 'ወሶበሰ፡በጽርሐ፡አርያም፡ፀንሰቶ፡እምኮነ፡ክብረ፡ወልዕልና፡ ለባሕቲታ፡፡ ንህነሰ፡ እምኢረከብነ፡ በቶዔተ፡ በልዕልናሃ፡፡ ምንተ፡ነአምር፡ ምሥጢረ፡ ዘበሰማያት፡ ይትገበር፡ ወምንተ፡ ንሬኢ፡ ኅቡአተ፡ ዘበአርያም፡ ሀሉ፡፡ ወሶበሂ፡ ዲበ፡ ሠረገላ፡ ኪሩቤል፡ ወለደቶ፡ መኑ፡ ዘርእየ፡ ሑታሬሁ፡ ወመኑ፡ እምገሰሰ፡ ሥጋዌሁ' 'በጽርሐ አርያም ፀንሳው ቢሆን ኖሮ ክብርና ከፍ ከፍ ማለት ለእርስዋ ለብቻዋ በሆነላት ነበር። እኛም በእርስዋ ከፍ ማለት ጥቅም ባላገኘን ነበር። በኪሩቤል ሠረገላ ላይ ወልዳው ቢሆን መታቀፉን ማን ያይ ነበር? ማንስ አካሉን ይዳስሰው ነበር?'[122]

ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን እንዲያበሥራት መመረጡ ከቅዱሳን መላእክት ሁሉ የላቀ ያደርገዋል፡፡ ልብ እንበል ከመላእክት መካከል መመረጥ ውስን ቁጥር ካላቸው ከሰው ልጆች መካከል እንደመመረጥ አይደለም፡፡ 'በውኑ ለሠራዊቱ ቍጥር አላቸውን?' እንዲል

[122] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፳፣፸፩-፸፪

ቅዱሳን መላእክት ሥፍር ቍጥር የሌላቸው ፍጥረታት ናቸው። ኢዮ. ፳፭፥፫

እንደሰው ተዋልደው ያልበዙትና በቁጥራቸው ልክ በአንድ ጊዜ የተፈጠሩት ዘር አልባዎቹ መላእክት ለመላው የአዳም ዘር ለእያንዳንዱ በራሱ ጠጉር ልክ ቢከፋፈሉ እንኳን ቁጥራቸው አይፈጸምም። ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የወረደው ዝናም ነጠብጣቡ ቢቆጠርም ከዚያ የሚበዙ ሠራዊት ናቸው። ቅዱስ ያሬድ 'ዘኅሩይ፡እምአእላፍ፡ሊቀ፡መላእክት' 'ከእእላፋት መካከል የተመረጠው የመላእክት አለቃ' ብሎ የጠራው ቅዱስ ገብርኤል የተመረጠው ከእነዚህ ሁሉ መላእክት መካከል ነውና ክብሩ ከመላእክት ሁሉ ከፍ ያለ ነው።[123]

---

123 ቅዱስ ገብርኤል በአብሣሬ ትስብእትንቱ ከመላእክት ሁሉ ይበልጣል ሲባል ራሱ ቅዱስ ገብርኤል 'ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም' ብሎ ከመሰከረለት ከመላእክት ሁሉ አለቃ ከቅዱስ ሚካኤል በቀር መሆኑ ግን ግልፅ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ሊቃነ መላእክት ለሰው ባደረጉት በጎነት በክብር እንዲተካከሉ አድርጎአቸዋል። ሁለቱን ኪዳናት ለሁለት እካፍሎ ሚካኤልን 'መጋቢ ብሉይ' ቅዱስ ገብርኤልን 'መጋቢ ሐዲስ' አድርጎአቸዋል። ገብርኤልን ለሥጋዌው አብሣሪ ፣ ለቃል ጸያሒ ፍኖት ሲያደርገው ቅዱስ ሚካኤልን ደግሞ አስከትሎት እንደነበር ሊቃውንት ይገልጻሉ። 'ተለዎ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለቃለ እግዚአብሔር እስከ ምጽንአት ኃምስ በከመ ያስተፋት ሐራ መልአኮ' 'የመላእክት አለቃ ሚካኤል ጭፍራ አለቃውን እንደሚሸኝ እስከ አምስተኛው ሰማይ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ተከተለው' እንዲል /ድርሳነ ሚካኤል ዘሚያዝያ/ በትንሣኤው ዕለት ከመቃብሩ ራስጌና ግርጌ ሆነው ለቅዱሳት አንስት አብረው የታዩትም ሚካኤልና ገብርኤል ነበሩ። እግዚአብሔር ወልድ ቀዳማዊ ምጽአቱን እንዲያውጅ ገብርኤልን ሲመርጠው ዳግም ምጽአቱን ደግሞ ከመለከት ድምፅ ጋር የሚያውጀው ቅዱስ ሚካኤል ነው።

ቅዱስ ገብርኤል እንዲናገር የተመረጠው ዜና በገነት ውስጥ የተበላሸውን የሰው ልጅ ታሪክ የሚለውጥ ፣ ሰውና አምላክን ፣ ሰማይንና ምድርን ፣ ነፍስና ሥጋን የሚያስታርቅ ዜና ነበር፡፡ ወንጌል 'ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ መላእክት ዘንድ ደስታ ይሆናል' ይላል፡፡ሉቃ. ፲፭፥፲

ይደንቃል! ቅዱሳን መላእክት የአንድን ሰው መዳን ሳይንቁ ሐሴትን ያደርጉበታል፡፡ የአንድ ኃጢአተኛ ሰው መዳን መላእክትን ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ከሆነ የሰው ልጅ ሁሉ መዳን አንዱን መልአክ ገብርኤልን ምንኛ ደስ ያሰኘው ይሆን? ገብርኤልስ ይህን ለመላእክት ሁሉ ሐሴት የሚበቃ የሰው መዳን ዜና ሰምቶ ደስታውን ለብቻው እንዴት ቻለው? ለብሥራታዊው መልአክ ይህን ደስታ በልቡ ብቻ መያዝስ እንዴት ያለ ከባድ ነገር ይሆንበት ይሆን?

ቅዱስ ገብርኤል ይህን ዜና በምሥጢር ይዞ ለድንግሊቱ እንዲያበሥር ሲነገረውም በታላቅ ደስታ ደስ ብሎት ነበር፡፡ ዜናው ሰውን ከመላእክት በላይ ከፍ የሚያደርግና ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክል ዜና ቢሆንም ቅናትና ምቀኝነትን የማያውቀው ገብርኤል ዜናውን ሲሰማ ደስ አለው፡፡ 'ሰውን ስለመውደዱና ስለ ርኅራኄው በአዳም መውደቅ ያዝን ነበርና ከጌታው ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ደስ

አለው'[124] መቼም ፊትን አኮማትሮ 'ደስ ይበልሽ' ማለት የለምና ቅዱስ ገብርኤል በድንግሊቱ ፊት በደስታ ስለተናገረ ቤተ ክርስቲያናችን 'ፍሡሕ' 'ፍሡሐ ገጽ' (ደስተኛው ፤ ደስ የተሰኘ ፊት ያለው) ትለዋለች፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በፍርሃት የሚቆመው መልአክ በድንግል ማርያም ፊት ግን በደስታ ሊቆም ተመረጠ፡፡ 'በዚያ ገብርኤል በፍርሃት ይቆማል ፤ በዚህም ገብርኤል በሐሴት የምሥራች ይናገራል' 'ህየ፡ ገብርኤል፡ ይቀውም፡ በፍርሃት፡ ወበዝየ፡ ገብርኤል፡ ያበሥር፡ በትፍሥሕት' እንዲል፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ወደ ዳንኤል ሲላክ እንዴት እንደመጣ ዳንኤል እንዲህ ሲል ይገልጻል ፦

> 'ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ። አስተማረኝም፥ ተናገረኝም እንዲህም አለ፦ ዳንኤል ሆይ፥ ጥበብንና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ'

እየበረረ የመጣበትን መልእክትም ሲያስረዳው ትንቢት ነበረ ፦

> 'ስለዚህ እወቅ አስተውልም ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው

---

[124] ድርሳነ ገብርኤል ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፤ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ዘመጋቢት

እስከ መሚሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች ...ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሚሕ ይገደላል' ዳን. ፱፥፳፭-፳፮

ቅዱስ ገብርኤል ለዳንኤል ስለ መሲሑ ክርስቶስ መምጣትና ስለሞቱ ጭምር ስንት ሱባዔ እንደ ቀረ አብራርቶ ነገረው፡፡ አሁን ደግሞ የተናገረው ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ ደርሶ ወደ መሲሑ እናት እንዲሔድ ታዘዘ፡፡ ነቢያት ትንቢቱን ተናግረው ሲፈጸም ሳያዩ ሞተዋል፡፡ መሰንበት ደግ ነውና የማይሞተው ገብርኤል ግን ለዳንኤል የነገረውን ትንቢት ሲፈጸም ሊያይ ተላከ፡፡

ለድንግሊቱ ሒደህ ተናገር የተባለው ተደርጎ የማያውቅና የማይታመን ነገር ነበር፡፡ 'አምላክ ሰው ይሆናል' ፡ 'ከአንቺ ይወለዳል' ፡ 'ያለ ወንድ ዘር ትፀንሺያለሽ' ብሎ ለአንዲት ብላቴና እንዲናገር ትእዛዝ ወጣ፡፡ ይህ ብሥራት ገብርኤል ሌላ ቀን ሒዶ እንደተናገራቸው ዜናዎች አልነበረም፡፡ እርሱና የመላእክት ማኅበር ፊታቸውን በክንፎቻቸው ሸፍነው የሚንቀጠቀጡለት አምላክ በአንዲት ድንግል ማሕፀን ሊያድር መሆኑን መናገር ቀርቶ ማመን ራሱ ከባድ ነበር፡፡ ፈጣሪውን ሰው እንደሚሆን ማሰብ ለአንድ መልአክ እጅግ የረቀቀ ምሥጢር ነው፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ግን አምላኩን ገና ሳያውቀው 'አምላካችንን እስክናገኘው ድረስ ጸንተን እንቁም' ያለ በእምነቱ የመላእክትን እምነት ያጸና መልአክ ነውና የአምላክን ሰው መሆን ዜና ሲናገር አላመነታም፡፡

ሙሴ ለእስራኤል ሔደህ እግዚአብሔር ላከኝ ብለህ ንገራቸው ሲባል 'ማን ላከህ ቢሉኝስ' 'እነሆ አያምኑኝም ፣ ቃሌንም አይሰሙም' ብሎ ነበር፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ግን ድንግሊቱ ቃሌን ባታምነኝስ? ብሎ ለመሔድ አላንገራገረም፡፡ እንደ ነቢዩ ዮናስም ፈጣሪ ያለውን ባያደርግስ ብሎ የታዘዘውን ላለመናገር አልኮበለለም፡፡ ዘጸ. ፬፥፩ ፣ ዮና. ፩፥፫

ሊቁ አባ ዮሐንስ ዘደማስቆ የገብርኤልን እንደበት እንደበት አድርጎ እንዲህ ይቀኛል፡-

'ገብርኤል በሰማያት እንዲህ አለ፦ በከፍታዎች የሚኖር እርሱ ማንም ሊመረምረው የማይቻለው እርሱ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሰማይ ዙፋኑ ምድር የእግሩ መረገጫ የሆነ እርሱ እንዴት በአንዲት ድንግል ማሕፀን ሊወሰን ይችላል? ስድስት ክንፍ ያላቸው ኪሩቤልና ሱራፌል ሊያዩት የማይቻላቸው እርሱ የፍጥረቱን ሥጋ ሊለብስ እንደምን ወደደ? እዚህ መቶሚ ስለምንድርን ነው? ወደ ባሪያይቱ ሔጀ ፦ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ፣

ንጽሕት ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ ፣ የሕይወት እናት

ሆይ ደስ ይበልሽ ልበላት እንጂ'[125]

ወዳጄ ለአንድ ሰው ሕይወቱን የሚለውጥ የምሥራች ተናገር ብትባል ወደዚያ ሰው የምትሔደው እንዴት ነው? በእግርህ ከሆነ ትሮጣለህ ፣ በፈረስ ከሆነ ትጋልባለህ፡፡ ከመቸኮልህ የተነሣ ክንፍ ቢኖርህም አትጠላም፡፡ ገብርኤል ግን ብርሃናዊ ክንፎች ያሉት መልአክ ነውና የሰውን ልጅ ሕይወት የሚለውጥ ዜና ይዞ እንደ አብርሃም ሎሌ 'እግዚአብሔር መንገዴን አትንቶልኛልና አታዘግዩኝ' ብሎ ክንፉን እያማታ በረረ፡፡ ኪሩቤል የተባሉት መላእክት የገነትን በር በሚነድድ የእሳት ሰይፍ ዘግተው ሰው ወደ ገነት እንዳይገባ ሲጠብቁ ቅዱስ ገብርኤል ግን እንዴት ወደ ገነት እንደምንመለስ በምሥጢር ሊነግረን ገሰገሰ፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን 'የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፡ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም ፤ ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም' ብሎ ነበር፡፡ መክ. ፩፥፱ ቅዱስ ገብርኤል ግን ከፀሐይ በታች የሚፈጸም አዲስ ነገር ይዞ ተላከ፡፡ የአምላክ ሰው መሆን

---

[125] Holy Apostles Convent : The Life of the Virgin Mary, The Theotokos, page

'የዜናዎች ሁሉ ዜና ፤ ከፀሐይ በታች የተደረገ ብቸኛው አዲስ ነገር ነው'[126] ይላል አባ ዮሐንስ ዘደማስቆ

ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ይገልጸዋል :-

'ከንጉሡ ሸንጎ ትእዛዝ ወጣ ፤ ቅዱሱ ጠባቂ መልእክቱን ተሸከመ፡ ፡ ከሰማያውያን ኃይላት በላይ በፍጥነት በረረ። ከመላእክት ማኅበር በላይ ገሰገሰ። በመላእክት እለቶች መካከልም አልዘገየም።

በነገዶች መካከል በረረ እንጂ በጭፍሮች ውስጥ አልቆየም። የእሳት ነበልባልን መንኰራኵር እየሰነጠቀ ፤ ነፋሳትን እየከፈለ ፤ በእሳት ፍሕም እየተራመደ መጣ'[127] 'የሰው ልጅ ደስታን ይናገር ዘንድም መንፈሳዊው ረቂት መልእክ እየተንቦገቦገ ወረደ'[128]

- ***ደስ ይበልሽ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበልሽ!***[129]

[126] St. John of Damascus, Exposition about the way of conceptionof the Word & divine incarnation book III 46

[127] St. Jacob of Serugh, Homily on the Nativity , Gorgias Press 155

[128] ርቱዐ ሃይማኖት ትርጉም ፤ መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ ፤ ማኅበረ ቅዱሳን 140

[129] ቅዱስ ጳውሎስ የደስታ መልእክት ተብሎ በሚጠራው የፊልጵስዩስ መልእክቱ ላይ ዐሥራ ስድስቴ ደስ ይበላችሁ ብሏል፡፡ ከሁሉ የሚታወቀው 'ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ' የሚለው ነው፡፡ ሊናገር የወደደው የደስታ ቃል በአንድ የማይበቃ ሆኖበት ደገመው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ያመጣው ደስታስ አንድ ይበቃው ይመስላችኋል? አባቶቻችን ደስ ይበልሽን በጸሎቶቻችን 'ተፈሥሒ'ን የሚያስደግሙን ይህን ስለተረዱ ነው፡፡ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበልሽ ያልሁት ለዚህ ነው፡፡

'ማርያም ከገብርኤል ጋር የተነጋገረችበት ይህ ቅጽበት ድንቅ ነገርን የተሞላ ነው። አንዲት የድሆች ልጅ እና አንድ መልአክ ተገናኝተው ድንቅ ነገርን ተነጋገሩ። ንጽሕት ድንግል ከእሳታዊው ጠባቂ ጋር ተነጋገረች። ይህ ምልልስ የሰማይና የምድርን ነዋሪዎች ያስታረቀ ነበር።

አንዲት ሴትና አንድ የሠራዊት አለቃ ለመላው ዓለም ዕርቅ ስምምነትን አደረጉ። በሰማያውያንና በምድራውያን መካከል ቁጭ ብለው ተወያዩ ተነጋግረውም ሰላምን አደረጉ።

በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል ስለነበረው ጠብ ባሪያይቱ ከጠባቂው ጋር ተገናኝተው ተከራክረው ተስማሙ። በገነት ዛፎች መካከል የተፈጠረው ታላቁ ጠብ ለውይይት ቀረበ። ችግሩም ፍጻሜ አገኘና ሰላም መጣ። ምድራዊትዋና ሰማያዊው በፍቅር ተነጋገሩ። በሁለቱ ወገን የነበረው ትግል ቆመ ሰላምም ተደረገ'[130] ይላል ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ የገብርኤልን ተልዕኮና የድንግልን መበሠር ትርጉም ሲያብራራ፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ናዝሬት ገሊላ ወደምትባል ከተማ ቢወርድም ያበሥራት ዘንድ ወደ ድንግሊቱ የገባበት መንገድ የተለየ ነበር፡፡ መልአኩ ከዚህ ቀደም ለብዙ ሰዎች በተለያየ መልክ ተገልጾ አናግሮአቸዋል፡፡ ቅዱስ ያሬድ እንዳለው ለሙሴ በዕፀ

[130] St. Jacob of Serugh, On the mother of God, Homily 1 626- 627

ጳጦስ ፡ ለበለዓምና ለሰብአ ሰገል በኮከብ ታይቶአል፡፡[131] ለዳንኤልና ለሕዝቅኤል በሰው አምሳል ፡ ለነነዌ ንጉሥም በሚያስፈራ ነበልባል መካከል ታይቶታል፡፡ ወደዚህች ድንግል ሲሔድ ግን ወዳለችበት ከመግባቱ በፊት ምን ሆኖ እንደሚታያት ፡ በምን መንገድ እንደሚገለጽላት ቆም ብሎ ማሰብ ነበረበት፡፡ ለሰው ልጅ ማብሠር የመጀመሪያ ጊዜው ባይሆንም አምላክ ሰው ይሆናል ብሎ መናገር የመጀመሪያው ነውና በጥንቃቄ አየው፡፡

በሕልምዋ ታይቶ እንዳይነግራት በሕልም የታየ ነገር የመታመን ዕድሉ ጠባብ ነው፡፡ በተለይም 'አምላክን ትወልጃለሽ' የሚል መልእክትን በሕልምዋ ብታይ 'የዛሬው ሕልም ደግሞ እንዴት ያለ ነው?' ብላ ለብዙ ትርጉም የተጋለጠ አሻሚ ነገር ሊሆንባት ይችላል፡፡

ስለዚህ :-

[131] 'ክብሮሙ ለመላእክት ከመ መንኰራኵር ወረደ መልአከ እግዚአብሔር ፤ ኀበ ማርያም ድንግል ዘተናገር ለሙሴ በኀበ ዕፀ ጳጦስ ይእቲ ማርያም ገብርኤል ሰበከ ላቲ ዜና ዘለእኩ ኵሉ ነገረ' /ዘታኅሣሥ ገብርኤል/ ፤ 'ሕዝቅኤል ዘነጸረከ በአምሳለ ብእሲ ክቡር' 'ሐዋርያ ልደት ገብርኤል ለበለዓም ኮከበ ሕልሙ' 'The Watcher, of whom you spoken is he who came as a star' St. Ephrem the Syrian Hymn XV' 'ንጉሠ ነነዌ ዘርእዮ በማዕከለ ነበልባል መፍርሕ' /መልክዓ ገብርኤል/

> 'በሕልም ሳይሆን በፊትዋ በሚታይ አካል ቶሞ ተገለጠ ፤ የሚነግራት ዜና ታላት ነውና ጉዳዩ ከመነሣቱ በፊት ታላት መገለጥን ሊታይ ይገባታል'[132]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የሾመው ቅዱስ ድሜጥሮስ ዘአንጾኪያ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግሊቱ ሲላክ የተሠጠውን መመሪያ እንዲህ ይገልጸዋል ፦

> 'እግዚአብሔር ገብርኤልን እንዲህ ሲል ላከው ፥ ታናሽ ብላቴና ናትና እንዳታስደነግጣት ፤ ፍርሃትንም ልትሸከም አትችልም። በዘካርያስ ላይ እንዳደረግኸው የትግትን ማስጠንቀቂያ በእርሰዋ ላይ እንዳታደርግ። በደስታና ሐሴት ሆነህ ተገለጥላት። በእርስዋ ላይ ስለሚሆነው ስለ እኔ ክብርም ንገራት አለው'[133]

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በመገለጡ እንዳያስደነግጣት በሽማግሌ አምሳል ተገለጠላት ሲል ጨርሶ ምድራዊ እንዳይመስላት ግን መልኩ ብርሃናዊና መልአካዊ መሆኑን ሁሉም ሊቃውንት ይስማማሉ፡፡[134] ቅዱስ ገብርኤል ወደዚህች ብላቴና ለመግባት የተጨነቀውን ያህል ወደ ባቢሎን

[132] St. John Chrysostom, Homily 4

[133] St. Dimetrius od Antioch, Discourse by Dimetrus, pg 262

[134] ግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ወንጌል ዘመርጡለ ማርያም

እሳት ለመግባት አልተጨነቀም፡፡ ሊያናግራት የተላከባት ድንግል በዕድሜዋ ትንሽ ናት ፤ በክብርዋ ግን ትልቅ ናት፡፡ ፈጣሪ ለማደሪያነት የመረጣት ይህች ድንግል እንዴት ያለች ትሆን? ምድርን የሚያረሰርሰውን ንጹሕ ዝናም የምታስገኝ ታናሽ ደመና እንዴት ያለች ናት? የፈጣሪውን የከበረች ሕያዊት ዙፋን ለመቅረብ መልአኩ በአክብሮት 'ወደ እርስዋ ገባ'፡፡[135] ለዘካርያስ በቤተ መቅደስ እንዳደረገው በባዶ ሥፍራ ላይ ድንገት አልተገለጠም በእርጋታ ወደ እርስዋ ገባ እንጂ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ለብዙ ደናግል 'ወደ እርስዋ ገባ' ተብሎ የተነገረላቸው ስለ ወንድ ነበር፡፡ 'አብርሃምም ወደ እርስዋ ገባ ፀነሰችም' ፤ 'ያዕቆብም ወደ እርስዋ ገባ ፀነሰችም'፤ ይሁዳም ወደ እርስዋ ገባ ፀነሰችም ወንድ ልጅም ወለደች' የሚሉ ጥቅሶች መጽሐፉን ሞልተውታል፡፡ ዘፍ.፲፮፡፬፡ ፳፱፡ ፳፫፡ ፴፰፡፪

---

[135] ቅዱስ ገብርኤል ለድንግሊቱ ከማብሠሩ አስቀድሞ ቃሉን እንዳሰማት የነገረ ማርያም መጻሕፍት ያስረዳሉ፡፡ ይህ የቅድመ ብሥራት ታሪክ /Pre-annunciation story/ ቁጥሩ ቢለያይም በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የመጀመሪያውን ቃለ መልአክ ሰምታ ምን ይሆን ያለችበት ሥፍራ ውኃ ትቀዳ የነበረችበት ሥፍራ መሆኑን እና በኋላም በዮሴፍ ቤትና በቤተ መቅደስ እንደተበሠረች ነገረ ማርያም ይተርካል፡፡ በ400 ዓ.ም ቅዱስ የሮኒመስ የጻፈው ከታብም ይህን እውነታ የሚያጸና ሲሆን በሀገረ እስራኤል ከሚጎበኙ ቅዱሳት መካናት አንዱም የማርያም ምንጭ ተብሎ የሚጠራው ሥፍራ ነው፡፡ (St. Jerome, Letters to Eustochium, The Life of Virgin Mary, The Apostles Convent 1989 pg 87 )

ወደዚህች ድንግል ግን የገባው ወንድ አልነበረም:: ወደ እርስዋ የገባው ብርሃናዊ መልአክ ነበር:: በእርስዋ ዕድሜ ያሉ ሌሎች ደናግል ሴቶች 'አንቺ እኮ ከሌሎች ሴቶች ሁሉ ትበልጫለሽ' የሚል የውዳሴ ንግግርን በደስታ ከወጣት ወንዶች አንደበት በተመስጦ ይሰማሉ:: 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?' ብለው እንኳን ሳይጠይቁም በከንቱ ውዳሴ ልባቸውን ይሠጣሉ:: የሥጋ ፈቃድ ባታለላቸው ወጣቶች እጅ በሎሚ በቀለበት ፡ በሥጦታ ተታልለው ይወድቃሉ:: ይህች ድንግል ግን እግዚአብሔር በገብርኤል በኩል ካሰማት ቃል በቀር በጆሮዋ የወንዶችን የማባበል ቃል አልሰማችም:: 'ድንግል ሆይ የሚያታልሉ ጎልማሶች ያረጋጉሽ አይደለሽም ፤ የሰማይ መላእክት ጎበኙሽ እንጂ' 'ኦ፡ድንግል፡ እኮ፡ወራዙት፡ሰፋጣን፡ዘናዘዙኪ፡አላ፡መላእክተ፡ሰማይ፡ሐወጹኪ'[136] እንዲል አባ ሕርያቆስ::

'ደናግል ሆይ የሰማያዊ ሕይወት አርኣያና አምሳል የሆነችው የድንግል ማርያም ሕይወት ይኑራችሁ። እርስዋ ለክርስቶስ እናት ለመሆን በምንም የምታንስ አልነበረችም' የሚለው ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ስለ ድንግሊቱ ሕይወት እንዲህ ይላል:-

[136] ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፳፩፻፫

> 'እግዚአብሔር ዳኛዋ እንዲሆንላት ትጸልይ ነበር እንጂ በወንዶች መታየትን አትሻም ነበር። ከቤት ለመውጣት አትቸኩልም ነበር። በሕዝባዊ ሥፍራዎች የሚያውቃት ሰው አልነበረም። ማር እንደምትሠራ ንብ በቤትዋ ውስጥ ብቻ መቆየትን ትመርጥ ነበር። በቤትዋ የተረፈውን ሁሉ ለድሆች በቸርነት ትሠጥ ነበር። ቃላትዋ ጥንቃቄን የተሞሉ ነበሩ ፤ ድምፅዋም የተመጠነ ነበር። ጮኻ አትናገርም ነበር። ማንም ላይ ክፉ ነገርን አልተናገረችም። ክፉ ወሬን ለመስማትም አትፈቅድም ነበር'[137]

'ተፈሥሒ፡ ባሕታዊት፡ እንተ፡ ኃጣእኪ፡ መሦለስ'የሚመስልሽ ያጣሽው ብቸኛይቱ ሆይ ደስ ይበልሽ' እያልን የምናመሰግናት ይህች ድንግል ከዕድሜ እቻዎችዋ በተለየ በፍጹም ጭምትነት የምትኖር ቅድስት ነበረች፡፡

ቅዱስ አምብሮስ ደግሞ ለደናግል በጻፈው ክታቡ እንዲህ ይላል፦

> 'በእርግጥም ቅዱስ ገብርኤል ወደ እርስዋ ሲገባ ብቻዋን በቤት ውስጥ ነበረች። ከማንም ሰው ጋር አልነበረችም። ማንም እንዲያውካት አልወደደችም ነበር። እኩዮችዋን

[137] St. Athanasius, Corpus Scriptorum Christianorum Orientalusm, Louvain 1903, 60-61, St. Athanasius, Letters to the Virgins 256-259

በምንም ነገር ለማስተናት ሞክራ አታውቅም። አሳቦችዋ ጓደኞችዋ ነበሩና ሌሎች ሴቶችን ጓደኛ ልታደርግ አልወደደችም።

ይልቁንም ብቸኝነት የማይሰማት ብቻዋን በሆነች ጊዜ ነው። ብዙ መጻሕፍት ፣ ብዙ ነቢያት ፣ ብዙ መላእክት ከእርስዋ ጋር ሆነው እንደምን ለብቻዋ ትሆናለች? በሕልምዋ ሳይቀር ቅዱሳት መጻሕፍትን ትሰማ ነበር። ብዙ ጊዜ ከቤትዋ አትወጣም ነበር። ቅዱስ ገብርኤልም ያገኛት በቤትዋ ሆና ነበር'[138]

ቅዱስ ገብርኤል ሌሎችን ሲያበሥር 'ዳንኤል ሆይ ቃልህ ተሰምቶአልና ወደ አንተ መጥቻለሁ 'ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ' እንዳለው ድንግሊቱን 'ማርያም ሆይ ጸሎትሽ ተሰምቶልሻል' አላላትም፡፡ ምክንያቱም ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ለመሆን አንድም ቀን ጸልያም አስባም አታውቅም፡፡ ብዙ የእስራኤል ደናግል 'መሲሑን እኔ እወልደው ይሆናል' ብለው ድንግልናቸውን ጠብቀው ኖረዋል፡፡ እርስዋ ግን የተመረጠችው ራስዋን አጭታለት ለማታውቀው

[138] St. Ambrose, Concerminig Virgins, The Niciene PNF, 2nd Series Vol.X Philp Scaff, pp 374-375

ጉዳይ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን በልብዋ እንጂ በማሕፀንዋ ፀንሶ መኖር በእርስዋ ዘንድ አሳብ ሆኖ አያውቅም፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም እንዲህ ይላል ፡-

'ብዙ ሴቶች "ድንግል ትፀንሳለች" የሚለውን ትንቢት ሰሙ የነገሥታት ሴት ልጆችና የባለጠጋ ልጆች [መሲሑን] ሊወልዱ በተስፋ ተጠባበቁ:: እርሱ ግን ከድሆች ልጅ ተወለደ:: ጌታ ሆይ በአንተ ምክንያት የነገሥታት ልጆች በድሆች ልጅ ቀኑ:: ወደ ደሃዋ ቤትም ነገሥታት እጅ መንሻ ይዘው ሔዱ'

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜው ፦

'መኝታውን በወርቅ ያጌጠ ማድረግ ሲችል በግርግም ውስጥ ማድረግን መረጠ ፤ እናቱንም ከንግሥታት አንዲቱን ማድረግ ሲችል አላደረገም'[139] ብሏል፡፡

ድንግል ማርያም እንዲህ ናት:: ታላላቅ ሀብታትን ሳትጠይቅ የተቀበለች ፣ ሳትለምን የተመረጠች ፣ ሳታገባ የፀነሰች ፣ ሳታምጥ የወለደች ፣ ድንግልናዋን ሳታጣ እናት የሆነች ፣ አንዳች ሳትሻ ሁሉን ያገኘች የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እርስዋ ናት፡፡

---

[139] St. John Chrysostom, Commentary on the Psalms 45, Robert C.Hill, Vol.1, 260

ሶርያዊው ድንግሊቱን ልጅ ለመውለድ ከተማፀኑ ሌሎች ሴቶች ጋር እያስተያየ እንዲህ ይገልጻታል፦

'ሐና የሳሙኤል እናት ለመሆን ስክረሻል እስክትባል ድረስ ጸለየች። ራሔልም ባልዋ ያዕቆብ ላይ 'ልጅ ካልሠጠኸኝ እሞታለሁ' ብላ እስከመጮኽ ደረሰች። ሣራና ኤልሳቤጥም ልጅን ለማግኘት ለዓመታት ለመኑ። ድንግል ማርያም ግን ያለ ስእለት ያለ ጸሎት ፤ በድንግልናዋ ፀንሳ የፍጥረታትን ጌታ ወለደች' ፩ሳሙ.፩:፲፫ ፤ ዘፍ.፴:፩ ፤ ሉቃ.፩:፲፫

ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግሊቱ ሲገባ ከዚያ በፊትም በኋላም ለማንም አቅርቦት የማያውቀውን ሰላምታና ምስጋና አቀረበላት፡፡

'ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ'

ልብ በሉ ፤ ገብርኤል ወደ ዳንኤል በተላከ ጊዜ ንግግሩን የጀመረው እንዲህ ነበር ፡- 'ዳንኤል ሆይ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬያለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል ቀጥ ብለህም ቁም' ወደ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ በተላከም ጊዜ የንግግሩን መክፈቻ 'ዘካርያስ ሆይ፤ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ' የሚል ነበር፡፡ መልአኩ ነቢዩንና ካህኑን ያናገረው 'አስተውል ፤ ቀጥ ብለህ ቁም ፤ አትፍራ' በሚል መግቢያ ነበር፡

፡ ወደዚህች ድንግል ሲመጣ ግን በቀጥታ ስለመጣበት ጉዳይ መናገርን አላስቀደመም፡፡ በስምዋ እንኳን አልጠራትም፡፡ እሳታዊው መልአክ ገብርኤል በዓሥራ አምስት ዓመትዋ ብላቴና በድንግል ማርያም ፊት ቆሞ ለእርስዋ የሚገባን ምስጋናን የተሞላ ሰማያዊ ሰላምታ አቀረበ፡፡

ቅዱሳን መላእክት የዘወትር ሥራቸው በደስታ ፈጣሪያቸውን ማመስገን ነው፡፡ ነቢዩ ‘የቃሉን ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ’ እንዳለ ቅዱሳን መላእክት ‘ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች’ እያሉ ሲያመሰግኑ ‘ቀንና ሌሊት አያርፉም’ ኢሳ. ፮፥፫ ፣ ራእ. ፬፥፰

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በየትኛውም ሥፍራ ቅዱሳን መላእክት ለሰው ተገልጸው የአክብሮት ሰላምታ እንደሠጡ ወይንም ‘አንቺ ከሴቶች የተባረክሽ ነሽ’ ብለው ምስጋና እንዳቀረቡ አልተጻፈም፡፡ ለዚህች በዕድሜዋ ገና ታናሽ ለሆነች ድንግል ይህን ሰላምታ ያቀረበው ከመላእክት ሠራዊት አንዱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ከሚቆሙት ከዋነኞቹ የሠራዊት አለቆች አንዱ የመላእክት አለቃ ገብርኤል ነው፡፡ ይህ መልአክ በአክብሮት ከፊትዋ ቆሞ ‘ደስ ይበልሽ’ ብሎ ለዚህች ድንግል ያቀረበው ሰላምታ ተሰምቶ የማያውቅ ነበረ፡፡ ይህ ሰላምታ እንኳን ሌላውን ሰው ሰላምታው የቀረበላትንም ድንግል ያስደነቀ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍትን የምታውቀው ድንግል ማርያም ይህን ሰላምታ ለሌላ ሰው ሲቀርብ በመጻሕፍት ስላላነበበች 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?' ብላ ተደነቀች::

ድንግል ሆይ 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው' አልሽን? እኛንም ለአንቺ የቀረበው ከእግዚአብሔር የተላከ ሰላምታና የምስጋና ቃል እጅግ አስደንቆናል:: አንብበን አንጠግበው ብለን እኛም ዘወትር 'በመልአኩ በገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን' እያልን ከእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ገብርኤል ከፊትሽ በቆመልሽ በአንቺ ፊት እንቆማለን:: ለድንግሊቱ 'እመቤታችን ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን' የሚለውን ጸሎት ለመጸለይና ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተሠጣትን የምስጋና እጅ መንሻ እንኳን በድጋሚ ለመሥጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ምንኛ ያሳዝናል?

ወዳጄ ለድንግሊቱ የገብርኤልን ሰላምታ ለመጸለይ ውስጥህ ደስ ካልተሰኘ ሳትፈልግ እንዳትሞክረው:: ደስ ሳይልህ 'ደስ ይበልሽ' ማለት እንዴት ይሆናል? ሰላም ሳይሆኑስ ሰላምታ ማቅረብስ እንዴት ይቻላል? ምስጋናዋን ውስጥህ ካልተቀበለው ለእርስዋ ሰላምታ ከማድረስህ በፊት ገና ልትወጣባቸው የሚገቡ ብዙ ገብርኤላዊ እርከኖች አሉብህ ማለት ነው:: እንደ ገብርኤል 'ባለንበት እንጽና ብለህ' አምላክህን በማመን

የምትጸና ፡ በእግዚአብሔር መቅደስ ፊት የማይታጎል የምስጋና ሕይወት ያለህ ፡ ከሊቃነ መላእክት ጋር አብረህ ፈጣሪህን የምታመሰግን ከሆንህ ድንግሊቱን ሰላም ለማለት ምናልባት ትመረጥ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከፈጣሪህ ጋር ታረቅ 'በእግዚአብሔር ፊት' እንደ ገብርኤል መቆም ካልቻልህ ድንግሊቱም ፊት ለመቆምና ለማመስገንም ገና ብቁ አይደለህም፡፡

እርሱ ፊት ለጸሎት ከቆምህ ግን 'ገብርኤልን ወደ እናትህ የምስጋና እጅ መንሻ አስይዘህ የላክኸው ሆይ እባክህን እኔንም ላከኝ' ብለህ ተማጸነው፡፡ ጸሎትህ ከሠመረ በደስታ 'በመልአኩ በገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ' ለማለት ትበቃ ይሆናል፡፡ እንደ ገብርኤልስ መሆን አልችልም ካልከኝ ደግሞ እርስዋን ማመስገንም እንደማይገባህ ተረድተሃል ማለትህ ነውና የእኛን ዝቅታና የድንግሊቱን ከፍታ ከተረዳን ልጆችዋ ጋር አብረህ መጥተህ 'እመቤቴ ሆይ የጻድቃን ትዳሴ ይበቃኛልና የኃጢአተኛ ምስጋና ለምኔ ነው አትበዪ ፤ የእኔ ኃጢአት የአንቺን ትድስና አያረክሰውምና' እያልክ አመስግናት፡፡

'ደስ ይበልሽ' የሚለው የደስታ ብሥራት ቃል የሐዲስ ኪዳን አሳብ አጠቃልሎ የያዘ ቃል ነው፡፡ 'ወንጌል' (evangelion) የሚለው የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ የምሥራች ማለት ነው፡፡ ክርስትና ማለት

'ጌታ ተወልዶአል ደስ ይበላችሁ' 'ጌታ ተነሥቶአል ደስ ይበላችሁ' 'በጌታ ደስ ይበላችሁ' የሚሉ ደስታዎችን የያዘ እምነት ሲሆን የመጨረሻ ተስፋውም 'ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' መባል ነው:: የመጀመሪያው ወንጌል 'ደስ ይበልሽ' በሚል ርእስ የተሰበከላትና ይሁንልኝ ብላ ያመነችው ብፅዕትም ድንግል ማርያም ናት::

መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤልም በሰባኬ ወንጌል ወግ ሰላምታ ሠጥቶ የአምላክን ሰው መሆን ዜና ፤ የምትወልደውን የዘለዓለም ንጉሥ ማንነት ፤ በድንግሊቱ ላይ የሚሆነውን የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም በሚል መደምደሚያ በአግባቡ ሰብኮ ድንግሊቱን አሜን ያሰኘ ፤ እንደ ዮሐንስ ለቃል መንገድ ጠራጊ የሆነ ሰማያዊ ሰባኪ ነው:: የትኛውም የወንጌል ሰባኪም ቅዱስ ገብርኤል በድንግሊቱ ፊት ከተናገራቸው ሃሳቦች ቢያንስ አንዱን ሳይነካ ወንጌልን ሊያስተምር አይችልም:: የአክብሮት ሰላምታ ሳይሠጥ ፤ ከዚያም የልዑልን ልጅ ኢየሱስን ሳያነሣ ፤ የድንግል ማርያምን መመረጥና ጸጋን የተሞላች ቡርክት መሆንዋን ሳያወሳ ፤ የመንፈስ ቅዱስን ድንቅ ሥራ ሳይናገር ፤ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ሳይመሰክር ስብከት ሊሰብክ የሚቻለው ማን ነው? ይህን ካላደረገም

ገብርኤልን የላከ አምላክ ያልላከው ሰባኪ ይሆናል፡፡ 'እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና' ዮሐ. ፫፥፴፬

ቅዱስ ገብርኤል ለሰባክያነ ወንጌል የስብከትን ቅርፅ ብቻ ሳይሆን ሰባክያነ ወንጌል ምን ዓይነት ማንነት ሊኖራቸው እንደሚገባም አሳይቶአል፡፡ ስለ ራሱ 'እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ' ብሎ የተናገረው የእግዚአብሔርን የምሥራችን ቃል የሚሰብኩ ሁሉ በሰው ፊት ከመቆማቸው በፊት እግዚአብሔር ፊት በትጋት መቆም እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ እግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ሳይቆሙ ሰው ፊት የቆሙ ሰባክያን የሚናገሩት ቃል እንደ ገብርኤል ግዳጅ አይፈጽምም፡፡

መልአኩ ለድንግሊቱ በሰበከው ወንጌል ሰባክያን የእግዚአብሔርን መልእክት የሚነግሩትንም ሰው በብሩህ ገጽ በፍቅር መንገር እንዳለባቸው ፤ ለማወቅ ፈልገው በትሕትና ለሚጠይቋቸው ሰዎች አብራርተው መልስ መሥጠት እንደሚገባቸው ፤ ባለማመንና በጥርጣሬ ለሚጠይቁ ደግሞ በተግሣፅ አፋቸውን መዝጋት እንደሚገባ የመምህራነ ወንጌልን ሥርዓት አበጅቶ ሔዶአል፡፡ 'መልአኩም ከእርስዋ ሔደ' የሚለው ቃል ደግሞ ሰባኬ ወንጌል የእግዚአብሔርን ቃል ነግሮ ሕዝቡን ይሁንልኝ እሜን ካሰኘ በኋላ ምእመናንን አትርሱኝ ብሎ ሳያስጨንቅ የተሰበኩትን

እንዲፈጽሙ ለፈጣሪያቸው ትቶ ዘወር ማለት እንዳለበት የሚያስረዳ ነው፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ለድንግሊቱ 'ደስ ይበልሽ' አላት፡፡ 'የእግዚአብሔር አገልጋይ የንጉሡን እናት አያት ፤ ተሳለማትም። ሰላም የተጻፈበትን ደብዳቤ አውጥቶ አነበበላት። የሰው ልጅ የምሕረት አዋጅ ለድንግሊቱ ተነበበላት ፤ [የሲኦል] እስረኞች መፈታት ዜናም ለእርስዋ ታወጀ'[140] ይህ የደስታ መልእክት በእርስዋ ፊት ይቅረብ እንጂ የሚመለከተው የሰው ልጆችን ሁሉ ነው፡፡ መልአኩ 'ምስር ብላ' ሊባል የማይችል እሳታዊ ሆነ እንጂ የምሥራቹስ 'በአምላክህ' የሚያሰኝ የምሥራች ነው፡፡ ይህ የምሥራች 'ሰው ሆይ ፈጽመህ ደስ ይበልህ ፤ እግዚአብሔር ዓለሙን ወድዶታልና አንድ ልጁንም የሚያምንበት ሁሉ እስከ ዘለዓለም ፈጽሞ ይድን ዘንድ አሳልፎ ሠጥቶአልና'[141] የተባለለት የምሥራች ነው፡፡ የሰው ልጆች መመኪያ ድንግል ማርያም የሰው ልጅን ወክላ የሰማችው ይህን ደስታ ነበረ፡፡

'ደናግል ሁሉ ደስ ይበላቸው ፤ ከእነርሱ አንዲቱ ፍጥረቱን ሁሉ የሚሸከመውንና ከባርነት ነጻ የሚያወጣውን ኃያል ወልዳለችና። በእባብ የተነደፈው

[140] St. Jacob of Serug, Homilies on the Nativity165 Gorgias Press, pg. 30
[141] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰኑይ ፮ ፤

አዳም ዛሬ ደስ ይበለው ፤ የመድኃኒትን ቀበል ሠጥታዋለችና። ሊቃነ ካህናት ሁሉ ደስ ይበላቸው በግን ከመሠዋት ያሳረፋቸውን ሊቀ ካህናት ሠጥታቸዋለችና'[142]

እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም ደስ ይበልሽ የሚለው ጥሪ ለሁሉ የሚሆን ነው፡፡

ስለዚህ የምሥራች ዜና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ 'ከቀደመው ዜና የተለየ ዜና ለሴት ልጅ ተነገረ። በቀድሞው ኃጢአት ምክንያት በምጥ የመውለድ ዜና ተነግሮ ነበረ ፤ የአሁኑ ዜና ግን በደስታ ኀዘንን የሚያስወግድ ነው' ብሏል፡፡[143]

መጽሐፈ ባሕርይም ፡-

'ዛቲ፡ ይእቲ፡ እንተ፡ እስሰለት፡ ኀዘነ፡ እምትዝምደ፡ ለብእ፡ አንስት፡፡ በከመ፡ ይቤላ፡ እግዚአብሔር፡ ለሔዋን፡ አበዝኆ፡ ለኀዘንኪ፡ ወበኀዘን፡ ትወልዲዮሙ፡ ለውሉድኪ፡፡ ወይቤላ፡ ለዛቲ፡ ተፈሥሒ፡ ኦ፡ ምልእተ፡ ጸጋ፡፡እንታክቲ፡ ተመልዓት፡ እምክረ፡ ክደሲ፡፡ወኮና፡ ኀዘነ፡ ለአዝማዲሃ፡ እምድኅሬሃ፡፡ወዛቲሰ፡ ተመልዓት፡ እምጸጋ፡ እምላክ፡ ወኮና፡ ፍስሐ፡ ወለአዝማዲሃ፡ እምድኅሬሃ፡እስ፡ተወልዱ፡በመንፈስ፡በልደት፡ዳግማዊ' ከሴቶች ወገን ኀዘንን ያስወገደች እርስዋ ነች።

[142] Sr. Ephrem the Syrian, Hymns on Mary 1.6-8,
[143] St. Gregory of Nyssa, Oration on Christ

እግዚአብሔር ለሔዋን ኀዘንሽን አበዛለሁ ፤ ልጆችሽንም በኀዘን ትወልጃቸዋለች ባላት መጠን ይህችኛዋን ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ አላት። ያቺኛዋ በእባብ ምክር ተሞላች ፤ ለእርስዋም ለዘመዶችዋም ኀዘን ሆነባቸው ፤ ይህችኛዋ በእምላክ ጸጋ ተሞላች ለእርሷና ከእርስዋም በኋላ በዳግማዊ ልደት በመንፈስ ለተወለዱ ዘመዶችዋ ደስታ ሆነላት'[144]

ደስ ይበልሽ የሚለው ቃል በድንግሊቱ ጆሮ የፈሰሰው ለሴት ልጅ ሁሉ ነው:: ኀዘንተኛይቱ ሔዋን በማርያም ጆሮ 'ደስ ይበልሽ' የሚል ቃልን ሰማች::

'ደስ ይበልሽ' የሚለው ምስጋና በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ከተማ ለሆነችው ለጽዮንና ለልጆችዋ የሚቀርብ ምስጋና ነበረ:: ነቢዩ ኢሳይያስ 'አንቺ በጽዮን የምትኖሪ ሆይ የእስራኤል ቅዱስ በመካከልሽ ከፍ ከፍ ብሏልና ደስ ይበልሽ' ሲል ነቢዩ ዘካርያስ ደግሞ 'አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ' ብሏል:: ነቢዩ ሶፎንያስም በዚሁ የዝማሬ ስልት 'እስራኤል ሆይ እልል በዪ ፤ የጽዮን ልጅ ሆይ ዘምሪ ፤

[144] መጽሐፈ ባሕርይ ፤ አንቀጽ ፪፡፳፩-፳፯ ፤ ፀሐይ አሳታሚ 2009 ዓ.ም.

የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ በፍጹም ልብሽ ሐሴት አድርጊ ደስም ይበልሽ' ብሎ ነበር:: ኢሳ. ፲፪፥፮ ፤ ዘካ. ፱፥፱ ፤ ሶፎ. ፫፥፲፬

ነቢያቱ ለእግዚአብሔር ሀገር ለእስራኤልና ክርስቶስም 'የታላቁ ንጉሥ ከተማ' ብሎ ለጠራት ለጽዮን ኢየሩሳሌም 'ደስ ይበልሽ' ብለው ነበር:: ማቴ. ፭፥፴፭ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ይህን ለሀገር የቀረበ የምስጋና ቃል የእግዚአብሔር ሀገሩ ለመሆን ለተመረጠችው ፥ ማሕፀንዋን ከተማ አድርጎ ሊያድርባት ለተመረጠችው ለእውነተኛዋ ጽዮን ለድንግል ማርያም ደገመው:: ወደ ነቢያት ቅዱስ መንፈሱን የላከው እግዚአብሔር የላከውና ከላይ ወደታች እንደሚፈስ ወንዝ ከአርያም ወደ ምድር የወረደው ገብርኤል ድንግሊቱን 'ደስ ይበልሽ' ብሎ እንደ ከተማ እያነጋገረ 'የወንዝ ፈሳሾች የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛሉ ፤ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ' የሚለው ትንቢትም ስለ እርስዋ የተነገረ መሆኑን አስረዳን:: መዝ. ፵፮፥፬

ቅዱስ ገብርኤል ደስ ይበልሽ የማለቱን ምክንያት በእርስዋ የተከናወነውን ነገር ሁሉ እያሰብን የምናብራራው ነው:: ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ መባል ከፍጥረታት ሁሉ ይልቅ ለአንቺ ይገባል:: በቍስሉ የሚፈውሰውን መድኃኒት ልትወልጂ ነውና ደስ ይበልሽ:: በጨለማ ለሚሔዱ ሁሉ የሚያበራው ብርሃንን ልትወልጂ ነውና ደስ ይበልሽ::

በሞት ፍርድ ለተያዙ ሁሉ ሕይወትን ልትወልጂ ነውና ደስ ይበልሽ::

ቅዱሳን አባቶቻችን ደስ ይበልሽ የሚለውን ቃል ጥልቀትና እምቅነት ከሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ጋር በማገናዘብ አብራርተውታል:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተፈሥሒ ፍስሕትን በተረጎመበት ድርሳን እንዲህ ብሏል :-

'እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ በአንቺ ሰው የሆነ ሙሽራ ከጫጉላው እንደሚወጣ ከአንቺ የወጣ እመቤታችን ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። መዝ. ፲፱፥ ፮ የጠፋ በግ አዳምን የፈለገውን ባገኘውም ጊዜ የተሸከመውን ቸሩን እረኛ የወለድሽልን ሆይ ደስ ይበልሽ። ሉቃ. ፲፰፥፩-፬ እግዚአብሔር በሲኦል የጣላት የሔዋን የሚጎዳ ማሠሪያዋ ባንቺ የተቈረጠላት እመቤታችን ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። ዘፍ. ፫፥፲፭ ፤ እግዚአብሔር በብሩህ ደመና ተጭኖ መጥቶ በማሕፀንሽ ያደረ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። መዝ. ፻፴፥፫ ፤ ኢሳ. ፲፱፥፩ በትዱሳኑ ላይ አድሮ የሚኖር ካንቺ ሰው ሆኖ የተገለጠልን እመቤታችን ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። ኢሳ. ፮፥፩ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምንሰግድለት ቃል ከአንቺ ይወለድ ዘንድ የወደደ እመቤታችን ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ።

እኔ ለምእመናን ወንጌልን የማስተምርለት የጌታዬ እናቴ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። ከወለድሽው በኋላ ማኅተመ ድንግልናሽ እንዳይለወጥ አድርጎ የጠበተሽን አማኑኤልን የወለድሽው እመቤታችን ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። ልዩ መድኃኒታችንን በመውለድሽ እናትም እገልጋይም ተብለሻልና። እግዚአብሔር ባሕርይሽን ባሕርዩ አድርጎ ባለሟልነትን አግኝተሻልና እመቤታችን ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። እኛ ከምንወድደው እርሱም ከሚወደን ልጅሽ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ለምኚልን'[145]

## • ጸጋን የተመላሽ ሆይ

መልአኩ ከደስታ ብሥራት ቃሉ ጋር ድንግሊቱን 'ጸጋን የተሞላሽ ሆይ' አላት፡፡ በቀጥታ በስምዋ ከመጥራትም ይልቅ ድንግሊቱን ለመጥራት ያስቀደመው የመጀመሪያ ስምዋ 'ጸጋን የተሞላሽ ሆይ' 'ምልዕተ፡ ጸጋ' የሚል ነበረ፡፡ ይህም ማንነትዋንና ክብርዋን በማየት በትውልድ ሁሉ ከሚወጡላት ከአምላክ እናት ብዙ ስሞች መካከል በመልአክ የተነገረላት የመጀመሪያ ስም ነበር፡፡

[145] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፡ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፡ ፳፰፡፴፰-፴፱ ፡ መጋቤ ሐዲስ ፍቅረ ማርያም ባዘዘው

ጸጋን ስለመሞላት የምናገኘው ሌላ ሐዲስ ኪዳናዊ ቃል የመጀመሪያው 'ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ' ተብሎ ስለ ቃል ሥጋ መሆን የተነገረው ነው:: ክርስቶስ ጸጋን ተሞልቶ ማለት የመለኮታዊ ባሕርይ ክብሩን ከእኛ ለነሣው ሥጋ ጸጋ አድርጎ ሠጠ ከሥጋችን ጋር ተዋሐደ ማለት ነው::[146] ዮሐ. ፩፥፲፬

ድንግል ማርያም 'ጸጋን የተሞላሽ' የተባለላት ምስጋና ክርስቶስ 'ምሉዓ ጸጋ' ከተባለበት ነገረ ተዋሕዶ ጋር ቃሉ ቢመሳሰልም ምሥጢሩ ጨርሶ የማይገናኝ ሲሆን ለእርስዋ የተነገራት ለፍጡራን የሚሠጥ አምላካዊ ጸጋን የሚመለከት ምስጋና ነው::[147]

ከፍጡራን 'ጸጋን የተሞላ' የሚለው ቃል የተነገረለት ሌላ ሰው ቀዳሚ ሰማዕት ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነበር:: 'እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅትንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር' ስለ ቅዱስ እስጢፋኖስ 'ጸጋን ተሞልቶ' የተባለው በዚያን

[146] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ፤ ዘዮሐንስ ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ 1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገጽ 379

[147] ቃሉ ተመሳሳይ ቢሆንም ትርጉሙ ግን የሚለያይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አለ:: ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ 'እኔ ለዓለም ከተሰቀልሁበት ዓለምም ለእኔ ከተሰቀለበት ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ' ብሏል:: ገላ. ፮፥፲፬ ፤ ቃሉ ተመሳሰለ ብለን ጳውሎስ ለዓለም ተሰቅሏል እንዳንል ደግሞ 'ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን?' ብሎ ራሱ ይመልሰናል:: ፩ቆሮ. ፩፥፲፫ ንባብ ቢያሳብራቸውም ምሥጢር የማያሳብራቸው እንደዚህ ያሉ ብዙ ቃላት በቤተ ክርስቲያን ይዘወተራሉ::

ወቅት የደረሰበትን መንፈሳዊ ደረጃ ለማሳየት ነው፡፡ በጥቅሉ ብቻዋ እስጢፋኖስ መቼ ጸጋ እንደተሞላ ማወቅና በጸጋ ሙላት ምክንያት ምን ምን እንደሠራ ተዘርዝሮ እናገኛለን፡፡ የቅዱስ እስጢፋኖስ የታወቀ የአንድ ወቅት በጸጋ መሞላት ደግሞ ድንግል ማርያም ከተጠራችበት 'ጸጋን የተሞላሽ' ካሰኛት አብሮአት የቆየ ምልዓተ ጸጋ ጋር የሚደራረስ አልነበረም፡፡ ሐዋ. ፮፥፰

'ጸጋን የተሞላሽ' የሚለው ቃል ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ለዚህች ድንግል ገና ጌታን ከመፅነስዋ በፊት የተናገረው መሆኑን አስተውሉ፡፡ ገና 'ጸጋን ትሞዪአለሽ' አላላትም፡፡ መልአኩ ድንግሊቱን ያገኛት ጸጋውን በስስት ሠፍሮ የማይሠጠው እግዚአብሔር ሞልቶ በሚፈስስ ለሌላው በሚተርፍ ጸጋ አስጊጦአት ነበርና 'ጸጋን የተሞላሽ ሆይ' አላት፡፡ ጸጋን የሞላብሽ ሆይ ማለት እግዚአብሔር ሥጦታውን የሞላብሽ ሆይ ማለት ነው፡፡ ድንግሊቱ ጸጋን ያገኘችው 'እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላላችኋል' 'እንደ ክርስቶስ ሥጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ሠጠን' ተብሎ ከተነገረለት አምላክ ነውና 'የሞላብሽ ሆይ' የሚለው ቃል እንደ ሠጪው ባለጠግነት ምንኛ የበዛ እንደሚሆን ያሳያል፡፡ ፊልጵ. ፬፥፲፱ ፤ ኤፌ. ፬፥፯

ስለ እግዚአብሔር የጸጋ ሥጦታ

'የጸጋ ሥጦታ ልዩ ልዩ ነው ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ትዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥትም ይሰጠዋል' ይላል፡፡ ፩ቆሮ. ፲፪፥፬

ድንግል ማርያም በሁሉም ጸጋ ያጌጠች ናት፡፡

'አንዲት ድንግል' የተባለችው ማርያም የመጀመሪያው ጸጋዋ ድንግልናዋ ነው፡፡ ጌታችን ስለ ድንግልና ሲናገር 'ይህ ነገር ለተሠጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም' ብሎአል፡፡ ማቴ. ፲፱፥፲፩

ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ድንግልና ሕይወት ምርጫው በተናገረበት ሥፍራ 'ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወድዳለሁ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር የጸጋ ሥጦታ አለው። አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ' ብሏል፡፡ ፩ቆሮ. ፯፥፯ እመቤታችን በመውለድ ያልፈረሰ ፣ በመፅነስ ያልተገሰሰ ጽንዓ ድንግልና ያላት በዚህም ምክንያት 'ድንግል' የሚለው ቃል ስምዋ እስከመሆን የደረሰ የደናግል መመኪያ ናትና ድንግልናዋ የተጠራችበት ጸጋዋ ነው፡፡

'ልጆች የእግዚአብሔር ሥጦታዎች ናቸው' እንዲል መውለድም ጸጋ ነው፡፡ እርስዋ የእግዚአብሔር ልጅ ልጅዋ የሆነላት የእናትነት ጸጋ አክሊል ናት፡፡ 'ሳታምጥ የወለደችው' ልጅዋን ሲሰቀል እያየች በነፍስዋ

ሰይፍ እያለፈ በኀዘን ምጥ ስትሠቃይ አይቶአት ምጥ ካለ ዘንድ ልጅ አይቀርምና 'እነሆ ልጅሽ' ብሎ ልጅ የሠጣት እንደ ዮሐንስ በጊታ እምነው ለጸኑ ሁሉ እናት ትባል ዘንድ ያላት የዓለም ሁሉ እናት ናት፡፡ መናፍስትን መለየት ቢባል 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?' ብላ መልአከ የምትመረምር ፤ በጥበብ መናገር ቢባል ቃልዋ የጣፈጠ ፤ ሌላው ቀርቶ ቅዳሴያችን

'ተውህቦ ምሕረት ለሚካኤል ወብሥራት ለገብርኤል
ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል' 'ለሚካኤል
ምሕረትን ፤ ለገብርኤል ብሥራትን ፤ የሰማይን ሀብት
ሁሉ ደግሞ ለድንግል ማርያም ሠጣት'

እንደሚል በፊትዋ ከቆመው ቅዱስ ገብርኤልና ከመላእክት ሠራዊት ሳይቀር ይልቅ በጸጋ የምትልቅ ናት፡፡ 'ከሱራፌልና ከኪሩቤል ግርማ የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ። በእውነቱ የባሕርያችን መመኪያ ነሽ' እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም፡፡

መልአኩ 'አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ'[148] አላት፡፡ ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከው ይህ መልአከ

[148] አንዳንድ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትጂዎች 'ከሴቶች መካከል' የሚል ትርጉም ጽፈው ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ለአማርኛው ትርጉም ምንጭ ቋንቋ (Source language) የሆነው ግእዝ ግን 'ቡርክት አንቲ እምአንስት' ይላል እንጂ 'ቡርክት አንቲ እማእከለ አንስት' አይልምና

ድንግሊቱ ተለይታ ስለመባረከዋ ሲናገር እርስዋን ከድንግልናዋ ይልቅ ጾታዋን ማስቀደምን ለምን መረጠ?

ሊቁ ጠርጠሉስ ይህን አስተውሎ ይጠይቃል :-

'ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ተላከ ፤ የተባረከች መሆንዋን ከተናገረ በኋላ 'ከሴቶች' አላት እንጂ 'ከደናግል' አላላትም። መልአኩ ድንግል ብትሆንም ሴት ተብላ እንደምትጠራም አውቋል' ይላል።

ቅዱስ ገብርኤል ድንግሊቱን 'ከሴቶች' ጋር የቆጠራት ከሰባው ሊቃናት አንዱ እንደነበረው እንደ አረጋዊው ስምዖን ድንግል ሆና መፅነስዋን ሳያውቅ ቀርቶ አልነበረም:: ቅዱስ ጳውሎስም 'ከሴት የተወለደ ልጁ' ብሎ በተናገረ ጊዜ 'ሴት' ብሎ ጠርቶአታል:: ልጅዋ ክርስቶስም በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤትና በቀራንዮ እናቱ ከማለት ይልቅ 'አንቺ ሴት' ማለትን መርጦአል:: ሊቁ ጠርጠሉስ 'ጳውሎስም

---

በቁጥር ውሱን ከሆኑ ሴቶች ከሚመስለው 'መካከል' የሚለው ትርጉም ይልቅ 'ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ' የሚለው በጠቅላላ ከሔዋናች ሁሉ የተለየች ወኪላቸው መሆንዋን የሚያሳየው ትርጉም የተሻለ ነው:: በ፳፻ ዓ.ም. በታተመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ በዚህ መልኩ ተስተካክሏል:: ይህን ትንሽ የሚመስል የትርጉም ስኅተት ሳላስተውል በጉባኤ ቆሜ ባነበብኩበት ወቅት ሰምተውኝ በኋላ ቃለ እግዚአብሔርን ስንጨዋወት የነገሩኝ በዚህች መጽሐፍ ስማቸውን ጽፌ ልዘክራቸውና በረከታቸውን ልሳተፍ የፈለግሁት ለቀናት እውቀአቸው በጥልቅ ፍቅራቸውና በንስር ዓይን በሚያይ ወርቃማ ሊቅነታቸው ከልቦናዬ የተጻፉት የአለላው መጋቢ ምሥጢር አለቃ መሠረት ተሰማ (1928-2013) ነበሩ::

ገብርኤልም 'ሴት' ብለው የጠሯት እስተድሞ ሔዋን በተጠራችበት መንገድ ነው' ይላል፡፡[149]

በእርግጥም ቅድስት ማርያም ከተለመደው ውጪ ሳትወልድ በፊት ሴት ፤ ከወለደች በኋላም ድንግል ተብላ የምትጠራ የተለየች ናት፡፡ ሴት በሚለው መጥሪያ ልጅዋም መላእክቱም ሐዋርያቱም የጠሯት ግን ሌላ ጥልቅ መልእክት ስላለው ነው፡፡ እርስዋ እግዚአብሔር 'በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ' ካለ በኋላ 'እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል ፤ አንተ ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ' በማለት በትንቢት የተናገረላት ሴት ድንግል ማርያም መሆንዋንና ዘርዋ የተባለውም 'አሕዛብን በብረት በትር የሚገዛው' ፤ 'የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል' የተባለለት ክርስቶስ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ ዘፍ. ፫፥፲፭ ፤ ሮሜ ፲፮፥፳ ፤ ራእ. ፲፪፥፭

ገብርኤል ድንግሊቱን 'ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ' ሲል ከወንዶችና በአጠቃላይ ከፍጥረታም ሁሉ ይልቅ በቅድስናዋ የምትበልጥ መሆኑን ስቶት አይደለም፡፡ ቀጥሎ የሚነግራት ዜና 'ትፀንሻለሽ' የሚል ነውና መፅነስና መውለድን በተመለከተ ከወንዶች ጋር ልትነፃፀር

[149] Tertullian, De Virginibus velandis 6, I Pl 2, 945-46

አትችልም፡፡ በዚያ ላይ ይህ ምስጋና 'ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' ብሎ በኤልሳቤጥ ቤት የሚቀጥል ነውና ድንግሊቱን በማሕፀንዋ ፍሬ ከወንዶች ትበልጣለች ብሎ ማነፃፀር የሚሆን አይደለም፡፡

'ከሴቶች ይልቅ የተባረከች' የሚለው ምስጋና ከድንግሊቱ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ለሌላ ሴቶች የቀረበ ይመስላል፡፡ አንደኛይቱ 'ከሴቶች ይልቅ የተባረከች ትሁን፤ በድንኳን ውስጥ ከሚኖሩ ሴቶች ይልቅ የተባረከች ትሁን' ብለው ዲቦራና ባርቅ የተቀኙላት ኢያዔል የተባለች ሴት ስትሆን ሁለተኛዋ በጠቢቡ ሰሎሞን መጽሐፍ 'መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ ፤ አንቺ ግን ከእነርሱ ትበልጫለሽ' ተብሎ የተጻፈላት ሴት ናት፡፡ መሳ. ፭፥፳፬ ፤ ምሳ. ፴፩፥፳፱

ኢያዔልን 'የተባረከች' ያሰኛት የእስራኤልን ልጆች ሃያ ዓመት ሙሉ ያስጨነቃቸውን ሲሣራ የተባለ ሰው በተኛበት አግኝታው መዶሻ አምጥታ የድንኳን ካስማ በጆሮ ግንዱ አስገብታ ስለገደለችው ነበር፡፡ መሳ. ፬፥፳፩ ይህ ሰው ለገደለች ሴት የቀረበ ምስጋና ለንጽሕት ድንግል ከቀረበው ምስጋና ጋር ሊደራረስ አይችልም፡፡ ያመሰገኗት ምስጋናም 'በድንኳን ከሚኖሩ ሴቶች' በመለየትዋ ብቻ ነበር፡፡ በዚያ ላይ ዲቦራና ባርቅ ኢያዔልን 'የተባረክሽ ሁኚ' አሏት እንጂ የተባረክሽ ነሽ አላሏትም፡

፡ የተባረከች የምትሆነውም የተመረቀችው ምርቃት ከሠራላት ነው፡፡ ገብርኤል ግን ድንግል ማርያምን 'የተባረክሽ ነሽ' አላት እንጂ 'የተባረክሽ ሁኚ' አላላትም ፤ ተባርካ አገኛት እንጂ መልአኩ አልባረካትም፡፡ 'የተባረክሽ ነሽ' ማለቱ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የምታድይ አንቺ ነሽ ሲል ነበር፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን 'ከሁሉ ትበልጫለሽ' ያላት ሴትም እንዲሁ ከድንግል ምስጋና በታች ናት፡፡ የተመሰገነችው ሴት ትዳርዋን በአግባቡ የምትመራ ፤ ቤተሰብዋን በሚገባ የምታስተዳድር ፤ ንግድ የሚሳካላት ባተሌ ሴት ስትሆን በዚህ ማንነትዋ 'ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል፦ መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፤ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ' ነው የሚለው፡፡ ለባል ሚስቱ ከብዙ ሴቶች ትበልጣለች ፤ የሚያገባትም ይህን አምና ነው፡፡ ይህ አንድ ባል ሚስቱን ለማመስገን የተናገረው ምስጋና ቃል ለአብ ሙሽራ ለድንግል ማርያም ከቀረበው ምስጋና እጅግ ያነሰ ነው፡፡

ለመልአኩ የከበረ ሰላምታና ምስጋና የድንግሊቱ ምላሽ በጥበብ የተሞላ ነበር፡፡ 'እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ የተነሣ በጣም ደነገጠች ፤ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ብላም አሰበች'

'ርግብዋ ንስሩን አየችው ፤ በፊትዋ ባበራ ጊዜ ማን እንደላከው አላወቀችምና ደነገጠች'[150]

መጽሐፍ 'ወዳጆች ሆይ፣ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ' ይላል። ፩ዮሐ. ፬፥፩ ብዙዎች ማንኛውንም ዓይነት የመንፈስ መገለጥ ያለ ምንም ምርመራ አምነው ይቀበላሉ። በዚህም ብዙዎች ወድቀዋል። ከእድሜዋ በሚበልጥ መረጋጋትና ጥበብ ውስጥ ያለችው ድንግል ግን የተላከላት መልእክተኛ ከእግዚአብሔር ሆኖ እንደሆነ መረመረች።

ምስጋና ነው ብላ ልብዋን ከፍታ ከመስማት ይልቅ ከምስጋናው በስተጀርባ ምን ይኖር ይሆን? የሚለውን አሰበች። ልጅዋ በአንድ ሰው እንደበት 'ቸር መምህር ሆይ' ተብሎ ሲጠራ 'ስለምን ቸር ትለኛለህ?' ብሎ እንደጠየቀ አሳብዋ እንደልጅዋ አሳብ የሆነላት ይህች ቅድስትም ተመሰገንኩ ብላ ሳትቀበል ምስጋናውን መረመረች። የቂሣርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት እንዲህ ይላል :-

'ከማን እንደተላከ ሳታውቅ ሥጦታን የማትቀበለው
ድንግል ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? አለች።
ከዚህ ሥጦታ በስተጀርባ ምን አለ? ከሰማይ

[150] St. Jacob of Serug, Homily on the Nativity 170

መጥተሃል ግን በምድር እየሔድህ ነው። ስትታይ
እንደ ሰው ትመስላለህ ፤ በብርሃን ግን ተከበሃል'[151]

በዜና አበው እንደምናነበው በርካታ ቅዱሳን በተሳሳቱ መገለጦችና ራእዮች ተሰናክለው ወድቀዋል፡፡ ይህን የሚያውቀው ዲያብሎስ 'የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን' እየለወጠ በመገለጥና የሐሰት መልእክትንና የማይገባቸውን ውዳሴ በማቅረብ ለዓመታት በመንፈሳዊ ተጋድሎ የኖሩ ቅዱሳንን ሳይቀር ከመንፈሳዊ መንገድ አስወጥቷቸዋል፡፡ በመልአክ መገለጥ ተደስተው ያለ ምንም ጥያቄ ያመኑትን ሰዎች ራሳቸውን እስከማጥፋት ድረስ ያሳታቸው የሚቀርብላቸውን ሰላምታ 'ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?' ብለው እንደ ድንግሊቱ መመርመር ባለመቻላቸው ነው፡፡

ድንግል ማርያም ግን የቀረበላትን ምስጋና ሰምታ ከመቀበል ይልቅ 'እንዲህ ያለውን የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን እቀበለዋለሁ?' ብላ ፈራች፡፡ ለቅዱሳን ሰዎች ከመሰደብ ይልቅ መመስገን ያስፈራቸዋልና ድንግሊቱ በምስጋናው ደስ ከመሰኘት ይልቅ ለመቀበል ፈራች፡፡ ይህን ያየው መልአኩ 'ማርያም ሆይ አትፍሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አግኝተሻልና' አላት፡፡ የመልአኩ ምስጋና ሲደንቅሽ

[151] St. Gregory the wonder worker, Bishop of the New Caeserea (215-270)

እኔንም እንቺንም በፈጠረ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻል ሲል አረጋጋት፡፡

ገብርኤል አትፍሪ አላት ፤ ድንግል ሆይ አትፍሪ፡፡ 'አትፍሩ እኔ ነኝ' የሚለውን ጌታ ፤ ፍርሃት ራሱ የሚፈራውን አምላክ ልትወልጂ ነውና አትፍሪ፡፡ 'እኔ እናትሽን [ሔዋንን] በኤደን ገነት እንዳሳተው እባብ አይደለሁም። እኔ የመጣሁት በገነት እንደሆነው ክብርሽን ልገፍፍ አይደለም። ዕርቃናቸውን የወደቁ ወላጆችሽን የምታለብሺበትን ልብስ ይዤ መጥቻለሁ'[152] ሲል አረጋጋት፡፡

ሞገስን ማግኘት ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ተሰሚነትን ባለሟልነትን ፤ ክብርን ማግኘት ማለት ነው፡፡ አብርሃም ለእግዚአብሔር 'በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ' ብሎ በቤቱ ተቀብሎታል፡፡ ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ሳለ 'ጌታው ፊት ሞገስን አገኘ፤ እርሱንም ያገለግለው ነበር በቤቱም ላይ ሾመው፤ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው' ይላል፡፡ እግዚአብሔርም ለሙሴ 'በፊቴ ሞገስ ስላገኘህ በስምህም ስላወቅሁህ ይህን ያልኸውን ነገር አደርጋለሁ' ብሎታል፡፡ ዘጸ. ፴፫፥፲፯ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ሞገስን ማግኘት ማለት ለሹመት ለክብር መታጨት ፤ ተናግሮ ተሰሚነትን ፤ ጠይቆ ተቀባይነትን ማግኘት

152 St. Jacob of Serugh, Homily on the Nativity, 275, Gorgias Press, pg 42

ሲሆን ድንግል ማርያም 'በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻል' መባልዋ ስምዋ በእግዚአብሔር ዘንድ የሠለጠነ ፤ ልመናዋ ተሰሚነት ያለው ፤ ክብርና መደመጥን ያገኘች መሆንዋን የሚያሳይ ነው፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ለድንግሊቱ :-

'እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ፤ እርሱም ታላቅ ነው ፤ የልዑል ልጅ ይባላል። ጌታ አምላክም የዳዊት የአባቱን ዙፋን ይሠጠዋል። በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘለዓለሙ ይነግሣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም' ብሎ የተመረጠችበትን ታላቅ ክብር ነገራት፡፡

ቅዱስ ገብርኤል ለድንግሊቱ ከክርስቶስ ብዙ ስሞች አንዱ የሆነውን 'ኢየሱስ' የሚል ስም ነገራት፡፡ ይህ ስም መድኃኒት ማለት ሲሆን አስቀድሞ የነዌ ልጅ ኢያሱ የተጠራበት ስም ነበር፡፡ 'እክሊለ፡ስምከ እንዘ፡ ይትቄጸል፡ በርእርሱ ፲ እህጉረ፡ ጸር፡ ወረሰ፡ ኢያሱ' 'የስምህን ዘውድ በራሱ ላይ ጭኖ የጠላትን ሀገር ኢያሱ ወረሰ' እንዲል፡፡ የስሙን መድኃኒትነት ቅዱስ ገብርኤል ለእረኞች ባበሠረ ጊዜ 'ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና' ብሎ ተርጉሞታል፡፡ ሉቃ. ፪፥፲፩

ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ሲያጸና :-

'ከዳዊት ዘር እግዚአብሔር እንደ ተሰፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ' ሐዋ. ፲፫፥፳፫

'እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፤ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን' ብሏል፡፡ ፊልጵ. ፫፥፳

መልአኩ 'ኢየሱስ ትይዋለሽ' ይበል እንጂ የምትወልደው ሕፃን አንድ ስም የማይበቃው ፤ ስም ሁሉ የማይገልጸው ወንድ ልጅ ነበር፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ 'እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች' ሲል በሌላ ሥፍራም 'ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሠጥቶናል' ካለ በኋላ 'ስሙም ድንቅ ፤ መካር ፤ ኃያል አምላክ ፤ የዘላለም አባት ተብሎ ይጠራል' ብሎ የሕፃኑን ስም መብዛት ይገልፃል፡፡ ኢሳ. ፯፥፲፬፤ ፱፥፯

እናቶቻችን በየዋህነት እውቀታቸው 'አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው' ብለው የሚዘምሩለት ይህ ጌታ ስሙ እጅግ ብዙ ነው፡፡ ኢየሱስ ፤ ክርስቶስ ፤ መድኃኔ ዓለም ፤ ወልድ ፤ ቃል ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ፤ የሰው ልጅ ፤ የእግዚአብሔር ጥበብ ፤ ብርሃን ፤ ልዑል ፤ የዳዊት ልጅ ፤ የአብርሃም ልጅ ፤ መምህር ፤ የአይሁድ ንጉሥ ፤ የጽድቅ ፀሐይ ፤ የይሁዳ አንበሳ ፤ ኋለኛው አዳም ፤ የማዕዘን ድንጋይ ፤ የፋሲካ በግ ፤

ሊቀ ካህናት ፤ የመዳን ቀንድ ፤ ፊተኛውና ኋለኛው ፤ መጀመሪያውና መጨረሻው ፤ ያለና የነበረው ለእርሱ የሚበቃ አንዳች ስም የሌለው እርሱን ትወልጃለሽ አላት፡፡

## • መልስ አልባ ጥያቄ

ድንግል ማርያም መልአኩ የነገራትን እንደሰማች እጅግ ወሳኝ የሆነና ከጥያቄነት ያለፈ ብዙ ትርጉም ያለው አስደናቂ ጥያቄን ጠየቀች፡፡ 'ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?' ይህ ጥያቄ ደጋግመን ስናነብበው ተራ ይመስለናል እንጂ ማንኛውም ሰው ጨርሶ ሊጠይቀው የማይችለው አስገራሚ ጥያቄ ነው፡፡

ማንኛዋም ሴት 'ትፀንሻለሽ ፤ ትወልጃለሽ' የሚል መልእክት ብትሰማ 'የምፀንሰው ከማን ነው?' ብላ ትጠይቅ ይሆናል እንጂ በምንም ተአምር 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' አትልም፡፡ እንደ ማርያም ለወንድ የታጨች ድንግል ከሆነች ደግሞ ከታጨችለት ወንድ እንደምትፀንስ ምንም ጥርጥር ስለማይኖራት ጨርሶ ይህን ጥያቄ አታነሣም፡፡ ትፀንሻለሽ ከተባለች ድንግል ሴትም ብትሆን ከዚያ በኋላ ከወንድ ጋር በሚፈጸም ሩካቤ እንጂ ሌላ በምንም መንገድ ልትፀንስ እንደማትችል በማንኛዋም ሴት ዘንድ የታመነ ነው፡፡

ድንግል ማርያም ግን 'ትፀንሻለሽ ትወልጂያለሽ' ስትባል 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ብላ ጠየቀች:: ልብ በሉ መልአኩ ቀድሞ 'እነሆ ያለ ወንድ ዘር ትፀንሻለሽ' ብሎአት 'እንዴት ያለወንድ ልፀንሰ እችላለሁ' ብላ የጠየቀች አይደለም:: መልአኩ ስለ ፅንሱ ተአምራታዊነት ምንም ፍንጭ አልሠጠም:: ያለ ወንድ የመፅነስን ጉዳይ የሚያናግር ከመልሱ በላይ የሚያስደንቅ ጥያቄ ቀድማ ያነሣችውና 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆንልኛል?' ያለችው ድንግሊቱ ነበረች::

ድንግል ሆይ የትኛዋ ሴት ያለ ወንድ ፀንሳ ታውቃለች? ወንድ ሳያውቁ መፅነስ እንደምን ያለ ነው? ይህን ዓይነቱን ፅንስ እንኳንስ ሳይፈጸም ቀድሞ ለመጠየቅ ከተፈጸመም በኋላ ለማሰብ የሚከብድ ነው:: አባ ሕርያቆስ እንዳለው :- 'እንደ ንብ[153] ያለ ሩካቤ ከቃል ድምፅ

[153] ቅዳሴው ያለ ወንድ ዘር ለመውለድ ንብን ምሳሌ አድርጎ ያነሣል:: ይህንን የሚደግፍ እውነታ በንቦች ዓለም ውስጥ አለ:: የመጀመሪያው ንግሥቲቱ ንብ ከምትጥላቸው ሁለት አይነት እንቁላሎች ውስጥ - የወንድ ዘር ያለባቸው እና የሌለባቸው ይገኛሉ። የወንድ ዘር ያለባቸው እንስት ንብ ሆነው ሲያድጉ ዘሩ የማይደርሳቸው እንቁላሎች ደግሞ ድንጉላ (ተባእታይ) ንቦች ይሆናሉ። በቅርቡ በተገኘ ጥናት ደግሞ በፊንቦስ ተፈጥሯዊ ክልል ውስጥ የሚገኙት የኬፕ ንቦች ግን ከዚህ ለየት ያለ የእርባታ ስርዓትን ፈጥረዋል። በአንዳንድ ቀፎዎች ውስጥ ተባእት ንቦች ቢኖሯቸውም እንስት ሠራተኛ ንቦች ንግሥቲቱ ንብ በምትሞትበት ወቅት ያለወንድ ዘር ወደሴት ንብነት የሚያድጉ እንቁላሎችን የመጣልን ችሎታ አዳብረዋል። ይህ የሚከናወነው ቴሊዩቶኪ በተባለ ስርአት ሲሆን ሁለት የኬፕ ንብ የሴት ልጅ ሕዋሶች (daughter cells) እርስ በእርስ በመዋሃድ ሁለት የክሮሞዞም ስብስቦችን የያዘ ወደንብነት የሚያድግን ነጠላ ሕዋስ በመፍጠር ነው።

የተገኘ ፅንስ ፤ ከድንግልና ጋራ አንድ የሆነ ወተት እንደምን ያለ ነው? ድንግሊቱ ግን ይህን የማይታሰብ ነገር ጠየቀች፡፡

'ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?' የሚለው የድንግል ማርያም ንግግር ድንግልናዊ ሕይወትዋን ያረጋገጠ ንግግር ነው፡፡ ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ባወቀ ለዮሴፍ እንድትታጭ ለካህናቱ አዝዞ የታጨች ብትሆንም እርስዋ ግን አግብታ ወልዳ የመኖር አሳብ ጨርሶ እንዳልነበራትና ለድንግልና ሕይወት ብፅዓትዋ ለመኖር የወሰነች መሆንዋን ያሳያል፡፡ 'ለወንድ ታጭታ ከወንድ ጋር እያለች ወንድ አላውቅም ማለትዋ እኔ የብፅዓት ልጅ ነኝ መታጨቴም መንፈሳዊ ነው። ብቻ ፀንሶ መውለድ እንዴት ይሆንልኛል? ማለትዋ ነው'[154]

ለድንግልናዊ ሕይወት ካላት ቁርጥ ውሳኔም የተነሣ 'የልዑልን ልጅ ትወልጃለሽ ፤ በያዕቆብም ቤት ለዘላለሙ ይነግሣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም' ተብሎ ሲነገራት እንኳን የሚወለደው ልጅ ማንነት አንጉቶአት የድንግልና ብፅዓትዋን አልተወችም፡፡ 'ወንድ ስለማላውቅ እንደት ይሆናል?' ብላ መልአኩን ጠየቀች፡፡

በየዘመናቱ የድንግል ማርያምን ድንግልና ለማቃለል የሚሞክሩና ብዙ ልጆች አሏት ሊሉ የሚደፍሩ አሳዛኞች ተነሥተዋል፡፡ ነቢዩ

[154] ትንቢተ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው ፵፬፥፩ ፤ 1916 ዓ.ም. ታተመ

ሕዝቅኤል በራእይ አይቶ ፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፤ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል' ብሎ የተናገረላት እግዚአብሔር ገብቶባት ያልተከፈተችው በር ድንግል ማርያም ናት፡፡ ሕዝ.፵፬፥፪

> 'ሕዝቅኤል ሆይ ትናገር ዘንድ ዛሬ የመናገር ዕጣው የአንተ ነው። ስለ ማርያም ተናገርና ስለእርስዋ የሚደረገውን ምርምርንም ግታ ፤ ስለማትመረመረው ድንግ እናት የተናገረውን የነቢዩን ትንቢት ኑ እንስማ'[155]

እርስዋ ቅድመ ዓለም ወልድን ብቻውን የወለደው የአብ ምሳሌ ናትና እርሱ ከወልድ በቀር ልጅ እንደሌለው እርስዋም ሌላ ልጅ የላትም፡፡

> 'የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ናትና ከሥጋው ቃል በቀር ለዕሩት ብእሲ እናት መሆን ፤ በባሕርይዋ ሁለተኛ መውለድ አትችልም። በጳጳስ ወንበር ቄስ ፤ በንጉሥ ወንበር ራስ ደፍሮ ይቀመጣልን? ወይስ ሊቀመጥ ይገባዋልን? እንዲሁም አምላክ ባደረበት ማሕፀን ዕሩት ብእሲ

155 St. Jacob of Serug, On the Perpetual Virginity of Mary, ix

አያድርም። ሠዓሊ ሕገናት በተሣለበት ሰሌዳ በተቀረጸበት ሰፋድል ዘርዐ ብእሲ ቀለም ሆና ሊሣልበት ሊቀረፅበት አይቃጣም አይታሰብም። ዐውደ ማሕፀንዋ አሰተድሞ በትንቢት ታጥሯል በብፅዓት ተቀጥሯል ፤ ተዘግቶ ይኑር አይከፈት ሰው አይግባበት የሚል አዋጅ ተነግሮበታል'[156]

ወዳጄ እስቲ አስተውለን እናስበው:: እውነት ድንግል ማርያም የወለደችው ልጅ ሌላ ልጅ የሚያስመኝ ልጅ ነውን? የእርስዋ ልጅ አዳምና ሔዋን በዝተው ተባዝተው ያልሞሉትን ምድርና ሰማይ በመለኮቱ የሞላ ፤ ምድርን በደሙ ያጠበ ፤ በሥጋው የመገበ ፤ በብርሃኑ ያበራ ሁሉ በእርሱ ፤ ለእርሱ ፤ ከእርሱ የሆነለት ንጉሥ ነው:: ይህ ሁሉን ቻይ ልጅዋ አልበቃት ብሎ ሌላ ልጅን መመኘት በዚህች ድንግል ልብ ውስጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል? ገና ሳትወልድ በፊት እንኳን ድንግልናዋን ለፈጣሪዋ መባ አድርጋ ልታቀርብ ወስና 'ወንድ አላውቅም' ብላ የተናገረች ንጽሕት ለአምላክ ማደሪያነት ከተመረጠች በኋላ ሌላ ሥጋዊ አሳብ ይኖራታል ብሎ ማሰብስ እንዴት ያለ ነው? እግዚአብሔር በተቀመጠበት ዙፋን ላይ ሌላ ፍጡር ተቀምጧል ለማለት መትጋትስ እውነት እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚመጣ ሙግት ነው? ድንግሊቱ

---

[156] ትንቢተ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው ፵፬፥፩ ፤ 1916 ዓ.ም. ታተመ

ሌሎች ልጆች ወልዳለች ለሚሉና ድንግልናዋን ለሚያቃልሉ ሰዎች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ የተቀመጠውን ጥያቄዋን አሁንም ደግማ ትጠይቃቸዋለች :- 'ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?'

መልአክነቱን አይታ ጥያቄን ለመጠየቅ የማትፈራዋ ይህች ድንግል ለቅዱስ ገብርኤል 'ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?' አለችው:: እንደ ሔዋን የነገሯትን ዝም ብላ የምትቀበል ሳትሆን የምትመረምር ናትና አስቀድማ ሰላምታውን አሁን ደሞ መልእክቱን መረመረች::

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ይላል :-

'ሔዋን ወደ ጥፋት ሲወስዳት አባብን አልጠየቀችውም ነበር። በፈቃድዋ ዝም ያለችዋ እርስዋ በተነገራት ተንኮል አመነች። ይህችኛይቱ ድንግል እውነትን ከታማኙ መልአክ ሰማች። ይህ ቢሆንም ማብራሪያን ጠየቀች። ያቺኛይቱ ከዛፍ በልቶ አምላክ መሆን እንደሚቻል ሰምታ 'ይህ ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል?' አላለችም። ይህችኛይቱ ግን መልአኩ የእግዚአብሔርን ልጅ ትፀንሻለሽ አላት። እርስዋ ግን ሳትረዳ አልተቀበለችውም። ዝም ማለት ለድንግል

ማርያም ቀላል ነገር ነበር ፤ እርስዋ ግን መርምራ
በመጠየቅ እውነትን ከመልአኩ አገኘች'[157]

ቅዱስ ገብርኤል ከስድስት ወራት በፊት እንደ ድንግሊቱ ለሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ሊያበሥረው ተልኮ ሔዶ የነበረበትን ቅጽበት እናስታውስ፡፡ ዕድሜውን ሙሉ ከሚስቱ ኤልሳቤጥ ጋር ልጅን ለማግኘት የጸለየው አረጋዊው ዘካርያስ በቤተ መቅደስ እያጠነ እያገለገለ ሳለ ቅዱስ ገብርኤል ታየው፡፡ 'ዘካርያስ ሆይ፡ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች' ብሎም አበሠረው። ዘካርያስም መልአኩን፦ 'እኔ ሽማግሌ ነኝ ምስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ?' ብሎ ጠየቀው። መልአኩም መለሶ፦ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፡ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤ እነሆም፥ በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፡ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው'

ዘካርያስን ዲዳና ደንቆሮ ያደረገው ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም በመጣና ባበሠራት ጊዜ ግን 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ብላ ስትጠይቀው አልተቆጣትም፡፡ ዘካርያስን በተግሣፅ ቃል ፦ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እኮ ነኝ ፤ እንዴት አታምነኝም?

[157] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, 630

ብሎ እንደተቆጣው ድንግሊቱን ምንም አላላትም፡፡ የዕድሜዋን ማነስ አይቶ ለእርስዋ አድልቶ ይሆን? አይደለም፡፡

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ርቱዐ ሃይማኖት ድንግሊቱን እንዲህ ሲል ጥያቄዋን ሳትፈራ እንድትጠይቅ ያነጋግራታል ፡-

'ማርያም ሆይ ወንድ ሳላውቅ እንዴት ይሆናል እያልሽ ተከራከሪው አትፍሪው፡፡ አንቺን እንደ ዘካርያስ ቁጣ አያገኝሽም፡፡ እርሱ ኦሪትን የሚያነብብ ካህን ነውና ተግሣፅ አገኘው፡፡ አብርሃምና ሣራም በሽምግልናቸው ልጅ እንዳገኙ እያወቀ የጽድቅ መልአክን ተከራክሯልና የተግሣፅ ፍርድ በእርሱ ላይ ወረደ፡፡ ዲዳም ሆነ፡፡

ማርያም ሆይ ለአንቺ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለ ሩካቤ ድንግል ሴት እንደወለደች አልተሰማምና፡፡ ያለ ዘር ከሴት ወንድ ልጅ እንደተገኘም አልተሰማም፡፡ የአዳም እባቱ ምድር ነበረች ፤ የሔዋን አባትዋ አዳም ነበረ፡፡ በአንቺ ላይ የተደረገው ግን ሕሊናን ያሸንፋል፡፡ ከእኛ ከመሬታዊያኑ ይቅርና ነገሩ ከመንፈሳውያኑም የተሠወረ ነው፡፡

> ስለዚህ አንቺ ግን እምነሽ ተከራከረ፣ ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆንልኛል? እውነት ከሆነ ነገሩን መልስልኝ ፤ አስገራሚ የሆነ ምሥጢሩንም ተርጉምልኝ ፤ በሚያስደነግጥ ነገር እጅ ነሥተኸኛልና አሳታዊ መልአክ ሆይ አታውከኝ በይው'[158]

የዘካርያስና የድንግሊቱ ጥያቄ የተለያየ ነው:: እርሱ ያለው 'ይህን በምን አውቃለሁ?' ሲሆን እርስዋ ያለችው 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ነው:: ድንግሊቱ የጠየቀችው የተነገራት ነገር እንዴት ሆኖ ሊፈጸም እንደሚችል የቃል ማብራሪያ እንዲሠጣት ሲሆን ዘካርያስ የጠየቀው ግን የተነገረው ነገር እንደሚፈጸም ማስረጃ የሚሆን ምልክት እንዲሠጠው ነው::

ድንግሊቱ የመልአኩን ቃል አምና ስትቀበል ፤ ዘካርያስ ግን የመልአኩ ቃል እንደሚፈጸም 'በምን አውቃለሁ?' ብሎ ሌላ ማስረጃ ጠየቀ:: ዘካርያስ ሲጸልይበት የኖረውን ነገር ይሆናል ሲባል አላመነም ፤ ድንግል ማርያም ግን ያልጠየቀችው ነገር ይሆናል ስትባል አመነች::

---

[158] ርቱዐ ሃይማኖት መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ እንደተረጎሙት 11.4

'መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ' እንዲል ዘካርያስ በአይሁዳዊ ልማድ ከገብርኤል ቃል በላይ ሌላ ማስረጃ ፈለገ፡፡ ፩ቆር. ፩፡ ፳፪ ቅዱስ ገብርኤል እንዳለው 'በጊዜው የሚፈጸመውን ነገር' ለማየት ዘጠኝ ወር መታገሥ አቅቶት ሌላ ምልክት ጠየቀ፡፡ 'ዓይንህ ነገ ጠዋት ይበራልሃል ቢሉት ዛሬን እንዴት ላድር ነው?' አለ እንደሚባለው ብሂል ሚስቱ እስክታረጅ የታገሠው ጻድቅ ሰው ዘጠኝ ወር መታገሥ ግን እኔ ገብርኤል መምጣቴ ብቻ አይበቃህምን? ካልበቃህ ልሳንህንና ጆሮህን ስዘጋው እርሱ ምልክት ይሁንህ፡፡ ልሳን የሚዘጋ ማሕፀንን የሚዘጋው ነው፡፡ ልሳንን የሚከፍትም ማሕፀንን የሚከፍተው ነው አለው፡፡

ፈጣሪን መጠራጠር በማንኛውም ሰው ላይ አያምርም፡፡ መቅደስ ውስጥ ቆሞ በእጁ ጽና ይዞ እያጠነ ባለ ካህን ላይ ሲሆን ግን የበለጠ ያሳፍራል፡፡ ዘካርያስ 'አብርሃም በመቶ ዓመቱ ፣ ሣራ በዘጠና ዓመትዋ ሳሉ ልጅ ወለዱ' እያለ ባስተማረበት አፉ 'እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና በምን አውቃለሁ?' ሲል መስማት ምንኛ ያሳዝናል? ቅዱስ ገብርኤል ግን አዝኖ አልተወውም፡፡ ይህን የጥርጣሬ ንግግር የተናገረበትን አፉን ዘጋው፡፡ እርሱ ፊት የተናገረውን ሌላ ሰው ፊት እንዳይደግመው አንደበቱን ዘጋው ፤ አሪት ሲነበብ ስትሰማ ኖራ ያላስታወሰች ጆሮውንም ሰምታም አልጠቀመችምና ዘጋበት፡፡ ጆሮው

መዘጋቱን ልጁ የተወለደ ቀን ስም እንዲጠቁም ሲጠይቁት 'አባቱንም ማን ሊባል እንዲወድ ጠቀሱት' የሚለው ቃል ያሳያል፡፡ ሉቃ. ፩፡፷፪

'በእርስዋ በበደለባት አካሉ ፍርድም በእርስዋው ሆነ ፤ የዚህም ምክንያቱ ጆሮዎቹና አፉ ስለ አምላካዊት ብሥራት አብረው ተሰናክለዋልና ነው' 'እስመ፡ አባሉ፡ ዘአበሰ፡ ባቲ፡ ወባቲ፡ ኮነ፡ ኰነኔ፡፡ ወምክንያቱሰ፡ ለዝንቱ፡ እስመ፡ እዘኒሁ፡ ወአፉሁ፡ ተአቅፉ፡ ኅቡረ፡ እንበይነ፡ ብሥራት፡ አምላካዊት' እንዲል፡፡

ዘካርያስ አንደበቱ የመዘጋቱ ሌላ ጥቅም ከመቅደስ ሲወጣ ለጠበቁት ሰዎች ያየውን ራእይ እንዳይነግራቸው ስለሚያደርገውም ጭምር ነው፡፡ ቀድሞ ስለ ዮሐንስና እርሱ መንገድ ስለሚጠርግለት ጌታ የሰማውን ቢናገር ወሬው ሔሮድስ ዘንድ ደርሶ መከራው ቀድሞ በመጣ ነበር፡፡ ስለዚህ 'ይህች ምሥጢር እስከ ጊዜዋ ድረስ የተጠበቀች እንድትሆንም' ነው ፤ 'ከመ፡ ትኩን፡ ዛቲ፡ ምሥጢር፡ ዕቅብተ፡ እስከ፡ ጊዜሃ' እንዲል፡፡

የድንግል ማርያም ለቅዱስ ገብርኤል ያቀረበችው ጥያቄ እንደ ዘካርያስ የጥርጥር አልነበረም፡፡ የጥርጥርም እንኳን ቢሆን የተነገራት ነገር ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅ ነገር ነውና ድንግሊቱ እግዚአብሔር ከማይቀየማቸው ተጠራጣሪዎች ትቆጠር ነበር እንጂ አትነቀፍም ነበር፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ 'የጥርጥር ማሕፀንም እውነትን ሊወልድ ይችላል'[159] እንዳለው በመጠራጠራቸው የተጠቀሙ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ አረጋዊው ስምዖን 'ድንግል [በድንግልና] ትፀንሳለች' የሚለውን ትንቢት መጠራጠሩ ዕድሜ አስጨምሮለታል ፤ ቶማስም የጌታን ትንሣኤ መጠራጠሩ ከጌታ ችንካር እጁን ለማስገባት አብቅቶታል፡፡

አባ ጊዮርጊስ እንዲህ አለ ፦

'አረጋዊው ስምዖን 'እነሆ ድንግል ትጸንሳለች' የሚለውን ትንቢት ተጠራጠረ። ይህ ጥርጣሬው ግን በደል ሆኖ አልተቆጠረበትም ይልቁንም ስሙ አማኑኤል የተባለውን ሕፃን ለማቀፍ አበቃው እንጂ። [ወኢተኈለቈ፡ሎቱ፡ኑፋቄሁ፡ኀበ፡ ጌጋይ፡ አላ፡ አብጽሖ፡ ኀበ፡ ሐቀፈ፡ ሕፃን፡ ዘስሙ፡ አማኑኤል] ቶማስም የጌታን ትንሣኤ ተጠራጠረ። ትንሣኤውን መጠራጠሩ ግን የጌታን ጎን ለመዳሰስ በችንካሩ እጁን ለማስገባት አበቃው። [ወአብጽሖ፡ኑፋቄሁ፡ኀበ፡ገሠሠ፡ አጽላእቲሁ፡ ለመድኃኔ፡ ዓለም] በእውነት 'መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው' እግዚአብሔር የወደደው ሰው ቍስሉ አይመረትዝም በደሉም

---

[159] St. Jacob of Serugh, Homlies on the Nativity, Gorgias Press, 2010, pg 50, 340

አይታሰብም' መዝ.፹፯፥፩[160] ድንግል ማርያም ግን ጥያቄዋ የጥርጥር አልነበረም:: የተጠየቀ ጥያቄ ሁሉም ጥርጥር (ኑፋቄ) አይደለም::

በአንድ ወቅት ደግሞ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው በሌሊት ወደ ጌታ መጥቶ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ከጌታ እንደበት ተምሮ ነበር::

ጌታችን ለዚህ የአይሁድ አለቃ :-

እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም' ብሎ ጥምቀት ለዳግም ልደት እንደሚያስፈልግ ነገረው:: ዮሐ. ፫፥፫

ይህን ሰምቶት የማያውቀውን አዲስ ትምህርት የሰማው የአይሁድ መምህር :-

> 'ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው'

ጥያቄው ተገቢ ስለነበረ ጌታችን 'እንዴት ሊወለድ ይችላል?' የሚለውን ኒቆዲሞስ እንዳሰበው ወደ እናት ማሕፀን በመመለስ ሳይሆን

---

[160] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር

ከማሕፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት የሚገኝ ዳግም መወለድ መሆኑን 'እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም' ብሎ ተረጎመለት:: 'ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍሳል' ብሎም በወደደው የሚያድረው መንፈስ ቅዱስን በነፋስ መስሎ አስረዳው::

የጌታችንን ማብራሪያ የሰማው ኒቆዲሞስ ግን የተነገረውን ከመቀበል ይልቅ 'ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?' አለ:: ይህን ጊዜ ክርስቶስ አንተ የአይሁድ መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? ብሎ አለምልሞ ከብሩን ጠብቆ ገሠፀው::

ኒቆዲሞስ ያነሣው የመጀመሪያ ጥያቄ በየዋህነት ነገሩን በሚገባ ለማወቅ ከመፈለግ የመነጨ ጥያቄ ነበረ:: እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ አይጠላም:: ቅዱስ ባስልዮስ አምፊሎኪዮስ ለተባለ ተማሪው በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንዲህ ይላል ፦

> 'ለመማር ያለህ ፍላጎት የማያውቁትን ለማካፈል ዳተኞች የሆኑ ሰዎችን ሳይቀር የሚያነቃቃ ነው። ከአንተ ላይ አብልጬ የማደንቀው ግን ጥያቄዎችህ በዚህ ዘመን እንደምናያቸው ብዙ ሰዎች ሰውን ለመፈተን የተዘጋጁ ጥያቄዎች ሳይሆኑ በቅንነት

እውነትን ለማወቅ ከመጓጓት ብቻ የመነጨ በመሆናቸው ነው'[161]

ኒቆዲሞስም መጀመሪያ ትሑት ጠያቂ ነበረ፡፡ በትሕትና መጠየቅ ጀምረው የሚሰሙት ምላሽ እንዲመለስላቸው እንደሚፈልጉት አልሆን ሲላቸው ትሕትናቸው የሚጠፉ አንዳንድ ሰዎችን ይመስላል፡፡ በመሆኑም ሁለተኛው ጥያቄው ለማወቅ ሳይሆን ለመከራከር ያነሣው እምነት ከማጣት የመጣ ጥያቄ ነበር፡፡

'እንደ ዘካርያስ ሳትጠራጠሪ ፤ እንደ ኒቆዲሞስ ሳትከራከሪ ያመንሽ ብዕዕት ነሽ' የምንላት ድንግል ማርያም ግን 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ያለችው ጥያቄ ትሕትናን የተሞላ ማወቅን ከመሻት የተነሣ ጥያቄ ነው፡፡ ድንግል ማርያም ለገብርኤል ይህን ጥያቄ ባትጠይቅ ኖሮ ምድር ትናወጽ ነበር፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፦

> 'ማርያም በጥያቄዎችዋ የደፋሮችን ጥያቄ ሰባበረች። በጥያቄዋ ተከራካሪዎችን ዝም አሰኘች። መልአኩን አጥብቃ ባትጠይቀው ኖሮ ጌታን ስለ መውለድዋ በዓለም ላይ የሚነሡ ጥያቄዎች በጨመሩ ነበር። እነሆ ትፀንሻለሽ

[161] St. Basil the Great, On The Holy Spirit, chp.1.1 SVS Press, 15

የሚለውን ቃል ዝም ብላ ተቀብላ ቢሆን ብዙ ክርክርና ጥያቄ ዓለምን ባንቀጠቀጠ ነበር'[162]

እመቤታችን ይህን ጥያቄ መጠየቅዋ የብዙ ጥያቄዎችን ማዕበል ጸጥ ያደረገ ሆነ፡፡ ድንግሊቱ በጥያቄዋ ጥያቄን አስቁማ ለቤተ ክርስቲያን ግን ትምህርተ ሥላሴንና ትምህርተ ሥጋዌን በአንድ ላይ አሠጠቻት፡፡

'ቅድስቲቱ ማርያም ለገብርኤል በጠየቀቻቸው ጥያቄዎች የተሠወረውን ምሥጢር ለዓለም አስተማረች። እንዴት ይሆናል? ብላ ባትጠይቅ ኖሮ የወልድን ነገር ሳናውቀው በቀረን ነበር። በዚህ ጥያቄ ጥበበኛይቱ ማርያም የቤተ ክርስቲያን እንደበት ሆነች። የፍጥረታትን ሁሉ ትርጉም ተማረች። እርስዋ ንጽሕና ባይኖራት ኖሮ በመልአኩ ፊት ለመናገር ባልበቃች ነበር። ውስጣዊና ውጪአዊ ቅድስና ባይኖራት ኖሮም ገብርኤል አክብሮ ባልመለሰላት ነበር'[163]

ቅዱስ ገብርኤል የድንግሊቱን ትሕትናና ድንግልና የተሞላ ጥያቄ ምላሽ ቢሠጣትም የጠየቀችውን ጥያቄ ግን በጠየቀችበት ልክ አልመለሰም፡፡ ሊመልሰውም አይችልም፡፡ አምላክ ያለ ወንድ ዘር

---

[162] St. Jacob of Serug, On the Nativity of Our Redeemer, T. Kollamparampil, 57
[163] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, SVS Press, 635

በድንግልና መፀነሱ 'እንዴት ይሆናል?' የሚለውን ጥያቄ ቅዱስ ገብርኤል የመለሰው 'መንፈስ ቅዱስ ይበልልሻል የልዑል ኃይል ያድርብሻል' ብሎ ነበር፡፡ ይህ ግን ድንግሊቱን እንድትፀንስ የሚያስችላት ማን እንደሆነ የሚገልፅ ነው እንጂ እንዴት እንደምትፀንስ የሚያስረዳ አይደለም፡፡ የድንግሊቱ ጥያቄ በፍጡር የሚመለስ አልነበረምና መልአኩ 'መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል' ብሎ እርሱ ይመልስልሽ አላት፡፡ 'መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምራችኋል' ከሚለው ቃል ጋር የሚተያይ ቃል ነው፡፡

ሊቁ ያዕቆብ ዘሥሩግ በገብርኤል አንደበት ሆኖ ይቀኛል :-

'ብሥራቱን እንድነግርሽ በላከኝ ጊዜ አልመረመርሁትም። ያሰማሁሽ ሳልጠይቅ የሰማሁትን ነው። እንዴት እንደሚፈጸም አልጠየቅሁትም። በዝምታ ተቀበልሁ እንጂ'

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማቴዎስ ወንጌልን 'በመንፈስ ቅዱስ ፅንሳ ተገኘች' የሚለውን ቃል ሲተረጉም እንዲህ ይላል :-

'ከተጻፈው በላይ አትመራመሩ ፤ በቀላሉ ከተነገረው ነገር በላይም አትፈልጉ። መንፈስ ቅዱስ እንዴት በድንግል ውስጥ ይህን ፅንስ አደረገ? ብላችሁ አትጠይቁ። ተፈጥሮአዊው ፅንስን እንኳን እንዴት እንደሚፈጠር በቀላሉ ማብራራት አይቻልም። መንፈስ ቅዱስ ተአምራትን ባደረገበት በዚህ ፅንስ ላይ እንዴት ያለ

ማብራሪያ ልንሠጥ እንችላለን? ... ገብርኤልም ሆነ ማቴዎስ ስለዚህ ፅንስ ከመንፈስ ቅዱስ ነው ከማለት ውጪ ምንም አላሉም። ምክንያቱም ምንም ተብሎ ሊገለፅ ስለማይችል ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ስለተባለ ጥያቄው የተፈታ እንዳይመስልህ። እየተማርናቸውም የማንረዳቸው ብዙ ነገሮች አሉ። በሁሉ የሞላው እንዴት በማሕፀን አደረ? ሁሉን የያዘው አምላክ እንዴት በማሕፀን ገና ያልተወለደ ፅንስ ሆኖ እንዴት ተቀመጠ? ድንግል ፀንሳ እንዴት ድንግል ሆና ቆየች? መንፈስ ቅዱስ እንዴት የሰውነትን መቅደስ አነፀ?' የዚህ ሁሉ ጥያቄ 'ኢይትነገር፡ አላ፡ ይትነከር'፡ 'ይደነቃል እንጂ አይነገርም' እንደሚባለው ነው፡፡

ድንግል ማርያም መልአኩ ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ 'የሚሳነው የለም' ሲላት ሌላ ጥያቄ አልጨመረችም፡፡ 'እሺን የሚሳነው እንደሌለ አውቃለሁ ፤ ነገር ግን እንዴት ነው የሚፈጸመው' ብላ አልቀጠለችም፡፡ የሚሳነው የለም ከሚለው በላይ ምንም የተሻለ መልስ የለም፡፡ ብዙዎቻችን የምንቸገረው ለእያንዳንዱ ነገር መልስ እንዲሠጠን የምንፈልገውን ያህል በፈጣሪ ባለማመናችን ነው፡፡ ለሚያምን ሰው

እግዚአብሔር መልስ ሠጪ ብቻ ሳይሆን ራሱም መልስ ነው ፤ እርሱን ሳያምኑ መልስ ከማግኘትም በእርሱ አምኖ መልስ ማጣት የተሻለ ነው፡፡ የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ እንዳለ ፦

> 'ሰው ሁሉ መልስ እንኳን ባያገኝ ደስ ይበለው ፤ አንተን አጥቶ ምላሽ ከሚያገኝ ምላሽ አጥቶ አንተን ማግኘት ይሻለዋልና'[164]

አምላክ ያለ ወንድ ዘር በድንግልና እንዴት ተፀነሰ? የሚለው ጥያቄ እስከ አሁንም ያልተመለሰ ጥያቄ ነው፡፡ የዚህን ጥያቄ መልስ የሚያውቀው በድንግሊቱ ማሕፀን የሠራውን ታላቅ ሥራ የሚያውቀው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከፍጡራን ወገን ደግሞ ይህን የምታውቀው 'ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራን ለእኔ አድርጎአል' ያለችውና በሰውነትዋ ውስጥ የሆነውን የምታውቀው ድንግል ማርያም ብቻ ናት፡፡

ዝምተኛዋ ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወደ እርስዋ ሲወርድ በሰውነትዋ የሆነውን ልትናገር ብትወድድ እንኳን መስማት የሚቻለው ምን ዓይነት ጆሮ ነው? 'ስለ እርስዋ ድንቅ ሆኖ የሚነገረውን ነገር መናገር የሚቻለው ምን አንደበት ነው?' ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን ወደ

---

[164] St. Augstine, Confessions, 6:10

ገነት በተነጠቀ ጊዜ የሆነውን ለመግለፅ ተቸግሮ እኔ ብሎ ላለመናገር በሌላ ሰው አርቆ እየተናገረም ቢሆን እንዲህ ብሎ ነበር ፡-

> ‘እንዲህ ያለውንም ሰው አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል። ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ’ ፪ቆሮ. ፲፪፥፫-፬

ቅዱስ ጳውሎስ ገነት ደርሶ በመጣ ጊዜ በሥጋው ይሁን በነፍሱ መለየት እስከማይችል ድረስ ሌላ ዓለም ውስጥ ነበረ፡፡ የሰማውን ቃል መናገር ተስኖት ሰው ሊናገር የማይገባው እንደሆነ መሰከረ፡፡ ልብ አድርጉ ሐዋርያው ጳውሎስ የሰው ልጅ አስቀድሞ ይኖርበት ወደነበረው ወደ ገነት ተነጥቆ እንዲህ ካለ መንግሥተ ሰማያት የተባለ ክርስቶስ ወደ አንቺ የገባ ድንግል ሆይ በአንቺ ዘንድ የተፈጸመው ነገር ምንድርን ነው? እርሱ ሰው ሊሰማው የማይችለውን ቃል ሰማሁ አለ፡፡ አንቺ የሰማሽው ምን ነበረ?

ዮሐንስ ክርስቶስን ባየ ጊዜ ‘ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ’ ብሏል፡፡ ዮሐንስን በግርማው እንደ ሞተ ሰው ያደረገው ይህ አምላክ በአንቺ ሰውነት ሲመጣ

የተፈጠረው ምን ነበር? ወደ አንቺ የመጣው ባሕር አይታው የምትሸሸው ፤ ቀላያትም ወደ ኋላ የሚመለሱለት አምላክ ነው፡፡ እርሱን እንደምን ተቀበልሽው? መንፈስ ቅዱስ በኃይል ወደ አንቺ ሲመጣ ፤ እግዚአብሔር ወልድ በሆድሽ ሲያድር ፤ እግዚአብሔር አብ ሲያፀናሽ በሰውነትሽ የሆነው ምን ነበር? እንዴት ፀነስሽው? እንዴትስ በድንግልና ተፀነሰ?

የእግዚአብሔር ምሥጢረኛው ድንግል ማርያም ሊሸከመው ለማይችለው ለሰው ልጅ ያልነገረችው እጅግ ብዙ ነገር በልብዋ አለ፡፡ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ሐዋርያት እመቤታችንን ይህን ጥያቄ ጠይቀዋት እንደነበረ እንዲህ ሲል ይተርካል :-

ሐዋርያት እመቤታችንን እንደምን ፀነስሽው እንደ ምን ወለድሽው ንገሪን አሏት። እንግዲያስ ሳስበው ጭንቅ ጭንቅ ይለኛል እጄን እግሬን ያዙኝ አለቻቸው። ወትሮ የማውቀው መልአክ ቀርቶ ወትሮ የማላውቀው መልአክ መጣ ጊዜው ካፊያ ነበረ። ቀኝ ዐፅፉን ቢባርከው ሕብስተ ሕይወት ሆነ በልቶ አበላኝ ፤ ግራ ዐፅፉን ቢባርከው ማየ ሕይወት ሆነ ጠጥቶ አጠጣኝ ብላ ነገር ጀምራላቸው ሳለች ግሩም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ድምፅ አሰማቸው።

እንደ ቅጠል ረገፉ ፤ እርስዋ ለበታችው ምሥጢር አልበቃችሁም ሲል ነው። መምህር ኤስድሮስ ግን አብ ብቻ

መውለድን ቀምሶ አቀመሰኝ፡፡ ወልድ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ተወልዶ ድኅረ ዓለም ያለ አባት እንድወልደው አደረገኝ ስትል ነው ብለዋል፡፡

## • የአብርሃም ድንኳን

አባታችን አብርሃም በመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳን አክብሮ በመቀበል ወደር የሌለው ጻድቅ ሰው ነበር፡፡ ምንም እንኳን ኑሮው የድንኳን ቢሆንም ወደ አብርሃም ቤት ገብቶ ሳይስተናገድ የወጣ ሰው በዘመኑ አልነበረም፡፡ 'በምድር እንግዳ ተቀባይ የነበረውን አብርሃም እግዚአብሔር በሰማይም ነፍሳትን እንግዳ ተቀባይ አድርጎታል'[165]

ወደ አብርሃም ቤት በአንድ ቀትር ላይ የመጡት እንግዶች ግን የተለዩ ነበሩ፡፡ ምዕራፉ ሲጀምር እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት ይልና ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ይላል፡፡ ሦስቱን እንግዶች ካየ በኋላ የአብርሃም ንግግር የተለመደውን የሰዋስው ሕግ መጠበቅ አቆመ፡፡

ሦስቱን ሰዎች ጠጋ ብሎ አንድን ሰው እንደሚያናግር ንግግሩን ፦ 'አቤቱ፥ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ' ብሎ በነጠላ ይጀምራል፡፡ ዘፍ. ፲፰፥፪ 'ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፥ እግራችሁን ታጠቡ፥

[165] ሊቁ ንቡረ ዕድ ክፍለ ዮሐንስ ሲያስተምሩ እንደ ሰማሁት

ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ' ብሎ በብዙ ይፈጽማል፡፡ ዘፍ. ፲፰፥፬-፭

አብርሃም ብቻ ሳይሆን የዘፍጥረት ጸሐፊ ሙሴም እንደ አብርሃም የሰዋስው ሕግ ጥሶ አንድ ጊዜ 'እነርሱም እንዲህ አሉት' ብሎ በብዙ ይጠራቸውና መልሶ ደግሞ ከሦስቱ አንዱም እንዲህ አለ በማለት ፈንታ 'እርሱም እንዲህ አለው' ብሎ በነጠላ እንግዶቹን ይጠራል፡፡ ዘፍ.፲፰፥፱-፲ አብርሃምም ለሚስቱ የሠጣት መመሪያ ሦስት መስፈሪያ ዱቄት እንድታዘጋጅና አንድ አድርጋ እንድትለውሰው መሆኑ ያለ ምክንያት የተቀመጠ አላስፈላጊ ዝርዝር አይመስልም፡፡ ዘፍ. ፲፰፥፮

በአብርሃም ቤት በሦስት ሰዎች አምሳል ራሱን እንግዳ ያደረገውና ከሌሎች የተሠወረ ሦስትነቱን ለወዳጁ ለአብርሃም የገለጠው እግዚአብሔር ነበረ፡፡ በነጠላ የተነገሩት ቃላት አንድነቱን ፣ በብዙ የተነገሩት ደግሞ ሦስትነቱን የሚገልጡ ናቸው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ 'ስለ አንድነታቸው ማሰብ በጀመርሁበት ቅጽበት ራሴን በሦስትነታቸው ግርማ ተከብቤ አገኘዋለሁ። ስለ ሦስትነታቸው ለይቼ ባሰብሁኝ ቅጽበትም ራሴን ወደ አንድነታቸው ተመልሼ አገኘዋለሁ'[166] ላለው ከአብርሃም ታሪክ የተሻለ ማሳያ የለም፡፡

[166] St. Gregory Nazianzus, On Holy Baptism, Sermon 40

ይህንኑ ታሪክ ከቀጣዩ ምዕራፍ ጋር በማያያዝ 'በአብርሃም ቤት የተገለጡት ሁለቱ መላእክት ሲሆኑ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ነበር' የሚሉ ቀደምት አበው ብዙ ናቸው፡፡ የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜም ሥላሴ ከተረጎመ በኋላ 'አንድም ሠለስቱ ዕደው ያላቸው ሁለቱ መላእክት ናቸው፤ አንዱ ጌታ ነው' ብሎ በአንድታም ማስቀመጡ ይህ አሳብ በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ስልት ውስጥ ምን ያህል መሠረት ያለው አሳብ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሆኖም በአብርሃም ቤት የተገለጠውን ምሥጢር ለምሥጢረ ሥላሴ ማብራሪያ አድረገው ያስተማሩ እንደ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ፡ እንደ ቅዱስ አምብሮስ ፡ ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ ያሉ ቅዱሳን አባቶች አሉ፡፡[167] ታሪኩ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ላይ ያለው ክብደት የላቀ መሆኑን በመገንዘብም አስቀድመው የቤተ አብርሃም መስተንግዶን ታሪክ የሚሥሉ የምሥራቃውያን ሠዓሊያንም ሳይቀሩ ከሦስቱ አንዱን አጉልቶ ከመሣል እኩል አድርጎ ወደ መሣልና

[167] The Mystery of the Trinity, Trinitarian Experience and Vision in the Biblical and Patristic Tradition, Boris Bobrinskoy, SVS Press, 1999, pg 140-141

የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌያዊ መገለጥ እንደሆነ ጠቅሶ ወደ ማስተማር አዘንብለዋል፡፡[168]

በአብርሃም ቤት የሥላሴን መገለጥ አስፍታ አምልታ በምታስተምረውና በዓል ሠርታ የምታከብረው የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አሳብ ግን የእንግዶቹን ነገር ለመላእክት የሚሠጠውን ትርጓሜ እንዲህ ጠንከር ብሎ የሚወቅስ ነው፡፡

‘ወአንተሰ፡ ክርስቲያናዊ፡ እመን፡ ዘንተ፡ ሃይማኖተ፡ ንጽሕተ፡፡ ቤተ፡ አብርሃምሂ፡ እለ፡ ቦኡ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ እሙንቱ፡፡ ወሰገደ፡ ሎሙ፡ አብርሃም፡ በእግርዮ፡ ወለመላእክትሰ፡ ኢይሰግዱ፡ ሎሙ፡ ምስለ፡ እግዚአብሔር፡ በእግርዮ፡ እሐተ፡ ሰግደተ፡ በከመ፡ ሰገደ፡ አብርሃም፡ እንዘ፡ ይብል፡ እጋእዝትየ፡፡ ወኢነገሩነ፡ ኦሪት፡ ወነቢያት፡ ወንጊል፡

---

[168] R.M. Grant, ‘Greek Litrature in the Treatise on the Trinity and Cyril against Julianum, Journal of Theological Study, Vol. 15 1964, 265-299 ; Augstine of Hippo, On Trinity, ii. 20, S.Mckenna, ‘Saint Augstine : The Trinity’ The Fathers of the Church, vol. 46 DC 1963, 7 በእኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት የአብርሃም ቤት ማዕድ ሥዕል የተለመደ አይደለም፡፡ ምሥጢረ ሥላሴን የሚያሳየው ሥዕል በካህናተ ሰማይ ተከብበው በአንድ ዙፋን ተቀምጠው ዓለምን በእጃቸው ይዘው በሦስት አረጋውያን አምሳል የሚሣለው ሥዕል ነው፡፡ አንዳንድ ሰው እግዚአብሔርን ማን አይቶ ሣለው ብሎ ይህንን እሚሟል ይተቻል፡፡ ሆኖም ይህ ሥዕል ‘ሥዕለ ሥላሴ’ /የሦስትነት ሥዕል/ ነው እንጂ እግዚአብሔር ይህን ይመስላል ተብሎ የሚሣል አይደለም፡፡ በሥዕሉ በአንድ ዙፋን መሣሉ አንድነታቸውን ፣ በሦስት አካል መሣሉ ሦስትነታቸውን ፣ አረጋውያን መሆናቸው ቅድምናቸውን የሚገልፅ [illegible]

ወሐዋርያት፡ ከመ፡ ይሰግዱ፡ ኵሉ፡ ፍጥረት፡ ለእግዚአብሔር፡ ጸባኦት፡ በአዕርዮ፡ ምስለ፡ መላእክት፡፡ዘንተ፡ዘኢየአምን፡ወድቀ፡እመዓርግ፡ ሃይማኖት፡ ወለነሰ፡ ይዕቀበነ፡ በሥላሴሁ፡ ንጽሕት’፡

‘አንተ ክርስቲያናዊ ሆይ ይህችን ንጽሕት የሆነች እምነትን እመን። በአብርሃም ቤትስ የገቡት አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው። አብርሃምም አስተካክሎ በአንድነት ሰገደላቸው። ለመላእክትስ አብርሃም ጌቶቼ እያለ እንደሰገደው ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክለው አንድን ስግደት ሊሰግዱላቸው አይገባም። ኦሪትና ነቢያት ፤ ወንጌልና ሐዋርያት ፍጥረት ሁሉ ለእሽናፊ እግዚአብሔር ከመላእክቱ አስተካክለው ጋር በአንድነት ሊሰግዱለት እንደሚገባ አልነገሩንም። ይህን የማያምን ከሃይማኖት መዓርግ ወደቀ ፤ እኛንስ ንጽሕት በሆነች ሦስትነቱ ይጠብቀን’[169]

[169] መጽሐፈ ሥላሴ ፤ ዐ፪ ዘርዐ ያዕቆብ ገጽ ፻ | ወደ ሰዶም የወረዱትን በተመለከተ መጻሕፍተ ብሉያት አብና መንፈስ ቅዱስ ናቸው ፤ ከአብርሃም ቤት የቀረው ወልድ ነው፡፡ ከቤተ አብርሃም ሰው የሆነ እርሱ ነውና ሲል መጽሐፈ ሥላሴ ደግሞ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው ፤ የቀረው አብ ነው ይላል፡፡

እግዚአብሔር በአብርሃም ድንኳን በሦስትነት በተገለጠበት በዚያ ዕለት 'የዛሬ ዓመት ወደ ቤትህ እመጣለሁ ፤ ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች' ብሎት ነበር:: ይህን በጓዳ ሆና የሰማችው አሮጊትዋ ሣራም እንዴት ይሆናል? ብላ ሳቀች::[170] 'እግዚአብሔርም ፡ እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው። ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራም ልጅን ታገኛለች' አለው:: እግዚአብሔር በዓመቱ ወደ አብርሃም ቤት ተመልሶ መጣ የሚል ቃል በዘፍጥረት ላይ አልተጻፈም ፤ አመጣጡ በሥራው ነበርና የይስሐቅ መወለድ የእግዚአብሔር ረድኤት መገለጫ ሆነ::

እግዚአብሔር ወደ አብርሃም ቤት ተመልሶ የመጣበት ትክክለኛው ጊዜ ግን ከድንግል ማርያም ተፀንሶና ተወልዶ 'የአብርሃም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ' ተብሎ የተጠራበት ዘመን ሥጋዌ ነው:: ይህ መሆኑን እንድናውቅ እግዚአብሔር በአብርሃም ቤት በመጣ ጊዜ 'እንደት

[170] የአብርሃምና ሣራ ቤተሰብ ሳቅ ያዘወትራል:: ተግሣፅ 'አኮ ስሐቅ ዘይከውን ኃጢአተ እላ ዘእንበለ ጊዜሁ ወአብዝኖቱ' 'መሳቅ ኃጢአት የሚሆን አይደለም ፤ ያለ ጊዜውና ሲበዛ ካልሆነ በቀር' እንደሚል ሳቅ በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን የጥርጥር ይሆናል:: አብርሃም ሚስቱ እንደምትወልድ ሲነገረው እየሰገደ ስቆ ነበር ዘፍ. ፲፯፡፲፯ አሁን ሳቁን ሚስቱ ደገመችው:: እነርሱ ቢስቁም እግዚአብሔር ግን ሳቃቸውን ልጅ አደረገው:: ይስሐቅ ማለት ይስቃል ማለት ነው:: ዘፍ. ፳፩፡፯ እስማኤልን ሲስቅ አይታ ያባረረችውም ከይስሐቅ ሌላ ማንም አይሳቅ ብላ ልጅዋን ከአብርሃም ቃልኪዳን እንዳይነጥቅባት ነበር:: ዘፍ. ፳፩፡፱

ይሆናል?' ላለችው ሣራ 'በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?' ብሏት እንደነበረ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም መጥቶ ሲያበሥራት 'እንዴት ይሆናል?' ላለችው ጥያቄ የሠጣት መልስ መደምደሚያው 'ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም' የሚል ነበር:: እግዚአብሔር ሣራን የረታበትን ቃል ድንግሊቱን በገብርኤል ሆና ባበሠራት ጊዜ ረትቶበታል:: በመሆኑም በአብርሃም ድንኳን ያደረው እግዚአብሔር ያደረባት የሐዲስ ኪዳንዋ የአብርሃም ድንኳን ድንግል ማርያም ናት:: ዘፍ. ፲፰፥፲፬ ፤ ሉቃ. ፩፥፴፯

ቅዱስ ገብርኤል ለድንግሊቱ 'መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል ፤ የልዑል ኃይልም ያድርብሻል ፤ ከአንቺ የሚወለደው የልዑል ልጅ ይባላል' አላት:: መልአኩ ለድንግሊቱ እግዚአብሔር አብን 'ልዑል' ፤ እግዚአብሔር ወልድን የልዑል ኃይል ፤ የልዑል ልጅ ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን መንፈስ ቅዱስ ብሎ በመጥራት ያለ ወንድ ዘር የምትፀንሰው በሥላሴ ሥራ መሆኑን ነገራት::

የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ብዙዎች የሚያምኑት ነገር ግን ገና ሲነሣ ይከብዳል ብለው የሚሸሹት ርእሰ ጉዳይ ነው:: አንድ ምሥራቃዊ ጸሐፊ 'የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ለሰብአዊው አስተሳሰብ [ለመሸከም

የሚከብድ] መስቀል ነው' ብሎ እንደገለጠው ነገረ ሥላሴ ለብዙዎች ለማሰብ ራሱ የሚከብድ የሕሊና መስቀል ሆኖ ይታያል፡፡[171]

ምሥጢረ ሥላሴን አስፍቶ አምልቶ በማስተማር ወደር ያልተገኘለትና በዚህም ምክንያት በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በተጠራበት ስም ነባቤ መለኮት ብላ የሰየመችው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም ምሥጢረ ሥላሴን የመሰሉ ጥልቅ የነገረ መለኮት ትምህርቶች ላይ መራቀቅ ለሁሉ እንደማይቀልል ሲያስረዳ ፦

> 'ወዳጆቼ ነገረ መለኮትን ማራቀቅ ለሁሉም ሰው የሚሆን ነገር አይደለም ፤ (Philosophising God is not for everyone) ርእሰ ጉዳዩ በቀላሉ የምታገኘው ወይም ለምድራዊ አስተሳሰብ የሚሆን አይደለም ፤ ለሁሉም አድማጭ ፤ ለሁሉም ጊዜ ፤ ለሁሉም ጉዳይ የሚሆንም አይደለም፡፡ በሆኑ ቦታዎች ከሆኑ ሰዎች ጋር በገደብ የሚነካ ርእስ ነው'[172]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይህን ይበል እንጂ የረቀቀ ነገር ለመረዳት የሚቸገሩ ምእመናንንም የተወሳሰበውን ቋንቋ ለሊቃውንቱ ተወት

[171] Vladimir Lossky, The Orthodox Way, Bishop Kallistos Ware, SVS, 1999, 28
[172] St. Gregory of Nazianzus, The Five Theological Orations, 27.3

አድርገው በእውቀታቸው ውስንነት ልክ ምሥጢረ ሥላሴን ሊረዱ እንደሚገባ ካስተማረ በኋላ ሊቃውንቱም ምእመናኑም የሚድኑት አንዱን እምነት በማመናቸው እንጂ በእውቀታቸውና በመራቀቃቸው ልክ አለመሆኑን አስረድቷል፡፡[173]

የእግዚአብሔር አንድነት እንጂ የእግዚአብሔር ሦስትነት በብሉይ ኪዳን የተሠወረ ትምህርተ መለኮት ነበረ፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር 'ቀስ በቀስ ሦስት ሆነ' የሚል የትምህርተ መለኮት እመርታ (dogmatic progression) ሳይሆን ለሰው ልጆች ቀስ በቀስ የተገለጠ በቅድምና የነበረ እውነታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን ትምህርት ለእስራኤል ከመነገር የሰወረው የሦስትነቱ ነገር ለመረዳት የሚችሉት መንፈሳዊ ጫንቃ ስላልነበራቸውና ሦስት አማልክት አድርገው ወደ መረዳት ስሕተት እንዳይገቡ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሦስትነቱን በግልጥ አይናገር እንጂ በብሉይ ኪዳንም አብን አባት ፣ ወልድን ጥበብ ፣ መንፈስ ቅዱስን የእግዚአብሔር መንፈስ እያሉ የሚጠሩ እጅግ ብዙ ቃላት በብሉያት መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡

ሥላሴን በፀሐይ መስለው ካስተማሩ ሊቃውንት አንዱ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም 'ወደ ፀሐይ ለመመልከት ዓይናችንን ቀስ በቀስ

[173] St. Gregory of Nazianzus, Oration on the Moderation in debate, 32.21. 24-25

እንገልጣለን እንጂ በአንድ ጊዜ የገለጥን እንደሆነ ዓይናችን ይጎዳል ፤ እግዚአብሔርም ሦስትነቱን በአንድ ጊዜ ለሰው ልጅ ቢገልጥ ኖር የሰው ልጅ ዓይን ልቡና ይጎዳ ነበር'[174] እንዳለ ምሥጢረ ሥላሴ ቀስ በቀስ ፍንትው ያለ አምላካዊ ምሥጢር ነው:: ፀሐይን በራስዋ ብርሃንነት ካልሆነ በቀር ልናያት እንደማንችልም እግዚአብሔርንም በእርሱ ምሥጢር ገላጭነት ካልሆነ በቀር ልንረዳው አንችልም:: 'በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን' እንዳለ ነቢዩ:: መዝ. ፴፭፥፱

ወዳጄ ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት ትፈልግ እንደሆንህ ብዙ መጻሕፍትን ማገላበጥና መመራመርህን ቆም አድርገህ አንድ መጽሐፍ እንድትገልጥ ልጠቁምህ:: መጽሐፉ እስከዛሬ ያላነበብኸው ነገር ግን አብሮህ የኖረ መጽሐፍ ነው:: ይህች ምሥጢረ ሥላሴ የተጻፈባት መጽሐፍ የገዛ ነፍስህ ናት:: የሰው ነፍስ ከሌሎች ሁሉ የተሻለች የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ናት:: እግዚአብሔር 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር' ብሎ ሲፈጥረው 'ምሳሌያችን' ተብላ የተጠራችው ነፍስ ነበረች::

[174] St. Gregory Nazianzen, Oration XXXI (Theological Orations) 26, pg 36:161, NPNF, 2nd ser., Vol. 7, p.326

አንድ ሰው ነፍስ ስላለው ሦስት ነገሮች ያከናውናል ፤ በልቡ ያስባል ፡ በቃሉ ይናገራል ፤ በእስትንፋሱ ይኖራል፡፡ ልብህ ካሰበው ነገር በቀር በቃልህ ምንም ልትናገር አትችልም፡፡ ቃልህና ልብህም ያለ እስትንፋስህ ሕይወት የላቸውም፡፡ ሦስት ነገሮች ቢኖሩህም አንድ ሰው ነህ እንጂ ሦስት ሰው አትባልም፡፡

በእግዚአብሔር ዘንድም ሦስት ኩነታት አሉ፡፡ 'እግዚአብሔር አብ በራሱ መሠረትነት ለራሱ ለባዊ ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ እውቀት ይሆናል ፤ እግዚአብሔር ወልድም በአብ መሠረትነት ለራሱ ቃል ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ይሆናል፤ መንፈስ ቅዱስም በአብ መሠረትነት ለራሱ ሕያው ሆኖ ለአብና ለወልድ ሕይወት ይሆናል'[175] የእግዚአብሔርን ልብ አብ እንለዋለን ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ወልድ እንለዋለን ፤ የእግዚአብሔርን እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ እንለዋለን፡፡ በእርሱ ዘንድ ሦስት ሁኔታዎች (ኩነታት) ቢኖሩም ሦስት አምላክ አይደለም በህልውና አንድ ናቸውና አንድ አምላክ እንባለን እንጂ፡፡ 'በአብ ለባውያን በወልድ ነባብያን በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ይባላሉ' እንጂ መለያየት በእነርሱ ዘንድ የለባቸውም፡፡

[175] መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ፤ ኰኩሐ ሃይማኖት ገጽ ፻፵፩፤ ዝጉራ መጻሕፍት ፤ ፲፱፻፶፪ ዓ.ም.

ስለ እግዚአብሔር አብ ልብነትና ስለ ወልድ ቃልነትና ስለ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ብሏል:: 'ጎሥዓ፡ልብየ፡ቃለ፡ ሠናየ' 'ልቤ [አብ] በጎ ቃል [ወልድን] አወጣ' 'የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች ፤ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ፤ ሠራዊቶቻቸውም በአፉ እስትንፋስ' 'የውዴ ቃል በተራሮች ላይ ሲወረወር ይመጣል' 'ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ' 'ቃልም ሥጋ ሆነ' 'በደም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል ፤ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል' የሚሉት ቃላት ለዚህ ምስክር ናቸው:: መዝ. ፵፬፡፩ ፤ ፴፪፡፮ ፤ መኃ. ፪፡፰ ፤ ዮሐ. ፩፡ ፩፡፲፬ ፤ ራእ. ፲፱፡፲፫

ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳለ ሆኖ የአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነገር ብዙ ጥያቄዎችን ይወልዳል:: በስም አጠራራችን አብን ማስቀደማችን አብ ይቀድማል ለማለት ባይሆንም በብዙ ሰው ሕሊና ግን እግዚአብሔር አብ ለወልድና መንፈስ ቅዱስ መገኛ መሆኑን ከመቀዳደምና ከመዓርግ ብልጫ ለይቶ ለማሰብ እንዲቸገር ምክንያት ሆኖአል:: አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ላከ ሲባልም የላኪና የተላኪ ተዋረድ አድርጎ የሚያስብም ሰው ብዙ ነው:: ይህን ተከትሎም ብዙ ጥያቄ ይመጣል::

‘ወልድ ከአብ ተወለደ ፤ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ወጣ’ የሚለውን ትምህርት ያለ መቀዳደም እንዴት ልንረዳው እንችላለን? ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተገኙ ናቸው:: በመውለድና በማስረፅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ወልድ ሠረፀ ፤ መንፈስ ቅዱስ ተወለደ ለምን አልተባለም? ወልድ ከአብ መወለዱ እንዴት ነው? ከተወለደ በኋላስ ከአብ ጋር አንድ መሆኑ እንዴት ነው? የሚሉ ብዙ ጥያቄዎች ይከተላሉ:: የአብን ልብነት ፤ የወልድን ቃልነትና የመንፈስ ቅዱስን እስትንፋስነት መረዳት ግን እነዚህን ጥያቄዎች ይመልሳል::

እግዚአብሔር አብ ወልድን ላከ ሲባል ነቢዩ ‘ቃሉን ላከ ፤ ፈወሳቸውም’ እንዳለ ሰው በቃሉ ቢጣራ ቃሉ የእርሱ የበታች እንደማይባል ወልድም ከአብ የተገኘ ከአብ የማያንስ የሚሠራ ቃል ነው ማለት ነው:: መዝ. ፻፱፥፫ ጌታችን ‘እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና’ ሲል በልቡ በአብ ፈቃድ እንጂ በራሱ ፈቃድ ብቻ እንዳልመጣ ተናግሮአል:: ‘የላከኝም ከእኔ ጋር ነው ፤ ብቻዬን አይተወኝም’ በማለት ደግሞ ከአብ ቢላክም አብ ከእርሱ ጋር በህልውና እንዳልተለየ ያሳያል:: ዮሐ. ፰፥፵፪ ! ፰፥፳፱ ‘ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም’ እንደሚል ወልድም

ከአባቱ ሳያንስ የልቡን የአብን ፈቃድ የሚፈፅም 'እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ' የሚል የአብ ቃሉ ነው:: ኢሳ. ፶፫፥፲፩ ፤ ዮሐ. ፲፯፥፬

ሰው በልቡ ከሚያስበው ውጪ በቃሉ ሊናገር እንደማይችል ሁሉ ቃል ወልድም በልቡ አብ ካሰበው በቀር ምንም አያደርግም::[176]

እነዚህ ጥቅሶች ይህንን ያሳያሉ፡-

'እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወድዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል' ዮሐ. ፭፥፲፱-፳

የዚህ ቃል ትርጓሜ በልቤ በአብ ካሰብሁት በቀር በቃልነቴ ብቻ አንዳች አላደርግም:: ወልድ ከአብ ጋር በህልውና አንድ ነውና አብ ወልድ የማያውቀው አንዳች ነገር አያደርግም ፤ ወልድ በህልውና ከአብ ጋር አንድ ሆኖ ያየውን ያደርጋል እንጂ ማለት ነው::

[176] እዚህ ላይ ነቢዩ ዳዊት 'በአፋቸው ይባርካሉ ፤ በልባቸው ይረግማሉ' እንዳለ በአፉ ሌላ ነገር እየተናገረ በልቡ ሌላ የሚያስብ ሰው ነፍሱን ባልተቀደሰ ሦስትነት (unholy trinity) እያስጨነቃት ነውና ልቡ ያሰበውን ብቻ በታማኝነት እስካልተናገረ ድረስ ልብና ቃል ያልተስማሙባት ነፍሱ ለቅድስት ሥላሴ አንድነትና ሦስት ምሳሌ አትሆንም::መዝ. ፷፩፥፬

'እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ' ሲልም ከልቡ ከአብ ካሰብሁት በቀር ፤ በህልውና አንድ ሆኜ ከሰማሁት በቀር ከአብ የተለየ ፍርድ የለኝም ማለት ሲሆን 'ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፤ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም' ማለት ደግሞ የወልድና መንፈስ ቅዱስ ልባቸው አብ ታይቶ በማንም ላይ ፍርድ አይሰጥም ፤ በእርሱ ልብነት እያሰበ ታይቶ መፍረድን ለቃሉ ለወልድ ሠጠው እንጂ ማለት ነው። ዮሐ. ፭፥፲፱-፴

ልባችን ድምፅ ባያወጣም ያለማቋረጥ እያሰበ ቃልን በውስጡ ያመላልሳል ፤ በቃል ስንናገርም ድምፅ አውጥተን እያሰብን (thinking outloud) ነው። በቃል የምንናገረው ነገር ከልባችን ስለተገኘ በህልውና አንዱ ከሌላው እንደማይቀዳደም እንዲሁ በአብና በወልድ ዘንድ መቀዳደም የለም። 'ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ናቸው እንጂ ከአብ በኋላ አይደሉም ፤ ፀሐይ ከብርሃንዋና ከሙቀትዋ እንደማትቀድም እንዲሁ አብ ከመንፈስ ቅዱስና ከወልድ አይቀድምም'[177] አሳብ ከልብ ያለማቋረጥ እንደሚፈልቅ ፤ የወልድ ከአብ መወለድም እንደ ሥጋዊ ልደት አንድ ጊዜ ሆኖ በመለያየት የሚያበቃ ሳይሆን መለያየት የሌለበት የማይፈጸም

[177] St. Gregory of Nazianzus, The Five Theological Orations, On the Son 1:3

ልደት ነው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ስለዚህ ጉዳይ 'ኢይትፈለጥ እምኔሁ ወኢየኃልት ልደቱ እምኔሁ' 'ከእርሱ፡ አይለይም ፤ ከአብ፡ የተወለደው፡ ልደቱ፡አይፈጸምም' ሲል እንዳብራራው 'ልደቱ ተመትር የለውም' ፡፡[178]

ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ መገኘታቸውን ለመግለፅ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ወልድን 'ከአብ ተወለደ' ፤ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ሠረፀ (ወጣ) እንላለን፡፡ በመወለድና በመስረፅ መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት ለሚሻ ሰው አሁንም ቀላሉ መንገድ ወደ ራሳችን ነፍስ መመለስ ሲሆን በመውለድና በማስረፅ መካከል ያለው ልዩነት በመናገርና በመተንፈስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡ አንድ ሰው ተናገረ ማለት ተነፈሰ ማለት አይደለም ፤ ተነፈሰ ማለትም ተናገረ ማለት አይደለም፡፡ እየተነፈሰ ይናገራል ፤ እየተናገረ ይተነፍሳል፡፡ እግዚአብሔርም በቃሉ ይናገራል በእስትንፋሱ መንፈስ ቅዱስ ህያው ሆኖ ይኖራል፡፡

ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተገኙ ቢሆኑም መንፈስ ቅዱስን እንደ ወልድ 'ከአብ ተወለደ' አንልም፡፡ ቃላት የሚያመጡትን የዶግማ ተፋልሶ የሚገነዘቡት ጓደኛሞቹ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ እንዳሉት መንፈስ ቅዱስን ተወለደ ብንል ኖሮ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት 'ወንድማማችነት' ይሆንና የህልውና አንድነትን የሚያዛባ ይሆን

[178] ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፲፻፣ ፲፰ ፣ ፩፬

ነበር፡፡ ከአብ የሠረፀው መንፈስ ቅዱስን ከወልድም ሠርፆአል ብለው የሚያስተምሩ ሰዎችም መንፈስ ቅዱስን የአብ የልጅ ልጅ እያደረጉት ነው፡፡

ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንዲህ ይላል :-

'መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጻሕፍት ከአብ የተወለደ ተብሎ አልተጠራም። ይህም ለእግዚአብሔር ወልድ ወንድም ስለሚያሰኘው ነው፡ ፡ መንፈስ ቅዱስን ከወልድ የተገኘም አንለውም። ይህን ብንልም እግዚአብሔር አብን አያት ማሰኘት ይሆናል። ስለዚህ ወልድን የአብ ልጅ ስንል መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሚወጣ መንፈስ እንለዋለን'[179]

ከልባችን ሃሳብ እንዴት እንደሚወለድና ወደ ቃልነት እንደሚለወጥ ማብራራት አንችልም፡፡ የወልድን ከአብ መወለድና የመንፈስ ቅዱስን መሥረፅም እንዲህ ነው ብለን በቀላሉ መግለፅ አንችልም፡፡ በሕሊናችን ያለው የተከማቸ የሃሳብ እውቀትና ትውስታ በዚህች ቅፅበት በውስጣችን ወደሚመላለስ ቃልነት አለዚያም ወደ ድምፅ ተለውጦ በሌሎች ወደሚሰማ ንግግር የሚለወጥበት ሒደት እንዴት ያለ ነው?

'መመርመር ከተቻለን የሥጋዊውን ነገር ምሥጢር እስቲ እንመርምር? ይህም ሃሳብ ከልብ የሚወለደው እንዴት

---

[179] St. Gregoryof Nazianzus, Homily 31, p.g.36 (Orthodox Teachings) pg 109 , St Basil the Great, Against Sabellius, Homily 24, pg 31

ነው? የሚለውን ነው። የፍጡራንን አፈጣጠር እናውቅ ዘንድ ከተቻለንስ ከእንደበት የቃል መወለድ ምን እንደሚመስል እስቲ እንመርምር። በእኛው ውስጥ ያሉ እነዚህን ነገሮች መርምሮ ማወቅ ካልተቻለን ሕሊናት ሁሉ የማይመረምሩት ፍጡር ያይደለ የፈጣሪን ምሥጢር እንዴት ልናውቅ ይቻለናል?' ይላል ቅዱስ ጎርጎርዮስ 'ወዳእሁ፡ እመሰ፡ ከህሉነ፡ ንኅሥሥ፡ ከመ፡ ናእምር፡ ምሥጢሮ፡ ለሥጋዊ፡ ዘውእቱ፡ ልደተ፡ ሕሊና፡ እምልብ፡ እፎ፡ ውእቱ፡ እው፡ ንክህል፡ ናእምር፡ ፍጥረተ፡ ፍጡራን፡፡ ወልደተ፡ ቃል፡ እምልሳን፡ ምንተ፡ ይመስል፡፡ ለእመ፡ ኢይትከሃለነ፡ ናእምር፡ እሉንተ፡ እለ፡ ሀለዉ፡ ውስቴትነ፡ እፎኑመ፡ ነእምር፡ ምሥጢሮ፡ ለፈጣሪ፡ ለዘኢተፈጥረ፡ ዘይትሌዓል፡ ኮሉ፡ ሕሊናተ'[180]

ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ከአብ መወለድ እና የመንፈስ ቅዱስም ከአብ መውጣት የሚደነቅ እንጂ ሊነገር የማይችል ረቂቅ ምሥጢር ነው፡ ፡ ቅዱስ ዲዮናስዮስም 'ልደተ፡ ወልድ፡ ወጻእተ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እምአብ፡ ይትነከር፡ ወኢይትነገር' 'የወልድ ከአብ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ይደነቃል እንጂ አይነገርም' ብሏል፡፡[181]

---

[180] ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ዘጎርጎርዮስ ፲፫፣ ፲፮

[181] ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ዘዲዮናስዮስ ፲፡ ፲፪

ቅዱስ ገብርኤል ግን ለድንግሊቱ በተናገረው የብሥራት ቃል ላይ ከብሉይ ኪዳን ሰዎች ተሠውሮ የነበረውን ምሥጢረ ሥላሴ ለድንግሊቱ በመንገርና በእርስዋ ላይ እንደሚገለጥ በማብሠር ትምህርተ ሥላሴን አስጀመረ፡፡ መዝገበ ምሥጢር ማርያምም መልአኩ የነገራት የእግዚአብሔር ልጅ ነገር እንደ አይሁድ መምህራን እንግዳ አልሆነባትም፡፡ በጥያቄዋም ስለ ድንግልናዋ ጠየቀች እንጂ ልዑል አብ ልጁ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ብሎ የተናገረው ነገር አዲስ አልሆነባትም፡፡ ምሥጢረ ሥላሴ ከዚያ በኋላ በዮርዳኖስ ወንዝ ፤ በታቦር ተራራ በተከሰቱት ተአምራት ግልጥ ሆኖአል፡፡ አባ ጽጌ ድንግል እንዳለ ፡-

'በላዕሌኪ፡ወበዮርዳኖስ፡ወበታቦር፡ሠለስ፡ጊዜያተ፡፡
ዘአልቦ፡ተውላክ፡ወአልቦ፡ሕጸተ፡፡
ለውሉደ፡ሰብእ፡ያርኢ፡ዘሠላሴሁ፡ገጻተ፡፡
ጽጌኪ፡ድንግል፡ተአምረሁ፡ከሠተ፡፡
ወበጸዳሉ፡አብርሃ፡ጽልመተ'

'ጭማሬም ጉድለትም በሌለበት ሥራ
ምሥጢረ ሥላሴን በዓለም ሊያብራራ
ማርያም ሆይ ልጅሽ በክብር የሚጠራ
በአንቺ ፤ በዮርዳኖስ ፤ በታቦር ተራራ

ሦስትነቱን ገለጠ ተአምራትን ሠራ

በብርሃኑም ኃይልም ጨለማን አበራ'[182]

በድንግሊቱ ማሕፀን የሆነው ይህ ነው ፤ እግዚአብሔር አብ ድንግሊቱን መለኮትን ለመቀበል እንድትችል አድርጎ አጸናት ፤ ወልድ በማሕፀንዋ አደረ ፤ መንፈስ ቅዱስ ፅንሱን አከናወነ፡፡ ከእርስዋ ሰው የሆነው ሰውን እንፍጠር ብሎ የፈጠረው ቃል ራሱ ነበር፡፡ ቀሌምንጦስ 'የፈጠረው ቃሉ ነውና በቃሉ ሊያድነው ይገባል' እንዳለው ነው፡፡ በቃሉ የፈረደበትም እርሱ ነውና እርሱ ሊያድነው ወደደ፡፡ ነቢዩ ሆሴዕ 'እርሱ ሰብሮናልና እርሱ ይፈውሰናል ፤ እርሱ መትቶናልና እርሱ ይጠግነናል ፤ ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን' ብሎ ሰው መሆኑን እስከ ሞቱና ትንሣኤያችንን ስላወጀው ትንሣኤው ሳይቀር እንደተናገረ ሰውን በቃሉ ሊያድን ወረደ፡፡

ከድንግል ማርያም የተወለደው ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ ነው፡፡ ስለዚህ በሥላሴ ሥራ አንዱን ወልድ ወለደች እንላለን፡፡ ከእርስዋ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ለምን አልተወለዱም?

---

182 አባ ጽጌ ድንግል ፤ ማሕሌተ ጽጌ ፤ ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻፫ ዓ.ም. ገጽ ፸፬ ፤ አማርኛው መምህር ኤፍሬም የኔሰው ውብ አድርገው እንደተረጎሙት፡፡

ለምን ወልድ ሰው ሆነ? የሚለው ጥያቄ ሌላው የሊቃውንትን ትኩረት የሳበ ነው፡፡

መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት እንዲህ ይላል ፡-

'አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ቢሆኑ ኖሮ የባሕርይ ስም የባሕርይ ግብር በተፋለሰ ነበር። ምክንያቱም የወለደው አብ የተወለደ ፣ የተወለደው ወልድ የወለደ ፣ የሚሠርፀው መንፈስ ቅዱስም የተወለደ በተባለ ነበር። እንዲህ እንዳይሆን ግን እግዚአብሔር ወልድ በባሕርይ ስሙ ፤ በባሕርይ ክብሩ ለመጠራት በሦስቱ ፈቃድና ሥምረት ሰው ሆኖ ተወለደ'[183]

ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም ስለዚሁ ጉዳይ በድርሳኑ ላይ አብራርቶአል፡-

'ማንም ሰው የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም የወልድ ስም ወደ መሆን ይፋለሳል እንዳይል አብ ሰው ለመሆን በድንግል ማሕፀን ውስጥ ያደረ አይደለም። ለሦስቱ ቅዱስ ፈቃዳቸው አንድ ነውና ወልድ በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ሆነ እንጂ'

[183] መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ፣ ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ፣ አሥመራ ፣ ፲፱፻፰፰ ዓ.ም. ገጽ. ፪፭፪

'ወእኮ፡ እብ፡ ዘኀደረ፡ ውስተ፡ ከርሠ፡ ድንግል፡ ለተሰብኦ፡ ከመኢይበሉ፡ መኑኂ፡ ይትፋለስ፡ ስመ፡ እብ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለከዊነ፡ ስመ፡ ወልድ፡ እላ፡ ውእቱ፡ ወልድ፡ በፈቃደ፡ እቡሁ፡ ወበሥምረተ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተሠገወ፡ እስመ፡ እሐቲ፡ ፈቃድ፡ ለሥሉስ፡ ቅዱስ' [184]

እግዚአብሔር አብ ሁልጊዜም አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድም ሁልጊዜም ወልድ እንደተባለ ይኖር ዘንድ በሥጋዌውም ከድንግል መወለድ የወልድ ሆነ፡፡ ይህም በአካላት ሦስት በሆኑት በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ የስምና የግብር ተፋልሶ እንዳይኖር አደረገ፡፡ [185]

ቅዱስ ገብርኤል ለሐዲስ ኪዳንዋ የአብርሃም ድንኳን ለድንግል ማርያም ተገልጦ 'እንዴት ይሆናል?' ለሚል ጥያቄዋ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በእንቺ ላይ ይሠራል አላት፡፡ የአብርሃም ታሪክ በዘመን ከእርስዋ የራቀ ታሪክ ነው፡፡ ሆኖም ለድንግል ማርያም እንደ አብርሃምና ሣራ በእርጅናቸው ልጅ ሊወልዱ የተቃረቡትን የኤልሳቤጥና ዘካርያስን ነገር ነገራት፡፡ በቀደመችው የአብርሃም ድንኳን በእርጅና የመውለድ ዜና ተነግሮ 'በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው አለን?' በሚል

---

[184] ቅዱስ ሳዊርስ ዘአንጾኪያ ፣ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፣ ፻፱፡፲፩

[185] The Word was incarnated in order that the Hypostatic Attributes of the Three Persons of the Holy Trinity would remain unmovable. It was not intended for the Father to become the Son of the Man, rather than the Word Who has the attribute of being 'The Son' in the Trinity ' Orthodox Teachings, By His Eminence Panteleimon Lampadarios, Port Said 2006, pg 231

ቃል እንደተጠናቀቀ በዚህችኛዋም የሐዲስ ኪዳን ድንኳን ፊት በእርጅና የመውለድ ዜና ተነብቦ 'ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም' በሚል ቃል ተፈጸመ::

ልብ በሉ ፤ በአብርሃም ድንኳን የተነገረው ቃል 'በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው አለን?' የሚል ሣራን ለምን ሳቅሽ የሚል ወቀሳ ያዘለ ንግግር ነበር:: ለድንግል ማርያም ግን የተነገረው ጥያቄ ሳይሆን 'ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና' የሚል አስረጂ ቃል ነው::

ለዚህም ምክንያቱ ሣራ በእርጅና ከባልሽ ትወልጃለሽ ስትባል እንደሳቀችው ድንግል ማርያም ያለ ወንድ ዘር ትወልጃለሽ ስትባል ስላልሳቀች ነው:: ሣራ በተፈጥሮአዊ መንገድ ትፀንሻለሽ መባልዋ ሳቅዋን መቆጣጠር እንዳትችል አደረጋት:: እንግዳ ሲናገር በእንግዳው መሳቅ ከአረጋዊያን የማይጠበቅ ቢሆንም ሣራ ግን የሰማችው ነገር በስተርጅና አሳቃትና በኋላም 'ኧረ አልሳቅሁም' ብላ ለመካድ እስከምትሞክርና ከጌታ ጋር 'ስቀሻል አልሳቅሁም' የሚል ክርክር እስከትገጥም ድረስ አሳፈራት:: ዘፍ. ፲፰፥፲፭

የልጅ አዋቂዋ ድንግል ማርያም በመልአኩ የተነገራት ዉርሶ ሊታመን የማይችል ነገር ነበር:: ሆኖም ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ

ትወልጃለሽ ስትባል 'እዩ ጉድ?!'[186] የትኛዋ ሴት ያለ ወንድ ዘር ፀንሳ ታውትና ነው እኔን እንዲህ የምትለኝ?' ብላ አልሳቀችም፡፡

ድንግሊቱ ልብዋ በፈጣሪ ፍጹም የሚያምን ነውና በዕድሜዋ ልጅ ብትሆንም የሰማዩን እንግዳ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ገብርኤልን እንደ አሮጊትዋ እናትዋ ሣራ እየሳቀች አላስከፋችውም፡፡ እንደ ዘካርያስ ምልክት ጠይቃ አላስቆጣችውም፡፡ 'ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና' ብሎ ሲነግራትም ሌላ ጥያቄ እንኳን ልትጨምር አልወደደችም፡፡ የእምነት ኃያልነት የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ሰምቶ ጥያቄ የሚያስጠይቅ አልነበረምና ለከሃሊነቱ ተረታች፡፡ የናዝሬት ገሊላዋ ድንግል ማርያም የሚሳነው ነገር ለሌለው አምላክ ተማርካ እጅዋን ብቻ ሳይሆን ራስዋን ሠጠች፡፡ 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' የሚሉ ከአልማዝ የከበሩ ቃላትን ከፉ ከማይናገሩ ፡ ማንንም ሰው በንግግር አስቀይመው ከማያውቁ ንጹሐን ከንፈሮችዋ አፈሰሰች፡፡

---

[186] መክ. ፩፥፲፯

# የፍጥረት ናፍቆት[187]

'እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ'!

ይህን ቃል እንደዋዛ ከሌሎች ቃላት ተርታ መጻፍ እንዴት ያስጨንቃል? በዚህ ቃል ምክንያት የሆነልን ካሰብነው እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ዓረፍተ ነገር በወርቅ ቀለም መጻፍ የሚገባው ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል በብርሃናዊ ብዕር ፡ በቅዱሳን እጅ ብቻ ሊጻፍ የሚገባው ቃል ነበረ፡፡ ሰማይና ምድርን ያገናኘውን ይህን ቃል እንዴት እንዲሁ አንብበን እናልፈዋለን? ይህ ዓረፍተ ነገር በሐዲስ ኪዳን ለተጻፉት ለሌሎች ቃላት ሁሉ መነሻ ነበር፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር የሰው ልጅችም እግዚአብሔርም ተጠባብቀው የሰሙት ድንቅ ቃል ነው፡፡ የዚህን ዓረፍተ ነገር ያህል የሰው ልጅን ታሪክ የለወጠ ቃል ከፍጡር አንደበት ተሰምቶ አይታወቅም፡፡

ብዙ ከማትናገረው የዓሥራ አምስት ዓመት ብላቴና ድንግል ማርያም አፍ የወጡት እነዚህ ውድ ቃላት በመነገራቸው ያስከተሉት ነገር ፍጥረታት ሁሉ ለዘመናት ሲናገሩ ውለው ቢያድሩ ሊያመጡት የማይችሉትን ነገር ነው፡፡ ይህ ቃል እግዚአብሔር ወልድን ከዙፋኑ ሰው

---

[187] የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጅ መገለጥ ይጠባበቃል' " 'እስመ ተስፋሁ ለዓለም ምጽአቱ ለወልደ እግዚአብሔር ይጸንሕ' ሮሜ ፰፡፲፱

ለመሆን የጠራ ቃል ነው:: ይህ ቃል የገነትን በር ያስከፈተ ፥ የኪሩቤልንም ሰይፍ ያስጣለ ቃል ነበረ:: ይህ ቃል የፍጥረት ናፍቆት የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ መገለጥ የወጠነ ፥ የምሕረት ዘመንን ያስጀመረ ፥ ዘመን ለማይቆጠርለት አምላክ ዘመን እንዲቆጠርለት የማስጀመሪያ ቃል ነበረ::

በምድር ላይ የማይረሱ ብዙ ታሪካዊ ንግግሮችን ያደረጉ ታላላቅ ሰዎች አሉ:: ድንግሊቱ የተናገረችውን ይህን አንድ ዐረፍተ ነገር ያህል ግን የሰውን ልጅ ታሪክ የለወጠ ቃል የለም:: ይህ ቃል 'ብርሃን ይሁን' ብሎ የዓለምን ጨለማ ካበራው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚተያይ ፥ የማይጠፋው የዓለም ብርሃን ክርስቶስ እንዲመጣና በጨለማና በሞት ጥላ ለሔደ ሕዝብ እንዲያበራ ምክንያት የሆነ ቃል ነው:: ይህ በገሊላዋ ብላቴና የተነገረ ቃል ክርስትናን የመሠረተ ፥ ቤተ ክርስቲያንን የሠራ ፥ ቃል ነው:: ሉቃ. ፩፥፴፱

ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከው ቅዱስ ገብርኤል የመጣበትን ለድንግሊቱ አስረድቶ ፥ ጥያቄዋን መልሶ የተላከበትን ሥራውን ፈጽሞአል:: አሁን የሚጠበቀው የመጨረሻ ነገር የድንግሊቱ መልስ ነው:: መልአኩ ይህን መልስ ካልሰማ ተልእኮው አያበቃም:: ይህ የድንግል ማርያም ምላሽ ቀጣዩን ነገር የሚወስን ነበረ:: መልአኩ

ከእርስዋ እንዲሔድና እግዚአብሔር ወደ እርስዋ እንዲመጣ ድንግሊቱ ይሁን ብላ መቀበልዋ የግድ ነበር፡፡ የሰው ልጅ የመዳን ዕድልም ድንግሊቱ መልስ እስከትሠጥ ድረስ የሚጠብቅ ነገር ነበረ፡፡

ድንግል ማርያም የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ከሰማች በኋላ የምትሠጠው መልስ ለአምላክ ሰው መሆንና ለሰው ልጆች መዳን እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ እግዚአብሔር ነፃ ፈቃድዋን ያከብራልና ድንግሊቱ የፈለገችውን ለመመለስ መብት ነበራት፡፡ ስለዚህ ሕይወትዋን ሙሉ ለሚያስከፍላት ለዚህ የእናትነት አገልግሎት መመረጥዋን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አብራርቶ ከነገራት በኋላ መልስዋን ቆሞ መጠበቅ ነበረበት፡፡ የእርስዋን ምላሽ የሚጠብቀው መልአኩ ብቻ ሳይሆን ገብርኤልን ልኮ ያስነገራት እግዚአብሔርም ነበረ፡፡ እኛ የሰው ልጆችም ሁላችን መልስዋን በጉጉት እየጠበቅን ነበር፡፡

> 'ማርያም ሆይ ለምን ትዘገያለሽ? ሞት የተፈረደብን እኛ እየጠበቅንሽ አይደለምን? የመዳናችን ዋጋ ቀርቦልሻልና እባክሽን ተቀበዪ። እግዚአብሔር በደሙ ሊገዛን እያናገረሽ ነውና እመቤት ሆይ ቶሎ መልስ

ሥጪ ! አትዘገዪ። የዓለም ድኅነት በአንቺ መስማማት

ላይ ተመሥርቶአልና አታዘገዪው'[188]

ነፍሳችን በጥም እየተሰቃየችብን ነውና የሕይወት ውኃ ከአንቺ እንዲፈልቅልን የአንቺን ይሁንታ እየጠበቅን ነው:: በረሃብ የተሠቃየን ሁላችን የሕይወት እንጀራ ከአንቺ እንዲወለድ እየጠበቅን ነውና እሺ በዩ:: የኃጢአት ሸክማችን የከበደንን ሁሉ የሚያሳርፈው አምላክ ከአንቺ ሊወለድ እያናገረሽ ነውና እመቤታችን ሆይ እሺ በዪና ከሸክማችን ገላግዪን::

ነፍሳት በሲኦል እስራት ሆነው ያንቺን ቃል ይጠባበቃሉ:: እግዚአብሔር ሊምረን እጆቹን ዘርግቶ ወደ አንቺ መጥቶአልና ንግሥት ሆይ ተቀበዪው:: ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራን በአንቺ ሊሠራ መርጦሻልና ዝም አትበዪ:: ሊቁ ድሜጥሮስ ዘአንጾኪያ 'የሁሉ እናት ሔዋን የአንተን ወደ ማርያም ማሕፀን መምጣት ትጠባበቃለች። የሰውን አካል የራስህ አድርገህ የሴት ልጅን ነፃነት እስከታውጅ ትጠብቃለች'[189] እንዳለው ኀዘንተኛይቱ እናትሽ ሔዋን በሲኦል ሆና እየጠበቀችሽ ነውና እባክሽን ፍጠኚ:: ነቢያቱ ሁሉ የትንቢታቸውን ፍጻሜ ሊያዩ እየጠበቁሽ ነውና መልስ ለመሥጠት አትቆዪ::

---

[188] St. Augstine, de Temp. Sermon 21

[189] Discourse by Demetrus of Antioch,page 660

እንቺ ለሺህ ዓመታት ዝም ብለሽ ብትቆዩ በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን ነው:: መዳናችንን በተስፋ ለምንጠብቅ ለእኛ ግን ረዥም ነው:: በሲኦል ላሉ ነፍሳት ደግሞ በሲኦል አንዲት ሰከንድ መቆየት ከምድር ላይ አንድ ዓመት ከመሠቃየት የከፋ ነውና ድንግል ሆይ እባክሽን ፈጥነሽ መልስ ሥጪ የሚያሰኝ ቅጽበት ነበር::[190]

ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወደ እርስዋ ያመጣው ጥያቄ ምን እንደሆነና የሚያመጣውን ድኅነት በሚገባ ተረድታለችና ለቀረበላት የነፍስ አዳኝ ጥሪ ምላሽ ለመሥጠት አልዘገየችም:: ሙሴ እስራኤልን ከባርነት ለማዳን መመረጡ ሲነገረው 'እነሆ አያምኑኝም ፤ እግዚአብሔር ከቶ አልተገለጠልህም ይሉኛል' ብሎ ከእግዚአብሔር ለመላኩ ማሳያ ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ምልክትን ጠይቆ ነበር:: ይህች ድንግል ግን 'በመንፈስ ቅዱስ ፀነስሁ ብዬ ስናገር ሰዎች አያምኑኝም' ብላ ምልክትን አልጠየቀችም:: እንደ መስፍኑ ጌዴዎን ስለመመረጥዋ ጠል በጸምር ላይ ወርዶልኝ ካላየሁ አላለችም:: ካለማመን በሚመነጭ ክርክርም የሰው ልጅን ድኅነት ለቅፅበት አላዘገየችም:: 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ' ብላ በትሕትና ተቀበለች እንጂ:: ዘጸ. ፬፥፩ ፤ መሳ. ፮፥፴፱

---

[190] The Departure of The Soul, A Patristic Anthology, St. Anthony Monastry, 2017, 4

በመጽሐፍ ቅዱስ 'እነሆኝ' ብለው የሚናገሩት አባታቸው የጠራቸው ልጆች ፤ ንጉሣቸው የጠራቸው ሎሌዎች ፤ ፈጣሪያቸው የጠራቸው ነቢያት ነበሩ፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ 'እነሆኝ እኔን ላከኝ' እንዳለ 'እነሆኝ' ማለት ለመታዘዝ ዝግጁ መሆንን የሚያሳይ ቃል ነው፡፡ ኢሳ. ፮፥፰ ድንግሊቱ አምላክ ከእርስዋ ሊወለድ እንደመረጣት ስትሰማ 'እነሆኝ' ብላ ራስዋን አቀረበች፡፡ ሰውነትዋን ዙፋኑ አድርጎ እንዲያድርበት ፤ ማሕፀንዋን ከተማ አድርጎ እንዲያርፍበት ፤ ሥጋዋን ምንጭ አድርጎ እንዲፈልቅበት ፤ አካልዋን እርሻ አድርጎ እንዲበቅልበት እነሆኝ አለች፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም አሳልፎ እንዲሠጥ ድንግል ማርያም አስቀድማ ራስዋን ለእግዚአብሔር አሳልፋ መሥጠት ነበረባት፡፡ ስለዚህ እነሆኝ ብላ ራስዋን ለፈጣሪዋ አስረከበች፡፡ አንድያ ልጁን ለዓለም ይሠጥ ዘንድ የወደደው እግዚአብሔርም ለዓለም ከመሥጠቱ አስቀድሞ ለድንግሊቱ ሠጣት፡፡ የሰው ልጆች 'አማኑኤል' 'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ' ብለን ደስ እንድንሰኝ አስቀድሞ እግዚአብሔር 'ከድንግሊቱ ጋር ሆነ'

ድንግሊቱ 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ' ብላ ሰውነትዋን አሳልፋ ለፈጣሪዋ ሠጠች፡፡ ባሪያህ አይደለሁምን? የፈጠርኸው ሰውነቴስ የአንተ አይደለምን? አንተ ጌታዬ ነህ እኔም ባሪያህ ነኝና የወደድኸውን አድርግ

ስትል እነሆኝ ባሪያህ አለች፡፡ ጌታ ባሪያውን 'ሂድ ቢለው ይሄዳል፥ ሌላውንም። ና ቢለው ይመጣል፥ ባሪያውንም። ይህን አድርግ ቢለው ያደርጋል' ድንግሊቱም ባሪያ መሆንዋን አምና ያላትን ለማድረግ 'እነሆኝ ባሪያህ' አለች፡፡ ማቴ. ፰፥፱

የድንግሊቱ 'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ሐሙስ ዕለት ማታ በጌቴሴማኒ ሲጸልይ የነበረው ጌታ 'አባት ሆይ ያንተ ፈቃድ ይሁን' ብሎ ራሱን ከሠጠበት ቃል እኩል ለእኛ መዳን እጅግ ወሳኝ ነበረ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚያድንበት 'የመዳን ቀንና የተወደደ ሰዓት' በደረሰ ጊዜ ነገረ ድኅነት የተፈጸመው በሁለት መልእካዊ ተልእኮዎችና በሁለት ይሁንታዎች ነበር፡፡ ፪ቆሮ. ፮፥፪

መልአኩ ገብርኤል ለድንግሊቱ በታየበት ዕለት ድንግሊቱ በፈራች ጊዜ 'አትፍሪ' ብሎ አበርትቶአት ፡ የተመረጠችበትን ነገር ነግሮአት በመጨረሻም 'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ብላ ተቀበለች፡፡ ሉቃ. ፩፥፴፰ ይህ ቀን የሰው ልጅ ድኅነት የተጀመረበት የጌታችን ዕለተ ፅንሰቱ ነው፡፡ ነገረ ድኅነት የተፈጸመው ደግሞ በምሴተ ሐሙስ 'በፍርሃት ሲጣጣርና አጽንቶ ሲጸልይ' ለነበረው ክርስቶስ 'ከሰማይ መጥቶ የሚያበረታው መልአክ' በታየው ጊዜ ሲሆን እርሱም 'አባት ሆይ የአንተ ፈቃድ ይሁን' ብሎ በመቀበሉ ነው፡፡ ሉቃ. ፳፪፥፵፫-፵፬

> 'የሚያበረታው መልአክ መጣ ማለትንም ከገብርኤል ዜና ጋር ቀጠርነው' 'ወብኪለ፡ መፀአ፡ መሬአክ፡ ዘይጼንዖ፡ ሐለብነ፡ ኀበ፡ ፍናዊሁ፡ለገብርኤል'

እንዳለ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ[191]

ድንግሊቱ 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ብላ የቀረበላት የእናትነት ነገር ከእርስዋ በድንግልናዊ ሕይወት የመኖር ፈቃድ ጋር የሚሔድ ይሆንን? በሚል እንደተጨነቀች ልጅዋም 'አባት ሆይ ብትወድድስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ' ብሎ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን እርስዋም 'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ብላ ፅንሰቱን ስታውጅ ልጅዋ ደግሞ 'የአንተ ፈቃድ ይሁን' ብሎ ስቅለቱን አውጆ የሰው ልጅ ድኅነት ተከናወነ፡፡ ማቴ. ፳፮፥፴፱

እናትና ልጅ የተናገሩት አንድ ዓይነት ቃል 'ይሁንልኝ' የሚለው ብቻም አልነበረም፡፡ ድንግል ማርያም 'እነሆኝ' ብላ የተናገረችውን ራስዋን ለፈጣሪዋ አሳልፋ የሠጠችበትን የትሕትና ቃልም ልጅዋ በመስቀል ላይ 'እነኋት' ብሎ እርስዋን ወክሎ ደግሞታል፡፡ እርስዋ ለእርሱ ማደሪያውና እናቱ ለመሆን ራስዋን ሠጠች ፤ እርሱም ከእርስዋ

[191] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፬፥፲፬

ተወልዶ የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጸመ፡፡ እነሆኝ ብላ ራስዋን ለእርሱ የሠጠችውን ድንግል ግን እንዲሁ ትቶአት አልሔደም፡፡ 'እነኋት እናትህ' ብሎ ነፍሱን ከመሥጠቱ በፊት ለሁላችን እናቱን ሠጠን፡፡ ጌታ ነፍሱን ስለ እኔ አሳልፎ ሠጠ ብሎ ፍቅሩን የሚያደንቅ ሰው ሁሉ እዚያው ቦታ ላይ ያለውን ከነፍሱ በፊት እናቱን የመሥጠቱን እውነታም መዘንጋት የለበትም፡፡ ዮሐ. ፲፱፥፳፯

'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' የሚለው ቃል የሰው ልጅ ለአምላኩ ከተናገራቸው አሜንታዎች ወደር የሌለው ነው፡፡ አሜን ማለት ይሁንልኝ ይደረግልኝ ማለት ነው፡፡ 'ለእግዚአብሔር በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው' አሜን ማለትም 'እግዚአብሔር እንዲሁ ያድርግ' ማለት ነው፡፡ 'ከአሜን ይቀራል' እንዲሉ ድንግል ማርያም ቢቀር ብዙ የሚያስቀር አሜን ከአንደበትዋ ተጠብቆ ነበር፡፡ እርስዋም አሜን ብላ ተቀብላ ለዘመናት የምናዜመውን 'አሚን፡ ወአሚን፡ ለይኩን፡ ለይኩን' 'አሜን አሜን ይሁን ይሁን' የሚል የክርስቲያኖች ቅዳሴ አስጀመረች፡፡ ፪ቆሮ. ፩፥፳ ፤ ኤር. ፳፰፥፮

ድንግል ማርያም 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' የሚለውን ቃል ተናግራ ስትፈጽም ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ ከሰማያት ወረደ፡፡ 'በብሩህ ደመና ተጭኖ መጥቶም' በማሕፀንዋ አደረ፡፡ ሠለስቱ

ምዕት እንዳሉ 'ወረደ፡እምሰማያት፡ወተሰብአ፡እመንፈስ፡ቅዱስ፡ ወእማርያም፡ እምቅድስት፡ ድንግል፡ ኮነ፡ ብእሴ' 'ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ፤ ከእመቤታችን የተነሣ ሰው ሆነ። መንፈስ ቅዱስ ከማዋሐዱ እመቤታችን ይሁንልኝ ከማለትዋ የተነሣ ሰው ሆነ'[192]

ድንግሊቱ የተናገረችውን ቃል ተከትሎ የሆነው ነገር ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ ማንኛውም ፍጡር በአንደበቱ ተናግሮ ከተፈጸመው ነገር ሁሉ እጅግ የከበረ ነው:: ኤልያስ በጻድቅ ሰው ጸሎቱ ሰማይን ለጉሞ ዝናም እንዳይዘንምም እንዲዘንምም አደረገ:: ኢያሱ 'በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም ፤ በኤሎን ሸለቆም ጨረቃ' ብሎ ተናግሮ ፀሐይን አቆመ:: ሐዋርያት 'ተነሣና ተመላለስ' ብለው ሽባውን አስነሡ:: 'ጣቢታ ሆይ ተነሽ' ብለው ሬሳ ቀሰቀሱ:: ያዕ. ፭፥፲፯ ፤ ኢያ. ፲፥፲፪ ፤ ሐዋ. ፫፥፮ ፤ ፱፥፵

ድንግል ማርያም ግን እግዚአብሔርን ከዙፋኑ ድረስ በቃልዋ የጠራችው:: ይሁንልኝ ብላ እንደ ኤልያስ ዝናም ከመለጎምና ከማዘንም አልፋ ንጹሑን ዝናም በእርስዋ እንዲያድር አደረገችው:: ይሁንልኝ ብላ እንደ ኢያሱ ፀሐይን ከማቆም በላይ የፀሐዮች ፀሐይ በሆድዋ ውስጥ እንዲያበራ በቃልዋ ጠራችው:: ሐዋርያት በስሙ ሽባ የፈወሱበትን ፤

[192] ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ዘሠለስቱ ምዕት ፲፮፥፮

ሙት ያስነሡበትን ጌታ ይሁንልኝ ብላ የፀነሰች ድንግል የቃልዋ ኃይል እንደምን ያለ ነው? በአንድ ዐረፍተ ነገር የሰው ልጅን ዳግም ተፈጥሮ ከፈጣሪዋ ጋር ተስማምታ ያስጀመረች ፤ የሰማይን መንገድ መርቃ የከፈተች ፤ የምሕረት ዓመትን መጀመር በቃልዋ ያወጀች ይህች ድንግል የቃልዋ ኃይል እንዴት ያለ ነው?

እመቤቴ ሆይ የአንቺን 'ይሁንልኝ' የሚል ቃል ተከትሎ እግዚአብሔር ሰው ሆነ፡፡ ሰው ሆኜ ተፈጥሬ ሰው መሆን ያቃተኝን እኔንስ ሰው የምታደርጊኝ መቼ ይሆን? አምላክ ሰው እንዲሆን ይሁን ያልሽዋ ሆይ ስለ እኔ ሰው መሆን 'ይሁን' የምትዪው መቼ ይሆን? 'በርታ ሰውም ሁን' የሚለውን ቃል መጠበቅ አቅቶኝ ኃጢአት ሠልጥኖብኝ 'ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም እንደሚጠፋ እንስሳት መሰለ' የሚያሰኝ ሕይወት ለምኖረው ለእኔ ፤ እንደ ቃሉ መሆን ላቃተኝ ለኔ ወደ መሐሪው ልጅሽ 'ይህ ኃጢአተኛ ባሪያህ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ብለሽ እኔንም እንደ ቃሉ የምታደርጊኝ መቼ ይሆን? ፩ነገሥ. ፪፥፫

ቅዱስ ጳውሎስ 'እኛ ከእግዚአብሔር ጋር የምንሠራ ነን' እንዳለ ለታላቁ ዓለምን የማዳን እቅድ ከእግዚአብሔር ጋር አብራ የምትሠራ ያደረጋት ድንግሊቱን ነበር፡፡ ፩ቆሮ. ፫፥፱ የድንግሊቱ 'ይሁንልኝ' የሚል ቃል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ሲስማማ አምላክን ከዙፋኑ ጠራ ፤

የእግዚአብሔርን ልጅ የሰው ልጅ አደረገ ፤ ሰማይና ምድርን አስታረቀ:
: ዝምተኛዋ ድንግል ማርያም ብዙ አትናገርም እንጂ በአንድ ነገር ላይ እምናበት ይሁን ብላ ለፈጣሪዋ ከተናገረች የሚሆነው እምላክን ከሰማይ እስከማውረድ ድረስ ታላቅ ነገር ነው::

በእውነት ይህች ድንግል ስለእርስዋ 'ታማልዳለች ወይስ አታማልድም' በሚል ተራ ክርክር ላጠፋነው ጊዜ ይቅር ትበለን:: ወዳጄ የአንተን ጊዜያዊ ችግር ለመፍታትስ ማንኛውም ተራ ሰው ሊጸልይልህ ይችላል:: ቅዱስ ጳውሎስም ለሁላችን 'ምልጃ ይደረግ' 'ስለ እናንተ ሲያማልዱ ይናፍቋችኋል' 'ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን' ብሎ እርስ በእርሳችን አንዳችን ለሌላችን ልንማልድ እንደምንችል ጽፎአል:: ፩ቆር. ፬፥፲፪ ፤ ፩ጢሞ. ፪፥፩ ፤ ፪ቆር. ፱፥፲፬ መቼም አብዛኛው ጥያቄያችን ከሥጋ አያልፍምና ደህና ገንዘብና ሥልጣን ያለውም ሰው የአንተን ችግር ለመፍታት አያንስም:: 'ይሁንልኝ' የሚል የእምነት ቃልዋን ተናግራ ሰማይና ምድርን በማሕፀንዋ ያስታረቀች የእግዚአብሔር ውድ ፍጥረት ድንግል ማርያም አንተን አማልዶ ማስታረቅ ትልቅ ነገር የሚሆንባት ይመስልሃል?

እውነት ለመናገር ለእኛ ተራ ጉዳይ 'አታማልድም' ብሎ መወዛገብ ቀርቶ 'ታማልዳለች' ብሎ መናገርም ከክብርዋ ጋር የማይመጥን ተራ

መልስ ነው፡፡ ስለ ሌሎች ጻድቃን እንኳን 'የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው ፤ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል' ተብሏል፡፡ ድንግል ማርያም ግን እናት ለልጅዋ እንደምታወራ የሰማይና ምድርን ፈጣሪ በእቅፍዋ ይዛ በጆሮቹ የእናትን የፍቅር ቃል ያፈሰሰች ናትና ከየትኛውም ሰው ድምፅ በላይ የእርስዋ ቃል ለፈጣሪ ጆሮ ጣዕም ያለው ነው፡፡

'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ያለችው ቃል ድንግል ማርያምን የአምላክ እናት ያደረገ ፤ አምላክንም ሰው ያደረገ ቃል ሆነ፡፡ 'መልአኩን እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለችው። ያን ጊዜ ቃል ከእርሰዋ ሥጋን ተዋሐደ። አይታ እንዳትደነግጥ ተመልክታም እንዳትፈራ ሰው በሆነ ጊዜ ከእርሱ ጋር አራቱን እንስሳ አላመጣም። በሰማይ ሥርዓት የተጠበቁ ሰማያውያኑን በዚያ ተወ'[193]

ድንግሊቱ ይሁንልኝ ስትል በመንፈስ ቅዱስ ጣት እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ በማሕፀንዋ ተቀረጸ፡፡ ቅዱስ ሰምዖን 'እሰግድ፡ለኪ፡እመ፡መድኃኒት፡ ዘተሠዐለ፡ በክርስኪ፡ ዘይሠዕሎሙ፡ ለሕፃናት፡ በከርሠ፡እማቲሆሙ' 'ሕፃናትን በእናታቸው ሆድ የሚሥላቸው እርሱ በሆድሽ የተሣለ የመድኃኒት እናት ሆይ እሰግድልሻለሁ'[194] እንዳለ ሕፃናትን በማሕፀን የሚሥላቸው እርሱ በድንግል ማሕፀንዋ ተሣለ፡፡

[193] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፳፥፫፬
[194] ጸሎተ ስምዖን ዘዐምድ ፤ ዘሰኑይ ፭

አባ ሕርያቆስ ድንግሊቱን 'አማኑኤል የሥጋ ልብስን የለበሰብሽ የሽማኔ ጉድጓድ አንቺ ነሽ'[195] በሽማኔ ጉድጓድ ሠሪውም ሥራውም እንደሚገኝ ለራሱ የሥጋ ልብስን ያዘጋጀው እግዚአብሔር በማሕፀንዋ ያደረባት እርስዋ ነበረች፡፡ 'እርሱ ራሱ በመወለጃ ማሕፀን ተሣለ ፤ እርሱን ለመሣል የተፈለገ ሠዓሊ የለም። ከድንግል ማሕፀን ሥጋን ለራሱ ፈተለ'[196]

መልአኩ 'መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል' ባለው ቃል መሠረት ድንግሊቱ 'እንደቃልህ ይሁንልኝ' ስትል መንፈስ ቅዱስ በእርስዋ ላይ ወረደ፡፡ እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ሲል 'ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር' ዘፍ. ፩፥፪ እግዚአብሔር ዳግመኛ በጨለማ የተዋጠውን ይህን ዓለም ድጋሚ ሲፈጥር በወደደ ጊዜም በአዲሲቱ ምድር በድንግል ማርያም ላይ መንፈስ ቅዱስ ሰፈነባት፡፡ እግዚአብሔር አብም መለኮታዊ ኃይሉን ትችል ዘንድ አጸናት፡፡ የማይቻለውን አምላክ እንድትችለው አደረጋት ፤ ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለ :-

> 'ታላቁ ተራራ ጌታ ሆይ ፤ ልትሸከምህ የቻለችው አንተ ራስህን አትልለህባት ነበር። የመገበችህ አንተ ረሃብን

[195] ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ፤ ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው ፪፡፳፱

[196] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፰፡፲፭

> መርጠህ ነው። ጡትዋን ያጠባችህ ፈቅደህ ተጠምተህ ነው። የእሳት ፍሕም ሆነህ ሳለ የዳሰሰችህ እቅፍዋን እንዳይጎዳ ጠብቀህላት ነው'[197].

በቅዳሴ ላይ 'ይወርድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በላዕለ፡ሕብስቱ፡ወወይኑ፡ሶበ፡ ይብል፡ ካህን፡ ጸጋ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፈኑ' እንደሚል ሕብስቱና ወይኑ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ የአምላክ ሥጋና ደም ወደ መሆን በቅጽበት እንደሚለውጠው በዚህች ሕያዊት መቅደስ በድንግል ማርያም ላይም መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በማሕፀንዋ ይህ የሕይወት እንጀራ ክርስቶስ መለኮት በተዋሐደው በሥጋና ደም እንዲፀነስ አደረገ፡፡[198]

ቅዱሳን አበው ይህ አምላክን የፀነሰችበትና ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደውን ወልድ ለሁለተኛው ልደቱ በማሕፀንዋ ያደረበትን ቅጽበት 'መቼ ተጠመቀች?' ተብሎ ለማይነገርላት በመውለድዋ ሁሉንም ምሥጢራት ለፈጸመችው ድንግል ማርያም ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ የተወለደችበት ዕለት ነበር ይላሉ፡፡[199]

---

[197] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity of our Lord, hymn 20

[198] 'Mary and the Eucharist, Sebastian Brock, an Oriental Perspective in SSS, Vol XIII.55' ፤ St. John of Damascus, Orthodox Faith 4.13

[199] እንደ ሶርያ ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ አብያተ ክርስቲያናት የነገረ ማርያም ትምህርት ሊታይባቸው ሊገባ ከቀደሙ አባቶቻቸው መንገድ በጥቂቱ ፈቀቅ ያሉ የሚመስሉት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጸሐፍት እመቤታችንን በተመለከተ የምዕራባውያን ተጽዕኖ ሲያርፍባቸው አልፎ አልፎ ይስተዋላል፡፡ ከእነዚህም መካከል ቄስ አትናስዮስ እስክንድር

ቅዱስ ኤፍሬም በእርሰዋ እንደበት በተቀኘው ቅኔ እንዳለ :-

'የልዑል ልጅ መጥቶ በእኔ አደረ ፤ እኔም እናቱ ሆንሁ፡ ፡ ሁለተኛውን ልደቱን በወለድሁት ጊዜ እርሱ እኔን ዳግም ወለደኝ፡፡ እርሱ የእናቱን ልብስ ሥጋን ለበሰ ፤ እኔም የእርሱን ክብር ለበስሁ' [200]

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም :-

'ከማርያም የተወለደው ሁለተኛ ልደቱ የእርስዋም ሁለተኛ ልደትዋና ጥምቀትዋ ሆነ'[201] ብሏል፡፡

'ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም' እንደሚል እግዚአብሔር በሁሉ የሞላ በቦታ የማይወሰን አምላክ ነው፡፡ ፩ነገሥ. ፰፥፳፯ በዚህች ብላቴና የእምነት ቃል ግን በሁሉ የሞላው እግዚአብሔር በማሕፀንዋ ውስጥ ተወሰነ፡፡ የተደረገው እጅግ ድንቅ ነገር ነው፡፡ የተፀነሰው አምላክ ዓለምን በእጁ የያዘው አምላክ ነው ፤ በእርስዋ

Defending St. Mary በሚል ርእስ ጠንከር ያለ የወቀሳ መጽሐፍ የጻፉባቸው Bishop Bishoy የተባሉ ጣዕመ ውዳሴዋ የራቃቸው ሰው አንዱ ናቸው፡፡ በረከታቸው ይደርብንና ከእኛ ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከእኚህ ሰው ጋር በዓለም አብያተ ክርስቲያናት መድረክ ላይ ተገናኝተው ሲጨዋወቱ 'ድንግል ማርያም የተጠመቀችው መቼ ነው?' ብለው ሲጠይቋቸው የሆነውን እንዲህ ሲሉ ነግረውኝ ነበር፡፡ 'በጣም ተበሳጩሁ፡፡ በእንድ በኩል አምላክን ወለደች እያላችሁ እንዴት ተጠመቀች ትላላችሁ? ከዚህ በኋላ እንዳያናግሩኝ ብዙ ቦታ ቀየርሁ'

[200] St. Ephrem the Syrian, On the Nativity, Hymn 16.11, Singer of the Word of God, Sebastian Brock, Gorgias Press, 213

[201] St. Jacob of Serugh, On the Mother of God, Mary Hansbury, SVS 1998, pg 37

ውስጥ ከእርስዋም ውጪ ነው። 'በድንግል ማሕፀን ውስጥ ባደረ ጊዜ ፀሐይ ከክበቡ ሳይለይ በቤቶች ሁሉ ውስጥ እንደሚያበራ እርሱም ከአባቱ አልተለየም' 'ወእመ፡ ኀደረ፡ ውስተ፡ ከርሠ፡ ማርያም፡ ኢተፈለጠ፡ እምወላዲሁ፡ በከመ፡ የኀድር፡ ጸዳለ፡ ፀሐይ፡ ውስተ፡ አብያት፡ ወኢይትፈለጥ፡እምክበቡ'[202]

'ከአባቱ ሳይለይ ቃል ወደ አንቺ መጣ ሳይወሰን ፀነሰሽው ፤ በላይ ሳይጎድል በታች ሳይጨመር በማሕፀንሽ አደረ'[203] እንዳለ የእርሱ በድንግል ማሕፀን እያለ በሁሉ መገኘት ፤ በሁሉ ሲገኝ በድንግል ማሕፀን መወሰን ከአእምሮ በላይ ነው።

> ቅዱስ ያዕቆብ የተፀነሰውን አምላክ እንዲህ ይለዋል :- 'የሚፈልግህ ሰው ቢኖር ወዴት ሊያገኝህ ይችላል? የሚወድድህስ ሰው ወዴት ሊያይህ ይችላል? በሰማያት በአባትህ እቅፍ ይፈልግህ? ወይንስ በኤፍራታ ቤተ ልሔም?'[204]

ይህ ነገር ለማሰብ የሚከብድ ድንቅ ነገር ነው። አባ ሕርያቆስ እንዲህ ሲል በመደነቅ ማዕበል ውስጥ ይንገላታል :-

---

[202] ዐሥርቱ ተስእሎታት ፤ Scritti Teologici Ethiopici, 1960

[203] ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ፤ ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፭፥፵፮

[204] St. Jacob of Serugh, Bride of Light, Hymns on Mary 15, Sebastian Brock 63

ከገረድነት ጋራ እናትነት እንደምን ያለ ነው? [ከመለኮት] ስፋት ጋራ የሆድ መጥበብ ... ይህንም ባሰብኩኝ ጊዜ ሕሊናዬ የልጅሽን የባሕሩን ጥልቅነት ሊዋኝ ይወድዳል። የወዳጅሽ የመሰወሪያው ማዕበልም ያማታዋል። ዳግመኛ ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ ተሰውሮ ወደ ላይ ወጥቶ የሕያው መሠወሪያ የሆነውን ሊገልጥ ይወድዳል። ከነደ እሳትነቱ የተነሣ ይፈራል። ከዐየራት ከእርቦአቸው እርቦ አይደርስም። ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ በነፋስ ትከሻ ተጭኖ በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ በዳርቻውም ሁሉ ሊበርር ይወድዳል። የፍጡራንን አኗኗር ያይ ዘንድ የአብርሕትንም ጥልቀታቸውን ይለካ ዘንድ ፤ የሰማይንም ርዝመቱን ያውቅ ዘንድ። በሁሉ ዘንድ በሁሉም ይዞራል። አትቶት ወደ ቀደመ አኗኗሩ ይመለሳል'

'ለዘይጸውርዎ፡ለማያት፡ኢያጽአቀ፡ከርሣ፡ለድንግል' እንዲል 'ለማያት ለማይሸከሙት ለእርሱ የድንግል ማሕፀን አልጠበበውም'[205]

---

[205] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፷፯፥፮

በእርግጥም 'የድንግል ሆድ በሰማይ ካለው የብርሃን ሠረገላ ሰፋ። የድንግል ሆድ ከአየር በለጠ ከፍ ከፍ አለ። በኪሩቤልም ዘንድ ተመሰገነ፡ ፡ የድንግል ሆድ የሰማይ ደጅ ሆነ። ሳይከፈትም የፀሐይ መውጫ መግቢያ ነው'[206]

እመቤታችን ጌታን የተሸከመችው መሸከም እንድትችል አድርጎ አጽንቶአት ነበር፡፡ የሚሸከሙትን የሚሸከመው አምላክ የያዘችውን ይዞአት ፤ የተሸከመችውን ተሸክሞአት ነበር፡፡ ማር ኤፍሬም ይዘምራል፡-

> 'ማርያም እንዲህ አለች ፦ የተሸከምሁት ታናሽ ሕፃን እርሱ እኔን ተሸክሞኛል። ክንፎቹን ዝቅ አደረገ ፤ በላባዎቹም መካከል አስቀመጠኝ። ወደ ሰማያት ይዞኝ ወጣ ፤ እንዲህም ሲል ቃል ገባልኝ ፦ ከፍታውም ዝቅታውም ጥልቁም የልጅሽ ናቸው'[207]

ድንግል ማርያም ኃያሉን አምላክ 'ለዘጠኝ ወራት በማሕፀንዋ በክብር ተሸከመችው ፤ ከእርስዋ ወተትን ሲጠባ ዝናምን የሚያዘንበውም እርሱ ነበረ'[208] ጠባቡ የድንግል ማርያም ሆድ ሰማይና ምድርን

---

[206] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ እርጋኖን ድንግል ዘሠሉስ ፱፥ ፶፫

[207] St. Ephrem the Syrian, Hymns on The Nativity of Our Lord, hymn 17

[208] St. Jacob of Serugh, Bride of Light, Hymns on the Nativity II, Sebastian Brock, 57

ለማይችሉት አምላክ ማደሪያ ሆነ፡፡ ማር ኤፍሬም ስለ ጌታችን ጥምቀት በዘመረው መዝሙር እንዲህ ይላል፡-

'ዮሐንስ ለጌታ አለው ፥ ለማያት ለኃያልነትህ አይበቁህም። ይህ ወንዝ ለአንተ ምንኛ ያንስህ ይሆን? ጌታም እንዲህ አለው፥ ማሕፀን ከዮርዳኖስ ወንዝ ይልቅ ያነሠ ነው። በዚያ ሳድርና ልወለድ ፈቅጄያለሁ። አሁንም በዮርዳኖስ ልጠመቅ ፈቀድሁ'[209]

በዚህች ድንግል ማሕፀን አምላክ የማደሩ ሌላው ድንቅ ነገር እርሱ በሰውነትዋ ባደረ ጊዜ በመለኮቱ እሳትነት ሥጋዋ አለመቃጠሉ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ 'አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና' እንዳለ በድንግሊቱ ያደረው መጠን የሌለው የመለኮት እሳት ነበረ፡፡ ዕብ. ፲፪፥፳፱ እርሱ በሲና ተራራ በወረደ ጊዜ 'እግዚአብሔርም በእሳት ስለ ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፥ ተራራውም ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር' ይላል፡፡ ወደዚህች ድንግል በሲና ተራራ ከሆነው በሚበልጥ 'የመለኮቱ ሙላት ተገልጦ' የመጣው ይህ አምላካዊ እሳት ነው፡፡ ዘጸ. ፲፱፥፲፰ ፤ ቆላ. ፪፥፱

[209] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity, Desert Fathers Series, Vol. 5, Hymn XIV

እሳት ስንል በምድር እንደምንለኩሰውና እንደምናጠፋው ዓይነት እሳት አይደለም:: 'እርሱን ግን በምድራዊ እሳት ልንመስለው አይገባም ፤ ለእሳትስ መጠን አለው ፤ ልክም አለው:: ለመለኮት ግን ይህን ያህላል ፤ ይህን ይመስላል ሊሉት አይገባም'[210] ይህች ድንግል 'ማርያም እሳትን በእጆችዋ ታቀፈች ፤ በክንድዋ ያዘች ፤ ጡቶችዋንም ለእሳት አጠባች'[211]

'ሳም እሳት ወለደች ፤ እንዳትለሰው ፈጃት እንዳትተወውም ልጅ ሆነባት' የሚባል ብሂል አለ:: ይህች አዲሲቱ እንቦሳ (ሐዳስ፡ ጣዕዋ) ድንግልም የገጠማት ይህ ነበር:: መጠን የሌለውን እሳት ወለደች ፤ እርስዋን ግን አልፈጃትም:: አቀፈችው ፤ አልተወችውም:: የመለኮቱ እሳትነትም የምትናገረውን የሐዲስ ኪዳን ቁጥቋጦ አላቃጠላትም:: ስለዚህ እንደ ሙሴ ጫማችንን አውልቀን በአክብሮት በፊትዋ ቆመን ከፈጣሪ ጋር እንነጋገርባታለን::

ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ሲል ይዘምራል፡-

'በተባረከው ማሕፀንሽ ውስጥ የእሳት ነበልባል አደረ ፤
ሱራፌል ይህን ነበልባል ቢያዩት ይንቀጠቀጣሉ።
ዓለማትን ያበጃጀው ሕያው እሳት በእንቺ ውስጥ ተዳፈነ።
ይህ እሳት የጣዖት አምልኮን የሚያጠፋ ዘጠኝ ወር

210 ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ፤ ቅዳሴ ማርያም ፳፡፵፰

211 St. Ephrem the Syrian, Hymns on Blessed Mary, 18.27, Palmer, pg 27

የተከደነ እሳት ነው፡፡ በምድር ሁሉ የበቀሉትን እሾኾች ሊያጠፋ የሚቻለው እሳት በማሕፀንሽ ውስጥ ሞላ'[212]

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቆብ አባት ቅዱስ ድሜጥሮስም እንዲህ ይላታል :-

'ሰማይ ታላቅ ነው ቢሉ ከአንቺ ጋር አይስተካከልም ፤ ሰማይና ምድርን የሞላው በማሕፀንሽ ሞልቶአልና፡፡ ሰዎች ከአንቺ ይልቅ ምድርን ታላቅ ናት ቢሉኝ ምድርማ የእግሩ መረገጫ ብቻ ናት እላቸዋለሁ፡፡ 'የኖኅ መርከብ ነሽ' ይሉሻል ፤ የኖኅ መርከብ ግን ያዳነችው ኖኅንና ቤተሰቦቹን ነው፡፡ በአንቺ ግን ዓለም ዳነ፡፡ ታቦት ነሽ ይሉሻል፡፡ ታቦቱ የያዘው በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ሁለት ጽላትን ነበር፡፡ አንቺ ግን የዓለማትን ጌታ በኃይሉ ቃል ፀነስሽው'[213]

እሳተ መለኮትን ተሸከመሽ ሳለሽ ያልተቃጠልሽው እመቤታችን ሆይ እኛ እንደ አንቺ አምላካዊውን እሳት ለመሸከምና ሳይቃጠሉ ለመቆየት የምንለምንበት ሕይወት የለንም፡፡ ሆኖም እኛ አንቺን ነከቶሽ

---

[212] St. Jacob of Serug, On the Visitation 79, Mariological Thoughts of Mar Jacob of Serugh, pg 97
[213] St. Demetrius, Discourses by Demetrius pg 666

በማያውቅ በሌላ እሳት እየነደድንና እየተቃጠልን ነውና እንድታጠፊልንና እንድታስችዪን እንማጸንሻለን፡፡

እኛን ያቃጠለን እሳት ፦

'በጉያው እሳትን የሚታቀፍ፥ ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? በፍም ላይ የሚሄድ እግሮቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው?' ምሳ. ፮፥፳፯

ተብሎ የተነገረለት የኃጢአት ፍትወት እሳት ነው፡፡

እኛን ያቃጠለን እሳት፡-

'እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል። አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል' ተብሎ የተነገረለት የምላሳችን እሳትነት ነው፡፡ ያዕ. ፫፥፮

እንደ አንቺ የመለኮትን እሳት መሸከም ባይቻለንም ፤ እንዳንቺ የሚያድንን እሳት ታቅፎ አለመቃጠል ባይሆንልንም ድንግል ሆይ የፍትወታችን እሳት መሸከም አስችዪን ፤ የምላሳችንንም እሳት መቆጣጠር አስተምሪን፡፡

ከአባ ጊዮርጊስ ጋር እንዲህ ስንል እንማጸንሻለን ፦

'አሳትን በሥጋ የወሰንሽ ድንግል ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን አማልጂኝ ፤ ሥጋንም እንደ ሰም ከሚያቀልጠው ከሥጋዊ ፈቃድ እሳትነት አድኚኝ'[214]

ድንግል ማርያም 'ይሁንልኝ' ብላ ቃሉን እንደተቀበለች ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ከእርስዋ ሔደ፡፡ ከመታየት ወደ አለመታየት ተሠወረ፡፡ የቅዱስ ገብርኤል የሐዲስ ኪዳን ተልእኮ ግን ድንግሊቱን በማብሠር ብቻ አላበቃም፡፡ ዮሴፍን በማረጋጋት ፣ ለእረኞች ልደቱን በማብሠር የቀጠለ ሆነ፡፡ በዕለተ ዐርብ ክርስቶስ ሲሰቀል ቅዱስ ያሬድ 'ወገብርኢል፡ ተደመ' 'ገብርኤልም ተገረመ' እንዲል በአምላኩ ሰው መሆን የተደሰተውን ያህል ያዘነውና በቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደሚነገረው ሰይፉን ጥሎ ድንግል ማርያም ከደናግለ እስራኤል ተካፍላ በፈተለችው ሐር የተሠራው የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለመቀደዱ ምክንያት ሆኖአል፡፡[215]

በጌታው መሰቀል ያዘነው ንስረ አርያም ቅዱስ ገብርኤል ጌታው በተነሣበት ዕለትም ከቅዱስ ሚካኤል ጋር የትንሣኤውን ዜና ለቅዱሳት

---

[214] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፣ አርጋኖን ድንግል ዘረቡዕ ፱፥፭

[215] The Life of Virgin Mary, Olga Moss, 2010, page 11

እንስት ካወጁት ሁለት መላእክት አንዱ ነበረ፡፡ ጌታችን በአርባኛው ቀን ወደ ሰማያት ሊያርግ ሲልም 'መኳንንት ደጆቻችሁን ክፈቱ ፤ የክብር ንጉሥ ይግባ' ብሎ ለመላእክት ያበሠረውና የጌታ በዓለ ዕርገቱ እንጋጥጠው በሚያዩት በሐዋርያት ኅዘን የታጀበ ብቻ ሳይሆን በመላእክት ዝማሬ እንዲታጀብ 'አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ' እንዲል የመላእክቱን ደስታ ያወጀው ይኸው መልአክ ነበረ፡፡ መዝ ፳፫፥፱፤ ፵፮፥፭

ቅዱስ ያሬድ እንዲህ በውብ ዜማ ይገልጸዋል ፡-

'ፀርሐ፡ገብርኤል፡እምሰማይ፡ዘይብል፡ገብርኤል፡ሊቀ፡መላእክት፡
ጻኡ፡ተቀበሉ፡መጽአ፡ወልደ፡አምላክ፡ለቢሶ፡ሥጋ፡ማርያም'፡

'ሊቀ መላእክት ከሰማይ እንዲህ ሲል ጮኸ ፦
የአምላክ ልጅ የማርያምን ሥጋ ለብሶ መጣ ውጡና ተቀበሉ'

# ፫

# ከፀሐይ አጠገብ የነበረው ኮከብ

የአምላክ ሰው መሆንና ተወልዶ የማደጉ ዜና ሲነገር ሁልጊዜም የሚዘነጋ ክብሩ ግን ከብዙ ቅዱሳን ክብር የሚበልጥ አንድ ታላቅ ሰው ዛሬ በልቡናዬ ውል አለ፡፡ መቼም ከፀሐይ አጠገብ ያለ ኮከብ በፀሐይ ብርሃን ምክንያት መሸፈኑ አይቀርምና በተወለደው የጽድቅ ፀሐይ ፣ የሰላም ንጉሥ በልደቱ ደስታ ተውጠን ፣ በገብርኤል ብሥራት ፣ በድንግል ምስጋና ፣ በመላእክት ዝማሬ ተስበን የዘነጋነውን ፣ ድምቀት ሳያንሰው የተሸፈነውን ኮከብ የቅዱስ ዮሴፍን ነገር ባሰብኩኝ ጊዜ ክብሩን ለመናገር ልቡናዬ ተጨነቀ፡፡

በቅድስናው እያመንን ፣ ውለታውንም እያወቅን የምንዘነጋውን ምናልባትም አንዳንድ ሰዎች የድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና

ለማቃለል ስሙን በክፉ ማስረጃነት ሲያነሱብን ከእነርሱ ሸሽን ብለን ሳናውቅ ከበረከቱ የሸሸነውን ጻድቅ ዛሬ ልዘክረው ብል ልቤ በጥፋተኝነት ስሜት ተጨነቀብኝ:: ስለ እርሱ ብዙ ያልዘመርንበትን ፣ ብዙ ያልተቀኘንበትን ዘመን ሳስብ 'ላዕከ ማርያም ቅዱስ ዮሴፍ ሆይ ስለረሳንህ ተኛችን ትርሳን ፣ ስላላሰብንህም ምላሳችን ከትናጋችን ይጣበቅ' ብዬ ይቅርታውን ለመለመን ተመኘሁ::

ቅዱስ ዮሴፍን ማን ብለን እንጥራው? እርሱ እንደሆን እንደ አብርሃም ዘመዶቹን የተወ አማኝ ፣ እንደ ይስሐቅ የታዘዘውን ብቻ ያደረገ ትሑት ፣ እንደ ያዕቆብ በእምነት ግብጽ የወረደ ስደተኛ ነውና እርሱን ለመግለፅ እንደምን ያለ ቋንቋ እንጠቀም ይሆን? እስቲ ንገሩኝ! 'መልካሙን እረኛ' ክርስቶስን የጠበቀውን እረኛ ቅዱስ ዮሴፍን ከቶ በምን ቃል እንገልጸዋለን? የአብን ልጅ ያሳደገውን (ሐፃኔ፡ ወልደ፡ አብ) ቅዱስ ዮሴፍን በምን ቅኔ እናወድሰው?

ሕዝቅኤል ያያትን የእስራኤል አምላክ ገብቶባት ለዘላለም የተዘጋችውን ደጅ የጠበቀውን ታማኝ ዘብ ፣ 'ከበሩ ደጇ ሰላም መንገድ በዚያ ይገባል በዚያም ይወጣል' ተብሎ የተነገረለትን የተዘጋችው በር ደጀ ጠኚ ፣ ከታላቅዋ ተራራ ከድንግል ማርያም ያለ ሰው እጅ ድንጋይ ተፈንቅሎ ሲወርድ ቆሞ የተመለከተውን የሐዲስ ኪዳኑን ዳንኤል ከቶ

እንዴት ባለ ቃል እንገልጸዋለን? በቤተ ልሔም ግርግም ውስጥ በላምና አህያ መካከል የተኛውን ሕፃን የተመለከተውንና እንደ ነቢዩ ዕንባቆም ‘በማዕከለ፡ክልኤ፡እንስሳ፡ርኢኩከ’ /በሁለት እንስሳ መካከል አየሁህ/ ሊል የሚቻለውን የቅዱስ ዮሴፍን ክብር በምን አቅማችን እንገልጸው? ወደ ግብጽ ወርዶ ለወገኖቹና ለዓለም ሁሉ ምግብን እንዳቀየው የብሉይ ኪዳኑ ዮሴፍ ወደ ግብጽ በመከራ ተሰድዶ የሕይወት እንጀራ ክርስቶስን ለሁላችን ላቆየልን ጻድቅ እንዴት ያለ የምስጋና ቃል እናዋጣ?

ሃምሳ ሁለት ዓመታትን በጋብቻ ፡ ዐሥራ ዘጠኝ ዓመታትን በብቸኝነት የኖረው አረጋዊው ዮሴፍ ሊቃነ ካህናቱ በቤተ መቅደስ ሲጠሩት ፍጥረትን የሚያጠግብ የማታ እንጀራ ወደ ቤቱ ሊገባ እንደሆነ አላወቀም ነበር፡፡ በቤተ መቅደስ ያደገች አንዲት ድንግልን ለማጨት የብዙዎች በትር ሲሰበሰብ በትሩን የሠጠው እውነተኛይቱ የአሮን በትር ወደ ቤቱ እንደምትገባ ሳያውቅ ነበር፡፡ ከካህናት ዘንድ ድንግሊቱን ማርያምን ይዞ ወደ ቤቱ ሲሔድም እርስዋ ለእርሱ እንደታጨች እንጂ እርሱ ለእርስዋ እንደታጨ አላወቀም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ እስኪገባው ድረስ ጻድቁ ዮሴፍ የሚያውቀው የታጨችለት በተለመደው ሥርዓት እንደነበረ ነው፡፡ ሆኖም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው

'ድንግል ማርያም ለዮሴፍ አደራ የተሠጠችው በመስቀል ሥር ለዮሐንስ አደራ በተሰጠችበት መንገድ ነበር'

ምንም እንኳን ክርስቶስ ከዮሴፍ ባይወለድም የዮሴፍ መኖር ለአምላካዊው የማዳን እቅድ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ የአምላክ ሰው መሆን ያለ ዘር ፣ ያለ ሩካቤ የሚፈጸም ነገር ቢሆንም ድንግሊቱ ለማንም ሳትታጭ በፊት ፀንሳ ብትገኝ ኖሮ በሰዎች ዘንድ እንደ አመንዝራ ትታያለች እንጂ ማንም ሰው ያለ ወንድ ዘር ፀነሰች ብሎ ሊያስብላት አይችልም፡፡ 'የፀነስሁት በመንፈስ ቅዱስ ነው' ብትልም መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆንና እንደ ደፋር ሐሰተኛ ከመቆጠር በቀር ሰሚ አታገኝም ነበር፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ይላል:-

> 'ከፀነሰችም በኋላ ድንግል መሆንዋን ሳትገልጽ ምሥጢርን ጠብቃ የያዘች ማርያም ብዕፅት ናት። ይህም የእፉኝት ልጆች የሚሆኑ የዕብራውያን ሴቶች እውነቱን በነገረቻቸው ጊዜ እንዳያፌዙባትና ሐሰተኛ ነሽ እንዳይሏት ነው። ጻድቅ ዮሴፍም የተመሰገነ ነው ! እርሱም ምሥጢሩን ሊጠብትና አባት መስሎ ሊታይ ፈቅዶአልና'

ስለዚህ ለዮሴፍ መታጨቷ በሰዎች ዓይን ፅንሱ ከዮሴፍ የተፀነሰ ሆኖ እንዲታይና ክርስቶስም 'እንደ መሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ' እንዲኖር ምክንያት ሆነ፡፡ ይህም ለዮሴፍ የመታጨትዋ ነገር ንጽሕት ድንግል ማርያምን ፅንስዋ በገሃ ቁጥር ባልፈጸመችው በደል በሰዎች ዓይን እንደ አመንዝራ ከመታየት አዳናት፡፡ ይህም በቅዱስ አምብሮስ አገላለጥ እግዚአብሔር በድንግልና መወለዱን ሰዎች እንዲያውቁ ከማድረግ በላይ ግድ የሠጠው ምን እንደነበረ ያሳያል፡፡ ሉቃ. ፪፥፳፪ ፦

> "ጌታ የሰው ልጆች የእናቱን ንጽሕና ከሚጠራጠሩ ይልቅ የእርሱን መለኮታዊ ልደት ቢጠራጠሩ እንደሚሻል መረጠ። የድንግሊቱ ትሕትና እንዴት ጥልቅ እንደሆነ ያውቃል። የንጽሕናዋ ነገርም እንዴት [በአይሁድ ዘንድ] በቀላሉ ሊሰደብ እንደሚችል ያውቃል። ስለዚህ የልደቱ ክብር በእናቱ መዋረድ ላይ እንዲገነባ አልፈለገም"[216]

ቅዱስ ዮሴፍ አገልጋይ የሆነው እንግዲህ ለዚህ ታላቅ ተልዕኮ ነበረ፡፡ የጌታን ፅንስ ነገር እንኳን ከአይሁድ ከአጋንንት ሳይቀር የተሠወረ

[216] St. Ambrose, Commentary on Saint Luke's Gospel, book 2, 1

እንዲሆን ቅዱስ ዮሴፍ ድንግል ማርያምን የጋረደ የወርቅ መጋረጃ ፤ ለንግሥቲቱ መጠለያ የወርቅ ድባብዋ ነበረ፡፡

ሆኖም ቅዱስ ዮሴፍ ይህን ሁሉ የእግዚአብሔር ዕቅድ ፈጽሞ አላወቀም ነበር፡፡ የተሠጠችው ንግሥትም ማን እንደሆነች 'የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም' ነበር፡፡[217] እርሱ 'አገልጋይ የሆነበት የተላከበት ምሥጢርም ምን እንደሆነ አላወቀም' 'ወኢያእመረ፡ ምንት፡ውእቱ፡ምሥጢር፡ዘኮነ፡ሎቱ፡ላዕክ' እንዲል ኤራቅሊስ፡፡[218]

አለማወቁ ደግሞ ቅዱስ ዮሴፍን የበለጠ እንድናከብረውና ከወንጌላዊው ጋር ጻድቅነቱን እንድንመሰክርለት ያደርገናል፡፡ ቅዱስ ዮሴፍን በቅዱስ ሉቃስ አንደበት 'ጻድቅ' ያሰኘው በኋላ ካደረገው ነገር ይልቅ የአምላክ እናት ለመሆን መመረጥዋን ሳያውቅ በፊት ለድንግሊቱ ባሳየው መልካምነት ነበር፡፡ ድንግል ማርያምን ክብርዋን በሚገባ ካወቀ በኋላማ እንኳን ቅዱስ ዮሴፍ ዓለም ሁሉ አገልጋይዋ ነው ፤ ክብርዋን ሳያውቅ በፊት ለእርስዋ መልካም መሆን ግን በእርግጥም ጽድቅ ነው፡፡

እስቲ ታሪኩን ልብ አድርገን እናስታውሰው፡፡ የሆነው እንዲህ ነበር፡፡ ድንግል ማርያም የመልአኩን የብሥራት ቃል መስማትዋን ቅዱስ

[217] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ አርጋኖን ድንግል
[218] ሃይማኖተ አበው ዘኤራቅሊስ ፬

ዮሴፍ አላወቀም:: የትሕትና ውቅያኖስ የሆነችው ድንግል ማርያምም በመልአኩ የተነገራት ዜና ወንድ የማያስፈልገው መሆኑን 'ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆናል?' ብላ ስትጠይቅ በተሠጣት መልስ ተረድታለችና እርስዋ ለዮሴፍ መንገር አላስፈለጋትም:: እንደ ፀነሰች ወዲያውኑ ተነሥታ ወደ ዘመድዋ ኤልሳቤጥ ሀገር ገሰገሰች:: [የሶምሶን እናት እንትኮዩ ማኑሔን ጠርታ ድጋሚ ብሥራቱን እንዲሰማ እንዳደረገች] በዚያ ሦስት ወራት ሰንብታ ስትመለስ ሆድዋ ገፍቶ ፅንስዋ ታይቶ ተመለሰች:: መሳ. ፲፫፥፮

ይህ ወቅት የቅዱስ ዮሴፍ የፈተና ወቅት ነበር:: ቅዱስ ኤራቅሊስ 'ወመልአ፡ ክርሣ፡ ለድንግል፡ ወተሀውከ፡ ልቡ፡ ለዮሴፍ፡ ሶበ፡ ርእየ፡ ልሕቀተ፡ክርሣ' ይላል 'የድንግል ሆድዋ ገፋ ፤ የዮሴፍ ልብም ታወከ ፤ ምሥጢርዋን መርምሮ እንደ ፀነሰች ባወቀ ጊዜ ሕሊናው በማውጣት በማውረድ ማዕበል ተናጠ'[219]

ቅዱስ ዮሴፍ ልቡ ተጨነቀ:: ድንግሊቱ ምንም የነገረችው ነገር የለም:: ያለ ወንድ ዘር ፅንሳ ይሆናል ብሎ መገመት ደግሞ ጨርሶ የማይመጣለት መላ ምት ነው:: ስለዚህ እንደ ማንኛውም ሰው 'ከማን ፅንሳ ነው?' ብሎ ከመጨነቅ ውጪ በድንግልናዋ ሳለች ያለ ወንድ ዘር

---

[219] ሃይማኖተ አበው ዘኤራቅሊስ ፵፰

ትፀንሳለች ብሎ ማሰብ ሊሞክር አይችልም፡፡ ስለዚህ ዮሴፍ ድንግሊቱን ከሕግ ወጥታ ድንግልናዋን እንዳጣች አድርጎ ደምድሞ ነበር፡፡

የድንግል ማርያም የመከራ ሕይወት የሚጀምረው እንግዲህ ከዚህ ነው:-

> 'ድንግል ማርያም ስለ ብዙ ነገሮች ሰማዕት ናት ! ዮሴፍ መልአኩ ሳይገልጽለት በፊት ፅንስዋ በዝሙት እንደሆነ አድርጎ ስለ እርስዋ ማሰቡን መሸከምዋ የመጀመሪያው ሰማዕትነትዋ ነው" ይላል ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ[220]

በእርግጥም እንኳን በድንግልና ለፀነሰች ድንግል ይቅርና በዝሙት ወድቃም ለፀነሰች ሴት ፅንስዋ በገሃ ቁጥር በሰዎች ዓይን ላይ የምታየው የፈራጅነት ሰይፍ ልብዋን ማድማቱ አይቀርም፡፡ በምንም ዓይነት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ገብታ የፀነሰች ብትሆንም ምክንያትዋ ፅንስዋን ከሚተቹ ሰዎች አፍ ሊያስጥላት አይችልም፡፡ ድንግል ማርያም ብትናገርም ማንም ሊያምናት የማይችል ተአምራዊ ፅንስ በሆድዋ ይዛ ወደ ዮሴፍ ቤት ስትመለስ በዮሴፍ ፊት ላይ የሚጠብቃትም ይህ በጥያቄ የተሞላ ዓይን ነበር፡፡

---

[220] St. Severus of Antioch, Homily XIV, In Memory of The Holy Mother of God and Ever-virgin Mary

ከሦስት ወራት በኋላ ከዘመድዋ ኤልሳቤጥ ቤት የተመለሰችው የድንግል ማርያም ሁኔታ ግን ለዮሴፍ የበለጠ ግራ የሚያጋባ ነበረ:: ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ይላል:-

> 'ጠባይዋ ንጽሕናን የተሞላ ነው ፡ በሆድዋ ውስጥ ግን ፅንስ አለ። ዮሴፍ ምን ሊል ይችላል? በፊትዋ ላይ ትድስና ይነበባል በሆድዋ ግን ፀንሳለች። በምን ዓይን እንደሚያያት ግራ ገባው'[221]

ድንግሊቱን አይጠይቃት ነገር በገጽዋ ላይ የሚነበበው ቅድስናዋ አስጨንቀው ፡ ዝም አይላት ነገር ደግሞ በሆድዋ የያዘችው ፅንስ ቸል የሚለው ነገር አልሆነም:: በፊትዋ ላይ አንዳች የጥፋተኝነት ስሜት አይታይም:: ለሰው ማብራሪያ ለመሥጠት ፡ ስለ ንፅሕናዋ ለመከራከርም አልተነሣችም:: ሰዎች ምን ሊያስቡ ይችላሉ ብላ ተጨንቃ ስለፅንሱ ምንም ዓይነት ማስተባበያ ልትሠጥ አልሞከረችም:: በማሕፀንዋ ሊያድር የመረጣት አምላክ ከዚያ በኋላ ምን ሊሆን እንደሚችልም ያውቃልና ምንም ያልተፈጠረ ያህል ሁሉን ለእርሱ ተወች:: በማሕፀንዋ በርትዕ የሚፈርደውን ዳኛ ፀንሳለችና የሰዎችን ፍርድ ፍለጋ ደጅ አልጠናችም:: ይልቁንስ ቅዱስ ኤፍሬም እንዳለው

[221] St. Jacob of Serugh, Homily on the Nativity 555, Texts from Christian Late Antiquity vol. 23

'ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አስምታ ትናገር ነበር ፤ መልአኩ ገብርኤል አክብሮ ከነገረኝ በቀር ምንም ምን የማውቀው እንደሌለኝ እግዚአብሔር ያውቃል አለች'[222]

ቅዱስ ዮሴፍ ድንግል ማርያም ለእርሱ የታጨች እንደመሆንዋ ገና ወደ ቤቱ በገባችበትና በእርሱ ጣሪያ ሥር መኖር በጀመረችበት ወራት ከሌላ ወንድ እንደፀነሰች ማሰብ እጅግ በቁጣ የሚያነድደው ነገር ነበር፡፡ እርሱ የወሰደው እርምጃ ግን በእውነት ጻድቅ የሚያሰኘው ነው፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል ፡-

> 'እጅግ ልዩ የሆነ የራስን መግዛት ጸጋ ባለቤት የሆነ ሰው አይታያችሁም? ይህ ሰው ማንንም ከቶ ሊለቅ ከማይችለው አስቸጋሪ ፈተና ከቅንዓት ነፃ የሆነ ሰው ነው። 'ቅንዓት የቁጣ እሳት ነው ፤ በበቀል ቀን አይራራም' 'ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናት' ተብሎ እንደተጻፈ ቅንዓት በሰው ልብ ውስጥ እንደተቀበረ ፈንጂ ነው። [ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር] በቅንዓትና ጥርጣሬ አብሮ ከመኖር ይልቅ ሕይወታቸውን ማጣትን የመረጡ ብዙ ሰዎችን እናውቃለን።

---

[222] ውዳሴ ማርያም ፤ ዘዓርብ ቍጥር ፱

ዮሴፍ የገጠመው ግን ተራ ጥርጣሬ አልነበረም። ለጥርጣሬው ማስረጃ የሆነ ፅንስ በማርያም ሆድ ውስጥ ተፀንሶአል። ይሁንና ዮሴፍ ከትናት ስሜት ፈጽሞ ነፃ ነበርና በድንግሊቱ ላይ በትንሹም ቢሆን ጭንቀትን ሊፈጥርባት አልወደደም"

ቅዱስ ዮሴፍ በነበረበት ዘመን በነበረው የብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት እንኳንስ ፀንሳ አይቶአት ይቅርና አንድ ወንድ በሚስቱ ወይም በሕግ በታጨችለት ሴት ላይ የቅናት ስሜት ቢሰማውና ቢጠራጠራት እንኳን ወደ ቤተ መቅደስ ወስዶ የማስመርመር መብትም ነበረው፡፡ በምትመረመርበትም ወቅት ሊቀ ካህናቱ ፊት ትቀርባለች፡፡ እግዚአብሔር ያደረግሁትን ይግለጥብኝ ስትል በፊቱ ከንብንብዋን ትገልጣለች፡፡

ካህኑም 'ባልሽን ትተሽ ረክሰሽ እንደ ሆነ፣ ከባልሽም ሌላ ከወንድ ጋር ተኝተሽ እንደሆነ ... እርግማንንም የሚያመጣ ይህ ውኃ ወደ ሆድሽ ይግባ..." እያለ ካስማላት በኋላ ሴቲቱን እርግማን የሚያመጣውን ውኃ (ማየ ዘለፋ) እንድትጠጣ ያደርጓት ነበረ፡፡ ዘኁ. ፭፥፳-፳፪ ከተርተር አልፎ ከማን ጋር እንዳመነዘረች ከታወቀ ደግሞ በድንጋይ ተወግራ ትሙት የሚለው ሕግ ነበረ፡፡ ዘዳ. ፳፪፥፳፫

ጻድቁ ዮሴፍ ድንግል ማርያም በሊቀ ካህናት ፊት ቀርባ ስለ ፅንስዋ እንድትመረመርና የእርግማንን ውኃ እንድትጠጣ የማድረግ መብትን ሕጉ ቢሠጠውም ድንግሊቱን ሌሎች ሰዎች እንዲጠይቋትና በአደባባይ እንድትዋረድ ሊያደርጋት አልፈለገም፡፡[223] ፅንሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑ ሳይነገረው ፤ ድንግሊቱም የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች መሆንዋን ሳያውቅ በፊት እንኳን ዮሴፍ አጋልጦ ሊሠጣት አልፈለገም፡፡ 'ፅንሱ ከሌላ ወንድ በኃጢአት የተፀነሰ ነው' ብሎ በልቡ ባመነበት ጊዜ እንኳን ከማዋረድ ይልቅ ለመሸፈን ወሰነ፡፡

ልብ በሉ ፤ ዮሴፍ ድንግሊቱ እንደፀነሰች እያወቀ በቤቱ ሸሽጎ ማቆየቱ በወቅቱ የነበረውን ሕግን መጣስ ሲሆን እርስዋን አጋልጦ መሥጠት ግን ሕጉን እንደ መጠበቅ ነበር፡፡ ዮሴፍ በድንግሊቱ ላይ በቅናት ተነሣሥቶ ቢጨክንባትና የመበቀል ፍላጎት ቢኖረው ኖሮ እርስዋን አሳልፎ መሥጠቱ የኦሪትን ሕግ የጠበቀ ጻድቅ ሰው ያሰኘዋል እንጂ ደግ

---

[223]ቅዱስ ዮሴፍ ድንግሊቱን ስለ ፅንስዋ ሳያስመረምራት በእግዚአብሔር መልአክ ስለ ፅንሱ ማንነት ካወቀ በኋላና ድንግል ማርያምን ሊያገለግል ከወሰነ በኋላ ከምቀኝነት የማያርፉት አይሁድ ግን ማየ ዘለፋን (water of conviction) እንድትጠጣ እንዳደረጓትና መራራውን የሚያጣፍጠውን ጨው ክርስቶስን የፀነሰችው ድንግልም በጠጣችው ፊትዋ እንደ ፀሐይ አብርቶ እንደታየች የነገረ ማርያም መጻሕፍት የሚያስረዱ ሲሆን በ9ኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉ ጥንታውያን ሥዕላት ላይ ካህናተ ኦሪት ማየ ዘለፋን ሲያጠጧት የሚያሳዩ ሥዕላት በብዛት ተገኝተዋል፡፡ (ውዳሴ ማርያም ዘዐርብ ትርጓሜ ፤ Holy Apostles Convent : The Life of the Virgin Mary, The Theotokos, page 145)

ሰው ከመባል የሚያስቀርበት ምንም ነገር አልነበረም፡፡ ርጉሩጉ ዮሴፍ ግን በድንግሊቱ ላይ ጨክኖ ትወገር ትቃጠል ብሎ የኦሪት ጻድቅ መባልን አልፈለገም፡፡ ምክንያቱም 'እርሱ ጻድቀ ወንጌል ነው እንጂ መች ጻድቀ ኦሪት ሆነና?' ይላሉ ሊቃውንት፡፡[224]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን በሕገ ኦሪት ዘመን ላይ ተወልዶ በሕገ ወንጌል ተመዝኖ የጸደቀ ጻድቅ ዮሴፍን የብርሃን ዘመን መምጣት ምልክት ነው ይለዋል :-

> 'ማርያምን በቤቱ ማቆየት ሕግን መተላለፍ ቢሆንም ማጋለጥና እንድትመረመር ማድረግም ለሞት የሚዳርጋት ነገር ነውና እንዲህ ያለ ነገር አላደረገም። ስለዚህ ዮሴፍ ከሕጉ በላይ ከፍ ባለ ሕግ ራሱን ሊገዛ ወሰነ። እነሆ አሁን ጸጋ ተገልጧልና የዚያ የከበረው የሐዲስ ኪዳን ዜግነት መገለጫ የሆኑ ብዙ ነጸብራቆች ሊታዩ ይገባቸዋል። ፀሐይ ገና ሳትወጣ ከርቀት ግማሹን መሬት ማብራት ትጀምራለች። ክርስቶስም ከማሕፀን እንደ ፀሐይ ከመውጣቱ በፊት በምድር ላይ ማብራት ጀመረ'

[224] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ፤ ገጽ ፶፭ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1997 ዓ.ም.

በማለት ዮሴፍ ለድንግሊቱ ያሳየውን ርኅራኄ ለሰው ሁሉ የሚያበራው የእውነተኛው ብርሃን ክርስቶስ የምሕረቱ ወጋገን ነው ብሏል፡፡[225]

ቅዱስ ዮሴፍ ለድንግል ማርያም ያሳየውን ርኅራኄና ምሥጢር ጠባቂነት ባየ ጊዜ ለየዋህን ቅርብ የሆነው እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ

> 'የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ። እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው'' ብሎ ነገረው፡፡

ጻድቁ ዮሴፍ ይህን በሰማ ጊዜ ለታላቅ ክብር እንደታጨ ተረዳ፡፡ ኢሳይያስ በትንቢት መነፅር ከሩቅ አይቶ 'ትፀንሳለች' ብሎ የተናገረላት ድንግል አጠገቡ እንዳለች አወቀ ፤ 'ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅ

[225] St. John Chrysostom, Homily on the Gospel of Matthew 4.4

ተሠጥቶናል' ብሎ የተናገረለት መድኃኒትም በማሕፀንዋ እንዳለ ተረዳ፡፡ ነቢያት ሁሉ ካሉበት ሆነው የትንቢታቸውን ፍጻሜ ለማየት ወደ እርሱ ቤት ዓይናቸውን እንዳማተሩ ፡ መላእክትም የፈጣሪያቸውን ዙፋን ሊከብቡ ወደ እርሱ ቤት እንደሚገሰግሱ ገባው፡፡ እናጺው ቅዱስ ዮሴፍ በቤቱ ሰማይና ምድርን ያነጸው ሐናጺ ልዑል እግዚአብሔር እንደገባ ሲያውቅ ሁሉን እርግፍ አድርጎ ትቶ ሕይወቱን የአምላኩን እናት ለማገልገል ሠጠ፡፡ ዕንቍ ያለበትን ሣጥን ያየ ነጋዴ ያለውን ሁሉ ሸጦ ሣጥኑን እንደሚገዛና በውስጡ ያለውን ዕንቍ እንደሚያገኝ ዮሴፍም እንደ ዕንቌ ባሕርይ የሚያበራውን ክርስቶስን የያዘችውን ሣጥን ድንግል ማርያምን ብሎ ያለውን ሁሉ ትቶ በረሃ ለበረሃ ሊንከራተት ወሰነ፡፡ ማቴ. ፲፫፥፵፭ ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ

በወንጌል አንድም ቦታ ላይ ዮሴፍ እንዲህ ብሎ ተናገረ ተብሎ የተጻፈ ቃል የለም፡፡ ስለ ፅንሱ ሲነገረው ፤ ወደ ግብጽ ሒድ ሲባል ፤ በቤተ መቅደስ የጠፋውን ጌታ ሲያገኘው አንድም ቃል ዮሴፍ እንደተናገረ አልተጻፈም፡፡ በዚህም በወንጌላዊያኑ ብዕር ቅዱስ ዮሴፍ ያለ ጥያቄ ሊታዘዝ የወሰነ አገልጋይና ከንግግሩ ይልቅ ሥራው የሚጎላ ጻድቅ መሆኑን እናስተውላለን፡፡ የጸጥታ ወደብ የሆነውን መድኃኔዓለም

ክርስቶስን ከእናቱ ጋር ይዞ በምንም አይታወክምና የቅዱስ ዮሴፍ ሕይወት በወንጌል ላይ የጸጥታ ሆነ፡፡

ቅዱሳን አባቶቻችን የቅዱስ ዮሴፍ ዝምታ ከንግግር በላይ ትርጉም ሠጥቶአቸው ስለእርሱ ብዙ ቅኔ ተቀኝተውለታል፡፡ በቅኔያቸውም ውስጥ የዮሴፍን እንደበት እንደበት አድርገው ዘምረዋል፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ስለ ዮሴፍ ውሳኔ ሲገልጽ 'እነሆ ከዛሬ ጀምሮ የመታዉትን አሳብ ከሕሊናዬ አጥፍቼያለሁ። ለንጽሕናሽም ራሴን አሳልፌ እሠጣለሁ። ልጅሽ አምላኪ ነውና'' ብሎ ራሱን ሊሠጥ ወሰነ ብሏል፡፡ በእርግጥም ቅዱስ ዮሴፍ ለቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ማደሪያነት የተመረጠች ታቦት መሆንዋን ሲያውቅ የእግዚአብሔርን ታቦት በእጁ ነክቶ እንደተቀሠፈው እንደ ዖዛ ከመሆን ይልቅ በንጽሕና ሆኖ ሊጠብቃትና ታቦቱ ከሀገር ሀገር ሲዞር መሸከሚያ እንደነበሩት ሁለቱ መሎጊያዎች ከሰሎሜ ጋር ታቦቲቱን ሊያገለግል ቆረጠ፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም ደግሞ በዮሴፍ ቦታ ሆኖ እንዲህ ተቀኝቷል፡-

"ዮሴፍ እግዚአብሔር ወልድን እንደ ሕፃንነቱ አቀፈው ! እንደ አምላክነቱም አገለገለው። በመሐሪነቱ እጅግ ደስ አለው በፈራጅነቱ ግን እጅግ ፈራው። እንዲህ ሲል፡-

> የእግዚአብሔርን ልጅ ለእኔ እንደ ልጅ ይሆን ዘንድ ማን ሠጠኝ? እናትህ በፀነሰች ጊዜ ተቆጥቼ ነበር ፤ በሰውር ልተዋትም አስቤ ነበር። በማኅፀንዋ ውስጥ ከድህነቴ ሊያወጣኝና ባለጠጋ ሊያደርገኝ የሚችል የተሰወረ ሀብት እንዳለ አላወቅሁም ነበር። ከእኔ ዘር የሚሆን ዳዊትስ አክሊል የደፋ ንጉሥ ነበር ፤ እኔ ግን የተናቀ ደሃ ሆንሁ። እንደርሱ ንጉሥ በመሆን ፈንታ አናጢ ሆንኩ። አሁን ግን እነሆ አክሊል ወደ ቤቴ መጣ ፤ የአክሊላት ሁሉ ጌታ በእቅፌ ነውና"[226]

ለፍቶ አዳሪው ሐናጺ ቅዱስ ዮሴፍ ድንግሊቱን ተቀብሎ ሲያገለግላት ታናሺቱን ብላቴና እና ተአምራዊውን ፅንስዋን ለመረዳት ከአእምሮው በላይ ሆኖበት ነበር፡፡ በነቢዩ ኢሳይያስ 'ማንበብንም ለሚያውቅ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ታትሞአልና አልችልም ይላቸዋል። ደግሞም መጽሐፉን ማንበብን ለማያውቅ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ። ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል' የተባለው ትንቢት በዮሴፍ ላይ ተፈጸመ፡፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይህን በተረጎመበት ሥፍራ 'ቦእት፡ ርግብ፡ ንጽሕት፡ ኀበ፡ በግዕ፡ የዋህ፤፡

[226] St. Ephraim the Syrian, Hymns of the Nativity of Our Lord 111

ቦእት፡ መጽሐፍ፡ ኅትምት፡ ኀበ፡ ብእሲ፡ ዘኢይክል፡ አንብቦታ' ይላል፡

ኢሳ. ፳፱፡፲፩

'የዋሂትዋ ርግብ ወደ የዋሁ በግ [ዮሴፍ ቤት] ገባች ፤ የታተመችው መጽሐፍ ማንበብዋን ወደማያውቀው ሰው [እጅ] ገባች። የተዘጋች መጽሐፍ ቅድስት ድንግል ናት። መጽሐፍዋን መሥጠታቸው ከቤተ መቅደስ ለዮሴፍ ቤት መሠጠትዋ ነው። ማንበብ አይቻለኝም ማለቱ ዕንሰዋን እለመረዳቱ ነው'[227]

በእርግጥም ድንግል ማርያም ለዮሴፍ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ከእግዚአብሔር የተላከች ለማንበብ የምታስቸግር የታተመች ደብዳቤ ናት፡-

'ማርያም ለኛ የተገለጠችው የእግዚአብሔር ወልድ ምሥጢራዊነቱና ጥልቀቱ የተሰወረባት ደብዳቤ ሆና ነው። እርስዋ ሰውነትዋን ንጹሕ ብራና አድርጋ አቀረበች ፤ የእግዚአብሔር ቃልም በሥጋ ተገልጦ ባሕርይውን ጻፈባት ፤ ቃሉ ወልድ ሲሆን ለመላው ዓለም የይቅርታ አዋጅ የተላከባት ደብዳቤ እርስዋ ናት። ደብዳቤዋ የታተመች

[227] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፬፥፱-፺፩

ሆና የምትነበብ መሆንዋም የድንግልናዋን ማኅተም ሳይነካ መወለዱ ነው'[228]

የልጅዋ ነገር እንኳንስ ለቅዱስ ዮሴፍ ለእኛ ለሰው ልጆችም ሁሉ ለመረዳት ያስቸገረ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ 'ስሙም ድንቅ!' ብሎ እንደተናገረው የታ·ተመችው ደብዳቤ ድንግል ማርያም የታቀፈችው ማድነቅ እንጂ ማወቅ የማይቻል ሕፃንን ነበር።

'የሚያደንቅ እምነት በነፍስህ ውስጥ ካለ ያ መደነቅ ከጥርጣሬ ይጠብቅሃል። ኢሳይያስ ለምን ድንቅ ብሎ እንደጠራው ከገባህ ያለ አንዳች ምርምር ቅዱስ የሆነውን እርሱን ታደንቀዋለህ'[229] እንዳለ ቅዱስ ያዕቆብ ይህ ሕፃን ድንቅ ነበረ።

እኛ የሰው ልጆች የጠበቅነው ፈራጅና ተበቃይ ፤ በእጆቹ ሰይፍን የያዘ ንጉሥን ነበር። እርሱ ግን የመጣው ሕፃን ሆኖ ነበር። እንደ ኃያል ገዢ ስንጠብቀው 'ከእናቱ ጡት ወተትን እየለመነ እንደ ሕፃናት አለቀሰ' የሰው ልጆች ራሳችንን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከል ለሠራነው በደል ቅጣትን ልንሰማ ለተጠያቂነት ዝግጁ ሆነን ጠበቅነው። እርሱ ግን ፍቅራችንንና እንክብካቤያችንን ፤ ደግነታችንን የሚጠይቅ ፤

[228] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, 636, SVS Press, 1998, pg 39
[229] St. Jacob of Serug, On the Perpitual Virginity, MTMJ pg 41

መታቀፍን የሚሻ ሕፃን ሆኖ እጆቹን ወደ እኛ ዘረጋ፡፡ እኛ መቼም በእግዚአብሔር ላይ ኖሮን የማያውቀውን እምነት እግዚአብሔር በእኛ ላይ አሳየ፡፡ የእኛ ኩራትና ትዕቢት ሳያግደው ራሱን ዝቅ በማድረግ ወደ እኛ ወረደ፡፡

በዚህ ሕፃን ዓለም ሁሉ ተደነቀ ፤ ሁሉም ከጠበቀው በላይ የሆነ ነገርን አገኘ፡፡ መካኒቱ ኤልሳቤጥ ወለደች ፣ ዲዳው ዘካርያስ ትንቢት ተናገረ ፣ ድንግሊቱ እናት ሆነች ፤ እረኞች ከመላእክት ጋር ቆመው ወጣ አወጉ ፤ የከብቶች በረት ቤተ መንግሥት ሆነ ፣ እንስሳት የወለደችን እናት ከብርድ ለመከለል ከበቡት ፣ ከዋክብት መንገድ መሪ ሆኑ ፤ ነገሥታት በድሆች ቤት እጅ መንሻ አቀረቡ ፤ አረጋዊው ስምዖን ሞትን መፍራት አቆመ ፤ ኃያሉ ንጉሥ ሔሮድስ ሁለት ዓመት ያላለፉ ጨቅላ ሕፃናትን እንደ ኃያላን ወታደሮች ፈራቸው፡፡ ይህ ሕፃን ያላመጣው ድንቅ ነገር አልነበረም፡፡

ይህ ሁሉ ለሰው ልጆች ከአእምሮአችን በላይ ቢሆንም በቤቱ ጣሪያ ሥር ሕፃኑን የመንከባከብ አደራ ለተጣለበት ቅዱስ ዮሴፍ ግን የበለጠ ድንቅ ነገር ነበር፡፡ ዮሴፍ የመለኮትን እሳት ተሸክማ ያልተቃጠለችው ዕፀ ጳጦስን ነገር እያየ ፣ እግዚአብሔር በመለኮቱ በእርስዋ አድሮባት እንደ ሲና ተራራ ያልነደደችውን ተራራ እየተመለከተ

የሐዲስ ኪዳኑ ሙሴ ቅዱስ ዮሴፍ ጫማውን ብቻ ሳይሆን ሌላውን ሕይወቱን ሁሉ አውልቆ ጥሎ 'ለድንግልናዋ ሰገደ ፤ ለንጽሕናዋም ተገዛ፡ ፡ 'ወሶበ፡ ሰምዐ፡ ዮሴፍ፡ ዘንተ፡ ቃለ፡ መልአክ፡ ሰገደ፡ ለድንግል፡ ወገነየ፡ ለንጽሓ':እንዲል፡ ፡[230]

ላዕከ ማርያም ቅዱስ ዮሴፍ ለድንግሊቱ የሠጠው አገልግሎት 'እርሱ ገዢሽ ይሆናል' ተብሎ የተወሰነው የሴት ወንድን አገልጋይነት ፍርድ የተለወጠበት የመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን በረከት ምልክት ነበረ፡ ፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ እንዲህ ይላል፡- 'ሕፃኑን በወለደችው ጊዜ እንደ እመቤት እያከበራት እንደ ባለሟል አገለገላት። እነሆ የሴት መገዛት ወደ ወንድ ተመለሰ። ሴቲቱም ለወንድ ራስ ሆነችው"[231]

ቅዱስ ዮሴፍ የአብራኩ ክፋይ ያልሆነውን ክርስቶስን እንደ አባት ሆኖ አሳደገ፡ ፡ 'ወደ ግብጽ ምድር በሚወርዱም ጊዜ ያልወለደውን ሕፃን ተሸክሞ ድንግሊቱን አገለገላት'[232] ምንም እንኳን በሥጋ ባይወልደውም ቅዱስ ዮሴፍ ለጌታ ያጎደለው ምንም ነገር ስላልነበረ ድንግል ማርያም እንኳን በሰው ፊት 'አባትህና እኔ ስንፈልግህ ነበር' ብላ በትሕትና እርሱን አስቀድማ ራስዋን አስከትላ ስትጠራው አላፈረችበትም፡ ፡ ቅዱስ ዮሴፍ

---

[230] ሃይማኖተ አበው ፤ ዘኤራቅሊስ ፶፰
[231] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፮፥፴፫
[232] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፮፥፴፫

በዚህ ድርጊቱ ያልወለዷቸውን ልጆች እንደ ልጅ ለሚያሳድጉ መልካም ሰዎች ሁሉ አርአያ ሆን፡፡ ይህን የተቀደሰ ተግባር የሚያደርጉ ሁሉ የቅዱስ ዮሴፍ በረከት ይደርሳቸዋል፡፡

በእውነት ጌታውን እንደ አባት ያሳደገው ቅዱስ ዮሴፍ በሰማይ ምን ዓይነት ዋጋ አግኝቶ ይሆን? 'ተርቢ አብልታችሁኛል ፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል' ብሎ ዋጋ የሚሠጠው አምላክ በስተርጅና ደካማ ጉልበቱ በረሃ ለበረሃ ተንከራትቶ ያገለገለውን ቅዱስ ዮሴፍን እንዴት ዓይነት ክብርን ሠጥቶት ይሆን? አምላክነቱ ከተነገረው በኋላ ወደ ግብጽ ይዘህ ሽሽ ሲባል እምነቱ ተፈትኖ 'እንደ ጴጥሮስ ፈርቶ አላውቀውም ብሎ ያልካደው'[233] መከራውንም ሊካፈል የፈቀደው ዮሴፍ ምን ዋጋ ተሠጥቶት ይሆን?

የሰማዩን አናውቅም ፤ በምድር ላይ ዮሴፍ ከክርስቶስ ጋር ያሳለፈው ጊዜ ግን በራሱ ሽልማት ነበር፡፡

'ዮሴፍ እግዚአብሔር ወልድን እንደ ሕፃን በፍቅር ዳሰሰው ፤ እንደ አምላክም አገለገለው። እንደ በረከት በደስታ ተቀበለው ፤ እንደ ጻድቅም በአክብሮት አየው ፤ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው?' ይላል ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፡፡ በእውነትም የሰው ልጅ ሁሉ መድኃኒት

[233] ሮቶዐ ሃይማኖት ፲፮፥፩ ፤ መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ እንደተረጎሙት

ሲፀነስና ሲወለድ የዓይን ምስክር ከመሆን በላይ ምን ክብር አለ? ክርስቶስን ከእናቱ እቅፍ ተቀብሎ ከማቀፍ ፣ በጀርባ ከማዘልስ በላይ ምን ጸጋ አለ?

በሰማይ በእሳት ዙፋን የሚቀመጠውን አምላክ ዙፋን የሚሸከሙ በአራቱ ማዕዘን ያሉት አርባዕቱ እንስሳ ኪሩቤል ናቸው፡፡ በቤተልሔም ግን 'ዮሴፍና ሰሎሜ በወዲህና በወዲያ ፤ ላምና አህያም በወዲህና በወዲያ በበረቱ ጎንና ጎን ሆኑ'[234] ድንግሊቱን 'ዮሴፍ ስላገለገላትም ዓይኖቻቸው ብዙዎች ከሚሆኑ ከኪሩቤል ይልቅ ጸጋው በዛ'[235]

የቅዱስ ዮሴፍ ትልቁ ሽልማት ሕፃኑ ክርስቶስ በቤቱ ማደጉ ነበር፡፡ ለክርስቲያን ሁሉ ትልቅ ምኞቱ መንግሥተ ሰማያት የሆነ ክርስቶስን ማግኘት ፣ ሰውነቱን ለክርስቶስ ዙፋን ማድረግ ፣ በፍቅሩ መቃጠል አይደለምን? ቅዱስ ዮሴፍ ይህን ጌታ በእቅፉ ይዞ መዋሉ ብቻ እንዴት ያለ ቅድስና ነበረ? እንኳን ዮሴፍ የዮሴፍ ልጆች እነ ያዕቆብና ዮሳ ፣ ዘመድ ጎረቤቶች ሳይቀር ሕፃኑን ክርስቶስን ማየት ማቀፍ የልባቸው ደስታ ነበር፡፡ ክርስቶስ ያደገበትን የዮሴፍን ቤት ሁኔታ

[234] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ ፩፥፬
[235] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፮፥፴፫

በራእይ የተመለከተው መናኙ አረጋዊ መንፈሳዊ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡፡

> 'የዮሴፍ ዘመዶች ሁሉ እርሱን እያዩ ይደሰቱ ዘንድ ይሰበሰቡ ነበር። የተወደደውን ሕፃን በክንዳቸው ይታቀፉ የነበሩ ሁሉ በመዓዛውና በመልኩ ደስ ይላቸው ነበር። በእጁ የታቀፈው ሰው በግድ ካልሆነ ወድዶ ለሌላው ሰው አይሠጠውም ነበር። ያቀፈው ሰው ሁሉ የሁሉ ጌታ የክርስቶስ መዓዛው በልብሱ ላይ ይቀር ነበር' ይላል፡፡

በእርግጥም ሕፃኑን መድኃኒት የማቀፍ ዕድል አግኝቶ ቶሎ ሊያወርደው ማን ይፈልጋል? እንደ ያዕቆብ 'ካልባረከኸኝ አልለትህም' የሚያሰኘውን ሕፃን የታቀፉ ሰዎች ምንኛ የታደሉ ናቸው?

> አረጋዊ መንፈሳዊ ይቀጥላል ፡- 'አልቦ፡ ዘይጸውሮ፡ በፍቅር፡ ወይፈቅድ፡ ኅዲጎቶ፲መኑ፡ ዘይሰምዕ፡ ቃለ፡ ሕፃን፡ ወኢነደ፡ ልቡ፡ ከመ፡ እሳት' ይላል፡፡ 'በፍቅር ተሸክሞት ሊተወው የሚፈቅድ ማንም አልነበረም። የሕፃኑን [ክርስቶስ] ቃል ሰምቶ ልቡ በፍቅሩ እንደ እሳት ያልነደደ ማን ነው? እርሱን አይቶ ደስ ያላለው የልቡን ኀዘንስ ያልዘነጋ ማን ነው? ከሴቶች ወገንስ

የምትወድደው ሞቶባት የጌታን የሕፃንነቱን ፊቱን ባየች ጊዜ ኀዘንዋን ያልዘነጋች ማን ነች? እርሱን ማግኘት ኀዘንን ሁሉ ያጠፋል ፤ እርሱን ማየት መከፋትን ሁሉ ያርቃል ፤ የቃሉ ድምፅ የልብን ሕመም ይነትላል። እርሱን አይቶ ልቡ እርሱን ለማየት የሰለቸ ማን ነው? የቃሉንስ ነገር ሰምቶ እርሱን ከመስማት የሰለቸ ማን ነው? መዓዛውን ያሸተተ እርሱን ለመያዝ እየቸኮለ ደረቱን ያልደቃ ማነው?" ይላል መናኙ፡፡

አረጋዊ መንፈሳዊ በዮሴፍ ቤት ሕፃኑ ጌታ ሲያድግ የነበረው ሁኔታ ተገልጦለት እያየ በመንፈሳዊ መቃተት እንዲህ ሲል ያመሰግናል፡ ፡ ጌታችን በእግሮቹ የዳኸበትንና የሮጠበትን የዮሴፍን ቤት ፤ እጆቹን እንደ ሕፃን ያሳረፈበትን የዮሴፍን ቤት ግድግዳ በዓይነ ሕሊናው እየሣለ 'እንሰ፡እስተበፅዕ፡አረፍተ፡ቤቱ፡ለዮሴፍ፡፡ወመሬተኒ፡ዘኬደ፡በእገሪሁ' 'እኔስ የዮሴፍን የቤቱን ግድግዳ በእግሮቹ የረገጠውን መሬትም አደንቃለሁ' ብሏል፡፡

ጌታችንን ለማቀፍ የዮሴፍ ልጆችና ዘመዶች በሚሻሙበት ጊዜ ወላዲተ አምላክ በስስት ትመለከት ነበር፡፡ 'ወሶበ፡ በዝኁ፡ እለ፡ ይትማሠጥዎ፡በቤተ፡ዮሴፍ፡ኮነት፡እግዝእትነ፡ማርያም፡እሙ፡ትፈቱ፡ሐቂፎቶ፡ወትጽሕቅ፡ከመ፡ትርአዮ' ይላል አረጋዊው፡፡ 'በዮሴፍ ቤት

ክርስቶስን [ሊያትፉት] የሚናጠቁት ሰዎች በበዙ ጊዜ እናቱ እመቤታችን ማርያም ልታቅፈው ትመኝ ነበር ፤ ልታየውም ትጓጓ ነበር' ልጅዋ እንደመሆኑ 'ይበቃችኋል አምጡ ልጄን' አትላቸውምን ቢሉ 'ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሠጥቶናል' እንዲል የእርስዋ ሕፃን የተወለደው ፡ የእርስዋ ልጅም የተሠጠው ለሁሉም ነውና ንጽሕት ድንግል ይህን አላደረገችም፡፡ ኢሳ. ፱፥፮

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ግን አይጠገቤውን ሕፃን ክርስቶስን እንዲህ ሲል ይማጸነዋል ፦

'በሁሉ ላይ የምትጠጋ አንተ ሕፃን ሆይ እንዴት የከበርህ ነህ? ለሚያገኝህ ሁሉ ፈገግታን ታሳያለህ። ሊያገኝህ የሚፈልገውን ሁሉ በፍቅር ትጠባበቃለህ። ፍቅርህ የሰውን ልጅ የተራበ ይመስላል። ፍቅርህ እንዴት ያለ ነው?

አንተ ሕፃን ሆይ ተጨንቆ ወደ አንተ የመጣ ሰው አንተን ባየ ጊዜ ጭንቀቱ ይጠፋል ፤ ፍርሃት የነበረበትም ሰው አንተን ሲያይ ፍርሃቱን ይረሳዋል። የተራበውም ፊትህን ሲያይ ይጠግባል። አንተ ድንት ሕፃን ሆይ እባክህን ለጥቂት ጊዜ ዕረፍ ፤ ሰዎቹንም ሥራቸውን ይሠሩ ዘንድ ተዋቸው። የድሃ ልጅ ነህና ድሆች ሔደው መሥራት እንዳለባቸውም

እንተም ከዚሁ ተማር እንጂ። ሰውን ወዳጂ ሆይ እባክህ ወደየሥራቸው እንዲሔዱ የፍትርህን ማሠሪያ ፍታላቸው'[236]

ቅዱስ ዮሴፍ ከማንም ሰው በላይ ከድንግል ማርያም ተቀብሎ ጌታችንን ለዓመታት የማቀፍና የማዘል ክብር የተሠጠው ክንፍ የሌለው ኪሩብ ነበር፡፡ ዳንኤል እንደተናገረው በዘመናት የሸመገለ ሰማያዊ አባት ላለው ክርስቶስ ዘመኑ የተቆጠረው ሽማግሌ ዮሴፍ አባት ሆኖ አዘለው፡፡ [237] በአረጋዊ ጉልበቱ ግብጽ ድረስ ተሸክሞት የሔደው ዮሴፍ ክብሩ ታላቅ ነው፡፡

> "ጌታን የተሸከምከውና ወደ ግብጽ ሀገር የወሰድኸው ዮሴፍ ሆይ ብፁዕ ነህ። የሚሸከሙትን የሚሸከም እርሱን መሸከምም ከባድ አይደለም" እንዲል
> ''ብፁዕ፡እንተ፡እ፡ዮሲፍ፡ዘጾርኮ፡ወብሒረ፡ግብጽ፡ዘወሰድኮ፫ኢኮነ፡ ክቡደ፡ ጾዊሮቱ፡ ለዘይጸውሮሙ፡ ለእለ፡ይጸውርዎ''

ቅዱስ ዮሴፍ ጌታችንን የወለደው ልጅ ያህል ይወድደው ነበር፡፡ ከእርሱ ተለይቶ መቆየት አይቻለውምና [እንጨት] ወደሚጠርብበት ቦታም ይዞት ይሔድ ነበር' ይላል አረጋዊው፡፡ እኛ መንግሥቱን ለመውረስና ፊቱን ለማየት የምንናፍቀውን ክርስቶስን ዕለት ዕለት ያየ ፡ ምድር ላይ

[236] St. Eprem the Syrian, Hymns on the Nativity, Desert Fahers Series Vol. 5, Hymn IX
[237] መጽሐፈ ምሥጢር ፭፥፭፫

ሆኖ የመንግሥተ ሰማያትን ኑሮ የተመለከተው ዕድለኛው ቅዱስ ዮሴፍ ጌታችን የዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ በመቶ ዐሥራ አራት ዓመቱ በክብር አርፎአል፡፡[238] አልዓዛር በሞተ ጊዜ ዕንባውን ያፈሰሰው ርኅሩኅ ክርስቶስ ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ የኀዘን ዕንባ ያፈሰሰበት ዕለት ሳይወልደው እንደ አባት ያሳደገው ቅዱስ ዮሴፍ በሞተበት ጊዜ ነው፡፡

ወዳጄ ሆይ በቅዱስ ዮሴፍ ክብርና ዕድል መንፈሳዊ ቅናት ተሰምቶህ ይሆን? ከሆነ ክርስቶስ ለአንተም ዕድሉን አልነፈገህም፡፡

አረጋዊ መንፈሳዊ እንዲህ ሲል ይመክርሃል ፦

> 'ያንተ ስላልሆነች ሀገር በማሰብና በመዘንጋት ውስጥ ምን ታገኛለህ? ይልቁንስ በእናቱ በማርያም አምሳል በኅንህ እንድታቅፈው የንጉሥ ልጅ ክርስቶስን በነፍስህ ውስጥ ፈልገው። ልብህን እንደ ጠራቢው ዮሴፍ የክብሩ ዙፋን አድርገህ አዘጋጅለት። ሐሳቦችህ እንደ ዮሴፍ ልጆች ክርስቶስን ለማቀፍ ይናጠቁት'

ይህን ስታነብ 'ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በተኮነንኩ' "እኔ እንደ ዮሴፍ ጌታዬን ማቀፍ ቀርቶብኝ ከኃጢአቴ ብዛት የተነሣ ሰይጣን

[238] መጽሐፈ ስንክሳር ፣ ምንባብ ዘሐምሌ ፳፮

ሠልጥኖብኛል ፤ ልቤ ጣዖት በሆኑ ምኞቶቼ ተሞልቶአል" የምትል ወዳጇም አረጋዊውን እንዲህ ሲልህ ስማው :-

'ምግባርህ እንደ ግብፃውያን ከሆነብህ ከርኵሰትህ ትነፃ ዘንድ ጌታን በፍትር ተቀበለው። ሕሊናና መታወኩ ተርቶ እንደ ግብጽ ገዳማት ጸጥ ይልልህ ዘንድ ለፈጣሪህ ልብህን ከፈትለት' ያን ጊዜ እግዚአብሔር በፈጣንዋ ደመና በእናቱ እቅፍ እየበረረ ወደ አንተ ይመጣል፡፡ የልቡናህ ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ ፤ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ልብህ ይቀልጣል፡፡

አንተ ብቻ እንዲህ ብለህ መጸለይን አትተው :-

"የተከዘ ፊት ያለውን ዮሴፍን ሕፃኑን ከምግባረ ጎደሉው ሔርድስ እንዲያሸሸው ያዘዝኸው ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ በቃልህ ጦር መሰበት ከልቤ ግብጽ አጋንንትን አሳድዳቸው ፤ በበትርህ ዕፀ መስቀልም የጣዖቶቻቸውን ራስ ቀጥቅጥልኝ"

'እ፡ዘአዘዝኮ፡ለዮሴፍ፡ትኩዘ፡ገጽ፡
ሕፃነ፡ያጕይይ፡እመዓተ፡ሔሮድስ፡ሕፁፅ፡
እግዚአብሔር፡ኃያል፡በሥረተ፡ቃልከ፡ሐፅ፡
ስድዶሙ፡ለአጋንንት፡እም፡ብሔረ፡ልብየ፡ግብጽ፡
ወርእሰ፡ጣዖቶሙ፡ቀጥቅጥ፡በበትርከ፡ዕፅ'

ጠቢበ ጠቢባን

፫

# የጻድቃን ቀጠሮ

## • ፈጥና ወጣች

ድንግል ማርያም 'ደስ ይበልሽ' የሚለውን የመልአኩን ብሥራት ከሰማች በኋላ 'ወደ ተራራማው ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች' ምንም እንኳን መልአኩ የነገራት 'ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላት የምሥራች' ቢሆንም እርስዋ ግን የዘመድዋን ኤልሳቤጥ የምሥራች ለመካፈል ጉዞ ጀመረች፡፡ መጽሐፍ 'ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ! ከሚያለትሱም ጋር አልትሱ' እንደሚል ድንግል ማርያም ፈጥና የምትደርሰው ወይን ላለተባቸው ኀዘንተኞች ብቻ ሳይሆን 'ሚስቶቻቸው በቤታቸው እልፍኝ እንደ ወይን ላፈራችላቸው' ደስተኞችም ነውና የዘካርያስና የኤልሳቤጥን ደስታ ልትካፈል ፈጥና ወጣች፡፡ ከታዳሚው

የተሸሸገውን የቃና ዘገሊላ ጉድለት ዜና አውቃ ለልጇዋ ተናገራ ያስተካከለችው ድንግል ዘመድዋ ኤልሳቤጥ ፈርታ አምስት ወር የሸሸገችውን የደስታ ዜናም አውቃለችና ፈጥና ገሰገሰች፡፡ ሉቃ. ፩፥፲ ፣ ሮሜ ፲፬፥፲፩ ፣ ዮሐ. ፩፥፫ ፣ መዝ. ፻፳፰፥፫

ድንግል ማርያም ለእርስዋ የተደረገላትን ለኤልሳቤጥ ከተደረገው ነገር ጋር አላነጻጸረችም፡፡ 'ኤልሳቤጥ ካረጀች በኋላ መፅነስዋ ምን ይገርማል? እኔ ያለ ወንድ ዘር የፀነስሁ አይደለሁምን? ኤልሳቤጥ የልጅ እናት ልትሆን መብቃትዋስ ምን ይገርማል? እኔ የአምላክ እናት ልሆን አይደለምን?' ብላ ሳትኩራራ የኤልሳቤጥን ታናሽ ደስታ ልትካፈል ተነሣች፡፡ በብርሃናዊ መልአክ 'ደስ ይበልሽ' የተባለችው ድንግል በማግስቱ አንዲትን ሴት 'ደስ ይበልሽ' ልትል ጉዞ መጀመርዋ ምንኛ የሚያስደንቅ ነው? 'ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ' የተባለላት ድንግል ከእርስዋ የምታንሰውን ከሴቶች አንዲቱን ልትጎበኝ መቸኮሏስ ምንኛ ድንቅ ነው?

እውነት ለመናገር ድንግሊቱ ከመልአኩ ገብርኤል የሰማችው ዜና ዓመት ሙሉ ከቤት የማያስወጣ እና እንዲሁ በመደነቅ ባሕር ውስጥ እየዋኘች ልትኖርበት የምትችለው ዜና ነበር፡፡ ሌላ ሰው ቢሆን ለዚህ ክብር መመረጡን ሲያውቅ ደስታው እስኪወጣለት ድረስ ሌላ ሰው ትዝ

አይለውም ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳን ጌታን ከሁለት ነቢያት ጋር ሆኖ ልብሱ ሲያበራ አይቶ 'በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው ! ሦስት ዳስ እንሥራ' ብሎ በታቦር ተራራ መቅረት አሰኝቶት ነበር። እግዚአብሔር አብ ያጸናት ፣ እግዚአብሔር ወልድ ያደረባት ፣ መንፈስ ቅዱስ የጋረዳት ፣ መልአክ ያመሰገናት ድንግል ግን በእርስዋ በተደረገው ድንቅ ነገር ምክንያት ተመስጣ በተበሠረችበት ቤት 'በዚህ መሆን ለእኔ መልካም ነው' ብላ መቅረትን አልፈለገችም።

ለጥቂት ጊዜ እንኳን በናዝሬት ልሰንብት ሳትል 'ፈጥና ወጣች'። ድንግል ማርያም የተነገራት ዜናም ሆነ የፀነሰችውን ፅንስ ነገር ለማንም ሰው ሌላው ቀርቶ ለዮሴፍ እንኳን አልተናገረችም። ብትናገርም ማንም ሰው አያምናትምና የተቀደሰ የፅንስዋን ነገር ተመልሰው ለሚነከሷት ሰዎች ልትነግር አልፈለገችም። ብርቱ የሚሆን እርሱ በእርስዋ ያደረገውን ታላቅ ነገርም ልታምናት የምትችለው በእርሱ የተጎበኘችው ኤልሳቤጥ ናትና ወደ እርስዋ መሔድን መረጠች።

ኤልሳቤጥ በራስዋ አንደበት 'ነቀፌታዬን ከሰው መካከል አስወገደልኝ' ብላ እንደገለጠችው የሊቀ ካህናት ሚስት ሆና መካን በመሆንዋ ምክንያት በሰው ዘንድ በረከት አልባ ተደርጋ ስለምትታይ ብዙ የነቀፌታ ስም ተሠጥቶአት ኖራለች። ምንም እንኳን ባልዋ ዘካርያስ

ሚስቱን በመካንነትዋ እንኳን ለሰው ሊያማት ይቅርና መልአኩ ገብርኤል ሲያበሥረው እንኳን 'ሚስቴ መካን ናት' ሳለማለት 'ሚስቴ አርጅታለች' ማለትን የመረጠና ሚስቱን ለእግዚአብሔር መልአክ እንኳን የማያማ ጻድቅ ሰው ነበረ:: 'የታገሰ ከሚስቱ ይወልዳል' እንዲሉ እግዚአብሔር በእርጅናቸው ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ በሚበልጥ ልጅ የጎበኛቸው ቢሆንም ኤልሳቤጥ ግን በፀነሰች ጊዜ እንኳን ፀንስሁ ብላ ለሰው ለመናገር እንድትፈራ በሚያደርግ የሕሊና ሕመም ውስጥ ነበረች::

ቸርነቱ የማያልቀው እግዚአብሔር ግን ሙት የማስነሣት ምሳሌ ሊሆን በሚችል ተአምራዊ መንገድ ኤልሳቤጥን ካረጀች በኋላ ለመፅነስ ኃይልን ሠጣት:-

> 'እግዚአብሔር ከሱ ዘንድ የምትደረግ ትንሣኤን በኤልሳቤጥ መፅነስ አስረዳ ፤ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ፅንስ የተቋረጠበትን ማሕፀን ለመፅነስና ከዘጠኝ ወራት በኋላ ለመውለድ አበቃው' 'ወከሠተ፡ እግዚአብሔር፡ ምሳሌ፡ ትንሣኤ፡ እንተ፡ ትከውን፡ እምኀቤሁ፡በፀኒሶታ፡ለኤልሳቤጥ፡፡ወረሰየ፡ማሕፀነ፡ ዘሞተ፡እምብዙኅ፡እዝማን፡ዘተፈጸመ፡ቦቱ፡ፅንስ፡፡

ወይሰድ፡ እምድኅረ፡ ተፍጻሜተ፡ ፱ቱ፡ አውራኅ'[239]

እንዳለ የቆጵሮሱ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፡፡

ድንግል ማርያም ይህችን የሐዲስ ኪዳን ሣራ ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ፀንሳ ልታያት ቸኩላ ወጣች፡፡ በሀገራችን ብሂል 'ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል' ይባላል፡፡ ድንግሊቱ ግን ከዓባይ የሚበልጠውን በሆድዋ ይዛ የታናሹን ምንጭ እናት ልትሳለም ፤ ፀሐይን በሆድዋ ይዛ የጨረቃውን እናት ልታይ ፤ ብርሃንን በማሕፀንዋ ይዛ የመብራትን እናት እጅ ልትነሣ ገሰገሰች፡፡ ክብሩ ከፍ ሲል ልቡ በትዕቢት የሚናወጥ ሰው በውስጡ እግዚአብሔር የሌለበት ሰው ነው፡፡ ድንግሊቱ ግን 'እግዚአብሔር በመካከልዋ ነውና አትናወጥም' ስለዚህ አጃቢ ሳትሻ በታላቅ ትሕትና ዘመድዋን ልትጠይቅ በተራሮች መካከል ተጓዘች፡፡ መዝ. ፵፭፥፭

ቅዱስ አምብሮስ 'ማርያም ትሑት ነበረች ፤ እንደተመረጠች ስታውቅ ደግሞ የበለጠ ትሑት ሆነች። ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ወደ ተራራማው ሀገር ተነሣች'[240] ይላል፡፡ ድንግሊቱ የሔደችበት መንገድ ምቹ አልነበረም ፤ ተራራማ ነበረ፡፡ ተራራማ ማለት ብዙ ተራሮች ያሉበት መሆኑን ልብ በሉ፡፡ በዚያ ላይ ዓይነ ከርም ውኃ ገብ የሆነ

---

[239] ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ፶፬፥፱

[240] St. Ambrose, Concerning Virgins, Book II, N & PNF vol.x, Philip Scaff pg 375

ረግረጋማ ሥፍራ እንደመሆኑ መንገዱ ጭቃ ያለው ለጉዞ የማይመች ነው:: ድንግሊቱ ግን እንዲቱን ኤልሳቤጥን ልታይ የሠላሳ ሰዓት መንገድ ብቻዋን ተጓዘች:: ሊቁ 'እይ፡ ይእቲ፡ ዛቲ፡ እንተ፡ ታዕተርኢ፡ እምርኁቅ፡ ከመ፡ ማህቶት፡ ብርሀት፡ ከመ፡ በሐይ፡ ሠናሊኒ፡ ርእያ፡ ሀገር፡ ቅድስት፡ ዕዝራኒ፡ ተናገራ፡ ዳዊት፡ ዘመራ'፡'ያቺ ከሩቅ እንደ መብራት የምትታየው እንደ ፀሐይም የምታበራው ሙሴ ያያት ዕዝራ የተናገረላት ዳዊት የዘመረላት ቅድስት ሀገር አይደለችምን?' ብሎ የተናገረላት የእግዚአብሔር ሀገሩ ድንግል ማርያም ከሩቅ ሀገር ወደ ኤልሳቤጥ እያበራች ፀሐይን በሆድዋ ይዛ ገሰገሰች::

አረጋውያንን የመርዳት ምሳሌ የሆነችው ማርያም አሮጊትዋን ኤልሳቤጥን ልታግዝ ፈጥና ገሰገሰች:: እንደ እኩዮችዋ በመንገድ የምትቆምና የምትዘገይ አልነበረችም:: 'ደናግል ሆይ በየመንገዱ አለመቆምን ከንጽሕት ድንግል ተማሩ' እንዳለ ሊቁ ድንግሊቱ በታላቅ ትጋት ወደ ኤልሳቤጥ ገሰገሰች::

በአንቺ ዘንድ ያለው ደስታ ከኤልሳቤጥ ደስታ የሚበልጥ ሲሆን የምሥራቹን ሳትንቂ ደስታዋን ልትካፈይ ወደ እርስዋ የገሰገስሽው እመቤታችን ሆይ አንቺ የደረሰብሽ ኀዘን ከኀዘናችን እጅግ ቢበልጥም ፤ አንቺ ያሳለፍሽው ስደት ከስደታችን እጅግ ቢልቅም ፤ ዐርብ ዕለት

ያለቀስሽው ልቅሶሽ ከልቅሶአችን ብዙ እጥፍ ቢሆንም የምናዝነውና መከራን የምንታገሠው በአቅማችን ነውና ኀዘናችንን ለመካፈል ወደ እኛም ከመምጣት እንዳትቀሪ:: እርግጥ ነው እኛ እንደ ኤልሳቤጥ ለእንቺ የሚሰግድ ፅንስ በሆዳችን የለም:: በእኛ ዘንድ የተፀነሰው 'ለዐነሱ ወዮላቸው' 'ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች' ተብሎ የተነገረለት የኃጢአት ፅንስ ነው:: እንደ ኤልሳቤጥ በደስታ የሚያስጮኽን ሳይሆን በኀዘን የሚውጠን የበደል ፅንስ ይዘናልና ድንግል ሆይ እኛን ለመርዳት ፍጠኚ:: በሆዳችን የያዝነውን የኃጢአት ፅንስ ነቢዩ ዳዊት እንደተመኘው በሆድሽ ውስጥ በያዝሽው ዓለት ላይ አስከንፈጠፍጠውና ዕረፍት እስክናገኝ ድረስ ጓጉተናልና ወደ ኤልሳቤጥ እንደመጣሽ ወደ እኛም ነዪ::[241] ሉቃ. ፳፩፥፳፫ ፤ ያዕ. ፩፥፲፰ ፤ መዝ. ፻፴፯፥፱ ፤ ፩ቆሮ. ፲፥፬

በተራራማው ሀገር በአስቸጋሪ መንገድ ወደ ኤልሳቤጥ የገሰገስሽው እመቤታችን ሆይ ወደ እኛ ነይ ስንልሽም መንገዱ እንደማይመችሽ እናውቃለን:: 'ተራራው ዝቅ ይበል' ተብሎ የተነገረለት ተራራማው ልባችን በትዕቢት ተራሮች ስለተሞላ ከይሁዳ ተራሮች በላይ ወደ እኛ መምጣት እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ሉቃ. ፫፥፫ ድንጋይ ብቻ የሆነው

241 "ጉዳትን ይፀንሳሉ በደልንም ይወልዳሉ፤ ሆዳቸውም ተንኰልን ያዘጋጃል" "ሕፃናቶቻችንን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው" ፤ 'ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ' ኢዮ. ፲፭፥፴፭ ፤ መዝ. ፻፴፯፥፱ ፤ ፩ቆሮ. ፲፥፬

ጥንሟው ልባችን ለመንገደኛ የማይመች እንደሆነ እናውቃለን:: የኃጢአት ውኃ ገብ የሆነው ሕሊናችንም አጻርጠሽ ለመምጣት የሚያስቸግር የበደል ጭቃ የሚበዛው መሆኑን እናውቃለን:: ሆኖም ወደ ተራራ ልባችን ፡ ወደ ጭቃው ሕይወታችን እንድትመጪ እንሻለንና ከአባቶቻችን ጋር 'ንዒ ኀቤየ' 'ንዒ ርግብየ' ከእናቶቻችን ጋር 'ነይ ነይ እምዬ ማርያም' ማለትን አናቆምም::

ልባችን ምንስ ዓይነት ተራራ ቢሆን ላንቺ ምንሽ ነው? 'ይሆን ተራራ ወደዚያ ሒድ' የምትይበት የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት 'ካመንሽው ብፅዕት' ዘንድ ይጠፋልን? እንደ ዘሩባቤል 'ታላቁ ተራራ ሆይ አንተ ምንድርን ነህ? በማርያም ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ' የምትዪበት የልዑል ኃይል በሆድሽ አይደለምን? ሕይወታችን ምንም እንኳን ቢጨቀይም አንቺ እንደሆንሽ ከነ ልጅሽ በሚሸት በረት ውስጥ እንኳን ለመምጣት አልተጸየፍሽም:: ሕይወታችን እንደ እንስሳ ቢሆንብሽ እንኳን ልጅሽን ከእንስሳት መካከል ለማስተኛት ፈቃድሽ አልነበረምን? ወደ እኛ መምጣትሽን ተስፋ እያደረግን ቅዱሳኑ ሁሉ 'ወደ እኔ ነይ' 'ወደ እኛ ነይ' ብለው የደረሱልሽን ዜማ እያደረስን መምጣትሽን እንጠባበቃለን:: ማቴ. ፲፯፥፳ ፤ ዘካ. ፬፥፯

ድንግል ማርያም ወደ ተራራማው ወደ ይሁዳ ከተማ የተጓዘችው የኤልሳቤጥን መፅነስ ከመልአኩ ስለሰማች የነገሩን እውነትነት ልታጣራ አስባ አልነበረም። ያለ ወንድ ዘር ትወልጃለሽ ስትባል 'ያመነችው ብፅዕት' የአሮጊትዋን መፅነስ ለማመን ተቸግራ ልታጣራ አልመጣችም። ሆኖም መሔድዋ ብዙ መልካም ነገሮችን አስከትሏል። በቅዱስ ገብርኤል እጅ ልሳኑ የተዘጋውን ዘካርያስም ለመጎብኘት የቻለች ሲሆን ምስክር በሦስት እንደሚጸና በመልአክ የተነገረላት እናትነት በኤልሳቤጥና በፅንሱ ምስክርነት ሊጸና ችሏል። ቤተ መቅደስ እንደማደግዋ ለዘካርያስና ኤልሳቤጥ እጅግ ቅርብ ናትና የኤልሳቤጥን የዘመናት ነቀፌታ መወገድ ፣ የዘካርያስም ጸሎት መልስ ማግኘት ዜና ሰምታ መቆየት አልወደደችምና ፈጣንዋ ደመና እንደ አሚናዳብ ሠረገላ በፍጥነት ተጓዘች።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ በአእምሮዬ መጣ። እመቤታችን ልትወልድ ሦስት ወር የቀራትን ዘመድዋን ለመጠየቅ ስትሔድ ምን ይዛላት ሔዳ ይሆን? እንኳን ደስ ያለሽ ለማለት የሚሔድ ሰው ምግብ ፣ መጠጥ ፣ የልጅ ልብስ ወዘተ ሥጦታ በእጁ ሲይዝ እናያለን ፤ ድንግሊቱስ ወደ ዘመድዋ ስትሔድ ምን ይዛ ይሆን? ብዬ ላስብ ጀምሬ በራሴ አፈርኩ። እውነት ድንግል ማርያም በማሕፀንዋ ካለው ሥጦታ

በላይ ለኤልሳቤጥ ምን ይሣላት ልትሔድ ትችላለች? የሕይወት ምግብና የሕይወት መጠጥ ፤ የብርሃን ልብስ ከሆነው ከእርሱ በላይ ምን ሥጦታ ሊመጣ ይችላል? ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ 'የአገልጋዮቹን ቤት ይጎበኝ ዘንድ ንጉሥ ኃይልን በተሞላች ሠረገላ ላይ ተቀመጠ' እንዳለ ከዚህ አምላካዊ ጉብኝት በላይ ምን ሥጦታ አለ?[242]

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ሀገር ባደረገችው ጉዞ እርስዋን አርአያዋና ምሳሌዋ አድርጋ ለምታያት ለማኅደረ መለኮት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ትምህርትን ተወች፡ ፡ እንደሚታወቀው ድንግል ማርያም ለክርስቶስ እናት እንደመሆንዋ ለቤተ ክርስቲያንም እናት ናት፡፡ ለራስ እናት የሆነች ለአካልም እናት ናት፡፡ ድንግል ማርያም በቤተልሔም ለቤተክርስቲያን ራስ ለክርስቶስ እናት ስትሆን በቀራንዮ ደግሞ ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን እናት ሆና ተሠጥታለች፡፡ በዚህ ምክንያት ያለ ወንድ ዘር ምእመናንን በጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ የምትወልደው ቤተ ክርስቲያን ያለ ወንድ ዘር ጌታን የወለደችውን ድንግልን ምሳሌዋ አድርጋ ትከተላታለች፡፡

ድንግል ማርያም ጌታን በማሕፀንዋ ይዛ በከተማ ከመቀመጥ ይልቅ ገጠር ድረስ ተጉዛ ኤልሳቤጥን እንደ ጎበኘቻት ቤተ ክርስቲያንም

242 St. Jacob of Serug, Homily on the Nativity 475

ክርስቶስን ይዛ መቀመጥ ሳይሆን በገጠር በተራራው እየተጓዘች ድምፅዋን የማሰማትና ሰዎችን በእምነት ደስ ብሏቸው እንዲመሰክሩ የማድረግ ሐዋርያዊ ተልእኮ አለባት፡፡[243]

- ## ያልተወለደው ባለ ቅኔ

ድንግል ማርያም ከኤልሳቤጥ ጋር ተገናኙ፡፡ ጌታና ዮሐንስም በማሕፀን እያሉ ተገናኙ፡፡ 'ሳህል፡ወርትዕ፡ተራከባ፤ጽድቅ፡ወሰላም፡ ተሰዓማ' 'ምሕረትና እውነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰላም ተሰማሙ' ብሎ ነቢዩ የዘመረው መዝሙር ጻድቅት ኤልሳቤጥና ሰላማዊት ማርያም በተለዋወጡት ሰላምታና ምሕረት ዮሐንስና እውነት ክርስቶስ በመገናኘታቸው ተፈጸመ፡፡ መዝ. ፹፬፥፲ ትር

ልብ አድርጉ ድንግል ማርያም ጌታን ስለ መፅነስዋ ለኤልሳቤጥ አልነገረቻትም፤ ኤልሳቤጥም ካረጀሁ በኋላ እግዚአብሔር ጎበኘኝ ብላ ለድንግል አልተናገረችም፡፡ 'ጻድቃን ሳይቀጣጠሩ ይገናኛሉ' እንደሚባለው መልእክት ሳይላላኩ ሁለቱም ስለፀነሱት ፅንስ በእግዚአብሔር ተረድተው ነበር፡፡ ኤልሳቤጥም የማርያም መምጣት ተራ የዘመድ ጥየቃ አለመሆኑን በመንፈስ ቅዱስ አውቃ እንደ ዘመድዋ ሳይሆን

---

[243] St. Ambrose, Exposition on the gospel of Luke 2.7

እንደ ጌታዋ እናት ያደረገችላት አቀባበል መገናኘታቸውን የጻድቃን ቀጠሮ ያደርገዋል፡፡

ኤልሳቤጥ የድንግል ማርያምን ሰላምታ ስትሰማ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፡፡ በሆድዋ ያለው ፅንስ በደስታ ዘለለ፡፡ እርስዋም ከባልዋ ዘካርያስ የተቀማው አንደበት የተጨመረላት እስኪመስል ድረስ በታላቅ ድምፅ ጮኻ መናገር ጀመረች፡፡

> 'የማርያም ሰላምታ የካህናትን ተልዕኮ ፈጸመ። ኤልሳቤጥ የጥምቀት ማሕፀን ሆነች ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ከባሕርይው መንፈስ ቅዱስን ሰደደ። ሕፃኑ ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ' ይላል ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፡፡

ድንግሊቱ በዕድሜ ከኤልሳቤጥ ያነሡች መሆንዋን አውቃ በአክብሮት ብትሳለማትም የዕድሜዋ ማነስ ግን በአርጊትዋ ከመመስገን አላገዳትም፡፡

> 'ጽድቅሰ፡ ኢኮነ፡ በቀዲመ፡ ዓመታት፡ ለብፅዕትነ፡ ማርያም፡ኢክልዓ፡ደቂቅናሃ፡ከመ፡ትኩን፡ቡርክተ፡ እምእንስት፡ ወምልእተ፡ ጸጋ፡ ፈድፋደ፡ እም፡ አረጊት፡ ኤልሳቤጥ' 'ጽድቅስ በዕድሜ በመቅደም አይደለም። ብፅዕት ማርያምን ልጅነትዋ ከአርጊትዋ

ኤልሳቤጥ ይልቅ ከሴቶች ሁሉ የተባረከችና ጸጋን የተሞላች ከመሆን አልከለከላትም' ፊልክስዩስ ተስእሉ ፵፯

ኤልሳቤጥ በታላቅ ድምፅ ጮኸች፡፡ ትውልድ ሁሉ ቅድስት ሆይ ለምኚልን እያሉ ወደ እርስዋ ለሚጮኹላት ድንግል ማርያም በታላቅ ድምፅ ጮኻ ተናገረች፡፡ ወደ ማርያም መጮኽም በዚያች ዕለት ተጀመረ፡፡ የመሲሑ የማዳን ተልእኮም በሴት ልጅ ታጅቦ ተጀምሮ በሴት ልጅ ተጠናቀቀ፡፡ ሴት ልጅ ለጌታ መፀነስ በታላቅ ድምፅ ጮኸች ፤ በስቅለቱ አለቀሰች ፤ ትንሣኤውን ደግሞ ሰባኪ ሆነች፡፡

ቅዱስ ገብርኤል 'በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል' ብሎ የተናገረለት መጥምቁ ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ሆኖ ዘለለ፡፡ ፈጣሪው ወደ እርሱ መምጣቱን በመንፈስ ቅዱስ አውቆ በማሕፀን ሰገደ፡፡ 'እምከርሠ፡ እሙ፡ አእመረ፡ እምከርሠ፡ እሙ፡ ሰገደ፡ ወአንፈርዓጸ' እንዳለ ቅዱስ ያሬድ፡፡

ዮሐንስ ፍጡራንን በዓይኑ ሳያይ ፈጣሪውን አወቀ ፤ ዓለም ምን እንደምትመስል ሳያውቅም የዓለምን ጌታ አወቀ፡፡ ለመወለድ ወራት ስለሚቀሩት 'የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ' ብሎ ለመናገር የሚችልበት ገና አንደበት የለውምና ባለበት ሆኖ ዘለለ፡፡

የሰማዩን እንግዳ ወጥቶ እንዳይቀበል ፡ 'ጨማህን ልፈታ አይገባኝም' እንዳይል በማሕፀን ውስጥ ተቆልፎበታልና ከውስጥ ሆኖ የእናቱን ሆድ በር በደስታ አንኳኳ፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዳለ 'ሊነበኘው የመጣው ጌታ ከበር እንዳይቆም የእናቱን ሆድ መምታት ጀመረ'[244]

'ምንም እንኳን በእምነት ወይም በማስተዋል ባይሆንም በደስታ መዝለልን ሕፃናትም ሌላው ቀርቶ እንስሳትም ሲያደርጉት ብዙ ጊዜ አይተናል። በዚህ ሥፍራ የሆነው ግን ያልተለመደና አዲስ ነገር ነው። ምክንያቱም ሁኔታው የተከሰተው በማሕፀን ውስጥ ሲሆን የሰውን ልጅ መድኃኒት የፀነሰችው ማርያም ስትመጣ የሆነ ነገር መሆኑ ነው። ለጌታ እናት የተደረገው አቀባበል መዝለልና ሰላምታ እጅግ ተአምራዊ ነበር። ከታላላት ተአምራትም ውስጥ ሊቆጠር ይገባዋል። ይህን እንዲያደርግ ለሕፃኑ ያስተማረው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው' ይላል የሂፓው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ[245]

የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ወንጌልም

244 St Jacob of serug, Homily on the Nativity 475

245 St Augustine, Letter 187.23

'ወነፈርዓጸ፡ ዮሐንስኒ፡ በከርሠ፡ እሙ፡ ኢኮነ፡ በሥርዓተ፡ ልማድ፡ እንተ፡ ሕፃናት፡ ሥጋዊት፡ ወኢእምነ፡ነፍስ፡እስመ፡ኢኮነ፡ከመ፡ይሰቡ፡ወየሓሊ፡ አላ፡ ባሕቱ፡ እመንፈስ፡ ቅዱስ፡ በከመ፡ አብርሃ፡ ልቦሙ፡ ለሐዋርያት፡ ግብተ፡ ከማሁ፡ ገብረ፡ ምስለ፡ ዮሐንስ፡ በከርሠ፡ እሙ'[246]፡ 'የዮሐንስ በእናቱ ሆድ ውስጥ መዝለል ሥጋዊ በሆነ የሕፃናት ልማድ የሆነ ነገር አይደለም። እውቆ ያመሰግን ዘንድ አይቻለውምና ከነፍሱ የሆነ ነገር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የሐዋርያትን ልብ በድንገት እንዳበራው እንዲሁ በዮሐንስም በእናቱ ማሕፀን ይህን አደረገለት' ይላል፡፡

አክሎም :-

'በእናቱ ሆድ ውስጥ እያለ መንፈስ ቅዱስ እንደሞላበት የሚያስረዳው እርሱ እመቤታችን ማርያም እናቱን ኤልሳቤጥን በጎበኘቻት ጊዜ ተደስቶ ዘለለ። ይህ ዓይነቱ ሀብት በዕብራውያን ዘንድ ከዮሐንስ እና ከኤርምያስ በስተቀር ለማንም አልተሠጠም። በዚህም የተነሣ የዮሐንስ መመረጥ ከበጎ ሥራው በፊት እንደሆነ

246 ትርጓሜ ወንጌል ግእዝ ዳራና ፤ ወንጌል ዘሉቃስ ፤ ዘመርመለ ማርያም ምዕራፍ 1

እናውቃለን፡፡ እርሱ መልካምን ሥራ ያደርግ ዘንድ ተመረጠ' 'ወዘያሴቡ ለ፡ በእንቲአሁ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ተመሰለ፡ እመንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዘ፡ ውእቱ፡ በከርሠ፡ እሙ፡፡ ውእቱሰ፡ ተፈሥሒሓ፡ ወእንፈራዓፀ፡ እመ፡ ሐወጸታ፡ እግዝእትነ፡ ማርያም፡ ለእሙ፡ ኤልሳቤጥ፡፡ ወዛቲሰ፡ ሀብት፡ ኢተውህበት፡ በውስተ፡ ዕብራውያን፡ ዘእንበለ፡ ሉቱ፡ ወለኤርምያስ፡፡ ወእንበይነ፡ ዝንቱ፡ ነአምር፡ከመ፡ተጎርዮተ፡ዮሐንስ፡ቀደመት፡እምግባሩ፡ ሠናይት' ይላል፡፡

በእርግጥም መጥምቁ ዮሐንስ ገና ሳይወለድ በእናቱ ሆድ ጳራቅሊጦስ የተደረገለት ሐዋርያ ነው፡፡ ሐዋርያት 'እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ' ተብለው እንደታዘዙ ዮሐንስም 'በእናትህ ማሕፀን ሳለህ ኃይልን አግኝ' የተባለ የእናቱ ሆድ ውስጥ ጸንቶ የቆየ ደቀ መዝሙር ነበር፡፡ ሉቃ. ፳፬፥፵፱ ሐዋርያት በአንድ ልብ ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ ድንግል ማርያም በመካከላቸው እንደነበረች ዮሐንስ እና እናቱ በመንፈስ በአንድ ልብ ሆነው ባመስገኑባት በዚህች ዕለትም ድንግሊቱ ከመካከላቸው ነበረች፡፡ ሐዋ.፩፥፲፬ ፤ ሉቃ.፩፥፵፩

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ ከመካከላቸው ተነሥቶ ጴጥሮስ በሰበከው ስብከት ልባቸው የተነኩትን ሕዝቡን 'ምን

እናድርግ' እንዳሰኘ ከእናቱ ጋር መንፈስ ቅዱስ የተቀበለው ዮሐንስም ከተወለደ በኋላ በሰበከው ስብከት ሕዝቡን 'ምን እናድርግ?' አሰኝቷል:: ሐዋ.፪፥፴፯ ፤ሉቃ.፫፥፲ መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ የዮሐንስም የጴጥሮስም የስብከታቸው ርእስ 'ንስሓ ግቡ' ነበረ:: ማቴ. ፫፥፩ ፤ሐዋ. ፪፥፴፰

ቅዱስ አቡሊዲስ ዘሮሜ ስለ ዮሐንስ ሲናገር:-

'እርሱም ማርያም ሰላምታ ስታቀርብላት ሰማ ፤ ደስ እያለውም በእናቱ ሆድ ውስጥ ዘለለ ፤ በድንግል ሆድ ውስጥ የዐነሰችውን የእግዚአብሔርን ቃል አይቶአልና' 'ውእቱ፡ ሰምዐ፡ እንዘ፡ ትትአምኃ፡ ማርያም፡ እንፈራዓጸ፡በከርሠ፡እሙ፡እንዘ፡ይትሬሣሕ፡እስመ፡ ደረኢ፡ ዘውስተ፡ ከርሠ፡ ድንግል፡ ዘፀንሰት፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር' ብሏል::[247]

ሌላው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ደግሞ ኤልሳቤጥን በመቃብር ዮሐንስን በመቃብር ውስጥ ባለ ሰው መስሎ እንዲህ ሲል ያራቅቃል:-

'የተቀበረውና የተከደነው ሰው ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ክርስቶስን ባየው በማሕፀን ውስጥ ሆኖ ባየው ጊዜ ፤ በዚያም የኪሩባውያን መላእክትን ያማረ ቅዳሴያቸውን

247 መጽሐፈ ምሥጢር ዘአቡሊዲስ በእንተ ክርስቶስ ወበእንተ ሐሳዌ መሲሕ፤ ብራና /Geez version, Hippolyte de Rome 1982/

በሰማ ጊዜ ከማዕሙ የተነሣ በእግሮቹ ቆሞ በጉልበቱ ሰገደለት። ለሙታን ሕይወትን ይሠጥ ዘንድ ፈጣሪ እንደመጣ አውቋልና ምስጋናን አቀረበ። የምትናገር መቃብሩም እርሱ አስተማሪ ሆኗልና እየዘለለች በእልልታ እንዲህ አለች፡ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ማን ነኝ? ሰላም ባልሽኝ ጊዜ ቃልሽን ስሰማ ፅንሱ በሆዴ ውስጥ በፍጹም ደስታ ዘለለ'

'ብእሲ፡ ቅቡር፡ ወከዱን፡ ሶበ፡ ርእየ፡ በውስተ፡ ማሕፀን፡ ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሰባሔ፡ ለስሙ፡ ወሰምዐ፡ በህየ፡ቅዳሴሆሙ፡ለኪሩባውያን፡መዓርዒር፡እም፡ጣዕመ፡ ዝንቱ፡ ቆመ፡ በእገሪሁ፡ ወሰገደ፡ ሉቱ፡ በብረኪሁ፡ ወአሌዓለ፡ ሰባሔ፡ በአፉሁ፡ እስመ፡ አእመረ፡ ከመ፡ መጽአ፡ ፈጣሪ፡ ደጸጉ፡ ሕይወተ፡ ለምውታን:: ወመቃብሪሁኒ፡ ነባቢት፡ የበበት፡በእንፈርዕጸ፡እስመ፡ኮና፡መምህረ፡እንዘ፡ትብል፡ ምንትኑ፡ አነ፡ ከመ፡ ትምጽኢ፡ ኀቤየ፡ እሙ፡ ለእግዚእየ፡ እስመ፡ ናሁ፡ ሶበ፡ ሰማዕኩ፡ ቃለኪ፡ እንዘ፡ ትትአምኅኒ፡ አንፈርዐጸ፡ እጎል፡ በውስተ፡ ከርስየ፡ በፍሥሓ፡ ወበሐሴት'[248]

ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ሆኖ ለፈጣሪው ሰገደ:: ሰው ሲሰግድ የሚሠራው ቅርጽ በእናቱ ሆድ ያለ ፅንስን ቅርፅ ነውና ዮሐንስ

248 ፊሎሬ ገጽ 162 I Scritti Teologici Ethiopici Dei Secoli XVI-XVII 1958

ሰገደ ማለት የሚያወዛግብ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ 'ዝንቱ፡ ውእቱ፡ ዘሰገደ፡ ሉቱ፡ ዮሐንስ፡ እንዘ፡ ሀሉ፡ ውስተ፡ ከርሠ፡ እሙ''በእናቱ ማሕፀን ሳለ ዮሐንስ የሰገደለት እርሱ ነው' እንዳለ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ[249] (በእናቱ ማሕፀን የሚለው ለጌታም ለዮሐንስም ሆኖ ይነበብ)

ዮሐንስ በጠባቡ የእናቱ ማሕፀን ውስጥ ቢወሰንም ስግደትን ከመጀመርና ለጌታው ከመመስከር ግን አላገደውም፡፡ ለነገሩ ዮሐንስ መንቀሳቀስ በማይችልበት ቦታ ሆኖ መመስከሩ በማሕፀን ያበቃ ሥራው አይደለም፡፡ በእስር ቤትም ሆኖ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌታ ይልክ ነበር፡፡ ወደ ሲኦል ወርዶም የጌታን መምጣት ቀድሞ የሰበከው እርሱ ነበር፡፡

ቅዱስ አቡሊዲስ :-

> 'ውእቱ፡ ካዕበ፡ እቅደመ፡ በጺሐ፡ ከመ፡ ይዜንዎሙ፡ ለእለ፡ውስተ፡ሲኦል፡ወእቅደመ፡ህየኒ፡ሰቢከ፡በእንተ፡ መድኃኒነ' እንዳለ 'ዳግመኛም እርሱ በሲኦል ላሉ ይሰብክላቸው ዘንድ መድረስን አስቀደመ በዚያም ስለ መድኃኒታችን መስበክን አስቀደመ'[250]

ቅዱስ ኤፍሬም :-

249 የሃይማኖተ አበው ንባብና ትርጓሜው ፤ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፴፮፡፰፮

250 መጽሐፈ ምሥጢር ዘአቡሊዲስ በእንተ ክርስቶስ ወበእንተ ሐሳዌ መሲሕ፤ ብሬና /Geez version, Hippolyte de Rome 1962/

'ዮሐንስ የወደፊት ሰብከቱን ለማወጅ በደስታ ዘለለ፤ የመካኒቱ ዕንስ በድንግሊቱ ዕንስ ፊት ሰገደ።የእናቱን አንደበት ሲዋስና ስለ ጌታው ትንቢት ሊናገር ፈለገ' ይላል::[251]

የድንግል ማርያምን ድምፅ ሲሰማ የተሰማውን ደስታ መናገር ባይችልም ፤ 'የተባረክሽ ነሽ' ብሎ ለማመስገን ባይታደልም እናቱ ኤልሳቤጥ ግን ልጅዋን ወክላ 'በደስታ ዘለለ' ብላ ተናገረችለት:: እርሱ ቃል አውጥቶ ማመስገን ባይችልም እናቱ የጌታን እናት አመስግና የልቡን አደረሰችለት:: እርሱ በመዝለልና በመስገድ እናቱ ደግሞ በታላቅ ድምፅ በማመስገን ድንግል ማርያምን ተቀበሏት::

በእናቱ ሆድ ውስጥ ያለ ሕፃን 'ኖር' ብሎ እጅ ነሥቶ የሚቀበላት ክብርት እንግዳ ከድንግል ማርያም በቀር ወዴት አለች? ገና ያልተወለደ ልጅ ድምፅዋን ሰምቶ ከእናቱ ሆድ ለመውጣት ከጓጓላት ማርያም ስም በቀርስ ሴት ልጅ ምጥ ላይ በሆነች ጊዜ ልጁን ልውጣ ልውጣ ለማስኘት ሊጠራ የሚገባው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስም ምን አለ?

ዮሐንስ በእናቱ ሆድ ሳለ የድንግል ማርያምን ድምፅ ስለሰማ ከተወለደ በኋላ የዓለምን ድምፅ መስማት አስጠልቶት ወደ በረሃ ሸሸ::

251 St. Ephrem the Syrian, on Tatian's Diatessaron 1.30

አረጋዊው ስምዖን 'ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ' እንዳለ ዮሐንስም 'ጆሮዎቼ የእናትህን ድምፅ ሰምተዋልና ባሪያህን አሰናብተኝ' ብሎ ለዓለም የሞተ ሆኖ በበረሃ ኖረ፡፡ ድንግሊቱን የሰሙ ሰዎች ልባቸው ወደ ምናኔ ሕይወት ያዘነብላል፡፡ ወደ ምድረ በዳ ሔደው ድንጋይ ተንተርሰው ሲተኙ ደግሞ እንደ ያዕቆብ እግዚአብሔር በላይዋ የተቀመጠባትን መሰላል ያያሉ፡፡

በማሕፀን የነበረውን ዮሐንስን በትኩረት ሳስበው በቤተ ክርስቲያን ያሉ የዋህን ምእመናንን ይመስለኛል፡፡ በድንግል ማርያም ፍቅር ልባቸው እየነደደ ስምዋን ሲሰሙ ፤ ምስጋናዋን ሲያዩ የሚናገሩት የሚጠፋቸው ፤ እመብርሃንን እየወደዱት ቃላት አሳክተው ስለ እርስዋ ለመናገር ግን እንደበት የሚያጥራቸው ምእመናን ይታዩኛል፡፡ በቅኔ ማኅሌቱ ዳር ቆመው ማኅሌት ሲቆም ለጌታና ለእናቱ ምስጋና ሲቀርብ እንደ ዮሐንስ የሚይዙት የሚጨብጡትን አጥተው በደስታ የሚዘልሉ ፤ አንድም ቃል ከአፋቸው ሳይወጣ በሐሴት የሚሰግዱ ብዙ የዋሃን ምእመናን ትዝ ይሉኛል፡፡

ወዳጄ አንተም ድንግሊቱን ለማመስገን እንደ ዮሐንስ መናገር ካቃተህ ብዙ አትጨነቅ፡፡ መንፈስ ቅዱስን የተመላች እናትህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከኤልሳቤጥ በላይ ለድንግሊቱ የሚሆን ብዙ ምስጋና

አላትና ለንግግርህ ሳትጨነቅ በደስታ እየዘለልህ እጅባት፡፡ በእናትህ ቤተ ክርስቲያን ሆድ ውስጥ እንደ ያዕቆብና ኤሳው ለብኩርና እየተጣላህ ሆድዋን መርገጥህን ትተህ እንደ ዮሐንስ ለምስጋናና ስግደት ከተጋህ ቤተ ክርስቲያን ፍቅርህን አይታ ምስጋናን ታስተምርህና እርስዋ 'የጌታዬ እናት እንዴት ወደ እኔ ትመጣለች' እንዳለች አንተም ነፍስ ስታውቅ እንደ ዮሐንስ 'ጌታ ሆይ አንተ እንዴት ወደ እኔ ትመጣለህ?' ብለህ ለመናገር ትበቃለህ፡፡

እዚህ ላይ ለዘጠኝ ወር ዲዳ የነበረው የሊቀ ካህናቱ ዘካርያስን ነገር ሳስበው እጅግ አሳዘነኝ፡፡ ድንግሊቱ በቤታቸው ሦስት ወራትን ስትቆይ ዘካርያስም የማገልገሉ ወራት ተፈጽሞአልና በዚያ ነበረ፡፡ ሆኖም የድንግል ማርያምን ድምፅዋን እንዳይሰማ መልአኩ ጆሮውን ዘግቶታል፡፡ የድንግል ማርያም ድምፅ በኤልሳቤጥ ጆሮ ሲንቆረቆርና ዮሐንስን ሲያዘልል ዘካርያስ ግን ከማየት በቀር አምላክን ፀንሳ የመጣችዋን ድንግል ድምፅ ለመስማት አልቻለም፡፡ ስለ እርስዋ ለመናገር እና ገብርኤል እንደነገረው የዘለለው ሕፃን ዮሐንስ ለጌታ መንገድ የሚያሰናዳ መሆኑን እንዳይናገር እንደበቱ ተይዞአል፡፡ የዘካርያስ ሁኔታ ጊዜያዊም ቢሆን እጅግ ያሳዝናል፡፡ በኋላ ግን ተአምረኛው ልጁ 'የሚጮኽ ሰው ድምፅ' የተባለ ዮሐንስ ሲወለድ ስሙን በመጻፍ ብቻ ልሳኑ ተከፍቶለት

ከድንግሊቱ መዝሙር ጋር የሚመሳሰል ምስጋናን ቢያቀርብም ድንግል ማርያም ቤቱ በከረመችበት ጊዜ ስለእርስዋ ቤቱ እያለች መናገርም ሆነ እርስዋን መስማትም አለመቻሉ ያሳዝናል፡፡

ዘካርያስስ ተይዞ ነው ፤ የበለጠ የሚያሳዝኑት ግን ስለ ድንግል ማርያም መናገርም ፡ መስማትም የማይወድዱ ሰዎች ናቸው፡፡ የድንግል ማርያምን ድምፅ ሰምተው እንደ ዮሐንስ የሚዘልሉትንና በታላቅ ድምፅ የሚጮኹትን በትዝብት እያዩ ምንም ተሳትፎ የሌላቸው ፤ ልሳን እያላቸው ስለ ድንግል ማርያምና ልጅዋ የማይናገሩ ፡ ጆሮ እያላቸው ውዳሴዋን የማይሰሙ ሰዎች ግን መልአክ ሳይቀሥፋቸው ራሳቸውን የቀሠፉ ናቸው ብል እንደ መሳደብ ይሆንብኝ ይሆን? ከሆነስ ይቅር፡፡

## • መዝሙረ ድንግል

‘ለማርያም፡ዘምሩ፡ለማርያም፡ዘምሩ፡
መስቀሉ፡ለወልዳ፡እንዘ፡ትጸውሩ’
‘የልጅዋን መስቀል ተሸክማችሁ
ለማርያም ዘምሩ ለማርያም ዘምሩ’ ቅዱስ ያሬድ

ኤልሳቤጥ ሀገር አቋርጣ ልትጎበኛት ከናዝሬት ድረስ የመጣችውን ድንግል ማርያምን ልትቀበላት ወጣች፡፡ ሆኖም በእርስዋ ላይ የሞላባት

መንፈስ ቅዱስ ወደ እርስዋ የመጣችው ለወትሮ የምታውቃት ዘመድዋ ብላቴናዋ ማርያም እንዳልሆነች ገለጠላት:: መልክዋ ባይለወጥም : ዕድሜዋ ባይጨምርም : ድምፅዋ ባይቀየርም ዛሬ ልትጠይቃት የመጣችው ግን ቀድማ የምታውቃት ማርያም እንዳልሆነች ግን ገና ድምፅዋን ስትሰማ በእርስዋ ሰውነት ላይ በወረደው ጸጋና በማሕፀንዋ በሆነው ነገር አውቃለች:: እንደ ወትሮ አጠራርዋ 'ማርያም ሆይ' ብላ አትጠራት ነገር ክብርዋ አስጨነቃት:: 'ደኅና ነሽ ወይ?' እትላት ነገር ፈጣሪ ያደረባት ቅድስት ደኅንነትዋ እንዴት ይጠየቃል? 'እንደት ውለሽ እንደት አደርሽ?' እንዳትላትም አውሎ የሚያሳድረው ጌታ በሆድዋ ውስጥ ነው::

ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያምን ትጠራበት ስም : ትቀበልበት ሰላምታ አጣች:: ቅዱስ ኤፍሬም:-

> 'ጌታ ሆይ እናትህን ማን ብለን እንጥራት? ድንግል እንዳንላት ፀንሳ አገኘናት : እናት እንዳንላት ድንግል ሆና አየናት። እናትህን መጥራት እንዲህ ካስቸገረ አንተንማ በምን ስም እንጠራሃለን?'

እንዳለው ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያምን ለመጥራት ‘ማን ብዬ ልጥራው ስምሽን’ በሚለው የእናቶቻችን መዝሙር ዓይነት መጠበብ ተጠበበች፡፡ ዘመድን በቤት መቀበልና ማስተናገድ ቀላል ነው ፤ የአምላከን እናት መቀበል ግን ያስጨንቃል፡፡ እግዚአብሔር ከነማደሪያው ፣ ንጉሥ ከነዙፋኑ ቤትዋ የመጣባት ኤልሳቤጥ የገጠማት ይህ ነበር፡፡

ይህን ዓይነቱን ጭንቀት በአንድ ወቅት ንጉሥ ዳዊት ተጨንቆት ነበር፡፡ ወደ ቤትህ የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦት እየመጣ ነው ብለው ሲነግሩት በፍርሃት ተውጦ ‘የእግዚአብሔር ታቦት እንዴት ወደ እኔ ይመጣል?’ ብሎ የሚይዝ የሚጨብጠው ጠፍቶት ነበር፡፡ ታቦቱን ሲያይ ግን ፍርሃቱ ሁሉ ጠፍቶ ሚስቱ ሜልኮል እስከትንቀው ድረስ በታቦቱ ፊት እየዘለለ ዘምሮ ነበር፡፡ ኤልሳቤጥም ድንግሊቱን ስታይ እንደ ዳዊት ‘የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?’ አለች ፤ ዳዊት በታቦቱ ፊት እንደዘለለም በኤልሳቤጥ ሆድ ውስጥ ያለው ዮሐንስ በደስታ ዘለለ፡፡ ከመጀመሪያው የታቦቱ አገልጋይ የአሮን ሚስት ጋር በስም አንድ የሆነችው ኤልሳቤጥ የካህን ሚስት እንደመሆንዋ

የእግዚአብሔርን ታቦት ክብር በሚገባ ታውቃለችና የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንግል ስትመጣ የምታደርገው ጠፋት፡፡[252]

ኤልሳቤጥ ለድንግሊቱ አቀባበል ልታደርግ ስትል የምትናገርበትን ሰላምታ መንፈስ ቅዱስ በአፍዋ አደረገላት፡፡ በታላቅ ድምፅ ጮኻ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' አለች፡፡ ይህ ሰላምታ ለድንግል ማርያም ሲቀርብ ለሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ባበሠራት ጊዜ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ' ብሎአት ነበር፡፡

ኤልሳቤጥ የቅዱስ ገብርኤልን ሰላምታ ደግማ ተናግራ 'የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' ብላ አከለችበት፡፡ ገብርኤል ሳትፀንስ በፊት የተናገረው ነበርና ኤልሳቤጥ ከፀነሰች በኋላ የሚሆን ስንኝ ጨመረችበት፡፡ እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው? ሰውና መላእክት ለድንግል ማርያም ስንኝ እየተቀባበሉ መዝሙር ሲያወጡላት ኑ ተመልከቱ፡፡ የገብርኤልና የኤልሳቤጥ ንግግር መመሳሰል ድንግል ማርያም በሰማይም በምድርም በሰውም በመላእክትም በአንድ ዓይነት ቃል የምትመሰገን መሆንዋን የሚያስረዳ ክስተት ሆነ፡፡

---

[252] ፪ሳሙ. ፮፥፱ እና ሉቃ. ፩፥፵፫ ፤ ፪ሳሙ. ፮፥፲፮ እና ሉቃ. ፩፥፵፩ ፤ ዘጸ. ፮፥፳፫ ሊቃውንት የአሮን ሚስትና የዘካርያስ ሚስት ስማቸው ኤልሳቤጥ መሆኑ ክህነት በኤልሳቤጥ ተጀምሮ በኤልሳቤጥ ለመሻሩ ምልክት ነው፡፡ 'ክህነት ተወጥነት እም ኤልሳቤጥ ብእሲተ አሮን ወምስለ ኤልሳቤጥ ብእሲተ ዘካርያስ ተፈጸመት' እንዲል

በዘወትር የአባታችን ሆይ ጸሎታችን ላይ አባቶቻችን ለድንግል ማርያም ሰላምታ እንድናደርስ ሥርዓት ሠርተዋል፡፡ አባታችን ሆይ ከወንጌል የተገኘ ጸሎት እንደ ሆነ ሁሉ 'እመቤታችን ሆይ' የሚለው ሰላምታም ከእዚያው ከወንጌል ቃል በቃል የተገኘ ጸሎት ነው፡፡ ክርስቶስም 'አባታችን ሆይ በሉ' አለ እንጂ 'ከአባታችን ሆይ በስተቀር ሌላ ነገር እንዳትሉ' አላለም፡፡ እንደ ዳዊት ያሉ ነቢያት የእግዚአብሔር ከተማ ለነበረችው ለኢየሩሳሌም እንደዘመሩ እኛም የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን ለተመረጠችው ድንግል እንዘምራለን፡፡ ኤልሳቤጥ እናትና ልጅን አከታትላ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' ብላ አብራ እንዳመሰገነች እኛም ድንግሊቱን ከማሕፀንዋ ፍሬ ጋር አብረን እናመሰግናታለን፡፡

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ 'ግነዩ፡ለእግዚአብሔር፡ወጸውዑ፡ስሞ፡እንዘ፡ ኢትፈልጡ፡እሞ' 'ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ስሙንም ጥሩ ፤ እናቱን ሳታስቀሩ' እንዳለ ድንግሊቱን ከፍሬዋ ጋር ፤ ዙፋንዋን ከንጉሡ ጋር አብረን እንጠራለን፡፡[253] ከሙሴ ጋር 'ሕዝቡም በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ' ተብሎ እንዲነገርለት የፈቀደ አምላክ 'በአሚነ፡ ዚአሁ፡ ለማርያም፡ ንገኒ' 'እርሱን በማመን ለማርያም እንገዛ' ስንል

253 መልክአ ቍርባን ፤ [illegible] ፤ መልክአ ትስቡ ፪፻፰፱ ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

አይቃወመንም:: ዘጸ. ፲፱፥፴፬ ከዳዊት ጋር 'ስለ እኔም ፤ ስለ ባሪያዬም ስለዳዊት ይህችን ከተማ አድናታለሁ' ብሎ ራሱን ከባሪያው ጋር የጠራ አምላክ 'እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ፤ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ' ብለን ከእናቱ ጋር ስንጠራውስ አይሰማን ይመስላችኋል? ለነገሩ እንኳን ስለ ማርያም 'በእንተ ጸላኢ' 'ስለ ጠላት' ዲያብሎስ ብለህ እርሱን ታሳፍረው ዘንድ ማረን ብንለውም ይሰማናል:: ፪ነገሥ. ፲፱፥፴፬ ይህን በኤልሳቤጥ ላይ ያደረ መንፈስ ቅዱስ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' እስኝቶ አስተምሮናል::

ለእመቤታችን ሰላምታ ለማቅረብ አባቶቻችን 'ምን እንበላት?' ብለው አልተጨነቁም:: ምንም ዓይነት ቅኔ ብናዋጣ ለእመቤታችን ከእግዚአብሔር ከተላከላት ከገብርኤል ሰላምታ በላይ የተሻለ ሰላምታ ልናቀርብላት አንችልም:: ስለዚህ ኤልሳቤጥ እንደተቀበለችው ተውሰን 'በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን' እያልን እናመሰግናታለን:: ድንግል ሆይ የእኛን ምስጋና ለአንቺ ይሆናል ብለን አስቀድመን አናቀርብልሽም ፤ ብርሃናዊው መልአክ ከራማ ድረስ ወርዶ ባቀረበልሽ ሰላምታ ፤ እግዚአብሔር ልኮት በነገረሽ ውብ ምስጋና ግን ምስጋናሽን እንጀምራለን:: 'ገብርኤል 'ደስ ይበልሽ የተባረክሽ ነሽ' ስላላት እኔ ደስ ይበልሽ አልላትም' የሚል ሰው ካለ በዚህ አቋሙ

መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ያመሰገኑትን አምላክ 'ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ' ብሎስ እንዴት ሊያመሰግነው ይችላል?

ኤልሳቤጥ ክርስቶስን 'የድንግል ማርያም ፍሬ' ብላ ጠራችው:: በእርግጥም ያለ ወንድ ዘር በመንፈስ ቅዱስ ግብር የፀነሰችው ልጇ ስለሆነ ክርስቶስ የድንግል ማርያም የማሕፀንዋ ፍሬ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ 'እግዚአብሔር ከሴት የተወለደ ልጁን ላከ' እንዳለ ክርስቶስ ከወንድ ያልተገኘ ከሴት ብቻ የተወለደ ነውና ለድንግሊቱ 'የማሕፀንሽ ፍሬ' መባል ይገባታል::[254] ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ክርስቶስ 'ከወንድና ከሴት ሩካቤ ቢወለድ ኖሮ ብዙ ሰዎች አምላክነቱን በካዱና ሐሰት ነው ባሉ ነበር። ስለዚህ እነሆ ከብቻዋ ከድንግል ተወለደ' ብሏል:: 'ወይእዜሰ፡ናሁ፡ተወልደ፡እምባሕቲታ፡ድንግል፡ማርያም' እንዲል::[255]

እርሱ ከወንድና ከሴት ፈቃድ ቢወለድ ኖሮ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን እኛም በጥምቀት ያለ ዘር ስለመወለዳችን 'ከእግዚአብሐር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ

---

[254] ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ቀን ነው' ኢዮ. ፲፬፡፩ እንደሚል ከሴት የተወለደ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የሰው ልጅን ለመግለጽ የሚጠቀመው ከፊል የሆነ አገላለጽ ቢሆንም በቀጥተኛ ትርጉሙ ግን ከሴት የተወለደ ሊባል የሚገባው ከሴት ብቻ የተወለደው ክርስቶስ ነው::

[255] ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ፰፡፰

አልተወለዱም' የሚለውን የወንጌል ቃል ለመጥቀስ ድፍረት ባጣን ነበር፡ ፡ ሆኖም ክርስቶስ ከአንዲቱ ሴት ብቻ የተወለደ የድንግል ማርያም 'የማሕፀንዋ ፍሬ' ነው፡፡ ገላ. ፬፡፬ ፣ዮሐ. ፩፣፲፫

እንደሚታወቀው ሞት የመጣው ሔዋን በውስጡ ሰይጣን ከሞላበት እባብ ጋር ስለ ዛፍ ፍሬ ንግግር ጀምራ ነበር፡፡ አሁን ግን ሁለተኛዋ ሔዋን ድንግል ማርያም መንፈስ ቅዱስ ከሞላባት ኤልሳቤጥ ጋር ሕይወትን ስለሚሠጥ የማሕፀን ፍሬ መነጋገር ጀመሩ፡፡ ይህ ፍሬ ሞትን የሚያመጣ ሳይሆን ሞትን የሚገድል ፍሬ ነው፡፡ ለሰው ልጆችም ሕይወትን የሚሠጥ የሕይወት ዛፍ ፍሬ ነው፡፡ ይህ ፍሬ ዕርቃንን የሚገልጥ ሳይሆን ለሚበሉት ሁሉ ልብስ የሚሆን ፣ መርገምን የሚያመጣ ሳይሆን በረከትን የሚያድል ፍሬ ነው፡፡ ስለዚህ ኤልሳቤጥ ያልተረገመችውን አዲሲቱን ሔዋን ድንግል ማርያምን ሕይወት ከሚሠጠው ፍሬዋ ጋር ባየቻት ጊዜ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፣ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' አለቻት፡፡

ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ሲሞላባት የድንግል ማርያምን ዘምድና ጨርሶ ዘነጋችው፡፡ አሮጊት እንደመሆንዋ በዕድሜ በምታንሳት ዘመድዋ መጠየቅ የሚገባት መሆንዋንም ከቁጥር አላስገባችውም፡፡ 'የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?' ብላ በድንግሊቱ

ለመንብኝት ያልተገባች መሆንዋን መሰከረች:: መንፈስ ቅዱስ ሲሞላብህ እንተ በድንግል ማርያም ፊት ምን ያህል ትንሽ እንደሆንህ ይገባሃል::

እግዚአብሔር እናቱ እንድትሆን የመረጣትን ንግሥት ክብርዋን ስትረዳ ሰማይና ምድር የእግርዋን እጣቢ እንኳን እንደማያህሉ ትገነዘብና ወደ ትቢያው እንተነትህ መምጣትዋ ያስጨንቅሃል:: ብቻ እንተ 'ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ' ብለህ እንደ ዳዊት ለምነው እንጂ ድንግሊቱ 'እኔ ማነኝ?' አሰኝታ እንደ ኤልሳቤጥ ራስህን ወደ ማወቅ ጸጋ ታደርስሃለች::

አንዳንድ አሳዛኝ ሰው ድንግል ማርያምን 'እንደ እኔ ሰው እኮ ናት' የሚል ምክንያት በማቅረብ ከእርሱ በምንም የማትለይ እንደሆነች ሊከራከርና ክብርዋን ሊያሳንስ ይሞክራል:: ወዳጄ እውነት አንተ እንደ እርስዋ ነህ? ብርሃናዊ መልአክ ከፊትህ ቆሞ አመስግኖህ ያውቃል? እንኳንስ ከሰማይ የተላከ እንግዳ መልአክን ቀርቶ አብሮህ ያለውን ጠባቂ መልአክህንስ አይተኸው ታውቃለህ? እንደ ድንግሊቱ የመላእክትን ዝማሬ ከሆድህ ውስጥ ሰምተሃል? እግዚአብሔር እንኳንስ በአንተ ሊያድር በሕልም እንኳን አነጋግሮህ ያውቃል? እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ እንኳን ሊወለድብህ በቃል ሊያነጋግርህም አልመረጠህም::

በዚህ ትዕቢትህ ከጸናህ ደግሞ ለሰማዩም እፈራልሃለሁ፡፡ በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም ብትባል ስለድንግሊቱ አሁን የተናገርከውን ነገር በፊቱ ደግመህ ትለዋለህ? እግዚአብሔርን 'እናትህ ከእኔ በምንም አትበልጥም' ልትለው ትደፍራለህ? በክንፎቻቸው ተሸፍነው የሚያመሰግኑት በንጽሕናቸው ወንድሞችዋ የተባሉ ኪሩቤልና ሱራፌል እንኳን እንዲህ ሊሏት አይደፍሩም፡፡ ይህ ዓይነቱ አነጋገር እግዚአብሔር 'በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም' ብሎ ሲነግረው እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበትን ጻድቅ ሰው የኢዮብን ክብር ለማሳነስ ምክንያት ከደረደረው ከዲያብሎስ ንግግር ጋር ተመሳሳይ ነውና አስተውለህ ተናገር፡፡ ኢዮ. ፩፥፰

ይህ ዓይነቱ ሰው ድንግል ማርያም በተፈጥሮ ሰው መሆኗን አይቶ እንዲህ የሚል ከሆነ እንደ ኤልሳቤጥ የቅርብ ዘመዱ ብትሆን ኖሮ ምን ሊላት እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሲቀርብህ ግን ድንግል ማርያምን እንኳን በሰውነትዋ ከፍጡራን እንደማትበልጥ እንደ አንዲቱ አድርገህ ልታስባት ይቅርና እንደ ኤልሳቤጥ የቅርብ የሥጋ ዘመድህ ብትሆንም እንኳን 'ወደ እኔ ልትመጪ እኔ ማን ነኝ?' ትላታለህ፡፡

ኤልሳቤጥን 'እንዴት ይሆንልኛል?' ያሰኛት ዝምድናዋ ሳይሆን ድንግል ማርያም የጌታዋ እናት መሆንዋን ማወቋ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ አይገባኝም ያለችውም በጌታ እናት መጎብኘትዋን ነበር:: በእርግጥ ኤልሳቤጥ ምን ዓይነት ሴት ነበረች? 'በአምላክ እናት ለመጎብኘት የማይገባኝ ነኝ' ስትልስ የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዋ ምን ላይ ነበረ? የጌታን እናት የማያስቀርብ የከፋ ኃጢአት ኖሮባት ይሆን?

የሉቃስ ወንጌል ስለ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሲናገር 'ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ' ይላል:: ሉቃ. ፩፥፮ ባልና ሚስቱ ልጅ አልባ ትዳር ውስጥ እየኖሩም እንኳን አንዳች ሳያጉረመርሙ ልብን በሚመረምረው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው ተገኝተዋል:: ጻድቅዋ ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያም ወደ ቤትዋ ስትመጣ ግን 'የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?' አለች:: ቅዱስ ጴጥሮስ 'ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?' እንዳለ ድንግል ማርያምን እንደ ኤልሳቤጥ ያለች ጻድቅ በጭንቅ የምትቀበላት ከሆነ እንደ እኛ ዓይነቱ ዓመፀኛና ኃጢአተኛስ ወዴት ይታይ ዘንድ አለው? ፩ጴጥ. ፬፥፲፰

ቅድስት ኤልሳቤጥ ያለ ነቀፋ ጻድቅ ሆና 'ወደ እኔ ልትመጪ እንዴት ይሆናል?' ካለች ብዙ የሚነቀፍ ሕይወት ያለን እኛ ለድንግል ማርያም ምን እንበላት ይሆን? ጻድቃን እንኳን አንቺን ሲያዩ 'እኔ ማን ነኝ' የሚሉልሽ ድንግል ሆይ አንቺ ወደ እኛ ትመጪ ዘንድ እኛ ማን ነን? በኃጢአት ባሕር ወደ ምንዋኘው ወደ እኛ ትመጪ ዘንድ ቤታችን ምንድርን ነው?

ወደ እኛ ባትመጪም እንኳን ቅር አንሰኝም:: የሰውነትሽ ጥላ ፤ የልብሽ ጫፍ ይበቃናል:: ነቢዩ ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስ በሌለበት በመጎናጸፊያው ብቻ ተአምር እንደሠራ ፤ ጴጥሮስ በጥላው ብቻ ፤ ጳውሎስ በጨርቁ ብቻ ይፈውስ እንደነበረ የአምላክ እናት የሆንሽ አንቺ ጥላሽ ብቻ ቢያርፍብን ፤ የለበስሽው ሰበን ቢዳስሰን ይበቃናል::[256] ፪ነገሥ. ፪፥፲፬ ፤ሐዋ. ፭፥፲፭ ፤ ፲፱፥፲፩ እግርሽ የረገጠውን ሥፍራ ብንስም ይበቃናል::

አባ ጊዮርጊስ እንዳለ :-

[256] ጌታችን 'በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል' ብሎ በገባው ቃል መሠረት ለደቀ መዛሙርቱ እርሱ ካደረገው የተለየ ተአምራትን እንዲያደርጉ ኃይልን ሠጥቶአቸዋል:: ዮሐ. ፲፬፥፲፪ አባ ጊዮርጊስ 'እነሆ የመፈወስ ጸጋ ከጌታ ኢየሱስ ይልቅ በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ በዛ:: እርሱ በመዳሰስ ነው ፤ ጴጥሮስ ግን በጥላው:: ሁለተኛም እርሱ ለብሶት ሳለ የለበሰውን የልብሱን ዘርፍ በመዳሰስ ነው:: ጳውሎስ ግን እርሱ በሌለበት ልብሱን በድውያን ላይ በማስቀመጥ ነው' መጽሐፈ ምሥጢር ፲፮፥፰፫

'ይትርታን የምታሠጥ ብላቴና ጥላዋ ይነካኝ ዘንድ ማን ባደለኝ። የብርሃን ልጅ ወደ ሔደችበት እከተላት ዘንድ ማን ባደለኝ ፤ የእግርዋን ጫማ እስመው ዘንድ ማን በሠጠኝ' 'መኑ፡ እምክፈለኒ፡ ከመ፡ ይሰክፈኒ፡ ጽላሎታ፡ ለወለተ፡ ሣህል፡፡፡ መኑ፡ እምክፈለኒ፡ ከመ፡ እፁር፡ እሣዕኒሃ፡ለወለተ፡ምሕረት'

በእርግጥ ኤልሳቤጥ 'ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆናል?' ብላ በመናገርዋ ለእኛ ኃጢአተኞቹ ለድንግሊቱ እንዴት መዘመር እንዳለብን አስተማረችን፡፡ ኤልሳቤጥን የቃኘ መንፈስ ቅዱስ የቃኛቸው አባቶቻችንም እነ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ አርጋኖን ድንግልን የመሰለ የምስጋና መጽሐፍ ጽፈው ሲጨርሱ 'እመቤቴ ሆይ ይህን የጻፍሁት ደስ የሚያሰኝሽ መስሎኝ ነውና ይቅር በይኝ' የሚሉት ኤልሳቤጥ ቃኝታ በሠጠቻቸው 'እንዴት ይሆንልኛል' የሚል የትሕትና በገና እየዘመሩ ስለሆነ ነው፡፡

ድንግሊቱም ለመምጣት እግርዋን የሚቀናት 'አንቺ ማን ነሽ?' ወደሚሏት ትዕቢተኞች ሳይሆን 'እኔ ማን ነኝ?' ወደሚሉ ትሑታን ነው፡ ፡ ድንግሊቱ ወደ አንተ ልትመጣ እንደማይገባህ ማሰብ ከጀመርህ እንደ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ቀርቦሃል ማለት ነው፡፡ እያቶችዋ በሕልማቸው

በጨረቃ ተመስላ ያዩአት ፤ አባቶቻችንም 'ሶልያና' (ጨረቃ) ብለው የሚጠሯት ድንግል ማርያም ጨረቃ በሌሊት ለሚመላለሱ ሰዎች እንደምታበራ በኃጢአት ጨለማ ለምንዳክር ሁላችን ተስፋችን ናትና 'የጌታዬ እናት ወደ እኔ ልትመጪ እኔ ማን ነኝ?' የሚለው ቃል የኃጢአተኞች መጽናኛ መዝሙራችን ርእስ ነው፡፡ ትሕትናዋን እናወድሳለን ፤ ድንግልናዋን እናደንቃለን ፤ ደሀ ኃጢአተኞች ነንና ርኅራኄዋን ግን አብልጠን መስማት እንወድዳለን፡፡ በእርግጥም ድንግል ማርያም ለኃጢአት ቁስለኞች የምትራራና ቅርባቸው እንደሆነች የብዙዎች ሕይወት ያሳያል፡፡ ሌላው ቢቀር ይህንን መጽሐፍ የጻፍሁት ፅኑዕ ቁስለኛ ታካሚዋ ምስክር ነኝ፡፡

'የጌታዬ እናት' የሚለው መንፈስ ቅዱስ የተሞላ የኤልሳቤጥ ንግግርስ ምንኛ የጣፈጠ ነው? በዕድሜ ልጅዋ ልትሆን የምትችለዋን ዘመድዋን በስምዋ መጥራትን ትታ 'የጌታዬ እናት' ብላ እንድትጠራት ያደረጋትስ እንዴት ያለ መገለጥ ነው? እምላክን ከፀነሰችና ከወለደች በኋላስ ድንግል ማርያምን በቀድሞ ስምዋ 'ማርያም' ብቻ ብሎ ሊጠራት የሚደፍር ማን ነው? የጌታዬ እናት ፤ የፈጣሪዬ እናት ፤ የአምላኬ እናት ፤ የመድኃኒቴ እናት ፤ የብርሃን እናት ፤ የበጉ እናት ፤ የአዶናይ እናት ፤

የሙሽራው እናት ሊላት የማይቻለውስ መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል የራቀው ሰው ነው?

መንፈስ ቅዱስ በኤልሳቤጥ አንደበት የገለጠው 'የጌታዬ እናት' የሚለው የድንግል ማርያም ስም በውስጡ ጥልቅ ነገረ መለኮታዊ አሳብን የያዘ አጠራር ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ስም አጠራራቸው አይታወቅና በየክፍለ ዘመናቱ የተነሡ መናፍቃን የተረቱበት መዶሻ የሆነ ቃል ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ የገለጠው 'ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ' የሚለው የአምላክ ሰው መሆን ምሥጢረ ተዋሕዶ የተፈጸመው በድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ እንደሆነ ይታወቃል:: አምላክና ሰው በማሕፀንዋ ከተዋሐዱ ጀምሮ የሰው ባሕርይ ከመለኮት ባሕርይ የተለየበት ቅጽበት የለምና ድንግል ማርያም የፀነሰችውና የወለደችው አምላክን በመሆኑ የአምላክ እናት መባል ይገባታል::

ቅዱስ ጳውሎስ 'የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ' በማለት ድንግል ማርያም የወለደችው የእግዚአብሔርን ልጅ መሆኑን አረጋግጦአል:: ገላ. ፬፥፬ ሐዋርያው 'የላከው ልጁ ከሴት ተወለደ' በማለት ፈንታ 'ከሴት የተወለደ ልጁን ላከ' ብሎ መናገሩ የላከው ከተወለደ በኋላ ነው ወይ የሚል ጥያቄን ይፈጥራል:: ሆኖም ሐዋርያው በዚህ ንግግሩ በሥጋና በመለኮት መካከል

ከተዋሕዶ በኋላ መቀዳድም እንደሌለና ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት ዘመን ሲቆጠርለት ቅድመ ዓለም ያልነበረ ሥጋም በቅድምና ያለ መሆኑን አሳይቶአል።

እምላክ በሥጋ ከመገለጡ በፊት የተጻፈው 'እግዚአብሔር፡ ፈጠረኒ፡ ወረሰየኒ፡ ሠቅድመ፡ ተግባሩ' 'እግዚአብሔር ለሥራው የመንገዱ መጀመሪያ አድርጎ ፈጠረኝ' የሚለው ብዙዎች የሳቱበት ቃልም ትርጓሜው ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ምሳ. ፰፥፳፫ 'ብኪሰ፡ ወለደኒ፡ ይተረጎም፡ በወሊደ፡ እግዚአብሔር፡ ወብኪሰ፡ ፈጠረኒ፡ በእንተ፡ ትስብእቱ' እንዲል ወለደኝ የሚለው ቃል መለኮቱን ፤ ፈጠረኝ ሲል ደግሞ የተዋሐደው ሥጋን የሚመለከት ቃል ነው።[257]

ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት ሥጋ ያልነበረው ቢሆንም ተዋሕዶ በተፈጸመ ጊዜ ግን የተዋሐደውን ሥጋ ቅድመ ዓለም የነበረ ስላደረገው 'ፈጠረኝ' ብሎ ተናገረ ብለው ሊቃውንት በጉባኤ ድል ነሥተውበታል። ፈጠረኝ ያለበት ምክንያትም በቅዱስ ቄርሎስ ሲብራራ ፦ 'ጥበብ ጌታ ፈጠረኝ ማለትዋ ለራሱ ከድንግል ማርያም ማሕፀን ሥጋን እንደፈጠረ ያስረዳል' 'ወጥበብኒ፡ ዘትብል፡ ፈጠረኒ፡ እግዚእ፡

[257] ቅዱስ ባስልዮስ ፤ ሃይማኖተ አበው ፤ ንባቡና ትርጓሜው ፴፮፥፲፰

ያኢሞር፡ በእንተ፡ ዘፈጠረ፡ ሰርእርሱ፡ ሥጋ፡ እሞክርሠ፡ ማርያም፡ ድንግል'[258]

'እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ ... ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፡ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ' የሚለው ቃል በኒቅያ ጉባኤ ለክርስቶስ ለመለኮቱና ለሥጋው ተዋሕዶ ከተተረጎመና ከዓለም አስቀድሞ ስለ ሥጋው 'ፈጠረኝ' ብሎ ከተናገረ ከእርስዋ ሥጋን የነሣባት ድንግል ማርያምም ከዓለም አስተድሞ በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር እንደነበረ ሊጠቀስ የሚገባው የተሻለ ምስክርም ይኸው ቃል ነው፡፡[259]

ቅዱስ አቡሊዲስ ዘሮሜም :-

'ድንግል ማርያም ሥጋን በወለደችው ጊዜ ቃልን ወልዳዋለች። በዚህ ምክንያት በእውነት የአምላክ እናት ናት' ብሏል፡፡ 'ወሶበኒ፡ወለደቶ፡ማርያም፡ድንግል፡ለሥጋ፡ወለደቶ፡ ለቃል፡፡ወበእንተ፡ዝንቱ፡ወላዲተ፡አምላክ፡ይእቲ፡ዘበአማን'

ድንግል ማርያም የወለደችው አምላክን ባይሆን ኖሮም ስሙን 'አማኑኤል' ብላ መጥራትዋ ትርጉም ባልኖረው ነበር፡፡ ሊቁ ጠርጠሉስ

---

[258] ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፸፮፡፲፩

[259] 'Mariology is a new creation or, perhaps, a new way of looking at creation. For this reason, the idea arose quite logically that Mary was chosen in eternity to be the Mother of God, and She is associated with Wisdom, who says in Proverbs 8:23 : 'Ages ago I was set up, at the first, before the beginning of the earth.' The Oxford Handbook of Mary, Oxford University, UK 2019 Press 2

ለግኖስቲኮች ሲመልስ 'አምላክ በድንግሊቱ በኩል ሰው ሆነ ወይም በድንግሊቱ ውስጥ ሰው ሆነ እንልም ፤ ከንጹሕ ደምዋና ሥጋዋ ነሥቶ ከድንግሊቱ ሰው ሆነ እንላለን እንጂ' ብሏል፡፡[260]

'ወላዲተ አምላክ' (ቴዎቶኮስ) የሚለው የድንግል ማርያም ስምም በቤተ ክርስቲያን ጽድቀ ሃይማኖት ውስጥ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በጉባኤ ኤፌሶን ድጋሚ ተነሥቶ ኤልሳቤጥን ያናገረ መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን እንዳልተለየ ተረጋግጦበታል፡፡ የጉባኤ ኤፌሶን ውሳኔም ስለ ድንግሊቱ እንዲህ ይላል 'የእውነተኛው ብርሃን እናት ሆይ እናከብርሻለን ! ቅድስት ድንግል የአምላክ እናት ሆይ ከፍ ከፍ እናደርግሻለን። መጥቶ ነፍሳችንን ያዳነውን የዓለም መድኃኒት ወልደሽልናልና' (ጉባኤ ኤፌሶን ፤ ጽድቀ ሃይማኖት)

# • ያመነች ብፅዕት

ኤልሳቤጥ ለድንግሊቱ ያቀረበችውን ምስጋና 'የጌታዬ እናት' ብላ ጀምራ 'ያመነች ብፅዕት' ብላ ፈጸመችው፡፡ 'ከጌታ ዘንድ የነገሩሽ ቃል ይፈጸማልና ያመንሽ ብፅዕት ነሽ' 'ወብፅዕት፡እንቲ፡እንተ፡ተአምኒ፡ከመ፡ ይከውን፡ቃለ፡ዘነገሩኪ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር' ሉቃ. ፩፡፵፭

---

[260] Tertullien, De carne Christi,20 /Orthodox Teachings 299/

ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን እምነት አደነቀች፡፡ በእርግጥም ከእመቤታችን የሚበልጥ እምነት ያለው ማነው? የእምነት አርበኞች ሁሉ ከያሉበት ቢመጡ በፊትዋ ሊቆሙ የማይቻላቸው የእምነትን ተራራ ወጥታ የምትጠብቅ ብፅዕት እመቤታችን ናት፡፡ አቤል ከቃየን የሚበልጥ መሥዋዕት በእምነት ለእግዚአብሔር አቀረበ ፣ ድንግሊቱ ግን 'እነሆኝ' ብላ ራስዋን ለእግዚአብሔር አቀረበች፡፡

ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ ፣ ድንግል ግን በእምነትዋ ሞትን የሚገድለውን ወለደች፡፡ ኖኅ ቤተሰቦቹን ለማዳን በእምነት መርከብን አዘጋጀ ፣ ድንግል ማርያም ግን እግዚአብሔር ዓለሙን ያድን ዘንድ ራስዋን መርከብ አድርጋ ሠጠች፡፡ ሣራ ዕድሜዋ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፅነስ ኃይልን በእምነት አገኘች ፤ ድንግል ማርያም ግን ያለ ወንድ ዘር በድንግልና ለመፅነስ በእምነት ኃይልን አገኘች፡፡ አብርሃም ይስሐትን እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣዋል ብሎ በእምነት አቀረበ ድንግል ግን ልጅዋን እግዚአብሔርነቱ ከሞት ያስነሣዋል ብላ ሞቱን በዝምታ አይታለች፡፡

ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት ንጉሥንም አልፈሩም ድንግል ማርያም ግን ልጅዋን በእምነት ሦስት ዓመት ሸሸገችው ሔሮድስንም አልፈራችም፡፡ ሙሴ ባልወለደው ፈርዖን

የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ እየተጠራ እናቱ ዮካብድ ልጅዋን እናትም ገረድም ሆና በእምነት አሳደገችው፡፡ ክርስቶስም ባልወለደው ዮሴፍ የዮሴፍ ልጅ ተብሎ እየተጠራ ድንግል ማርያም እናትም ገረድም ሆና በእምነትዋ አሳደገችው፡፡ 'ተፈሥሒ፡እ፡ማርያም፡እም፡ወአመት' እናትና ገረድ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ' እንዲል፡፡ ሁሉን እንዳንተርክ ጊዜ ያጥርብናል እንጂ የሁሉም በእምነት የተመሰከረላቸው ቅዱሳን የእምነት ተጋድሎ ቢደመር ያመነችውን ብፅዕት እምነት አያህልም፡፡ ዕብ ፲፩፥፬-፴፪

ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያምን 'ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከው የነገሩሽን ቃል ይፈጸማል ብለሽ የምታምኚ ብፅዕት ነሽ' ብላ አደነቀቻት፡፡ የኤልሳቤጥ ባል ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መጥቶ የነገረውን ቃል አላምን ብሎ 'ቃሌን ስላላመንህ ዲዳ ትሆናለህ' ተብሎ ተረግሞ ዲዳና ደንቆሮ ሆኖ በቤት ተቀምጦአል፡፡ ስለዚህ አለማመን የሚያስከፍለውን ዋጋ በባልዋ ያየችው ኤልሳቤጥ የድንግሊቱን እምነት አደነቀች፡፡ ዘካርያስ አላምንም ያለው ሚስትህ ካረጀች በኋላ ትፀንሳለች ሲባል ነበረ፡፡ ድንግል ማርያም ግን ታይቶ ተሰምቶ በማያውቅ ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ ትፀንሻለሽ ተብላ ያመነች ብፅዕት ናት፡፡

ድንግል ማርያም ያመነችው ለማመን ቀላል የሆነ ነገር
አልነበረም:: አምላክ ሰው ይሆናል ብሎ ማመን የመጀመሪያው ፈተ
ነው:: እንኳንስ ገና ሳይፈጸም ከተፈጸመም በኋላ ለማመ
የሚቸግራቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: ስለዚህ አምላክ ሰው ሆኖ ይገለጣል
ብላ መቀበልዋ የመጀመሪያው እምነትዋ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ሰው
የሚሆነውን አምላክ አንቺ ትወልጂዋለሽ ስትባል መቀበልዋ ሲሆን ከሁሉ
ከባዱ ደግሞ ያለ ወንድ ዘር በድንግልናሽ ሳለሽ ትወልጂዋለሽ ስትባል
ማመንዋ ነው:: እግዚአብሔር ምንም ነገርን በማንም ሰው ላይ ለማድረግ
የሚሳነው ነገር ባይኖርም ያንን ነገር ለማከናወን ግን እምነትን ከሰው
ዘንድ ይፈልጋል:: 'ብርቱ የሚሆን ታላት ሥራን' ለድንግሊቱ
እንዲያደርግም ብርቱ የሆነ እምነት በእርስዋ ዘንድ ተገኝቶ ነበር::

ካለመኖር ወደ መኖር (እምኀበ፡አልቦ፡ኀበ፡ቦ) ፡ ከሌለ ወዳለ
ነገር (እምኀበ፡ ኢምንት፡ ኀበ፡ ምንት) ማምጣት የሚቻለው ልዑል
እግዚአብሔር አንድን ነገር ያለ አንዳች መነሻ ሊያደርግ ይቻለዋል::
'አንበለ፡ እሳት፡ አንደደ፡ ወዘአንበለ፡ ማይ፡ አብረደ' እንዲል ያለ እሳት
ማንደድ ፡ ያለ ውኃ ማብረድ ፡ ያለ ብዕር መጻፍ ፡ ያለ ቀስት መንደፍ
ይችላል:: ድንግሊቱን ያለ ዘር መውለድ እንድትችል እንዳደረገ
በሕይወትህ ውስጥ ያለ እግር እንድትሔድ ፡ ያለ ክንፍ እንድትበርር ፡

ያለ ድምፅ እንድትሎኝ ፣ ያለ ሥልጣን እንድታዝዝ ፣ ያለ ምግ እንድትጠግብ ፣ ያለ ውኃ እንድትረካ ማድረግ ይቻለዋል፡፡ እር አንዳች ነገርን ያለ አንዳች ነገር እንዲያደርግልህ ግን እንደ ድንግሊ 'እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ብለህ በእምነት መቀበል አለብህ፡፡ ድንግሊ ግን ድንቅን ነገር በእርስዋ እንዲሠራባት 'ከጌታ ዘንድ የነገሯትን ያመነች ብፅዕት ነች'

እመቤታችን ጌታን የፀነሰችበትና የወለደችበት ሁኔታም ትልቅ እምነት የሚጠይቅ ነበር፡፡ በፀነሰችበት ወራት በሆድዋ ውስጥ ተወስኖ ያለው በዓለም ሁሉ የሞላው አምላክ መሆኑን ማሰብ ለድንግሊቱ እጅግ ከባድ ሊሆን የሚችል ነገር ነበር፡፡ በወለደችው ጊዜም የወለደችው ዓለም ሳይፈጠር የነበረውን አምላክ መሆኑን ማመንስ ምንኛ ከባድ ነው፣ ከእጠንብዋ ሳለ በሁሉ የሞላውን አምላክ እያየችው ቢሆንም ድንግሊቱ መርምራ ልትደርስበት አልቻለችም፡፡ 'በሆዷ የተሸከመችው ማርያምም እየሁት ልረዳው አልቻልሁም አለች' 'ማርያምኒ፡ትቤ፡እንተ፡ፆረቶ፡በከርሣ፡ርኢክዎ፡ወስእንኩ፡ጠይቆቶ'[261] እንዲል፡፡

---

[261] ድርሳነ ሚካኤል ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፣ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ዘመስከረም ፲፪ ፣ ቅዱስ ያሬድ ፣ ርቶዐ ሃይማኖት

የታቀፈችው አፉን ያልፈታ የማይናገር ሕፃን ቢሆንም እርሱ ግን በቃልነቱ ዓለምን የፈጠረ ነው፡፡ 'ማርያም መናገር የማይችል ዝምተኛ ሕፃንን አቀፈች ፤ በእርሱ ውስጥ ግን የዓለም ሁሉ ቋንቋ ተሸሽጎ ነበር'[262] 'እናቱ ብትሆንም ስለ እርሱ በእርግጠኝነት ሁሉን አታውቅም ነበር። በማሕፀንዋ የፀነሰችው ካልመረመረችው ማን ሊመረምረው ይችላል'[263] ይላል ማር ኤፍሬም

'እንደበትሽ ያመሰገነ እንጂ ያልተመራመረ ፤ አፍሽም የዘመረ እንጂ ያልተከራከረ ድንግል ሆይ የተባረክሽ ነሽ' ካላትም በኋላ ቅዱስ ኤፍሬም በድንግሊቱ ቦታ ሆኖ እንዲህ ሲል ይቀኛል :-

> 'ድንግሊቱን እፀንስ ዘንድ የሠጠኝ ማን ነው? ይህን አንድ ሲሆን የበዛ ፤ ታናሽ ሲሆን ታላቅ የሆነ ፤ ከእኔ ጋር ሲሆን በሁሉ የሞላ ሕፃን የሠጠኝ ማን ነው?
>
> በእኔ [ማሕፀን] ውስጥ እያለህ ከእኔም ውጪ በሁሉ ቦታ ነበርህ ፤ በወለድሁህ ጊዜም ረቂቅ አምላክነትነህም ከእኔ ውስጥ አልወጣም። በእኔ ውስጥ ነህ ፤ ከእኔም ውጪ ነህ! ይህ ነገር ለእኔ ለእናትህ ያስደነቀኛል።

[262] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity, Desert Fathers Series Vol. 5 III
[263] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity, Desert Fathers Series Vol. 5 HymnXVIII

የሚታየው ሰውነህን በፊቴ ባየሁ ጊዜ የማይታየው እምላክነትህን በሕሊናዬ አየዋለሁ። ቅዱስ ሆይ በሚታየው ሰውነትህ ውስጥ አዳምን አየዋለሁ ፡ በማይታየው መለኮትህ ውስጥ ደግሞ በአንተ ሕልው ሆኖ የሚኖረውን እግዚአብሔር አብን አየዋለሁ'

ድንግል ማርያም በሆድዋ ውስጥ ፅንስ ሆኖ የሚንቀሳቀሰው ከአምላካዊ ዙፋኑ ያልተለየ ፈጣሪ መሆኑንና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በእርስዋ ውስጥ ሳለ ዓለምን እያስተዳደረ መሆኑን ማመንዋ ትልቅ እምነት የሚጠይቅ ነበር፡፡ ይህ በእርግጥ ከሕሊና በላይ ነው፡፡ 'ሁሉን የሚገዛው ኃይል እንዴት በማሕፀን ውስጥ አደረ? በማሕፀንዋ ውስጥ ሳለ የዓለም ልጓም በእጁ ተይዞ ነበር። እናቱም ፈቃዱን ለመፈጸም ትጠባበቅ ነበር። ፀሐይ ወደ ማሕፀንዋ ገባ። ከእናቱ የቀደመ ሕፃንን ያየ ማን ነው?' ይላል ቅዱስ ኤፍሬም፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊም እንዲህ ሲል ያብራራል፡-

'ወእምነት፡ ዘእንበለ፡ ተኀሥሦ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ቃለ፡ አብ፡ እምላክ፡ ቃል፡ ሥጋው፡ ዘውእቱ፡ እመለኮተ፡ አብ፡ ሥጋው፡ በፈቃዱ፡ ወኢይትዌለጥ፡ እምሕላዌ፡ ዕበየ፡ መለኮቱ፡ ዘውእቱ፡ አሐዱ፡ ምስለ፡ አብ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ' 'ድንግል ወንድ ሳታውቅ የፀነሰችውን ሊዋሐደው በፈጠረው ሥጋ ወለደችው

> ፤ እርሱ ከአብ ባሕርይ የተገኘና በፈቃዱ ሰው የሆነ እንደሆነ ከጌትነቱ ባሕርይ የማይለወጥ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሆነ እርሱ እንደሆነ ያለ ጥርጥር አመነች'[264]

ከወለደችውም በኋላ ፈጣሪዋን እንደ ሕፃን ሲያለቅስ ስታይ እምነትዋ አለመናወጹ ምንኛ ድንቅ ነው? የአምላክዋን ዕንባ እየጠረገች 'ዕንባዎችን ሁሉ ከዓይን ላይ ያብሳል' የተባለለት የሁላችን የዕንባችን ሰፍነግ የሆነ ጌታ እንደሆነ አምናለች፡፡ በጨርቅ ጠቅልላ እያለበሰችው ተራሮችና ሜዳዎችን በአበባ የሚያለብሳቸው እርሱ እንደሆነ አልተጠራጠረችም፡፡

> 'ከማርያም ወተትን ሲጠባ የፍጥረቱን ጥም የሚያረካው ግን እርሱ ነበር። እርሱ በማርያም እቅፍ ውስጥ ቢተኛም ፍጥረታት ሁሉ ደግሞ በእርሱ እቅፍ ውስጥ ነበሩ.'[265]

ድንግሊቱ ወተትን እንደ ሕፃናት በለመናት ጊዜም ከድንግልናዊ ወተትዋ ስታጠባው የፍጥረቱ መጋቢ መሆኑን አለመጠራጠርዋ እንዴት ይደንቃል?

---

[264] ሃይማኖተ አበው ፤ ዘቅዱስ አትናቴዎስ 28፡19-20

[265] St. Ephrem the Syrian, Desert Fathers series, Vol. 5 Hymns on the Nativity, III

ቅዱስ ኤፍሬም እንዲህ ይላል :-

አንተ ምንጭ ሆይ ለአንተ ለማጠጣት የጡቶችን ምንጭ እንዴት ልከፍታቸው ይቻለኛል? ሁሉን ከገበታህ የምትመግብ ሆይ እኔ አንተን ልመግብህ እንዴት ይቻለኛል? የክብርን ነጸብራቅ የተጎናፀፍከው ሆይ እንደምን በጨርቅ ልጠቀልልህ እችላለሁ?

የልደት መዝሙራቱን 'አሹሩሩ' (lullaby) ብሎ የሰየመው ቅዱስ ኤፍሬም ድንግሊቱ የሚያለቅስ ልጅዋን በምን ዓይነት እሹሩሩታ ምን ብላ ልታባብለው ትችል እንደነበር እያሰበ በመደነቅ ይዘምራል፡፡

'እርስዋ ለልጅዋ የዘመረችውን የማባበል ዝማሬ የሚመስል ዝማሬ የለም። ከእርስዋ ዝማሬውን ተውሳ ልጅዋን ልታባብል የምትችል እናትስ ማን ናት? ልጅዋ ፈጣሪ የሆነ ሌላ እናትስ ከየት ትገኛለች?' በማለት ይጀምራል፡፡

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ መላእክት የሚዘምሩለትን አምላክ ለማባበል በእቅፍዋ የያዘችው ድንግል ማርያምን ሁኔታ ወደር እንደሌለውም እንዲህ ሲል ያራቅቃል፡-

'የድንግል ማርያምን የማባበል ቃል የሚመስል እሹሩሩ የለም። የእስራኤልን ልጆች ያባበሉ የልያና የራሔል

የላባና የዘለፋ የማባበል ቃል ምድራዊ አሹሩሩ ነው።
ድንግል ማርያም ያቀፈችው ሕፃን ሰማያዊ ነውና
እርሱን እንዴት ባለ ዝማሬ አባብላ ታስተኛው ይሆን?"
እያለ ይጨነቃል፡ ፡

የድንግሊቱን እንደበት እንደበት አድርጎም እንዲህ ሲል ይቀኛል :-

'ልጄ ሆይ አባትህ ዳዊት የመዝሙሩን ሀብት በመርከብ
ጭኖ ወደ እኔ ወደብ አሁን ያራግፍ። እርሱ የሳባ
ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ ብሎ ዘምሮልህ ነበር ፤
እኔ ግን እጅ መንሻን ሲያቀርቡልህ ያየሁ ነኝ'
'ለአንተ እንዴት ያለ የማባበል ዜማን ላዜምልህ
እችላለሁ? እንደማንኛውም ሕፃን ለአንተ አሹሩሩ ብዬ
እንዳልዘምርልህ እንደ ማንኛውም ሰው ተራ ልደትን
የተወለድህ አይደለህም። ፅንሰትህ አዲስ ነው ፤
ልደትህም ተአምር ነው። በመንፈስ ካልሆነ ለአንተ
ሊዘምር የሚችል ማን ነው?' ይላል፡ ፡

በሌላ መዝሙሩም ላይ ሶርያዊው ወርቅ እንዲህ ይላል:-

'ታናሺቱ ርግብ ጥንታዊውን ንሥር ተሸከመችው። ታቅፋውም
እንዲህ ስትል ዘመረችለት ፦

በታናሽ ጎጆ ውስጥ ያለኸው ባለጠጋ ልጅ ሆይ ጥዑም በገና የሆንኸው አንተ እንደ ሕፃን ዝም ብለህ ልታድግ ወደድህ። ንዝረቱ ኪሩቤልን በሚያንቀሳትስ በገና እንድዘምርልህ ፍቀድልኝ።

ልጅ ሆይ ቤትህ ከሁሉ በላይ ከፍ ያለ ነው። እኔን ቤትህ ልታደርገኝ ግን ወደድህ። ሰማይ ክብርህን ይሸከም ዘንድ አይቻለውም። ከፍጥረታት ሁሉ ምስኪንዋ እኔ ግን ተሸክሜሃለሁ። ሕዝቅኤል ይምጣና በጉልበቴ ላይ ሆነህ ይይህ። መጥቶ ይስገድልህና በኪሩቤል ሠረገላ ላይ ከፍ ከፍ ብለህ ያየህ አንተን እንደሆነ ይመስክር'[266]

ድንግል ማርያም ልጅዋን የምትጠራበት የሚበቃ ስም አጥታ ስትጨነቅም የኤፍሬጥስ ወንዝ በብዕሩ ያያታል፡-

> 'ማን ብዬ ብጠራህ ይሻለኛል? ከእኛ ጋር የነበርህ ! ለእኛም እንግዳ የሆንህ ነህ። ልጅ ብዬ ልጥራህ? ወንድሜ ልበልህ? ሙሽራዬስ ብዬ ልጥራህ? ጌታዬስ ልበልህ? ከዳዊት ቤት እንደመሆኔ እኅትህ ነኝ። ስለዐነሰሁህ እናትህ ነኝ ! ስለ ንጽሕናህ ሙሽራህ ነኝ ! መድኃኒቴ ነህና ባሪያህና ልጅህ ነኝ' ይላል፡፡

እመቤታችን ጌታን ባሳደገችበት ወቅት ሁሉ ትልቅ እምነት የሚሻ ውጣ ውረድን አሳልፋለች፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ 'ሕፃኑንና

[266] St. Ephrem the Syrian , Harp of Spirit, Sebastian Broock

እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ' ባለው ጊዜ ድንግሊቱ እንድትሰደድ የተነገራት ቃል በራሱ እምነትንና መታዘዝን የሚፈታተን ነገር ነበር፡፡ 'የተነገረኝ አምላክን እንድወልድ እንጂ ከተወለድሁበት ሀገር እንድሰደድ አልነበረም። ከሔሮድስ ለመሸሽ ግብጽ ድረስ መሔድ ለምን አስፈለገ?' ብላ ልትጠይቅ ትችል ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች 'እነሆኝ' ብለው እግዚአብሔርን ይቀበሉትና መከራ ሲመጣባቸው 'በዙፋንህ የለህም' እስከማለት ይደርሳሉ፡፡ ድንግሊቱ ግን መከራ እምነትዋን አላናወጸውም፡፡ ልጅዋን ከሔሮድስ ይዛው ስትሸሽ እርሱ ኃይል አምላክ መሆኑን አልተጠራጠረችም፡፡

ለሰብአ ሰገል 'እንድሰግድለት መጥታችሁ ንገሩኝ' ብሎ አሳቢ መስሎ ሐሰትን የተናገረውና የሰይጣን መሣሪያ የሆነው የሐዲስ ኪዳኑ አባብ ሔሮድስ ሠራዊቱን 'ከኋላዋ እንደወንዝ ሲያፈስስባት' እይታ እምነትዋ አልተናወጸም፡፡ ማቴ. ፪፥፲፫ ፤ ራእ. ፲፪፥፲፭ 'እስራኤልን በኤርትራ ባሕር ዳርቻ ፈርዖን ከነሠራዊቱ እንዳይደርስባቸው የደመና ዐምድ አቁመህ የከለልካቸው አንተ አይደለህምን? ስደት ከምወጣ ሔሮድስ እንዳይደርስብኝ ዙሪያዬን በእሳትና በደመና የማታጥርልኝ ለምንድርን ነው?' አላለችም፡፡ ስደት ወጥታ በግብጽ በረሃ እንደ ወፍ ስትንከራተት የፀሐዩ ሙቀት ፤ የአሸዋው ግለት ፤ ረሃቡና ጥሙ

ሲጸናባት ፡ ጌታን አንድ ጊዜ በጀርባዋ ፡ አንድ ጊዜ በጎንዋ በማዘል በደከመች ጊዜ ‘አምላክ፣ መሆንህ ለዚህ ቀን ካልሆነ ለመቼ ነው? ለምን ተአምርህን አትገልጥም? እንዲህ ከምንደክም በአምላካዊ ኃይልህ በነፋስ ተጭነን ፡ በደመና ተሳፍረን ፡ በእሳት ሠረገላ እየጋለብን ለምን ቶሎ አንደርስም? በዐሐይ ግለት ከምንቃጠል በደመና የማትጋርደን ስለምንድርን ነው? እስራኤልን መና አውርደህ የመገብህ ሆይ መና ከሰማይ አውርድ እንጂ ፡ በጥም ከምንሠቃይ ከዓለት ላይ ውኃን አታፈልቅምን?’ ብላ ፈጣሪዋን አልተፈታተነችም፡፡ ‘ጌታ ራሱ ምልክት ይሠጣችኋል ! እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች’ እንደሚል ከታቀፈችው ሕፃን የበለጠ ሌላ ምልክትን አልፈለገችም፡፡ ኢሳ. ፯፡፲፬

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ :-

> `ወሶበ፡ወለደቶ፡በቀበ፡ድንግልናሃ፡ዘእንበለ፡ርኩስ፡፡
> ከመ፡በፅንሳ፡መንክር፡ትኩን፡መራሂተ፡ለሃይማኖት፡
> ዐባይ’ ‘ድንት በሆነ ፅንሰዋ ለታላቁ ሃይማኖት መሪ ትሆን
> ዘንድ ከወለደችም በኋላ ያለመለወጥ በድንግልና አጸናት’

እንዳለ ድንግል ማርያም ለብዙዎች ማመን ምክንያት የሆነ ታላቅ እምነት ያላት መራሂተ ሃይማኖት (የሃይማኖት መሪ) ናት፡፡[267]

---

[267] ሃይማኖተ አበው ፤ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፷፮፥፴፪

እርስዋ አምላክ ሰው ይሆናል ፡ ከእኔ በድንግልና ይወለዳል ብላ ማመን መቻልዋ በስሙ ለምናምን ሁሉ የእምነታችን መሠረት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት 'ወደ ማርያም ከመጡት ... ብዙዎች በእርሱ አመኑ' ተብሎ ከተጻፈላት ከአልዓዛር እኅት ማርያም በላይ የእመቤታችን እምነት ለክርስቲያኖች ሁሉ መሠረተ ሃይማኖት ነው፡፡ ዮሐ. ፲፩፡፵፭

'በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል' ተብሎ የተነገረላቸው የእምነታችን አእማዶች የሆኑት የጌታችን ደቀ መዛሙርትም እምነታቸው ባመነችው ብፅዕት ምክንያት የመጣ እንደነበረ አስተውለነው ይሆን? ኤፌ. ፪፡፳

ደቀ መዛሙርቱ በጌታ ስለማመናቸው የተጻፈው የመጀመሪያው ቃል 'ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ' የሚል ነው፡፡ ዮሐ. ፪፡፲፩ በዚህ ሰርግ ቤት ድንግል ማርያም የነበረች ቢሆንም 'ማርያምም በእርሱ አመነች' የሚል ቃል አልተጻፈም፡፡ የቃናውን ተአምር ተከትሎ ያመኑት አዳዲስ አማኞች የሰርግ ቤቱ ንዑስ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ፡፡ ድንግል ማርያም ግን በልጅዋ ሁሉን ቻይነት ከማንም ቀድማ ስለምታምን ውኃ ወይን እስኪሆን ማየት አላስፈለጋትም፡፡

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንዳለ ፦

'ወባሕቱ፡አእመረት፡ከመ፡በጽላሉተ፡እብ፡ፀንሰቶ፡
ወበኃይለ፡ ሬቡሬ፡ ወለደቶ፡ ወለአለቶ፡ በእንተ፡
ወይን' 'ነገር ግን በአብ ጥላ ፈቃድ እንደ
ፀነሰችው በልዑል ኃይልም እንደወለደችው
ታውቃለችና ስለ ወይን ማለደችው'[268]

ድንግሊቱ ክርስቶስ ውኃን ወይን ከማድረጉ በፊት ድንግልናዋን ሳይነካ እናት ሲያደርጋት አይታለች፡፡ ስለዚህ አምላክ ሰው ሲሆን ያየች ድንግል ውኃ ወይን ሲሆን አይታ ልትደነቅና እንደ አዲስ ልታምን አትችልም፡፡

እመቤታችንን አምላክን ለመውለድ ክብር ያበቃት 'ይሁንልኝ' ብላ የተቀበለችበት እምነትዋ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ የምናመሰግናትም ጌታን ፀንሳ ከመውለድዋ በላይ ለዚያ ክብር ላበቃት እምነትዋም ነው፡፡ 'መቼም አንድ ጊዜ ወልዳዋለችና እናመስግናት' ብሎ የሚያስብ ሰው እመቤታችን አምላክ ባደረበት ሥጋዋ ብቻ ሳይሆን እምነትን በተሞላች ነፍስዋ ጌታን ያከበረች መሆንዋን ያላወቀ ሰው ነው፡፡

[268] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፡ መጽሐፈ ምሥጢር ፡ ምንባብ ዘቃና ዘገሊላ ፡ ቃና ዘገሊላ ፡ ሄኖክ ኃይሌ 2007 ዓ.ም

## • ብዕሰትና ብፁዓን

አንዲት ሴት ወደ ጌታችን መጥታ ፦

'የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው' አለችው። ጌታችን 'አዎን፤ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው አለ' ሉቃ. ፲፩፡፳፯

ሴቲቱ ለጌታ እናት ያቀረበችውን ምስጋና ክርስቶስ በመጀመሪያ 'አዎን' ብሎ ተቀበለው:: 'ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን' ብሎ የተናገረው ጌታ 'አዎን' ብሎ መናገሩ ትልቅ የማጽናት ንግግር ነው:: ማቴ. ፭፡፴፯ ሆኖም ለእናቱ ማሕፀንና ጡቶች የቀረበውን የወንጌል መልከዓ ማርያም ምስጋና በአዎንታ ቢቀበለውም የሚበልጠው ነገር ግን ምን እንደሆነ ግን ጨምሮ ተናገረ::

ሴቲቱ ድንግል ማርያምን ያመሰገነቻት ጌታን በማሕፀንዋ መሸከምዋ እና ጡቶችዋን በማጥባትዋ ብቻ ነበር:: እርግጥ ድንግሊቱ ለፀነሰችበት ማሕፀን እና ፈጣሪዋን ለመገበችባቸው ጡቶችዋ ምስጋና እናቀርባለን:: ሆኖም ጌታን ለመፅነስና ለማጥባት ያበቃት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተነገራትን ቃል ሰምታ ማመንዋና በልብዋ መጠበቅዋ ነው::

ኤልሳቤጥ ለድንግል ምስጋና ስታቀርብም ጌታን ስለፀነሰች ከማመስገን ይልቅ 'ከጌታ የነገሩሽ ቃል ይፈጸማልና ያመንሽ ብፅዕት ነሽ' ያለችውም እመቤታችን ለመውለድ የሚያበቃት እምነትዋ ቃላት በመሆኑ ነው፡፡

> የሂፖው ሊቀ ጳጳስ አውግስጢኖስ 'ማርያም ቡርክት የሆነችው ጌታን ከመፀነስዋ በፊት በእርሱ በማመንዋ ነበር፡፡ 'የተሸከመችህ ማሕፀን የተመሰገነች ናት' ሲባልም 'ይልቅስ ብፁዓን ቃሌን ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው' ስለዚህ ነው፡፡ በሥጋ ዘመዶቹ የሆኑትና በእርሱ ያላመኑት ሰዎች ጥቅማቸው ምንድርን ነው? ድንግል ማርያም በልብዋ በእምነት ባትፀንሰው ኖሮም በሥጋዋ ለመፅነስ ባልበቃች ነበር' ብሏል፡፡[269]

ለክርስቲያን ሁሉ ተስፋውም ይህ ነው፡፡ መልአኩ ሳትፀንስ በፊት 'ጌታ ከአንቺ ጋር ነው' እንዳላት ድንግል ማርያም ጌታን በማሕፀንዋ ለመፅነስ ያበቃት አስቀድሞ በእምነት በልብዋ ፀንሳው ስለነበረ ነው፡፡ ጌታ በሥጋ የተወለደው አንድ ጊዜ ነውና እርሱን በሥጋ የመፅነስ

---

[269] St. Augstine, Holy Virginity 3, Anicent Christian Commentaries on Scripture, NT III

ዕድል ከድንግሊቱ በቀር ለማንኛዋም ሴት ሊደርሳት አይችልም፡፡ ሆኖም አንድ ተጨማሪ ዕድል ግን ለሴቶች ሁሉ ተሠጥቶአል፡፡

አባ መቃራ ለአንዲት መነኩሲት እንዲህ ሲል እንደነገራት ፡-

'ይደሉኪ፡ላዕሌኪ፡ኦ፡እኅት፡ከመ፡ትጹረዮ፡ለእግዚእ፡
በሌብኪ፡በከመ፡ጾረቶ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡በከርሣ'

'እኅት ሆይ እመቤታችን ማርያም በማሕፀንዋ እንደተሸከመችው አንቺም ጌታን በልብሽ ትሸከሚው ዘንድ ይገባሻል'[270]

እመቤታችን ጌታን በእምነት በመፅነስ ያገኘችውን ብፅዓን ክርስቲያኖች ሁሉ በእርሱ በማመን ያገኙታል፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ይህን እንቀጽ በተረጎመበት ሥፍራ ፡-

'የተሸከመችህ ማሕፀን የተመሰገነች ናት ይላል። ክርስቶስ ከፀነሰችው ድንግል በረከትን እየወሰደ በእርሱ ለሚያምኑበት ሁሉ ያድላቸዋል። ይህ በረከት አስተድሞ ከድንግል ማርያም ጋር ብቻ የነበረ በረከት ነበረ። አሁን ግን ከሚያምኑበት ሁሉ ጋር ለዘላለም ይኖራል። ብፁዓንስ

---

[270] መጽሐፈ መነኮሳት ፤ ፊልክስዩስ ፤ ተስእሎ ፹

ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው የተባለውም ለዚህ ነው'
271

በማለት ያመነችው ብፅዕት ድንግል ማርያም ለምእመናን ሁሉ የበረከት ምንጭ መሆንዋን አስረድቷል፡፡

ቅዱስ ባስልዮስም ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ከመቀበላቸው በፊት እንዲጸልዩት በደረሰው የውዳሴ አምላክ ጸሎት ላይ ድንግል ማርያምን እንዲህ ይላታል፡-

'ከንጹሐን ይልቅ ንጽሕት የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ሆይ ባንቺ የተፀነሰን አምላክ ዛሬ የምቀበለው ነኝ። አንቺ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንድትሆኚ በሰው ሁሉ የደረሰ የአዳም ኃጢአት ስንኳ አልደረሰብሽም። እኔ ግን ኃጢአት የሠራሁ ስሆን ያንቺን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ልቀበል ወደ ቍርባን እቀርባለሁ።

መሓሪት እናት ሆይ ክፋቴ ብዙ ነውና እርሱን ስቀበል እንዲምረኝ እያዘንሽ አማልጂኝ። የእኔ መቀበል ክቡር ልጅሽን ማዋረድ መናቅ እንዳይሆን እርሱን ልጅሽን በምትቀበይበት ጊዜ የተደረገን የአንቺን መዘጋጀት

[271] St. Ephraim the Syrian, Commentary on Tatian's Diatessaron 11.10

ያንቺን ትሕትና ያንቺን ንጽሕና ስለ እኔ ፈንታ እንድታቀርቢልኝ እለምናለሁ'[272]

ይህ ከአባቶቻችን የተማርነው ወደ አመነችው ብፅዕት የምናቀርበው ጸሎት ነው:: የእርስዋን ወደር የሌለው እምነትና ቅድስና ባየን ጊዜ ከበረከትዋ ቆርሳ ትሠጠን ዘንድ እንማጸናታለን:: እርስዋ ለእርሱ ማደሪያው የሆነችለትን አምላክ በሕይወታችን እንዲያድር እየናፈቅን እንለምናታለን::

ድንግል ሆይ ወደ አንቺ መጥቶ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ያለሽ መልአክ ዛሬም ወደ እኔ ይምጣ:: ኃጢአት ያደቀቃት በኀዘን የተዋጠች ነፍሴን ከጸጋ የተራቆትሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ይበላት:: ጌታ በእኔ ልብ እንዳይፀነስ 'ያለ ኃጢአት መኖርን ስለማላውቅ እንደት ይሆንልኛል?' ብልም ወደ አንቺ የመጣው መንፈስ ቅዱስ ወደ እኔ በምሕረት ይምጣ:: በእስራኤል ልጆች ሠፈር መና እንደወረደ የልጅሽ ምሕረት በእኔ ላይ ይውረድ::

አንቺን ድንግልናን ከማጣት እንደ ጋረደሽ እኔን ከኃጢአት ይጋርደኝ:: አንቺን አምላክን ለመውለድ ያጸናሽ አብ እኔን ልጅሽን በማመን ያጽናኝ:: አንቺ በማሕፀንሽ ዘጠኝ ወር የፀነስሽውን ጌታ እኔ

[272] ቅዱስ ባስልዮስ ፤ ውዳሴ አምላክ ፤ ዘዐርብ ቁጥር 2

ለደቂቃዎች እንኳን በልቤ እንድፀንሰው ፍቀጂልኝ:: የፀነስሁትን የኃጢአት አሳብ ከልቤ አውጥተሽ በሕሊናዩ ልጅሽ እንዲያድር ለምኚልኝ:: ጌታን በእጆችሽ መሃል የያዝሽው ሆይ አንቺ ጌታን ለዓመታት ታቅፈሽው ነበር:: እኔ ግን ለአንድ ቀን እንኳን ሰውነቴ ከኃጢአት አርፎ እርሱን ብቻ ታቅፌ እንድውል ፍቀጂልኝ::

እርግጥ ነው ወደ እኔ ልጅሽን ይዘሽ ስትመጪ እንደ ቤተልሔም የእንግዶች ማደሪያ የእኔም ልብ የብዙ እንግዳ ኃጢአቶች ማደሪያ ነውና ልጅሽን ለማስተኛት ቦታ የለኝም ብዩ የልቤን በር ልዘጋብሽ እችላለሁ:: በሩን ብዘጋውም ግን ልጅሽ እንደሆነ 'በደጅ ቆሞ ማንኳኳት' እንደማይሰለቸው አውቃለሁ:: ራእ. ፫፥፳ እኔ ፈቅጄ ባልከፍትለትም እንኳን የድንግልናሽን ማኅተም ሳይከፍት እንደተወለደ የእኔን የተዘጋም ልብ ሳይከፍተው መግባት አይሳነውም:: ስለዚህ አመኔና እምቢታዩን ቸል ብለሽ ለልጅሽ ማደሪያ አድርጊኝ:: አንቺ እርሱን ከወለድሽ ወዲያ በታተመ ድንግልና ጸንተሽ እንደኖርሽ ለልጅሽ ማደሪያ ሆኜ ለሌላ የኃጢአት ፅንስ ዳግም ማደሪያ እንዳልሆን ነፍሴን አትሚልኝ::

የወለድሽው መድኃኒት እኔን ዙፋኑ አድርጎ ቢቀመጥ ሰዎች በእኔ እቅፍ ስላለ ብቻ በእኔ ምክንያት እንደ ሰብአ ሰገል እንደሚሰግዱለት በአንቺ ሲሆን አይቻለሁና ሰዎች በእኔ ምግባር ምክንያት ፈጣሪን

መስደብ ትተው እጅ መንሻ ያቅርቡለት:: ለልጅሽ በቀረቡ ሥጦታዎች ተከብቤ ከእንቺም ጋር ፡- 'ጌታ ሆይ ለአንተ የሚሰግዱልህ ሰዎች ዙሪያዬን ከበቡኝ ፤ ለአንተ በተረቡ ሥጦታዎችም ዙሪያዬን ታጠርኩ' ብዬ ላመስግነው::[273]

ድንግል ሆይ አንቺን ያሳደደሽ ሔሮድስ እኔን የማያሳድደኝ ጌታ በእቅፌ ስለሌለ ነው:: እኔ በልቤ ያነገሥሁት 'የተወለደውን የአይሁድ ንጉሥ' ስላልሆነ ሔሮድስ ከእኔ ጋር ጠብ የለውም:: የሔሮድስን ሥልጣን አደጋ ላይ የሚጥል ንጉሠ ሰላም በእኔ እቅፍ የለም:: አሁን ግን ፍቀጂልኝና ሔሮድስን ማስደሰት ትቼ ልጅሽን በልቤ ልቀበለው::

የልቤን ክርስቶስ ሔሮድስ እንዳይገድልብኝ እኔም እንደ አንቺ ልሰደድ:: እርሱን አቅፌ መከራ ቢደርስብኝ እንኳን ጽናት እንደማገኝ በአንቺ አይቻለሁና የልጅሽን ፍቅር በልቤ አኑሪልኝ:: ለሦስት ቀናት ከፊትሽ ዘወር ቢል ፍለጋ የወጣሽዋ ድንግል ሆይ ከእኔ ሕይወት ልጅሽ ከተሠወረ ቆይቶአልና ያለ እርሱ መስንበት የማልችል የፍቅሩ ምርኮኛ አድርጊኝ::

[273] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity, Desert Fathers Series Vol. 5 Hymn X

## • ነቢይት ማርያም

እስራኤላውያን ከግብጽ አሰቃቂ ባርነት የወጡበትን ያንን የመሻገር ዕለት ታሪክ መቼም የማያውቅ የለም፡፡ ለአራት መቶ ሠላሳ ዘመናት ከተጨነቁበት ከዚያ ምድር በአንድ ሌሊት የሞተ በኩር መቅሠፍት ብቻ ያለ ምንም ችግር ውሻ እንኳን ምላሱን ሳያንቀሳቅስባቸው በሰላም የወጡበትን ያንን ድንቅ ዕለት ማን ይረሳል? እግዚአብሔር 'ሕዝቤን ልቀቅ ብሎሃል' ሲባል 'እግዚአብሔርን አላውቅም ፤ እስራኤልንም አልለቅም' ብሎ በትዕቢት ሲፎክር የነበረው ፈርዖን 'ሒዱና እግዚአብሔርን አገልግሉ ፤ እኔንም ባርኩኝ' ብሎ የተማጸነበት ሌሊት እንዴት ይረሳል? ዘጸ. ፭፥፪፤ ፲፪፥፴፩-፴፪

'የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ወደ ወንዝ ጣሉት' ብሎ ያወጀውን ጨካኙን ንጉሥ እግዚአብሔር ከወንዝ በተገኘው ነቢዩ በሙሴ አማካኝነት ከነ ሠራዊቱ ወደ ወንዝ የጨመረበት ፣ ባሕር እንደ ግድግዳ የቆመበትና ጭቃ እንኳን የሌለው የብስ የሆነበት ፣ የኤርትራ ባሕር ወለል ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ ፀሐይ ያየችበት ድንቅ ታሪክ እንዴት ይረሳል? 'ታላቅ ነገርን በግብጽ ግሩም ነገርም በኤርትራ ባሕር

ያደረገውን ያዳናቸውን እግዚአብሔርን ረሱ' የተባለባቸው አንዳንዶቹ ቢረሱትም እኛ ግን አንዘነጋውም። መዝ. ፻፭፥፳፩

በዚያች ድንቅ ዕለት እስራኤላውያን በተሻገሩበት ባሕር ዳርቻ ሆነው 'ይህችን መዝሙር ለእናንተ ጻፉ' ብሎ መዝሙር ከሚያስተምራቸው መሪያቸው ሙሴ ጋር በአንድነት መዝሙርን ለእግዚአብሔር አቀረቡ። ዘዳ.፴፩፥፴ በዚያች የማኅሌት ቀን የሙሴ እኅት ነቢይት ማርያምም ከበሮ ይዛ ትዘምር ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ነቢይት ተብላ የተጠራችው ሴት የሙሴና አሮን እኅት ማርያም ነበረች። ሙሴን በዐባይ ወንዝ ላይ እናቱ በሳጥን ላይ በጣለችው ጊዜ ልብዋ አልችል ብሎ የተከተለችውና የፈርዖንን ልጅ ተርሙትን በድፍረት አናግራ ሙሴን እናቱ ዮካብድ እየተከፈላት እንድታሳድገው ያደረገችውም ይህች ማርያም ነበረች። ኩፉ. ፴፫፥፩ እግዚአብሔር ለዚህች ሴዋዊት ሴት የሠጣት ቦታ ከወንድሞችዋ ተርታ እንደነበረም በዚህ ቃል እንረዳለን። 'ከግብጽ ምድር አውጥቼሃለሁ ከባርነት ቤትም ተቤዥቼሃለሁ በፊትህ ሙሴንና አሮንን ማርያምንም ልኬልህ ነበር' ሚክ. ፮፥፬

ሙሴን 'ኢትዮጵያዊትዋን ሴት ለምን አገባ?' ብላ ከወንድምዋ አሮን ጋር ባማችው ጊዜ እግዚአብሔር በለምጽ እንድትነድድ አድርጓት

'ከሰፈር ውጪ ሰባት ቀን ተዘግታ ተቀመጠች ፤ ማርያምም እስክትመለስ ድረስ ሕዝቡ አልተጓዙም' ተብሎ እንደተጻፈ የእስራኤልን የምድረ በዳ ጉዞ ለሰባት ቀን ያዘገየችውም ይህች ማርያም ነበረች፡፡ ዘኁ. ፲፪፥፲፭

'በትሕትናውና በጸሎቱ ይህን ያህል ወገንን ሲጠብቅ ያልተበሳጨ አንድ ሰው እንኳን ያላጠፋ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ... አቤቱ ወገኖችህን ይቅር በል እያለ ሳሙት እግዚአብሔርም ያጠፋቸው ዘንድ ለወደደ ለእኅቱና ለወንድሙ በየዋህነቱ ኃጢአታቸውን አስተሠረየላቸው' እንዲል በሙሴ ልመና ከለምጽዋ ነጽታ የነበረችው ይህች ማርያም ነበረች፡፡ ሲራ. ፲፩፥፩

ነቢይት ማርያም እስራኤል ከግብጽ ባርነት በወጡ ጊዜ 'ንሴብሖ' ለሚለው የሙሴ ቅኔ ዝማሬ ከፊት ከፊት የምትመራ ነበረች፡፡ ራስዋም በዚያች ዕለት 'ከበሮ በእጇዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ። ማርያምም እየዘመረች መለሰችላቸው። በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ' ዘጸ. ፲፭፥፳-፳፩

ይህ ሁሉ መዝሙር የቀረበለት የእስራኤል ከግብጽ መውጣትና ባሕረ ኤርትራን መሻገር ግን በእኛ ዘንድ ሲፈጸም ካየነው ድንቅ ነገር አንጻር በጣም ትንሽ ነገር ነው፡፡ 'አይሁድ ሆይ ተአምር ተደረገልን

አትበሉ ፤ ለእናንተ ከተደረገው በላይስ ለእኛ የተደረገልን ይበልጣል' ይላል ቅዱስ ኤራቅሊስ፡-

'የትኛውን ድንቅ ነገር ልናደንቅ ይገባናል? መና የሚያዘንበውን ሰማይ እናድንቅ ወይስ ሥጋን የለበሰውን አምላክ? በእርሱ እንዲመላለሱበት የተከፈለውን ባሕር እናድንቅ ወይንስ ከወለደች በኋላ ድንግልናዋ ያልተከፈለውን ድንግል? ከዓለት ውኃን ያፈለቀን በትር እናድንቅ ወይንስ ዓለምን ያነጻውን መስቀል?' 'እይ፡ መንክር፡ይደሉ፡ከመ፡ናንክር፡ሰማየኑ፡ዘያዘንም፡ኅብስተ፡ ወሚመ፡አምላክ፡ዘለብሰ፡ሥጋ፡፡ባሕረኑ፡ዘተከፍለ፡ከመ፡ ያንሶስዉ፡ ውስቴቱ፡ ወሚመ፡ ድንግል፡ እንተ፡ ወለደት፡ ወኢማሰነ፡ ድንግልናሃ፡ እምድኅረ፡ ወሊዶታ፡፡በትርኑ፡ ዘአንቅዐ፡ ማየ፡ እምኰኵሕ፡ ወሚመ፡ መስቀል፡ ዘአንጽሐ፡ዓለመ'[274]

እስራኤል ስለመዳናቸው ያንን ያህል ከዘመሩ እኛ ምን ያህል ዝማሬ ይገባን ይሆን? የእስራኤልን 'ንሴብሖ' የሚል መዝሙር ከሴቶች ጋር ሆና የመራችው ነቢይት ማርያም ነበረች፡፡ የእኛን የሐዲስ ኪዳን ዝማሬ 'ታዓብዮ' ብላ የጀመረችውም ነቢይት ድንግል ማርያም ነበረች፡፡

[274] ቅዱስ ኤራቅሊስ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፴፱፡፴፮-፴፯

ይህችኛይቱ ማርያም የያዘችው በከበሮ ፈንታ የታተመ ድንግልናዋን ነበር፡፡

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እንዲህ ተርጉሞታል፡-

'ነቢይት ማርያም ባሕሩን እንደተሻገረች ከበሮን በእጅዋ ይዛ ሴቶችን በዝማሬ መራች። ይህ ከበሮ የድንግል ማርያምን ድንግልና ይመስላል። ከበሮ ትልቅ ድምፅን ቢያወጣም የታተመ ነው። እርስዋም [በታተመ] ድንግልናዋ የእግዚአብሔርን ቃል አስገኝታለች'

የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ከበሮውን ከምሥጢረ ሥጋዌ ሳይርቁ ስፊውን በመለኮት ፡ ጠባቡን በትስብእት ፤ ጠባቡን በአሪት ሰፊውን በወንጌል ይመስሉበታል፡፡

የሙሴ እኅት ማርያም ስትዘምር ሴቶች ሁሉ እንደተቀበሏት የሔዋን ዘር ሁሉ ዝማሬዋን ተቀብሎ የሚዘምርላት ሊቀ መዘምራት እመቤታችን ናት፡፡ ምክንያቱም በሔዋን ምክንያት እንደ ገነት በር የተዘጋው የሴቶች አንደበት የተከፈተው በድንግል ማርያም ነው፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እንዲህ ይላል፡-

'ሴቶች ሆይ ድምፃችሁ በእናታችሁ በሔዋን ተዘግቶ ነበረ። እነሆ አሁን እኅታችሁ ማርያም ለምስጋና ከፍታዋለች !

እርጊትዋ ሔዋን በልሳናችሁ ላይ የዝምታን ድንጋይ ጭናበት ነበር። ታናሽዋ ልጅ ግን ትጮኹ ዘንድ ከፍታላችኋለች ፤ ያገባችው ሔዋን በአፋችሁ ላይ የዝምታን ልጓም አድርጋባችሁ ነበር ፤ ድንግሊቱ ግን የተዘጋውን በር በዝማሬ አስከፈተችው'[275]

ድንግል ማርያም የዘመረችው ዝማሬ ከእስራኤል የድል ዝማሬ ጋር ብዙ ተመሳሳይ ይዘት አለው፡፡ የሙሴ እኅት ማርያም 'በክብር ከፍ ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ' ስትል ድንግል ማርያም 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ታደርገዋለች' ብላለች፡፡ ዘጸ. ፲፭፡፳፩ - ሉቃ. ፩፡፵ ፡ የሙሴ እኅት ማርያም 'ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ' ስትል ድንግል ማርያም 'ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋረዳቸው' ብላለች፡፡ዘጸ. ፲፭፡ ፳፩-ሉቃ. ፩፡፶፪ እነ ማርያምና ሙሴ 'በክንድህ ብርታት ፤ በታላት ኃይልህ በተዘረጋውም ክንድህ አወጣኸን' ሲሉ ድንግል ማርያም 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' ብላለች፡፡ ዘጸ. ፲፭፡፲፮ ፡ ዘዳ. ፱፡፳፱- ሉቃ. ፩፡፶፩ እነ ማርያም 'የእስራኤል ልጆች ግን በባሕሩ መካከል በየብስ ሄዱ' ሲሉ ድንግል ማርያም 'እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል' ብላለች፡፡ ዘጸ. ፲፭፡፲፱ -ሉቃ. ፩፡፶፬

275 St. Jacob of Serugh, Hymns on Paradise, 22

ድንግል ማርያም በመዝሙርዋ ብቻ ሳይሆን በነቢይነትዋም ከቀደመችው ማርያም ጋር አንድ ናት፡፡ እመቤታችን በእርግጥም በብዙ ምክንያቶች ከነቢያት ሁሉ የምትበልጥ ነቢይት ናት፡፡ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል በቃል የተነጋገረው ሙሴ እንኳን ከእርስዋ ያነሰ ነቢይ ነው፡፡ ምክንያቱም:-

'እግዚአብሔር ሙሴን ከሕዝብ ተለይቶ ወደ ሲና ተራራ በወጣበት ጊዜ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ምንም ቃል አልተናገረውም። ለማርያም ግን የሕሊናዋንና የሥጋዋን ድንግልና አውቆ ከአርያም በወረደበት በዚያው ዕለት በማሕፀንዋ አደረ። ሙሴስ ጽላትን ከእግዚአብሔር እጆች ይቀበል ዘንድ አርባ ቀንና ሌሊት ጾመ ማርያም ግን ሥጋዋን ይለብስ ዘንድ ከአርያም በወረደበት ዕለት የእግዚአብሔርን ቃል ፀነሰችው' እንዳለ ሊቁ አባ ዘርዓ ያዕቆብ 'ኢተናገሮ፡ እግዚአብሔር፡ በዕለተ፡ ዐርገ፡ ሙሴ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ሲና፡ ተፈሊጦ፡ እምሕዝብ፡ ዘእንበለ፡ በሰቡዕ፡ ዕለት፡፡ለማርያምሰ፡ አእሚሮ፡ ድንግልና፡ ሕሊናሃ፡ ወድንግልና፡ ሥጋሃ፡ ተጸውረ፡ በማሕፀና፡ በዕለተ፡ ወረደ፡ እምአርያም፡ ለለቢሰ፡ ሥጋሃ፡፡ ወሙሴሰ፡ ጾመ፡ ፵፡ መዓልተ፡ ወ፵፡ ሌሊተ፡ ለተመጥዎተ፡

ጽላት፡ እምዕዴሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወማርያምሰ፡ በዕለተ፡ ወረደ፡እምእርያም፡ፀንለቶ፡ለወልደ፡እግዚአብሔር'[276]

ከሙሴ ብቻ ሳይሆን እርሱ ነቢይ ከተሰኘባት እና ብዙ መገለጦችን ካየባት ከሲና ተራራም ድንግል ማርያም እጅግ ትበልጣለች፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ለድንግሊቱ እንዲህ ይላታል ፡-

'ከደብረ ሲና በእጆቹ ትእዛዝን የጻፈባቸውን ሁለት ጽላት እግዚአብሔር ለሙሴ ሰጠው። ከአንቺ ግን እግዚአብሔር ቅዱስ ጽላትን ፈጠረ። ይህም ሥጋው ነው። ከደብረ ሲና እሳትና ጨለማ ወጣ ከአንቺ ግን አምላክም ሰውም ወጣልን' [277]

ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለውን ሕግ ራሱም መፈጸም ተስኖት ምድረ ርስትን እንዳያይ እግዚአብሔር ፈርዶበት ሞቶአል፡፡ ሁሉም ነቢያት ከዐሠርቱ ትእዛዛት ቢያንስ አንዱን ጥሰው ወድቀዋል፡፡ ነቢይት ድንግል ማርያም ግን ከዐሠርቱ ትእዛዛት አንዱንም አላጎደለችም፡፡ ሊቁ እንዲህ ሲል ያብራራል ፡-

'ወባሕቱ፡እሴቦ፡ዘፈጸመ፡፲ተ፡ቃላተ፡በገቢር፡ዘእንበለ፡ ማርያም፡ ድንግል፡ በሕሊናሃ፡ ወድንግል፡ በሥጋሃ፡፡ ወማርያም፡ ድንግል፡ እሴቦ፡ እመ፡ ኀለየት፡ ዘኢያሠምሮ፡

---

[276] መጽሐፈ ብርሃን ዘጸሐፈ ንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ 85

[277] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፺፯፣፰-፱

ለእግዚአብሔር፡ ወእሉቦ፡ እመ፡ ገብረት፡ ዘኢያሠምሮ፡ ለእግዚአብሔር'ነገር ግን በሥጋዋም በሕሊናዋም ድንግል ከምትሆን ከማርያም በቀር በሥርቱ ቃላትን በሥራ የፈጸመ ማንም የለም። ማርያም ድንግልስ እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገር ያሰበችበትና የሠራችበት ጊዜ የለም'[278]

በእርግጥም ከዐሠርቱ ትእዛዛት ለብዙዎች ከባድ የነበረው 'አትመኝ' የሚለው ከአሳብ ኃጢአት የመከልከል ሕግ ነበር፡፡ ይህን ብዙዎች ነቢያት ወድቀውበታል፡፡ ጻድቁ ኢዮብ 'ልጆቼ በልባቸው እግዚአብሔርን ሰድበው ይሆናል' ብሎ መሥዋዕትን ቢያቀርብም ፤ ጠቢቡ ሰሎሞን 'በልብህ አሳብ እንኳን ቢሆን ንጉሥን አትስደብ' ብሎ ቢያስጠነቅቅም የሰው ልጆች ግን ከአሳብ ኃጢአት ነጽተው አያውቁም፡፡ ኢዮ. ፩፡፭፤ ፲፡፳ ድንግሊቱ ግን ነቢያት ቅዱሳን ሁሉ ያልቻሉት የአሳብ ድንግልና አላትና ከአቢግያ ይልቅ 'አእምሮችሽ የተመሰገነ ይሁን' መባል ለሚገባት ለእርስዋ 'ሰላም፡ ለሕሊናኪ፡ ሐልዮ፡ ሠናያት፡ ልማዱ' 'መልካም ነገርን ማሰብ ልማዱ ለሆነ ሕሊናሽ ሰላም እንላለን' እያልን እናመሰግናታለን፡፡ ፩ሳሙ. ፳፭፥፴፫

[278] አባ ዘርአ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ብርሃን 85

ድንግል ማርያም እንደ ቀደመችዋ መዘምርት ማርያም 'ነቢይት' ተብላ መጠራት ይገባታል:: ከብዙዎቹ የድንግል ማርያም ስሞች አንዱም ነቢይት መባል ነው:: በነቢዩ ኢሳይያስ :-

ወደ ነቢይቱም ቀረብሁ እርስዋም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች። እግዚአብሔርም፦ ሕፃኑ አባቱንና እናቱን መጥራት ሳያውቅ የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ምርኮ በአሦር ንጉሥ ፊት ይወስዳልና ስሙን፦ ምርኮ ፈጠነ፥ ብዝበዛ ቸኰለ ብለህ ጥራው አለኝ ኢሳ. ፰፥፬

ተብሎ የተነገረው ትንቢት ለነቢይቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ለልጅዋ የተነገረ ነው::

'እደ፡ ይእቲ፡ ነቢይት፡ ፀንሰት፡ ዘወለደት፡ ወልደ፡ ዘእንበለ፡ እግዝእትነ፡ ማርያም፡ ዘወለደቶ፡ ለመድኃኒነ' ይላል ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ:: 'መድኃኒታችንን ከወለደች ከእመቤታችን ከማርያም በቀር ይህች የፀነሰች ወንድ ልጅንም የወለደች ነቢይት ማን ናት?' [279]

ነቢይት የተባለችው ድንግል ማርያም ከሆነች 'ሕፃኑ አባቱንና እናቱን መጥራት ሳያውቅ የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ምርኮ በአሦር ንጉሥ ፊት ይወስዳልና ስሙን፦ ምርኮ ፈጠነ፥ ብዝበዛ ቸኰለ ብለህ

---

[279] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ፤ መጽሐፈ ምሥጢር ፲፱፥፴፬

ጥራው አለኝ' የተባለለት ሕፃንስ ማን ነው ለሚለው ቅዱሳኑ እንዲህ ይተረጉማሉ፡፡

ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ነቢይት ድንግል ማርያም መሆንዋን ገልጾ ስለ ሕፃኑ ሲናገር 'አማኑኤል ሕፃን ሆኖ እንደተወለደ ሰብአ ሰገልን ይሰግዱለት ዘንድ በጨርቅ ተጠቅልሎ ሳለ ያስገበራቸው እርሱ ነው። ወደ ግብጽ በሔደ ጊዜም ጣዖታትን እንዲርዱ ያደረገ እርሱ ነው'[280] በማለት አስረድቷል፡፡

ቅዱስ ቂርሎስ ዘእስክንድርያም 'ጌታ በተወለደበት ወራት የዲያብሎስ ኃይል ተማረከ ፣ ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ የሚለው ስም የሚገባው ለጌታ ነው። በተአምራታዊ ልደቱ ሕፃን ሆኖ ሳለ እንደ ሰውነቱ በጨርቅ ተጠቅልሎ በአምላካዊ ኃይሉ ሰይጣንን በዘበዘው ፣ ሰብአ ሰገልም ከምሥራቅ መጥተው ሰገዱለት'[281] ብሏል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ይህን ሲያጠቃልል ደግሞ 'ከሲኦል ከማረካቸው ከአባቶች ነፍሳት በተርስ ምርኮ የቱ ነው? ከፍርድ ቦታ ካወጣቸው ከነቢያት ነፍሳት በተርስ መድኃኒታችን የማረከው ምንድርን ነው?' ብሏል፡፡

'ጸጋን ለተሞላችው' ድንግል ማርያም ትንቢትን መናገርም አንዱ ጸጋዋ ነውና ነቢይት ናት፡፡ በመጽሐፍ 'በእውነት ጌታ እግዚአብሔር

[280] St. Severus of Antioch, Homily XIV 8-9 ሃይማኖተ አበው ዘሳዊሮስ ፶፬፣ ፲፫
[281] St. Cyril of Alexandria, Commentary on the gospel of Luck, Pascal Homily 17

ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም' እንደተባለ ነቢያቱ የእግዚአብሔር ምሥጢረኞች ናቸው:: አሞ. ፫፥፯ ነቢይት ድንግል ማርያም ግን ከነቢያት ሁሉ በላይ የፈጣሪ ምሥጢረኛ ነበረች:: አምላክ ከእርስዋ መፀነሱን ቀድሞ የነገራትና ምሥጢሩን ጠብቃ የያዘች እርስዋ ብቻ ናት:: በኋላም የምታየውን ድንቅ ነገር ሁሉ 'በልብዋ ትጠብቀው ነበር' የተባለላት እርስዋ ነች::

ሊቁ እንዳለ :-

'ስለነቢያትስ በነቢዩ አሞጽ አፍ እግዚአብሔር ከነቢያቱ ሳይነገር የሚያደርገው ነገር የለም ተብሎአል። ለድንግል ማርያም ከእርስዋ የተወለደው የእውቀት ጌታ እንዴት አይገልጥላትም? እንዴትስ ምሥጢሩን ሳይነግራት ይችላል ፤ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንደሰየሟት ማርያምስ እንደ አባቶችዋ ነቢይት ናት' 'ወበእንተ፡ነቢያት፡ተብህለ፡በአፈ፡አሞጽ፡ ነቢይ፡ እስመ፡ አልቦ፡ ዘይገብር፡ እግዚአብሔር፡ ዘኢክሠተ፡ ወኢነገረ፡ ለአግብርቲሁ፡ ነቢያት:: እፎኬ፡ ኢይከስት፡ ላቲ፡ ወኢይነግራ፡ ምሥጢራቲሁ፡ እግዚእ፡ አእምሮ፡ ዘተወልደ፡ እምኔሃ:: ማርያምሰ፡ ነቢይት፡ ይእቲ፡ ከመ፡ ነቢያት፡ አበዊሃ፡ በከመ፡ ሰመይዋ፡ ሐዋርያት፡ ነቢይተ፡እንዘ፡ይብሉ፡በሲኖዶሶሙ'[282]

---

[282] አባ ዘርአ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ብርሃን 87

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት የተፈጸመውም የድንግሊቱን ነቢይነት የሚያሳይ ክስተት ነበር፡፡ ወንጌሉ 'የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት። የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው። ኢየሱስም፡ አንቺ ሴት፤ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት። እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው' ይላል፡፡ ዮሐ. ፪፡፫-፭

ልብ በሉ! በዚህ ሰርግ ቤት ስለ ወይን ጠጅ ማለቅ ለድንግሊቱ የነገራት ሰው የለም፡፡ ለልጅዋ በነገረችው ጊዜም በሠጣት መልስ ወቅት 'አገልጋዮቹን እንዲህ በይልኝ' አላላትም፡፡ እርስዋ ግን ቀጥሎ የሚያደርገው ተአምር የአገልጋዮቹን ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደሆነ በነቢይነትዋ አውቃ አገልጋዮቹን 'የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ' አለቻቸው፡፡ 'ወእግዝእትነሰ፡ እእሚራ፡ ዘይገብር፡ በጊዜሁ፡ ትቤሎሙ፡ ለእለ፡ ይትለአኩ፡ ግበሩ፡ ዘይቤለክሙ' 'እመቤታችንስ በጊዜው የሚሠራውን አውቃ ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው' እንዲል[283]

እመቤታችን ነቢይት እንደመሆንዋ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት ገብታ ባደረገችው በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ረዥሙ የሴት ልጅ ንግግር በሆነው ጸሎትዋም እጅግ ብዙ ትንቢቶችን ተናግራለች፡፡ ይህ ጸሎትዋ

[283] መጽሐፈ ስንክሳር ፤ ዘጥር ፲፪፡፳፰

አስቀድሞ የነቢዩ ሳሙኤል እናት ሐና ከጸለየችው ጸሎትም ጋር እጅግ ተመሳሳይ መሆኑ በነቢያት ላይ የወረደው ሀብተ ትንቢት በእርስዋም ላይ እንደመጣ ምስክር ሲሆን እንግዳ ድርሰት ትናገር ዘንድ ጸጋን ለተሞላችው ድንግል የሚቻላት ሲሆን የአባቶችዋንና የእናቶችዋን መጸለይዋ ደግሞ የድንግሊቱን ትሕትናም ያሳያል፡፡

'መንፈስ ግን አንድ ነው' እንደሚል በሁለቱም አንዱ ቅዱስ መንፈስ ስላደረ የሳሙኤል እናት 'በማዳንህ ደስ ብሎኛል' እንዳለች እመቤታችን 'መንፈሴ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል' ብላለች፡፡ ሐና 'እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም' ስትል ድንግል ማርያም 'ስሙም ቅዱስ ነው' ብላለች፡፡ ሐና 'የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል ፤ ደካሞችንም ኃይል አስታጥቋቸዋል' ስትል ድንግሊቱ ደግሞ 'ብርቱዎችን ከዙፋናቸው አዋረዳቸው የተዋረዱትንም ከፍ ከፍ አደረጋቸው' ብላለች፡፡ ሐና በጸሎትዋ መጨረሻ 'እንጀራን ጠግበው የነበሩ ተራቡ ፤ ተርበውም የነበሩ ጠገቡ' ስትል እመቤታችንም 'የተራቡትን በቸርነቱ አጠገባቸው ፤ ባለጸጎችንም ባዶ እጃቸውን ሰደዳቸው' በማለት ደግማዋለች፡፡[284] ፩ቆሮ. ፲፪፥፬ ፩ሳሙ. ፪፥፩-፲ ሉቃ. ፩፥፵፮-፶፫

[284] ሃና እና ድንግል ማርያም የሚመሳሰሉት ሁለቱም በሊቀ ካህናት ያልተገኘ እምነት ስለተገኘባቸውም ጭምር ነው፡፡ ሃና እግዚአብሔርን በጸሎት ደጅ ስትጸና 'ሰክረሻል' ብሎ

እመቤታችን ነቢይት እንደመሆንዋ በጸሎትዋ ላይ በርካታ ትንቢቶች አሉ፡፡ 'እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል' ማለትዋ ስለ እርስዋ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ ድረስ የሚቀጣጠልና ትውልድ የሚቀባበለው የምስጋና ችቦ እንዳለ የሚያስረዳ ነው፡፡ 'ብፅዕት ይሉኛል' አለች እንጂ 'ብፅዕት ይበሉኝ' ብላ አላዘዘችም፡፡ ዛሬ ብፅዕት የምንላት ብፅዕት ይሉኛል ስላለች ሳይሆን ብፅዕት ይሉኛል ያለችው ስለምንላት ነው። ትንቢት ማለት መጻኢውን ቀድሞ ማየት ነውና በየትውልዱ እርስዋን ማመስገን እንደሚቀጥል ታይቶአት የተናገረችው ነው፡፡ ወዳጄ በዚህ ተጽናና፡፡ ዛሬ የምታቀርብላትን ምስጋና ድንግሊቱ ከሩቅ ተመልክታዋለች፡፡ በኤልሳቤጥ ቤትም ስለ ትውልድ የተናገረችውም አንተንም ጨምራ ቆጥራ ነውና ደስ ይበልህ፡፡

'በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞችን በታተናቸው' የሚለው ቃልዋ ደግሞ ስለ ቤተ አይሁድ መበታተን የተናገረችው ትንቢት ነበር፡፡

መጽሐፈ ብርሃን እንዲህ ይላል፡- ነቢይት፡ ይእቲ፡ እግዝእትነ፡ ለነቢያት፡ ወትንቢታኒ፡ መንክር፡ ውእቱ፡ ዘተነበየት፡ በእንተ፡ ዝርወቶሙ፡ ለአይሁድ፡ ወትቤ፡ ወዘረዎሙ፡ ለእለ፡ የዓብዩ፡ ሕሊና፡ ልቦሙ፡፡፡ አይሁድሰ፡

---

ከተናገራት ሊቀ ካህናቱ ኤሊ ይልቅ በእምነትዋ ተሽላ ተገኝታለች፡፡ ድንግል ማርያምም የመልአኩን ቃል በእምነት በመቀበልዋ የመልአክን ቃል ሰምቶ ካላመነው በዘመንዋ ከነበረው ሊቀ ካህናት ዘካርያስ ይልቅ በእምነት ተሽላ ተገኝታለች፡፡ ፩ሳሙ.፩፡፲፩ ፡ ሉቃ. ፩፡፲፰

ዕቡያን፡ ሕሊና፡ እለ፡ ክህድዎ፡ ለወልዳ፡ ተዘርዉ፡ እምተጋብኦ፡ ውስተ፡ አፀደ፡ ሃይማኖት፡፡፡ ወተዘርዎቶሙሰ፡ ኮነ፡ በኀበ፡ ሲኦል፡ በከመ፡ ይቤ፡ ዳዊት፡ ወተዘርወ፡ አዕፅምቲሆሙ፡ በኀበ፡ ሲኦል' 'እርስዋ ነቢይትና የነቢያት እመቤታቸው ናት። ስለ አይሁድ መበታተን የተናገረችው ትንቢትዋም የተደነቀ ነው። በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞችን በታተናቸው ብላለችና። በአሳባቸው ትዕቢተኞች የሆኑ ልጅዋን የካዱት አይሁድ በሃይማኖት አጸድ ከመሰብሰብ የተበተኑ ሆኑ። ዳዊት አጥንቶቻቸው በሲኦል ተበተኑ እንዳለ መበተናቸውም በሲኦል ሆነ' መዝ. ፻፵፡፯

በሲኦል ከመበተናቸውም በፊት ቤተ አይሁድ በዓለም ሁሉ የተበተኑ ዘሮች በመሆናቸው እስራኤላዊ ያልተበተነበት ሀገር ጨርሶ የለም፡፡ ድንግል ማርያም በቤተ እስራኤል ላይ ስለሚደርሰው ሥነ መንግሥታዊ ለውጥና ስደት ትንቢትን ቀድማ ተናግራለች፡፡ ድያስፖራ (dia speiro) የሚለው ከግሪክ የተገኘ ቃልም በአብዛኛዎቹ መዝገበ ቃላት ውስጥ ሲተነተን እንደ ምሳሌነት የሚጠቀሰው ከእስራኤል ውጪ የተበተነው የእስራኤል ሕዝብ ሲሆን በግሪኩ ድያስጶራ ማለት በግእዝ ዝርዋን በአማርኛ የተዘሩ የተበተኑ ማለት ነው፡፡'ወዘረዎሙ፡ ለእለ፡ የዓብዩ፡ ሕሊና፡ ልቦሙ' 'በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞችን በታተናቸው' የሚለው የነቢይት ድንግል ማርያም ትንቢትም 'በልባቸው

አብርሃም አባት አለን' እያሉ በሚታበዩት ቤተ አይሁድ ላይ በየዘመናቱ በተደጋጋሚ ተፈጽሞአል:: ማቴ. ፫፥፱

'ብርቱዎችንም ከዙፋናቸው አዋረዳቸው' ማለትዋ 'ልጅዋ የሰቀሉትን አይሁድ ከመንግሥትና ከክህነት ከትንቢትም ዙፋን አዋርዶአቸዋልና ነው' 'እስመ፡ ነሠቶሙ፡ ወልዳ፡ ለእለ፡ ሰቀልዎ፡ እመናብርቲሆሙ፡ እመንበረ፡ መንግሥት፡ ወክህነት፡ ወትንቢት' እንዲል:: በእርግጥም ፈሪሳውያን የሚመኩበትን ክህነት እና ሹመት ሁሉ ከእጃቸው ነጥቆአቸዋል:: ይህም ሐሙስ ማታ በገዛ ፈቃዱ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን በመቅደዱና ዐርብ ዕለት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ በመቀደዱ ተረጋግጦአል::

'የተዋረዱትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው' ማለትዋ ደግሞ በስሙ ያመኑትን የሚመለከት ነው:: መጽሐፈ ብርሃን ይህን ሲተረጉም 'በልጅዋ የሚያምኑትን ትሑታን አለቻቸው እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ እንዳለ ከእርሱ ትሕትናን ተምረዋልና' ብሏል::'ትሑታን፡ሰመየቶሙ፡ለእለ፡ የአምኑ፡በወልዳ፡ተሚህሮሙ፡ትሕትናሁ፡በከመ፡ይቤ፡ተመሀሩ፡ እምኔየ፡እስመ፡የዋህ፡አነ፡ወትሑት፡ልብየ'

'የተራቡትንም በቸርነቱ አጠገባቸው' ያለችው በቁሙ በየዘመናቱ ስለሚከሰተው ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ ረሃብ እና የእግዚአብሔር መግቦት ቢያሳይም ምሥጢሩ ግን ስለ ሥጋዊ ረሃብ አይደለም:: ይህ ረሃብ

'እነሆ፥ በምድር ላይ ራብን የምሰድድበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም' ተብሎ የተነገረለት የቃለ እግዚአብሔር ረሃብ ነው፡፡አሞ. ፰፥፲፩ ይህ ረሃብ 'ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው' የተባለለት ረሃብ ፡ 'ማንም የተጠማ ወደ እኔ መጥቶ ይጠጣ' ፤ 'እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ለዘላለም አይጠማም' የተባለለትና ጥምና ረሃብ ነበር፡፡ ማቴ. ፭፥፮ ፤ ዮሐ. ፯፥፴፯፡፬፡፲፬

ይህን ረሃብ ለዘመናት ተርበው የነበሩት ከእስራኤል ውጪ ያሉት አሕዛብ ነበሩ፡፡ እነዚህ አሕዛብ ግን በልጅዋ ቸርነት ቃሉን ጠግበዋል፡፡ ሊቁ ይህን ሲተረጉም

> 'ዘንተ፡ ተነበየት፡ በእንተ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ኮኑ፡ ርኁባነ፡ እምሰሚዓ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ እምቅድመ፡ ሰብከተ፡ ወንጌሉ፡ ለወልዳ፡፡ እስመ፡ ነበሩ፡ በአምልኮ፡ ጣዖት፡ ከዊኖሙ፡ ነግዳነ፡ እምሥርዓተ፡ ተሰፋሁ፡ ወሶበ፡ አምኑ፡ በወልዳ፡ ወተጠምቁ፡ በስመ፡ ሥላሴሁ፡ ጸግቡ፡ በረከቶ፡ በሃይማኖት፡ ዘይነብር፡ ለዓለመ፡ ዓለም' 'ይህን ከልጅዋ የወንጌሉ ሰብከት በፊት የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት የተራቡ ስለነበሩ ስለ አሕዛብ ተነበየች፡፡ እነርሱ ጣዖትን በማምለክ ከተሰፋው ሥርዓት እንግዶች ሆነው ይኖሩ

ነበርና። በልጅዋ ባመኑና በሦስትነቱ ሰም በተጠመቁ ጊዜ ለዘለዓለም በሚኖር ሃይማኖት ከበረከቱ ጠገቡ' ብሏል፡፡

## • የዝምተኛዋ ንግግሮች

አባ ጽጌ ድንግል 'እርምሞትኪ፡ማርያም፡ኀለፈ፡እምእንከሮ' 'ማርያም ሆይ ዝምታሽ ከማስደነትም አለፈ' ብሎ እንደዘመረው የድንግል ማርያም ሕይወት በአስደናቂ ዝምታ የተከበበ ነበረ፡፡ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ባበሠራትና ያንን ሁሉ ምስጋና ፣ ያንን ሁሉ ማብራሪያ በሠጣት ጊዜ 'ወንድ ስለማላውት ይህ እንደት ይሆናል?' 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ከሚሉ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች በላይ ብዙ ቃል አልተናገረችም፡፡ ጌታን በወለደችበት ጊዜም 'ማርያምም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር' እንደተባለላት በእረኞቹ ዝማሬና በልጅዋ ክብር በልብዋ ብቻ ከመደነቅ ውጪ ምንም ቃል አልተናገረችም፡፡ ሉቃ. ፪፥፲፱፥፶፩

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤትም 'ወይን እኮ የላቸውም' ፣ 'የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ' ከሚሉ ሁለት ፍቱን ቃላት በቀር ብዙ ቃልን መናገር አላስፈለጋትም፡፡ ልጅዋ በጭካኔ ተገርፎ ፣ በቆሰለ አካሉ መስቀል ተሸክሞ ወጥቶ ፣ የእሾኽ አክሊል ደፍቶ ፣ በተቸነከረበትና በተሰቀለበት

በዚያ የመከራ ዕለት የኢየሩሳሌም ሴቶች በጩኸት ሲያለቅሱ ድንግሊቱ ግን ድምፅዋን ለሰው ከማሰማት ይልቅ 'አውከውኛልና ዓይኖችሽን ከእኔ መልሺ' በሚያሰኙ ዕንባን የተሞሉ ዓይኖችዋ የተሰቀለ ልጅዋን እያየች በኀዘን እሳት ከመቃጠል በቀር ድምፅዋን አላሰማችም፡፡ መኃ. ፮፥፭

ይህች የጸጥታ ወደብ ረዥም ንግግር የተናገረችው በኤልሳቤጥ ቤት ነበር፡፡ የተናገረችውም የምስጋና ጸሎት በቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ቦታ የሚሠጠው የዘወትር ጸሎት ነው፡፡ በእርግጥም እናት ወደ ልጅዋ ፤ የፀነሰች ድንግል ወደ ፅንስዋ የምታቀርበው ምስጋናና ጸሎት እንዴት ልዩ ነው? ሆድዋ የእግዚአብሔር መቅደስ የሆነላትና ወደ ቤተ መቅደስ ሳትሔድ መጸለይ የተቻላት ድንግል የተናገረችው ጸሎት ፤ ወደ ሰማይ አንጋጥጣ 'በሰማያት የምትኖር' በማለት ፈንታ ራስዋ ሁለተኛ ሰማይ ሆና 'በእኔ ውስጥ የምትኖር' ብላ ወደ ፀነሰችው ጌታ የምትጸልይ እናት ጸሎት እንዴት ያለ ነው?

'ድንግል፡ እድንነት፡ ርእሳ፡ መንግስ፡ ክርሣ' እንደሚል ይህች ድንግል የምታቀርበው ምስጋና ሁለተኛ ሰማይ በሆነው በሆድዋ ውስጥ በምትሰማው መላእክት ለአምላካቸው የሚያቀርቡት ምስጋና ተመስጣ ነበር፡፡ 'ምስጋናን የተሞላች ድንግል እመቤታችን ማርያም ግን የድምፁ ጣዕም ሊተረጎም የማይችል ፍጹም ምስጋናን በሆድዋ ውስጥ የምትሰማ

ሆነች። መጻሕፍት እንደተናገሩ ጸጋን በሚሠጥ አምላክ በቸርነቱ ብዛት ትርጉሙን በነፍሱ በማድነት እየተመሰ ይኖራል እንጂ ሰው በጥበቡ ሚዛን ለክቶ ይህን ያህላል ፤ ይህን ይመስላል ብሎ ሊናገረው በማይችል ደስታ ሐሴትን እያደረገች ነበር' 'ወድንግልኒ፡ እግዝእትነ፡ ማርያም፡ ምልዕተ፡ ብፅዓን፡ እስመ፡ ኮነት፡ ትስምዕ፡ እምውስተ፡ ከርሣ፡ ውዳሴ፡ ወስብሐት፡ ዘኢይትከሃል፡ ለፈክሮ፡ ጣዕመ፡ ድምፁ፡ በከመ፡ ይቤላ፡ መጻሕፍት፡ ነበረት፡ እንዘ፡ ትትፌሣሕ፡ በፍስሓ፡ ዘኢይነገሮ፡ ብእሲ፡ ለካልዑ፡ በመዳልወ፡ ጥበብ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ዘንተ፡ የአክል፡ ወዘንተ፡ ይመስል፡ እላ፡ ይተርፍ፡ በዕፁብ፡ ፍካሬ፡ ውስተ፡ ነፍሱ፡ እንተ፡ ጥዕመ፡ በኂሩተ፡ ጸጋሁ፡ ለወሀቤ፡ ጸጋ'[285]

ኤልሳቤጥ በሆድዋ ስላለው ፅንስ ሁኔታ 'ፅንሱ በማሕፀኔ በደስታ ዘለለ' ብላ ጮኻ ከተናገረች ድንግሊቱ በሆድዋ ስላለው አምላክ ምን ትል ይሆን? ድንግል ሆይ አንቺስ 'ፅንሱ በማሕፀኔ ...' ብለሽ የምትነግሪን እንዳች ነገር የለሽ ይሆን? በአንቺ ውስጥ የነበረው ፅንስ የተራ ሕፃን አልነበረም፡፡ 'በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና' እርሱ በሙሉ መለኮታዊ ኃይሉ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው፡፡ ቆላ. ፪፥ ፱ ይህ 'የመለኮት እሳት በሆድሽ ውስጥ ባደረ ጊዜ ልብሱ እሳት ነው ፤ ቀሚሱ እሳት ነው እንደምን አላቃጠለሽም? ... የኪሩቤል ዙፋን በሆድሽ ውስጥ በወደት በኩል ተዘረጋ? በቀኝ ነውን? ወይንስ በግራ ነው?'

[285] ሐመረ ነፍስ ፤ Scritti Teologici Ethiopici Dei Secoli XVI-XVII, 1958, pg 162

ኤልሳቤጥ የነቢዩን ፅንስ ጮኽ ከተናገረች ድንግሊቱ በሆድዋ ውስጥ ስላደረው እሳት ብዙ የምትለው ነበራት:: እርስዋ ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር::

ወደ ጸሎቱ ይዘት ሳንገባ ድንግል ማርያም ይህን ምስጋና ከማቅረብዋ በፊት የሆነውን ነገር ማስታወስ ግድ ይለናል:: ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በገባች ጊዜ በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት:: በታላቅ ድምፅ ጮኸ :- ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ፤ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኔ በደስታ ዘሎአልና። ከጌታ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት' አለቻት::

ድንግል ማርያም ይህን በቀጥታ ለእርስዋ የቀረበ ምስጋና ከሰማች በኋላ ምን ምላሽ ሠጠች? ካልን መልሱ ምንም ነው:: 'ከሴቶች የተባረክሽ ነሽ' ስትባል ይህ ምስጋና በመልአኩም ቀርቦላት የነበረ መሆኑን አልተናገረችም:: ድምፅዋን ሰምቶ ፅንሱ ስለመዝለሉም ምንም አስተያየት አልሠጠችም:: ለእርስዋ የተደረገው አቀባበል ለእኛ ለትዕቢተኞቹ ተደርጎልን ቢሆን ኖሮ ተመስግነን ባልጠገብን ተወድሰንም ባልረካን ነበር:: ድንግሊቱ ግን ነገሩን ያልሰማች ያህል ሆነች::

እሮጊትዋ ዘመድዋ በታላቅ ድምፅ ጮኻ አመስግናት ስትጨርስ እርስዋ 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታላት ታደርገዋለች' አለች፡፡ መመስገንሽ ፈጣሪን ከማመስገን የማያስቆምሽ ድንግል ሆይ የአንቺ ትሕትና እንደምን ያለ ነው? ከፍ ማለትሽ ፈጣሪን ከፍ ከማድረግ የማያስተውሽ ድንግል ሆይ ያንቺ ቅድስናስ እንደምን ያለ ነው? ምስጋና ሲበዛብን ከፍ ያደረገንን ፈጣሪ ለምንዘነጋ ፤ ክብራችን ሲጨምር ከተዋረድንበት ያነሳንን ለምንረሳ ለእኛ የአንቺ ሕይወት እንዴት ያለ ድንቅ ተግሣፅ ነው?

## ➢ ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች

ድንግሊቱ 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች ፤ መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል' አለች፡፡ ይህ ንግግር ለፈጣሪዋ ያላትን አክብሮት ብቻ ሳይሆን እርስዋም ያለችበትን የቅድስና ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ መቼም ሁላችንም ብንጠየቅ 'እግዚአብሔርን አከብረዋለሁ ፤ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ' እንላለን፡፡ እግዚአብሔርን የምናከብረው በምንድርን ነው? በማመስገን ፤ በመስገድ ፤ በእልልታ ፤ በሽብሸባ ፤ በጭብጨባ ፤ የከንፈርን ፍሬ የዝማሬን መሥዋዕት በማቅረብ ፤ በመመድወት ፤ ቃሉን በመስማትና በማንበብ ፤ ዘወትር ስሙን በመጥራትና በመጸለይ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ማክበር እግዚአብሔርን በአንደበታችን ፤ በጉልበታችን ፤ በጆሮአችን ፤

በዓይናችን ፡ በእጃችን ፡ በእግራችን ፡ በምላሳችን እናከብረዋለን ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መንገድ እግዚአብሔርን እንድናከብር በብዙ ሥፍራ ያዝዛል፡፡ 'በምስጋና ቃል እሠዋልሃለሁ' 'በወይፈን ፈንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሠጣለን' 'በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ' 'አዲስ ቅኔ ተቀኙለት ፤ በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩ' 'ለድኃ ችርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል' ዮና. ፪፥፲ ፡ ሆሴ. ፲፬፥፪ ፡ መዝ. ፺፮፥፱ ፡ ምሳ. ፲፱፥፲፯ ይህ ዓይነቱ አክብሮተ እግዚአብሔር በሥጋችን የምናደርገው ማክበር ነው፡፡ ከኃጢአት በመለየት ሰውነትን 'እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ ፡ ሕያው መሥዋዕት አድርጎ' ማቅረብ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አገልግሎት ሲሆን 'በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ' ተብለን ታዝዘናል፡፡ ሮሜ ፲፪፥፩ ፡ ፩ቆሮ. ፮፥፲፱

ከኃጢአት ርቀን እግዚአብሔርን በሥጋችን ማክበርና በቅድስና መኖር የሁላችንም መንፈሳዊ ግብና ከረቂቃን መናፍስት ጋር የምንታገልበት ዓላማችን ነው፡፡ ይህን ማሳካት የቻሉና ንጽሐ ሥጋን ገንዘብ አድርገው በሥጋቸው በቅድስና ሕይወት የተመላለሱ ሰዎች በሙሉ እንደበታቸው 'ሥጋዬ በሕያው አምላክ ደስ ተሰኘ' 'ልቤ በእርሱ ታመነ ፤

ሥጋዬም በእርሱ ደስ ይለዋል' ብለው ሥጋቸው እግዚአብሔርን እንደምታከብር ይመሰክራሉ:: መዝ. ፻፪፥፩ ፤ ፴፫፥፪

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ግን በሥጋዋ እግዚአብሔርን ከማክበር አልፋ ወደ ንጽሐ ነፍስ እና ንጽሐ መንፈስ ደርሳለች:: ስለዚህ 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች ፤ መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል' ብላ ለመናገር ችላለች:: የነፍስ ንጽሕና ከኃጢአት አሳብ መለየትና 'በፍጹም ልብህ ፤ በፍጹም ኃይልና በፍጹም ነፍስህ እግዚአብሔርን ውደድ' የተባለውን ትእዛዝ መፈጸም ነው:: ዘዳ. ፮፥፭ ድንግል ማርያም በፍጹም ልብዋ ፤ በፍጹም ኃይልዋና በፍጹም ነፍስዋ እግዚአብሔርን መውደድ ላይ ደርሳለችና 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች' ለማለት ድፍረት አላት:: እርግጥ ነው በዚህ ቅድስና ላይ ያልደረሱ ሰዎችም በታወቁ ቀናት ነፍሳቸው ከኃጢአት አርፋ በጥልቅ መንፈሳዊነት ውስጥ ሲያልፉ ለጥቂት ጊዜም በነፍስ እግዚአብሔርን የማክበርን ጣዕም ይቀምሳሉ::[286]

[286] ጸሎት በምናደርግበት ወቅት አንዳንድ ጊዜ ውስጣችን የማይፈልጋቸው ጣልቃ ገብ ሃሳቦች (intrusive thoughts) ሕሊናችንን ይረብሻሉ:: በእነዚህ ቅጽበቶች ከሰይጣን እንጂ ከእኛ ልብ ያልሆኑ እግዚአብሔርን እስከመሳደብ የሚደርሱ በጣም ጸያፍ የሆኑ ቃላትና ምስሎች እየመጡብን እንታወካለን:: ቤተ ክርስቲያናችን አንድ ክርስቲያን ይህ ዓይነት ፈተና ሲመጣበት 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች' በሚል ማርያማዊ ቃል ሰይጣንን አሳፍሮ ጸሎቱን እንዲቀጥል ታዝዛለች:: መጽሐፈ መነኮሳት ፤ አረጋዊ መንፈሳዊ

የእርስዋ ነፍስ ግን ሁልጊዜም እግዚአብሔርን እንዳከበረች ትኖራለች፡፡ ማር ኤፍሬም እንዲህ ይላል፡-

'በልብዋና በአሳብዋ አንተ ያለህባት ድንግል የተመሰገንች ናት፡፡ የንጉሥ ልጅ ነህና እርስዋ ቤተ መንግሥትህ ናት፡፡ ሊቀ ካህናት ነህና እርስዋ ቅድስተ ቅዱሳንህ ናት'[287]

ቅዱስ ያዕቆብ 'በነፍስዋ የመጨረሻው የቅድስና መዓርግ ላይ ደርሳለችና መጠን የሌለው ጸጋ በእርስዋ አደረ'[288] እንዳለ፡፡ በእርግጥም እመቤታችን ከቅዱሳን መዓርጋት ያላለፈችበት የለም፡፡

በንጽሐ ሥጋ የሚገኙትን ጽማዌ (ውስጣዊ ጸጥታ) ያገኘች በመሆንዋ ለመናገር የዘገየችና ንጻሬ መላእክት ገንዘብዋ የሆነላት መላእክት የሚያናግሯት ነበረች፡፡ ልባዌ ቢባል ቃሉን በልብዋ መዝገብ አስተውላ የያዘች ፤ በልብዋ ትጠብቀው ነበር የተባለላት የተዘከሮ ልዕልት ናት፡፡ ጣዕመ ዝማሬ ቢባል ድንግሊቱ ነፍስዋ እግዚአብሔርን የምታከብር ስብሐተ እግዚአብሔርን በመውደድዋ በሆድዋ መላእክት ማኅሌት

[287] St. Ephrem the Syrian, Hymns on the Nativity hymn 17, Bride of light, Sebastian Brock, pg 23
[288] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, SVS press, 1998, pg 27

እንዲቆሙ የተመረጠች መቅደስ ናት፡፡ በንጽሐ ነፍስ ከሚገኙ መዓርጋትም ድንግል ማርያም ሁሉን ገንዘብ አድርጋለች፡፡

እንብዕ (ዕንባ) ቢባል እመቤታችን 'በልጅሽ ፊት የወረደውን መሪር ዕንባ አሳስቢ' የምንላት ሕይወትዋን በፍቅረ እግዚእ ስታነባ የኖረች ፡ የእኛን ኃጢአት ማጠብ የሚችል ዕንባ ያፈሰሰች ናት፡፡ ራማ ድረስ ከደረሰው ከራሔል ዕንባ በላይ ኃይል ያለው የሐዘን ዕንባ ያፈሰሰችው ድንግል ዕንባዋ እንደ እስራኤል ነፃ ያወጣናል ብለን አምነን 'እዘክሪ እንብአ መሪረ' እያልን በዕንባዋ እንማጸናታለን፡፡ ኵነኔ ቢባል ሥጋዋን ለነፍስዋ ያስገዛች ቅድስት ፤ ፍቅር ቢባል ኃጥእ ጻድቅ ሳትል ሁሉን የምትወድድ ናት፡፡ 'እርስዋ በፍቅር የተሞላች ነበረች ! ምክንያቱም ጌታችን ፍቅር በሌለበት ሥፍራ አያድርም' እንዳለ ሊቁ ድንግል ማርያም ፍቅርን እስከ መውለድ የተመረጠች ናት፡፡[289]

በንጽሐ ነፍስ ደግሞ መላእክትን ከነተልዕኮአቸው መረዳት ቢሉ ቅዱስ ገብርኤል ቆሞ የተላከበትን ያስረዳት ለእርስዋም አይደለምን? ተሰጥዎ ብርሃን ቢሉ የብርሃን እናት ማን ሆነና? ከዊነ እሳት /ሥላሴ ቅዱስ/ ቢሉ አብ ያጸናት ወልድ ያደረባት መንፈስ ቅዱስ የጋረዳት ከሦስቱ አካል ወልድን ከነጽሮ አልፋ በእጆችዋ አቅፋ ያሳደገች እርስዋ

[289] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, SVS Press, pg. 24

አይደለችምን? እመቤታችን ያልወጣችው የቅድስና መዓርግ የለምና 'ነፍሴ እግዚአብሔርን ታላት ታደርገዋለች' የሚለውን ማንነትዋን የሚገልጽ ጸሎት ልትጸልይ ይገባታል፡፡

መስታወት የቆሸሸ እንደሆነ ጥሩውን ነገር አበላሽቶ ፡ ንጹሑን አቆሽሾ ያሳያል፡፡ መስታወት ንጹሕ የሆነ እንደሆን ግን አንድን መልክ በውበቱ ልክ ያሳየዋል፡፡ በእግዚአብሔር አርኣያ የተፈጠረው የሰው ልጅ በኃጢአት የቆሸሸ ማንነት ካለው እግዚአብሔርን በውስጡ ሊያሳይ አይችልም ፡ ባይሆን በእርሱ እድፍ ምክንያት ንጹሑ እግዚአብሔር በሰዎች ዝቅ ተደርጎ እንዲታይ ምክንያት ይሆናል፡፡ ሥጋውንና ነፍሱን መንፈሱንም ንጹሕ ማድረግ የቻለ ሰው ግን እንደ ድንግል ማርያም በነፍሱ እግዚአብሔርን 'ታላት አድርጎ' እና አጥርቶ ማሳየት ይችላል፡፡

እመቤታችን እግዚአብሔርን ከፍ የምታደርግ ቅድስት ነፍስ እያለቻት ኃጢአት በሞላበት በዚህ የቆሸሸ ዓለም ውስጥ መኖርዋ ብቻ ሌላው ሰማዕትነትዋ ነበር፡፡ አባ ጽጌ ድንግል 'እሾህ በተባሉ በአይሁድ መካከል ያበበች የእምነት አበባ' የሚላት ድንግል ማርያም ቅንነትን ይዛ ግፍን በተሞላች ዓለም ውስጥ ኖራለች፡፡ ለእንስሳ የሚራራ የጻድቅ ነፍስ ይዛ በጨካኞች መካከል ኖራለች፡፡ ምሳ. ፲፪፡፲

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሎጥ የሰዶምና ገሞራ ኑሮ ሲገልጽ 'ጻድቱ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዓመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበር' ይላል:: ንጽሕት ነፍስ ያለቻት ድንግል ማርያም በከፋት በተሞላው ምድር ላይ በኖረችበት ዘመን ምንኛ ነፍስዋ ይጨነቅ ይሆን? ለዚህም ነው አባቶቻችን በድንግል ማርያም የዕረፍትዋ በዓል ዕለት 'እግዚአብሔርን ታከብረዋለች' ያለቻት ነፍስዋ ከሥጋዋ መለየትዋን አስመልክተው ሲያመሰግኑ 'ለዛቲ፡ድንግል፡ሠረቀ፡ላዕሌሃ፡ብዕለ፡ጸጋሁ፡ለአብ፲ወእግዓዛ፡እምእኩይ፡ውስተ፡ሠናይ'፡'በዚህች ድንግል ላይ የአብ የጸጋው ብዛት ተገለጠ ፤ ከክፉው ወደ መልካሙ ነፃ አወጣት' የሚሉት::

## ➢ መንፈሲም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይለታል

ድንግል ማርያም 'መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል' አለች:: የድንግሊቱን ጥበብ ተመልከቱ:: 'በመልአክ በመመስገኔ ደስ ይለኛል ፤ ከሴቶች ሁሉ የተባረከች በመባሌ ደስ ይለኛል ፤ አምላክን ለመውለድ በመመረጤ ደስ ይለኛል' አላለችም:: የእርስዋ የደስታ ምንጭ ከእግዚአብሔር የተሠጣት ነገር ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የደስታህ ምንጭ ከሆነ በሕይወትህ ምንም ነገር

ቢከሰት ደስታህን አይነካብህም፡፡ ድንግሊቱ ከሴቶች ሁሉ የተባረከች በመሆንዋ ደስ ያላት ብትሆን ኖሮ ከዚያ በኋላ ከሴቶች ሁሉ የተንከራተተች ፤ ከሴቶች ሁሉ ያዘነች ፤ ከሴቶች ሁሉ በዲያብሎስና ጭፍሮቹ የተጠላች ፤ በሔሮድስ በአይሁድ የተነቀፈች መሆንዋን ስታይ ደስታዋ በጠፋ ነበር፡፡ እርስዋ ግን ደስታዋ የመነጨው ከአምላክዋ ብቻ ነበር፡፡ ፍጹም የሆነ ውስጣዊ ደስታን ማግኘት የሰው ልጅ ትልቅ ምኞቱ ነው፡፡ ሰዎች ደስታን ፍለጋ ብዙ ይደክማሉ፡፡ ድንግሊቱ ግን የደስታ ሁሉ ምንጭ የሆነው አምላክ ከእርስዋ ጋር ነውና በፍጹም ደስታ ደስ ይላታል፡፡ የድንግል ማርያም ደስታ ልጅዋ 'ደስታችሁን የሚወስድባችሁ የለም' ያለው ዓይነት ደስታ ነበር፡፡ ዮሐ. ፲፮፡፳፪

'ተፈሥሒ፡ፍስሕት' (ደስተኛይቱ ሆይ ደስ ይበልሽ) ፤ ሙኃ፤፡ ፍሥሓ (የደስታ መፍሰሻ ሆይ) ብለን የምናመሰግናት እመቤታችን ከማንም የሚበልጥ ደስታ በእርስዋ ዘንድ ነበረ፡፡ ደስተኛ የነበረችው በምድር በነበራት ቆይታ የሚያስደስት ኑሮ ስለነበራት አይደለም፡፡ እንደ እርስዋ የተሰደደ ፤ ያለቀሰ ፤ የተጨነቀ ፍጡር የለም፡፡ እንደ ክርስቶስ መከራ የተቀበለ እንደሌለ እንደ ድንግል ማርያምም ያዘነ የለም፡፡ እርስዋ ግን ለሌሎች የሚተርፍ ወደ ኤልሳቤጥ የሚሸጋገር ፤ ሆድ ውስጥ ወዳለ ፅንስ የሚጋባ ጥልቅ ደስታ ነበራት፡፡ ቅዱስ ያሬድ 'ተፈሢሓ፡በነፍሳ፡

ያረቱ፡ በክርሣ 'በነፍስዋ ደስ ተሰኝታ በሆድዋ ተሸከመችው'[290] እንዳለ እርስዋ የተደሰተችው ሥጋዊ ደስታን አልነበረም፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ደስታ ነውና ቅድስቲቱ ማንም ጋር ያልነበረ ደስታ ነበራት፡፡ ገላ. ፭፥፳፪

በእርግጥም ደስታን ወልዳ ደስ ባይላት ይደንቅ ነበር፡፡ እርስዋ የወለደችው 'የመላእክት ተድላ ደስታቸው' ነው ፡ እርስዋ የወለደችው መወለዱ 'ለሰው ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላት የምሥራች' የሚሆን ልጅን አይደለምን? እግዚአብሔር አብ 'በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው' ያለውን እንድያ ልጁን ልጅዋ እንዲሆን ሠጥቶአታልና እርስዋም በልጅዋ ደስ ይላታል፡፡ ንጉሥ ዳዊት 'ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሒድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ' ካለ እግዚአብሔር የዘጠኝ ወር ቤቱ እድርጎ ያደረባት ድንግል ምንኛ ደስ ይላት ይሆን? መወለዱ ሰውና መላእክትን በደስታ እንዲዘምሩ ካደረገ የወለደችው ድንግል ምንኛ ደስ ይላት ይሆን?

ጌታ ለሐዋርያቱ 'ስማችሁ በሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ' ካላቸው እግዚአብሔር ሁለተኛ ሰማዩ እድርጎ ዙፋን ያደረጋት በምድር ያለች የጠፈር ባልንጀራ ፡ የአርያም እኅት ማርያም ምንኛ ደስ ይላት ይሆን? እመቤታችን ሆይ እባክሽን በአንቺ ላይ ከፈሰሰው ደስታ ቀድተሽ

[290] ቅዱስ ያሬድ ማሕሌታይ ፤ ድጓ ዘቅዱስ ገብርኤል

ወደ እኛ ወደ ኀዘንተኞቹ አፍስሺ፡፡ ኖኅ እንደ ላካት ርግብ የመከራችን ውኃ ጎደለ ብለሽ ታበሥሪን ዘንድ ወደ እኛ ነይ 'ንዒ፡ርግብየ፡ትናዝዝኒ፡ ኀዘነ፡ልብየ' 'ርግቤ ሆይ ከኀዘኔ ታረጋጊኝ ዘንድ ነይ' እንዳለ ሊቁ፡፡

## ➢ የባሪያይቱን መዋረድ አይቶአልና

ድንግል ማርያም በማስከተል 'የባሪያይቱን መዋረድ አይቶአልና' አለች፡፡ በሁለቱም አመስጋኞችዋ ፊት ራስዋን 'ባሪያ' ብላ ጠራች፡፡ በገብርኤል ፊት 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ' ያለችው ድንግል በኤልሳቤጥ ቤትም 'የባሪያይቱን መዋረድ አይቶአል' አለች፡፡ 'በትሕትና የተናገርሽ ተራራ ሆይ' የተባለላት ድንግል እርስዋ ራስዋን ዝቅ አድርጋ 'ባሪያ' ነኝ ትበል እንጂ እግዚአብሔር ግን የመረጣት ለእናትነት ነው፡፡ 'ርግብየ፡ ደቤላ፡በእንተ፡የዋሃታ፡...፡እንዘ፡እመቱ፡እሞ፡ረሰያ...ታዕካ፡ለማይ፡ኮነ፡ ማኅደራ' 'ስለየዋህነትዋ ርግቤ አላት ... ባርያው ስትሆን እናቱ አደረጋት ... የሰማይ አዳራሽም ማደሪያዋ ሆነ' እንዳለ ሊቁ፡፡

እግዚአብሔር ድንግል ማርያምን ከዓለም ሁሉ ሴቶች ለይቶ ለእናትነት የመረጠበት ብዙ ምክንያት አለው፡፡ 'በዓለም ላይ በድንግል

ማርያም ልክ ደስ ያሰኘችው ሌላ ሴት ኖራ ቢሆን በመረጣት ነበር'[291] በዚያ ዘመን ቁጥር የሌላቸው ደናግል በእስራኤል ቢኖሩም ንጉሥ እግዚአብሔር የቅድስና ውበትዋን ወድዶ 'ርግቢ መደምደሚያዬም አንዲት ናት' ብሎ የወሰነባት እርስዋ ነበረች፡፡ መኃ. ፮፥፰ ሆኖም ለምን እንደመረጣት ስትገልጽ 'ቅድስናዬን አይቶአልና' ፡ 'ንጽሕናዬን ተመልክቶአልና' ፡'ድንግልናዬን አይቶአልና' አላለችም፡፡ 'የባሪያይቱን መዋረድ አይቶአልና' ብላ የትሕትናዋን ጥግ የበለጠ የሚያሳይ ቃልን መረጠች፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ 'እርስዋ በእግዚአብሔር ዓይን በታየ የትድስና ውበት የተሞላች ነበረችና በእርስዋ ንጹሕ ማሕፀን ሊያድር ወደደ ፤ እንደ ድንግል ማርያም ራሱን ዝቅ ያደረገ ትሑት ማንም የለም' ይላል፡፡[292] 'በምድር ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ትሑት ነበረ' ተብሎ ከተነገረለት ከሙሴ ጀምሮ ትሑታን ከተባሉት ሁሉ እርስዋ በትሕትናዋ ትበልጣለች፡፡ ዘኁ. ፲፪፥፫ 'ወደ ትሑት መንፈሱም ወደ ተሰበረ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ' ያለው አምላክ ወደ ድንግል ማርያምም እንዲመለከት ያደረገው ጥልቅ ትሕትናዋ ነበር፡፡ ኢሳ. ፷፮፥፪

[291] St. Jacob of Serug, On The Mother of God. SVS, 1998, Homily 1. Page 23
[292] St. Jacob of Serugh, On the Mother of God. Homily II

የድንግል ማርያም ትሕትና እግዚአብሔር ከሰማይ የወረደበት
መሰላል ነበረ፡፡ ‘ትንሹ የናርዶስ ቅጠል መዓዛው ከሩቅ እንደሚያውድ
የድንግሊቱ ትሕትና ሰማይ ድረስ ደረሰ’ ‘እግዚአብሔር ሰሜንና ደቡብን
ምሥራቅንና ምዕራቡን ተመለከተ ፤ ተነፈሰ አሻተተም እንደ አንቺ ያ
አላገኘም የአንቺን መዓዛ ወደደ’ እንዲል በትሕትናዋ መዓ
እግዚአብሔርን ከእርስዋ እንዲወለድባት ያደረገች ትሕት ማርያም ብቻ
ነበረች፡፡

ድንግል ማርያም ‘እስመ፡ ርእየ፡ ሕማማ፡ ለአመቱ’ ‘የባርያዩቱ
መዋረድዋን አይቶአልና’ ስትል የራስዋን ብቻ ሳይሆን የሔዋንን እና የሴት
ልጆች ሁሉ መዋረድ ማብቃቱንም አብራ መሰከረች፡፡ ሴትነት የሰው
ልጅ ውድቀት ምክንያት ከመሆን ወደ ሰው ልጅ ድኅነት ምክንያትነት
በእርስዋ ምክንያት እንደተሸጋገረ፡፡ ትውልድ ሁሉ የሚረግሟት ሴት
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት በሚሏት ሴት መተካትዋን በሚያበሥር ቃል
እግዚአብሔር የባርያዪቱን የሔዋንን ሕማም መመልከቱን ገለጠች፡፡

## ➢ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል

‘እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል’ የሚለው
ንግግርዋ የእርስዋ ነገር በዘመንዋ በነበሩ ሰዎች ብቻ ተነግሮ የሚያበቃ ነገር

አለመሆኑን ያስረዳል፡፡ የአዳም ዘር በሙሉ ፤ ከጥፋት ውኃ በኋላ ምድርን የተከፋፈሉ የሴም ትውልድ ፤ የካም ትውልድና የያፌት ትውልድ ሁሉ ብፅዕት እንደሚሏት 'ትውልድ ሁሉ' ብላ ተናገረች፡፡ ክቡይቱ ድንግል ማርያም ፡-

'ለወደፊት የሚሆነውን ነገር አስቀድማ ተመለከተች ፤ ስለድንግልናዋ የምድር ሁሉ ሰዎች ብፅዕት እንደሚሏትም አየች። ልጅዋ የአሕዛብ ሁሉ ንጉሣቸው እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ ሲገልጥላት ከሀገራት ሁሉ ብፅዕት መባል እንዳላት ተናገረች'[293] ይላል ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፡፡

ዮሐንስ ዘደማስቆም ፡- 'ለሰው ዘር ሁሉ እንደተሠጠች የተመረጠች ክብርት ነሽ ሁሉም ትውልድ ያመሰግኑሻል። አንቺ የካህናት ኩራት ፤ የነገሥታት መደገፊያ ፤ የክርስቲያኖች ተስፋ ነሽ'[294]ብሏል፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ይህን ሲያብራራ 'ኵሉ፡ ትውልድ፡ ያስተበፅዑኪ፡ለኪ፡ለባሕቲትኪ፡ኦ፡እግዝእትነ፡ወላዲተ፡አምላክ' አለ ፤ ለአንዳንድ ሰው እንደሚመስለው መወለዱን መስቀሉን ስናነሣ በዚያው እርስዋንም እያነሣን እግረ መንገዳችንን የምናመሰግናት ሳይሆን ሥራዩ

[293] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, 637, SVS Press, 1998, pg 40
[294] St. John of Damascus, On The Nativity of the Holy Theotokos, 11, Wider than Heaven, 69

ብለን ፡ በእርስዋ የተደረገውን ድንቅ ነገር አስበን ለብቻዋ እናመሰግናታለንና 'እምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ አንቺን ብቻሽን ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑሻል' አለ። ትውልድ ሁሉ እርስዋን የሚያመሰግንበትን ምክንያትም ሲያብራራ 'የምድር ነገሥታት በብርሃንሽ ይሔዳሉ አሕዛብም በብርሃንሽ ይሔዳሉ ማርያም ሆይ ትውልድ ሁሉ ያመሰኙሻል' በማለት ከእርስዋ በተወለደው ብርሃን ክርስቶስ ፀሐይነት ስለሚሔዱ 'መንገድም ሕይወትም እውነትም' በሆነው ልጅዋ አምነው የሚጓዙ ሁሉ እንደሚያመሰኗት ገልጾአል::[295]

እመቤታችን ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ስትል ለወደፊት የሚወለዱትን ሕዝብና አሕዛብ ብቻ ሳይሆን ከእርስዋ በፊት የነበሩትንም የሚያካትት ቃል ነው:: ነቢያቱ በትንቢታቸውና በምሳሌያቸው ውስጥ ስለ ክርስቶስ በተናገሩበት ሥፍራ ሁሉ ድንግሊቱም አብራ ነበረችና በትንቢቶቻቸው ብፅዕት ይሏታል:: ትውልድ ሁሉ የሚለው ቃል ያለፈውን ትውልድ ሊያካትት የሚችለውም ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ጥላ ፡ ሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን አካል በመሆኑ ሲሆን ብሉይን ትቶ

[295] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ፤ ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ ፤ መዝሙራት ዘዳዊት ማኅበረ ሐዋርያት ፤ ኦሥመራ 1986 ዓ.ም. ፤ ገ.ሐ. ፲፬፥፮

ሐዲስን ብቻ ልረዳ ማለትም ሐዲስ ኪዳንን ጥላ ቢስ አካል ማድረግ ስለሆነ ነው።

በሐዲስ ኪዳን ለምናምን ፣ በወንጌል ለምንመራ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፣ የሙሴ ሕግጋት ፣ የነቢያት መጻሕፍት ፣ የዳዊት መዝሙራት ስለ ክርስቶስ የምንማርባቸው ከወንጌል የቀደሙ ወንጌላት ናቸው፡ ጌታችን 'በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ሊፈጸም ይገባል' እንዳለው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ በምሥጢር የሚናገሩት ስለ ክርስቶስ ነው። ሉቃ. ፳፬፥፵፬

‹ከሙሴና ከነቢያት ጀምሮ ስለ እርሱ የተጻፈውን ተረገመላቸው› ተብሎ የተነገረላቸው የኤማሁስ መንገደኞች ‹በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትን ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?› ብለው እንደተናገሩ ብሉይ ኪዳን በእርግጥ ስለ ክርስቶስ እንደሚናገር በሚገባ ትርጉሙን ከተረዳን ልባችን በጥልቅ ተመሥጦ ይቃጠላል። ይህን የአባቶችን ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ መነፅር በዓይናችን ካጠለቅን ብሉይ ኪዳንን እያነበብን በሐዲስ ኪዳን ባሕር ውስጥ መዋኘት እንችላለን። በኅብረ አምሳል (typology) አስቀድሞ የተነገረበትን ምክንያት (primary application) እና ፍጻሜውን (ultimate fulfillment)

ስንረዳ በታሪክና ትንቢት ሁሉ ውስጥ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን እያገኘነው ስንደነቅ እንኖራለን፡፡

በገነት መካከል ተኝቶ ከጎኑ የሁላችንን እናት ሔዋንን ያስገኘውን አዳም ታሪክ ስናነብ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በመስቀል ላይ አንቀላፍቶ ከጎኑ በፈሰሰው የጥምቀት ውኃ የሁላችን እናት ቤተ ክርስቲያንን ያስገኘውን ክርስቶስን እናየዋለን፡፡ ወይን ጠጥቶ ሰክሮ ዕርቃኑን የወደቀውንና ካም ሲዘብትበት ፡ ሴምና ያፌት ዕርቃኑን የሸፈኑለትን የኖኅን ታሪክ ስናነብ የሞትን ጽዋ ጠጥቶ በሰው ልጅ ፍቅር ሰክሮ ዕርቃኑን የተሰቀለውንና አይሁድ ሲዘብቱበት ፀሐይና ጨረቃ ዕርቃኑን የሸፈኑለትን ክርስቶስን እናየዋለን፡፡

አብርሃም የሚወድደውን ልጁን ይስሐቅን ሊሠዋ መፍቀዱንና በግ የመሠዋቱን ታሪክ ስናነብ አንድያ ልጁን እስኪሠጥ ድረስ ዓለሙን የወደደውን እግዚአብሔር አብንና እስከ ሞት ድረስ የታዘዘ ልጁን ንጹሑን በግ ክርስቶስን እናየዋለን፡፡ ዳዊት ጎልያድን ድል አድርጎ እስራኤልን ነጻ ሲያወጣ ስናይ ክርስቶስ ዲያብሎስን ድል አድርጎ የሰው ልጅን ነጻ ሲያወጣ ይታየናል፡፡ እስራኤል በበረሃ ተጉዘው በበትር ከተመታው ከዓለት ውኃ ፈልቆላቸው ሲጠጡ ስናይ በዕለተ ዓርብ ጎኑን

በጦር ተወግቶ በደሙ ጥማችንን ያረካልን መድኃኔ ዓለም ይታየንና ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ‹ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ› እንላለን፡፡

ወደ መገናኛው ድንኳን ገብተን ደብተራ ኦሪትን ብንጎበኝ እንኳን ክርስትናችን አይለቀንም፡፡ በመሠዊያ ላይ የሚሠዋውን በግ ስናይ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕሊናችን ይመጣብናል፡፡ ወደ ድንኳኑ ዘልቀን በመቅረዙ ላይ መብራት ሲበራ ስናይ እውነተኛው ብርሃን ክርስቶስ ፤ ዕጣን ስናይ የኃጢአት ሽታችንን ያራቀልን ክርስቶስ ፤ በወርቅ የተለበጠ ታቦት ስናይ በመለኮቱ መለወጥ የሌለበትን ክርስቶስ ፤ መናውን ስናይ የሕይወት እንጀራ ክርስቶስ እየታየን እንደ ኤማሁስ መንገደኞች ልባችን እየተቃጠለ 'ለካስ ኦሪትና ነቢያት ሁሉ የሚናገሩት ስለ ክርስቶስ ነበረ?' እንላለን፡፡

ይህን አድርገን ግን አናበቃም ፤ ጌታን ባገኘንበት ሥፍራ ሁሉ እመቤታችንን ፍለጋ ማማተራችን አይቀርም፡፡ አዳምን የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ስናየው አዳምን ያለ አባት ያስገኘችዋ መሬት ያለ ወንድ ዘር የወለደችውን ድንግል ሆና ትታየናለች፡፡ አብርሃም የሠዋውን ከዱር ቀንዱ እንደታሰረ የወጣ በግ ስናይ የድንግልናዋ ማኅተም ሳይፈታ የወለደችው የበጉ እናት ትታየናለች፡፡

ወደ መገናኛው ድንኳን ገብተንም እናርፍም ፡ እርሱ መብራት ሆኖ ሲታየን እርስዋ መቅረዝ ትሆንልናለች፡፡ እርሱ ዕጣን ሲሆን እርስዋ ማዕጠንት ትሆናለች ፡ እርሱ ታቦት ሲሆን እርስዋ ታቦቱ ያለበት ቅድስተ ቅዱሳን ትሆናለች ፡ እርሱ ጽላት ሲሆን እርስዋ የጽላቱ ማደሪያ ታቦት ትሆናለች ፡ እርሱ በጽላት ላይ የተጻፈው ቃል ሲሆን እርስዋ ጽላት ትሆናለች ፡ እርሱ የተሰወረ መና ሲሆን እርስዋ የመናው መሶበ ወርቅ ትሆናለች፡፡ ለሰብአ ሰገል ‹ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት› እንደተባለላቸው እኛም በሐድንበት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የጌታችንን ምሳሌ ባነበብንበት ሥፍራ ሁሉ እናቱንም እናያታለን፡፡ በዚህም ምክንያት 'ኦ፡ድንግል፡እምሳሌ፡ወትንቢት፡ዘነቢያት' 'ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢታቸውና ምሳሌያቸው አንቺ ነሽ' እንላታለን፡፡ ድንግሊቱን ሁሉም ነቢያት በምሳሌያቸውና በትንቢታቸው እንሥተዋታልና 'ትውልድ ሁሉ' ስትል እነርሱንም ይጨምራል፡፡

'እነሆ እኛም ብፅዕት የሆንችዋን ብፅዕት እንላታለን። የእርስዋም ብፅዕና ዓለም ሁሉ ከሚያቀርብላት ምስጋና ሁሉ የላቀ ነው' ይላል ቅዱስ ያዕቆብ፡፡ 'ብፅዕት ይሉኛል' የሚለውን ቃል ይዞ ድንግል ማርያምን 'ብፅዕት' የሚለውን አንድ ቃል በመናገር ብቻ የምትመሰገን የሚመስለው ታካች ሰው ይኖራል፡፡ 'ያስተበፅዑኒ' ማለት ያመሰግኑኛል

ማለት ሲሆን ብፅዕት መባል የምስጋናዋ ርእስ ነው እንጂ ምስጋናዋ ብዙ ነው፡፡ በትሕትናዋ 'ብፅዕት ይሉኛል' አለች እንጂ ለእርስዋ የሚገባው ልዩ ምስጋና 'ብፅዕት' ብቻ ከማለት ያለፈ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዋ ድንግሊቱ በሚገባ ታውቃለች፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ብፁዕ የተባሉ ሰዎች ሁሉ ለምን ብፁዕ እንደተባሉ በዚያው ተነግሮላቸው ተመስግነዋል፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ 'አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ' ብሎ ስለመሰከረ 'የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ፤ አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ' በማለት ብፁዕ ከመባሉ ጋር ዓለት መሆኑን ፣ እግዚአብሔር አብ ልቡናውን ያበራለት መሆኑን ፣ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ እንደተሠጠው በራሱ በጌታችን አፍ ተመስግኖ ተነግሮታል፡፡ ማቴ. ፲፮፥ ፲፯ ክርስቶስን 'የእግዚአብሔር ልጅ ነህ' ያለው ጴጥሮስ እንዲህ ከተመሰገነ 'የእግዚአብሔርን ልጅ የፀነሰችና የወለደች ፣ አብ የመረጣት' ድንግል እንዴት ያለ ምስጋና ይገርፍላት ይሆን? ትንሣኤውን 'ሳያዩ ያመኑ ብፁዓን ናቸው' ከተባለ እምላክ ሰው ሲሆን ፣ ያለ ወንድ ዘር ሴት

ፀንሳ ስትወልድ ሳታይ ያመነችው ድንግል ምስጋናዋ ምን ያህል ይበዛ ይሆን?

በአንቀጸ ብፁዓን ላይ የተጠቀሱት የብፁዕነት ምክንያቶችም ሁሉ በድንግሊቱ ሕይወት ሊነበቡ የሚችሉ ናቸው:: ማቴ. ፭፥፩-፲፩ 'በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው' ቢል ጌታን በመፅነስ ባለጠጋ ስትሆን በትሕትና ራስዋን 'ባሪያ' ብላ ያደኸየች እርስዋ ናት:: 'የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው' ቢል እንደርስዋ ስለ አምላኩ ያዘነ የለም:: 'የዋሆች ብፁዓን ናቸው' ቢባል 'የዋሂት ርግብ' የተባለችው እርስዋ ናት:: 'ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው' ቢል የግብጽ በረሃ ረሃብና ጥምዋ ይበቃል:: 'ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው' ቢል የልብዋ ንጽሕና እግዚአብሔርን ከማየት አልፋ እንድትወልደው ያበቃት ነው:: 'የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው' ቢል ሰማይና ምድር ፥ ሰውና መላእክት ፥ ፈጣሪና ፍጡር በማሕፀንዋ የታረቁባትና አንድ የሆኑባት እርስዋ ናት:: 'ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው' የግብጽ ስደተኛዋን የሚበልጥ ስደተኛ የለም::

ጌታችን አንቀጸ ብፁዓንን ያበቃው 'ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ' ብሎ ነበር:: ድንግል ማርያም ዛሬም ድረስ

የምትነቀፈውና ሔሮድስ ያሳደዳት አልበቃ ብሎ የምትሳደደው ጌታን ለመውለድ ከመመረጥዋ ውጪ ምንም ጥፋት ኖርባት አይደለም፡፡ መመስገንዋን የሚተቹ ፡ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን የሚንቅፉ ፡ የተሠጣትን ነገር ሁሉ የሚያጣጥሉና ምንም ባታደርግላቸው እንኳን ምን አደረገቻቸው የሚያሰኝ ጥላቻን የሚያሳዩ አሳዛኝ ሰዎች አሉ፡፡ ድንግል ማርያምን መውደድ ያልቻለ ሰው ከፍጡራን ከእርስዋ የተሻለ ንጹሕ ሰው ስለሌለ እርስዋን ጠልቶ ማንን ሊወድ ይችላል? ለጌታ የመጨረሻዋ ቅርብ መሆንዋን ማየት ባይችል እንኳን ስሙ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰ ሰው ያህል እንኳን ጨርሶ እርስዋን ላለመጥራት መሸሽ ምን ይባላል?

ሌላው ቀርቶ 'ማርያም' የሚለው ስምዋ እንኳን ጭራሽ ባይጠራ ደስ የሚለው ሰው ማየትስ ምንኛ ያሳዝናል? 'ማርያም' የሚለው ስም ሲጠራ ቅር የሚልህ ወዳጄ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ በልጅነቱ አፉን የፈታው 'ማርያም' እያለ እየተጣራ መሆኑን ላስታውስህ እወድዳለሁ፡፡ መቼም ለዚህም ጥቅስ እንደማትጠይቀኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም የድንግሊቱን ሥቃይ እንዲህ ሲል በእርስዋ እንደበት ከልጅዋ ጋር ያነጋግራታል፡-

'የእንደበቶች ሁሉ ጌታን እንደበት እንደሌለው ያደረገው ምን ይሆን? ልጂ ሆይ አንተን በድንግልና መፅነሴን ክፉ ሰዎች እየዘለፉ ነው። ቅዱስ ሆይ ለእናትህ አንደበት ሁነኝ ፡ እንተን ከማን እንደፀነስሁህ ይረዱ ዘንድ ተአምርህን አሳይ። ሁሉን የምትወድደው ሆይ እኔ ግን ስለ አንተ ብዬ የተጠላሁ ሆንሁ ፡ ለሰው ልጆች መሸሸጊያ የሆንህ አንተን በመፅነሴ መከራን ተቀበልሁ። እቤቱ በዮናስ ላይ እንደተቆጣ ባሕር በእናትህ ላይ ተቆጥቷል። ሔሮድስ የተባለ ማዕበል የባሕርን ጌታ ሊይዝህ ፈልጓል። የእናትህ ፈጣሪዋ ሆይ ወደት እንደምሸሽ ንገረኝ'[296]

ጌታችን 'ሲነትፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ' እንዳለው ድንግሊቱ በልጅዋ ምክንያት በሚወርድባት እጅግ ብዙ ነቀፋና የሐሰት ንግግር ብቻ ራሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆንላት ክብርዋ ብዙ ነው፡፡

እርስዋን ለማመስገን ግን ያለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት እጅግ ብዙ ነው፡፡ የተመሰገኑ ሰዎችን ሁሉ ማንነት ከእርስዋ ጋር ስናነጻጽረው የክብርዋ ከፍታ የበለጠ ይታየናል፡፡ ለፍቅራችን ስንል እናመሰግናታለን እንጂ የምናቀርብላት ምስጋና ሁሉ ከክብርዋ ጋር የሚደራረስ አይደለም፡

[296] St. Ephrem the Syrian, Hymns On the Nativity, Homily

፡ መላው የሰውነታችን አካል ሁሉ አፍ ቢሆንም ምስጋናዋን ተናግረን መፈጸም አንችልም፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ እርስዋን ለማመስገን እንዲህ ይጨነቃል፡-

'በቅድስና ውበት ስለተሞላችው ንጽሕት ትሕት እናገር ዘንድ እንደበቴ ብቁ አይደለም። ... የተራ ቀለማት መዋሐድ ለማይመጥኗት ለዚህች እጅግ ክብርት እንዴት ያለ ሥዕልን ልሣል? ውበትዋ ከእኔ መጠበብ በላይ ነው ፣ አእምሮዬም እንዲሥላት አልፈቅድለትም። የድንግል ማርያምን ክብርዋን ከመግለጥ ዐሐይን ከነብርሃንዋና ከነሙቀትዋ መሣል ይቀልላል። ምናልባት የዐሐይ ጨረር በሥዕል ሊቀመጥ ይችል ይሆናል። ስለ እርስዋ የሚነገረውን ነገር ግን አሟልቶ ለመስበክ አይቻልም።

እርስዋን ከነማን ጋር መመደብ ይቻላል? ከደናግል ጋር? ከቅዱሳን ጋር? ከንጹሐን ጋር? ካገቡ ሴቶች ጋር? ከእናቶች ጋር? ከአገልጋዮች ጋር? እነሆ የድንግልናን ማኅተም ከወተት ጋር የያዘ ሰውነትዋን እዩ! መውለድዋንም ከታተመ ማኅፀንዋ ጋር እዩ! ከደናግል መካከል ናት ስል ሕፃን ይዛ ስታጠባ

እያታለሁ! ከዮሴፍ ጋር ትኖራለች ስል በጋብቻ ቃልኪዳን እንዳልታሠረች እያለሁ!

ስለ እርስዋ እንድናገር ፍቅር ያስገድደኛል ፤ የክብርዋ ከፍታ ግን ያስቸግረኛል። ከቶ ምን ባደርግ ይሻለኛል? ስለ እርስዋ ለመናገር ብቁ እንዳሆንሁ በግልፅ እናገራለሁ። ከፍቅር የተነሣ ግን ተመልሼ መናገር ያምረኛል።... ሱራፌል ከእሳቱ የሚሸሸጉለትን የእርሱን ከንፈሮች በቡሩካን ከነፈሮችዋ የሳመች እርስዋ የተባረከች ናት! ዓለማት ሕይወትን የጠጡበትን ምንጭ እርሱን ያጠባች እርስዋ የተባረከች ነች'[297]

ድንግል ማርያምን ከትውልዱ ጋር ማመስገንን ብንወድም እንደበታችን ኮልታፋ ምግባራችን ደካማ መሆኑ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ለማመስገን አቅም ያጥረናል፡፡ ሆኖም ኤልሳቤጥን በእርጅና ዮሐንስን በእርግዝና ውስጥ የቃኘ መንፈስ ቅዱስ እንዲቃኘን እንለምናለን፡፡ በድንግል ማርያም የፍቅርዋ እሳት ያነደደው ኢትዮጵያዊው ሊቅ እርስዋንና ልጅዋን ለማመስገን ትረዳው ዘንድ ድንግሊቱን እንዲህ ይላታል፡-

[297] St. Jacob of Serug, On The Mother of God, Homily 1, SVS Press 1998

'የሚመታው ሰው ከሌለ መሰንቆ ተሰቶ ምን ይጠቅማል? በአንድነት ማሕሌት መካከል ካልተነፋስ እንዚራስ ተሰትሎ ምን ድምፅ ሊያሰማ ይችላል? ለበኵርሽ ክርስቶስ እንዚራው እሆን ዘንድ የልቤን መሰንቆ አውታር በመንፈስ ቅዱስ መምቻ ምቺው ፤ በአፌም ላይ እፍ በዪብኝ። ልትሶዪን መልሰሽ ደስ አሰኚኝ። ማቴን ቅደጂና ደስታን አስታጥቂኝ። የኃጢአቴን ሽታ አርቂው ፤ በሽቱሽ መዓዛ ቀቢኝ። መቶሸሼን እንጽተሽ በልጅሽ ደም ቀድሺኝ' ምንት፡ ረባኁ፡ ለመሰንቆ፡ ጽኑዕ፡ ለእመ፡ አልቦ፡ ዘይሰነቅዎ፡፡ ወምንተ፡ ይደምፅ፡ ንቃወ፡ እንዚራ፡ ዘስዮል፡ ለእመ፡ ኢተነፍሐ፡በድርገታተ፡ማሕሌት፡፡በድኅንፃ፡መንፈስ፡ ዝብጢ፡ አውታረ፡ መሰንቆሁ፡ ለልብየ፡፡ ወእስተንፍሊ፡ ውስተ፡ አፉየ፡፡ ከመ፡ እኩን፡ እንዚራሁ፡ ለበኵርኪ፡፡ ሚጢ፡ ላህየ፡ ወአስተፍስሕኒ፡፡ ሥጥጢ፡ ሰቅየ፡ ወሐሪተ፡ አቅንትኒ፡፡ አእትቲ፡ ጺአተ፡ ኃጣውእየ፡ በመዓዛ፡ዕፍረትኪ፡መዝሙዝኒ፡፡አንጽሒ፡ርስሐትየ፡ ወበደመ፡ወልድኪ፡ቀድሰኒ'[298]

## ➢ ታላቅ ሥራን ለእኔ አድርጎአል

---

[298] ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ፤ እሴብሕ ጸጋኪ ፤ ወእትጋነይ ለኪ

ድንግል ማርያም 'ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራን ለእኔ አድርጎአልና' በማለት 'ነኪር፡ በእንቲአኪ፡ ሀገረ፡ እግዚአብሔር' 'የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ በአንቺ የከበረ ነገር ይባላል' ተብሎ የተነገረው ስለ እርስዋ እንደሆን አስረዳችን፡፡ መዝ. ፹፮፥፫

እመቤታችን 'ለእኔ አድርጎአልና' 'እስመ፡ ገብረ፡ ሊተ' ብላ በምስጋና ቃል የተናገረችበት በእርስዋ ያደረገው ታላቅ ሥራ ብዙ ስለሆነ ነው፡፡ በእርስዋ ውስጥ የተፈጸሙት ታላላቅ ተአምራት ብዙ ናቸው፡፡

'ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው ፤ እርሱም እናቱን ፈጠረ' 'ድንግል፡ ወለደቶ፡ ለገባሬሃ፡ ፤፡ ወለሊሁ፡ ፈጠረ፡ ወላዲቶ'[299] እንደሚል ፈጣሪን ለመውለድ መብቃት በድንግሊቱ የተደረገ ታላቅ ሥራ ነው፡፡

ያለ ወንድ ዘር መፅነስ ሌላው ታላቅ ነገር ነው፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም 'የእግዚአብሔር ቃል በጆሮዋ ገብቶ በማሕፀንዋ ተፀነሰ' እንዳለው በቃል ብቻ የፀነሰች ከድንግል በቀር ማን ናት? በወለደች ጊዜም 'ሳታምጥ ወለደች ፤ ምጥም ሳያገኛት ወንድ ልጅን ወለደች' የሚለው ቃል የተፈጸመላት እርስዋ ነበረች፡፡ ኢሳ. ፷፮፥፯ ያለ ወሊድ ሕማም መውለድዋን ለመግለፅም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት

---

[299] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ፤ ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፵፮፥፱

ሥዕላት ሥርዓት የጌታችን ልደት ሥዕላት ሲሣሉ ድንግሊቱ በወለደች ጊዜ እንደተኛች ተደርጋ አትሣልም፡፡

ተነግሮ የማያልቅ የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ በእርስዋ ላይ ሆኖአል፡፡ እግዚአብሔር ታላላቅ ተአምራትን አደረገ በተባለባቸው ሥፍራዎች ከሆነው በላይ በእርስዋ ዘንድ የሆነው የበለጠ ነው፡፡ ምክንያቱም ከታላላቅ ተአምራት ሁሉ የሚበልጥ ተአምር በእርስዋ ላይ ተፈጽሞአል፡፡ 'እነዚህ ተአምራት ምንድርን ናቸው ትለኝ እንደሆን እኔም እንዲህ እልሃለሁ። ያለዘር ፅንስ እንደት ያለ ነው? ያለ እዋላጅ መውለድ ፣ ያለ ምጥና ያለ ድንግልና መጥፋት መውለድስ እንደት ያለ ነገር ነው?' 'ወሶበሂ፡ትቤ፡ምንት፡እማንቱ፡ተአምራት፡እነሂ፡እብለከ፡ ይእዜ፡ ምንት፡ ውእቱ፡ ፅንስ፡ ዘእንበለ፡ ዘርእ፡ ወወሊድ፡ ዘእንበለ፡ መወልዲት፡ወዘእንበለ፡ሕማም፡ወዘእንበለ፡ይማስን፡ድንግልናሃ'

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለሔሮድስ ስለ ጌታ መወለድ የተናገሩትን መምህራን አይሁድ እንዲህ ይላቸዋል ፦

'ንግረኒ፡እስኩ፡አይሁዳዊ፡ወዜንወኒ፡መኑ፡ዝ፡ዘወለደቶ፡ድንግል፡ ወአጠይቀኒ፡በከመ፡አጠየቆ፡ለሔሮድስ፡፡፡እንተሰ፡ኢታጠይቀኒዮ፡ሊተ፡ እላ፡ነገርኮ፡ለዝኩ፡ከመ፡ይቅትሉ፡ወለምንትኑ፡ኢትነግረኒ፡ሊተ፡ከመ፡ እስግድ፡ሎቱ''አይሁዳዊ ሆይ እስቲ ንገረኝ ፤ ድንግል የወለደችው ይህ ማን ነው? ለሔሮድስ እንዳስረዳኸው ለእኔም አስረዳኝ። አንተ ግን ለእኔ

አታስረዳኝም ለእርሱ ግን እንዲገድለው ብለህ ትነግረዋለህ። ለእርሱ እንድሰግድለት ለእኔ የማትነግረኝ ለምንድርን ነው?'[300] ብሎ እንደተናገረ እግዚአብሔር በእርስዋ ያደረገው ታላቅ ሥራ ሊሰገድለት የሚገባ ድንቅ ተአምር ነው፡፡

በድንግሊቱ የሆነው ሌላ ድንቅ ነገር እናትነትና ድንግልና በእርስዋ መገኘቱ ሲሆን ድንግል ሆና ሳለች ከእርስዋ ጡቶች ወተትን መጥባቱ ሌላው ድንቅ ነገር ነው፡፡ ቅዱስ ሰኑትዩ 'እስመ፡ናሁ፡ድንግል፡ኮነት፡ ዘታውኅዝ፡ ሐሊበ፡ ምስለ፡ ድንግልናሃ፡፡፡ ወዝንቱ፡ ግብር፡ ይትሌዓል፡ እምልቡና፡እጓለ፡እመ፡ሕያው፡እስመ፡ልማዶንሰ፡ለአንስት፡ኢያውኅዝ፡ ሐሊበ፡ዘእንበለ፡ተካቤ፡ብእሲ'፡'እነሆ ድንግል ከድንግልናዋ ጋራ ወተትን የምታፈስ ሆነች። ይህ ነገር በሰው ልጅ ልቡና ከመመርመር የራቀ ነው። ሴቶች ለልማዳቸው ከወንድ ሳይገናኙ ወተትን አያፈሱምና ነው'[301]

> ## ሰሙም ቅዱስ ፤ ምሕረቱ ለልጅ ልጅ

ድንግሊቱ የእግዚአብሔርን ስም 'ቅዱስ ነው' አለች፡፡ ሌሎች ፍጡራንን ቅዱስ ብለን ከስማቸው አስቀድመን 'ቅዱስ' የሚል ቃል ቀጽለን ቅድስናቸውን እንመሰክራለን፡፡ እግዚአብሔር ግን ስሙ ራሱ

---

[300] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ፤ ንባቡና ትርጓሜው ፤ ፷፮፥፷፭
[301] ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ ዘሰኑትዩ ፶፱፥፲፮

ቅዱስ ነው፡፡ ቅዱስ ማለት የተለየ የከበረ የተመሰገነ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስም ከሌሎች ስሞች ሁሉ የተለየ ስም ነው፡፡

የእርሱ ስም የመጠሪያ ስም (ስመ ተጸውኦ) ብቻ አይደለም፡፡ የእርሱ ስም ተጠርቶ ድውይ ይፈወሳል ፣ ሙት ይነሣል፡፡ የእርሱ ስም አጋንንትን ያርዳል ያንቀጠቅጣል ፣ የጣዖት አምላኪዎችን ልብ እንደ ሰም ያቀልጣል፡፡ ድንግሊቱ ስሙም ቅዱስ ነው እንዳለች ስሙ በእምነት የሚጠሩትን የሚቀድስ ስም ነው፡፡ የእርሱ ስም የሚጠራ ብቻ ሳይሆን በጉልበት ሁሉ የሚሰገድለት ስም ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስም በከንቱ የሚጠራውን ከበደል የማያነጻ በፍርሃት 'ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና በቃል መነገሩ ፣ በልቡና መታሰቡ ከፍ ከፍ ይበልና' ብሎ ለሚጠራው ሰው ግን ይቅርታን የሚሰጥ 'ስለ ስምህ ብለህ አድነን' 'አቤቱ ለእኛ አይደለም ለስምህ ነው' ተብሎ የሚለመንበት ቅዱስ ስም ነው፡፡

እመቤታችን ከስሙ ቅድስና ጋር አብራ 'ለሚፈሩት ምሕረቱ ለልጅ ልጅ ነው' ብላም የእግዚአብሔርን የምሕረቱን ብዛት መሰከረች፡፡ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለልጅ ልጅ ምሕረት ያደርጋል ማለት እንዴት ነው? አንድ ሰው በአባቱ ፣ በአያቱ ፣ በቅድም አያቱ ምክንያት ምሕረትን እንዴት ሊያገኝ ይችላል? አንድስ አባት የልጅ ልጆቹ ድረስ

የሚደርስ ምሕረትን እንዴት ሊያቆይ ይችላል? እስከ ሰባት እስከ ዐሥራ ሁለት ትውልድ ድረስ እምራለሁ የሚሉ ቃልኪዳኖች እንዴት ናቸው?

ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምራ ያደገችው ድንግል ማርያም 'ምሕረቱ ለልጅ ልጅ ነው' ከማለትዋ ከዘመናት በፊት ራሱ እግዚአብሔር 'በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፣ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ' ነኝ ብሎ ተናግሮ ነበር። ዘጸ. ፳፥፮

እኛ እግዚአብሔር እስከ ሰባት ትውልድ ይምራል ሲባል ለማመን ቢቸግረንም እርሱ ግን ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ እንደሚያደርስ በቃሉ ተናግሯል። ይህም ምሕረቱ ከእኛ አእምሮ በላይ መሆኑን ያሳያል። በቃሉ ላይ ለቅጣት ሲሆን እስከ አራት ትውልድ ድረስ እቀጣለሁ ሲል ለምሕረት ግን እስከ ሺህ ማለቱ 'መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ' አምላክ መሆኑን ያሳያል። በእርግጥም የእግዚአብሔር ምሕረት ከእግዚአብሔር ቁጣ እጅግ የበለጠ ነው። 'ምሕረቱ ለዘላለም ነውና' ተብሎ የሚመሰገነው አምላክ ቁጣው ግን ለዘላለም አይደለም። 'ቁጣው ለጥቂት ጊዜ ነው ፤ ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን ነው' 'ቁጣውን

ለዘላለም አይጠብቅም' የሚሉት ቃላት ይህን ያሳያሉ:: ኤር. ፫፥፲፪ ፥መዝ. ፹፱፥፭

ምሕረት ለልጅ ልጅ የሚደርሰው ከእግዚአብሔር ይቅር ባይነት በተጨማሪ የልጅ ልጅ የተባሉት ሰዎች በአባቶቻቸው መንገድ ሲሔዱ ብቻ ነው:: ባለቤቱ 'ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል' ብሎ እንደተናገረ በወላጆቻቸው የጽድቅ ጎዳና መጓዝ ለሚችሉ ሁሉ ምሕረቱ ለልጅ ልጅ ነው:: ሕዝ. ፲፰፥፩-፰

## ➢ ኃይልን በክንዱ አደረገ

ድንግል ማርያም እግዚአብሔር 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' አለች፡ ፡ የእግዚአብሔር ክንዱ ምንድርን ነው? እግዚአብሔር እንደ ሰው እጅ እግር ክንድ ጉልበት አለው ማለት ነው? 'ሰው በእግዚአብሔር አርኣያና ምሳሌ ተፈጠረ' የሚባለው ስለዚህ ይሆንን? የሚል ጥያቄን ያስከትላል::

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረው በሥጋው ሳይሆን በነፍሱ ነው:: ሰውም እግዚአብሔርን የሚመስል ሆኖ የተፈጠረው ለባዊት ፥ ነባቢት እና ሕያዊት በሆነች ነፍሱ እንጂ በሥጋው አይደለም:: ቅዱስ ባስልዮስ ይህን ሲያስረዳ ፦

'የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ምሳሌ ተፈጠረ የሚባለው ስለ ነፍሱ እንጂ ስለ ሥጋው አይደለም። እንደዚያ ቢሆን በተፈጥሮ አካል ጎድሎት የሚወለድ ሰው ወይንም ከጊዜ በኋላ አካሉ የጎደለ ሰው የእግዚአብሔር ምሳሌነት የጎደለው በሆነ ነበር'

የሰው አርአያ - እግዚአብሔርነት በሥጋ ባይሆንም እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የሰው አካላት እንዳለው ሆኖ ሲናገር እናገኘዋለን:: 'እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም' 'ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዓይንን የሠራው አያይምን' 'እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ' የሚሉት ቃላት እግዚአብሔርን በሰው አካልና ስሜት የሚገልጹ ቃላት ናቸው:: ኢሳ. ፶፱:፩ ፤ መዝ. ፺፬:፱ ፤ ዘፍ. ፮:፮ ይህ ግን የሰውን ድካሙን የሚያውቀው እግዚአብሔር አምላካዊ አእምሮ ድካመ ሰብእ (Divine consideratness) ማሳያ ሲሆን በሥጋ ከመገለጡ በፊት የተደረገ የቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ሥጋዌ ነው::

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ይህን እንዲህ ይገልጸዋል :-

'የሰውነትን አካላት ስም ሲለብስ ለፈቀደ ለእርሱ ምስጋና ይገባል። መጽሐፍ ስለ ጆሮው መናገሩ እግዚአብሔር እንደሚሰማን ለማስተማር ነው። ስለ ዓይን የሚናገረው

እንደሚያየን ለመግለጽ ነው። ምንም እንኳን ቁጣና ጸጸት በእርሱ ዘንድ ባይኖርም እነዚህም ነገሮች የእርሱ ጠባይ ሆነው እንዲጠራባቸው ስለእኛ ደካማነት ሲል ፈቀደ። እግዚአብሔር እነዚህን የሰው ልጅ መጠሪያ ስሞች ባይቀበል ኖሮ የሰው ልጅ ከፈጣሪ ጋር መነጋገር እንኳን ባልቻለ ነበር። እርሱ ግን የእኛ በሆኑት ነገሮች በኩል ወደ እኛ ቅርብ ሆነ። እኛ የእርሱን አምላካዊ ሕያውነት እንላበሰው ዘንድ እርሱ የእኛን ቋንቋ ለበሰ'[302] ብሏል፡፡

ሶርያዊው ማር ቅዱስ ኤፍሬም ይህን እግዚአብሔር የሰው ልጆች እርሱን እንዲረዱት ለማድረግ በመጽሐፍ ቅዱስ የእነርሱ ዓይነት ውስን አካል እንዳለው መስሎ 'እግዚአብሔር መጣ ሔደ ፡ ወጣ ወረደ ፡ በእግሩ ኮቴ ተመላለሰ ወዘተ' ተብሎ መጠራቱን ያፍ ነባቢትን (Parrot) ንግግር ከሚያስተምሩ ሰዎች ድርጊት ጋር ያነፃፅረዋል፡-

'ተናጋሪ ወፍን ንግግር የሚያስለምድ ሰው ከወፍዋ ፊት መስታወትን ያቆማል። ከመስታወቱ ጀርባ ሆኖም ድምፅን ያሰማል። ወፏ ድምፁን ወደ ሰማበት አቅጣጫ ሲያይ የገዛ ራሱን ፊት ያያል። ሌላ ተናጋሪ ወፍ ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ እንደሆነ ይመስለዋ። በዚህ መንገድም መናገርን

[302] St. Ephrem the Syrian, Hymns on Faith, 31.1-3

ያስተምረዋል። እግዚአብሔርም በመለኮታዊ ኃይሉ በሁሉ የሞላ አምላክ ሲሆን ለእኛ በምናውቀው መጠን ራሱን እያቀረበ በራሳችን ውስጥ እርሱን እንድንናውቀው ያደርጋል'[303]

ወደ ድንግሊቱ ጸሎት ስንመለስ 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' ያለችው ንግግር ከላይ ካየናቸው እግዚአብሔር እንደ ሰው ከሚገለጽበት አገላለጽ አንዱ ነው:: ሆኖም ድንግሊቱ ይህን ጸሎት ያደረገችው እግዚአብሔር በሰብአዊ ቋንቋ ተጠርቶ ከመነገር አልፎ ፍጹም ሰው የሆነበት ወቅት ነውና ትርጓሜው ከዚያም የጠለቀ ነው:: የድንግሊቱ 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' የሚል ንግግር ስለ አብ ቢሆን በልጁ ኃይልን አደረገ ፣ ስለ ወልድ ቢሉ በሥልጣኑ ኃይልን አደረገ ማለት ነው::

ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚጠራባቸው ብዙ ስሞች አንዱ የአብ እጁና ክንዱ መባል ነው:: ክንድ ከሰውነት ሳይለይ የወደቀውን ነገር እንደሚያነሣ እግዚአብሔር አብ የወደቀውን የሰው ልጅ ለማንሣት ከእርሱ ሳይለይ የላከው ክንዱ አንድያ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: 'ልዑል ክንዱን ሰደደልን' 'ፈነወ፡ ለነ፡ መዝራዕቶ፡ ልዑለ' እንዳለ ሊቁ::

---

[303] St. Ephrem the Syrian, Hymns on Faith, 31.4-7

ይህ ክንድ ነቢዩ ኢሳይያስ 'የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል?' ብሎ የተናገረለት የአብ ክንድ ነው፡፡ ኢሳ. ፶፫፥፩ ይህ ክንድ እግዚአብሔር 'ሰውም እንደሌለ አየ፡ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፤ ጽድቁም አገዘው' ተብሎ የተነገረለት ክንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢሳ. ፶፱፥፲፮ 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' ማለትም የማዳኑን ሥራ በልጁ በወልድ አደረገ ማለት ነው፡፡ ቅዱሳን ያችንም 'ወአድኃንኮሙ፡ ለሕዝብከ፡ በመዝራዕትከ'፡ ፲፡ ሐርከ፡ ውስተ፡ ሲኦል፡ ወአዕረገ፡ ጼዋ፡ እምነህየ'፡'ህዝብህን በክንድህ አዳንኻቸው ፤ ወደ ሲኦል ሔድህ ፤ ምርኮንም አወጣህ' በማለት ለአብ ክንድ ለወልድና ለሥልጣኑ ኃይል ምስጋናን ያቀርባል፡፡

ድንግሊቱ በክንዱ ያደረገውን ስትዘረዝር 'በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞችን በታተናቸው ፤ ብርቱዎችንም ከዙፋናቸው አዋረዳቸው ፤ የተዋረዱትንም ከፍ ከፍ አደረጋቸው ባለጠጎችንም ባዶ እጃቸውን ሰደዳቸው' አለች፡፡

ልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይሉ የበታተናቸው 'በልባቸው አሳብ የሚኮሩ ትዕቢተኞች' ዲያብሎስና ሠራዊቱ ናቸው፡፡ የሚያኮራቸው ማንነታቸው ሳይሆን ራሳቸውን እንደ አምላክ አድርገው ያዩበት

የልባቸው አሳብ ነበር:: እለቃቸው ዲያብሎስ 'በልብህ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ አልህ' 'ልብህ ኰርቶአል አንተም። እኔ አምላክ ነኝ፣ በእግዚአብሔር ወንበር በባሕር መካከል ተቀምጫለሁ ብለሃል' 'በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል' በታላት ጥበብህና በንግድህ ብልጥግናህን አብዝተሃል በብልጥግናህም ልብህ ኰርቶአል' ተብሎ ተደጋግሞ የተነገረለት ትዕቢተኛ ነው:: ኢሳ. ፲፬፥፲፫ ፤ ሕዝ. ፳፰፥፪፥፮፥፲፯

እግዚአብሔር ዲያብሎስንና የእርሱን የትዕቢት መንገድ የተከተሉትን አጋንንት አስቀድሞ ከክብራቸው አዋርዶአቸው ነበር::

አሁን ደግሞ 'ኃይልን በክንዱ አደረገ' በምድር ላይ ሠልጥነው የነበሩትን አጋንንት በኪደተ እግሩ በታተናቸው ፡ 'በማይታዘዙት ልጆች ላይ የሚሠራውን መንፈስ አለቃ ፣ በአየር ላይ ሥልጣን ያለውን አለቃ' ዲያብሎስንና የአየር አጋንንትን ደግሞ ክርስቶስ ከምድር ከፍ ብሎ በመስቀሉ በታተናቸው:: ኤፌ. ፪፥፩ የአለቃቸውን 'የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ተገለጠ' ፣ በሲኦል ያሉትን ቅጥራችቸውን ሰባብሮአልና 'ትዕቢተኞችን በታተናቸው' መባል ድንግሊቱ ለፀነሰችው የልዑል ክንድ ይገባዋል:: ፩ዮሐ. ፫፥፰ ፤ መዝ. ፺፩፥፲፫

በሰው ልጅ ላይ ብርቱዎች የነበሩትን አጋንንትንም የሰው ልጅን ልብ ዙፋን አድርገው ተቀምጠው እንዳልነበር የአብ ክንዱ ክርስቶስ

'በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን እያወጣ' ከዙፋናቸው የሰው ልጅ ሰውነት አዋረዳቸው፡፡ ሉቃ. ፲፩፥፳ በአጋንንት አሽከላ ተይዘው ሲሰቃዩ የነበሩትን እስከ ሰባት አጋንንት እንደወጡላት እንደ መግደላዊት ማርያም ያሉትን በአጋንንት ተይዘው በሰው ፊት 'የተዋረዱትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው' ከአጋንንት እሥራት ተላቅቀው ቅዱሳን እስከመሆን ፡ የትንሣኤው ዜና ሰባክያን እስከመሆን ከፍ ከፍ አደረጋቸው፡፡ ሉቃ. ፰፥፪ ፤ ማር. ፲፮፥፱

የሰዎችን ነፍሳት ይዘው ሲያስጨንቁና የእነርሱ ገንዘብ ያልሆኑትን ምርኮኞች በሲኦል ይዘው ባለጠጋ ሆነው የነበሩትን አጋንንት 'አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለም፤ ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል' እንደተባለ ዲያብሎስን 'በመስቀሉ ጠርቆ ከመንገድ ካስወገደ በኋላ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፈፈ' ነፍሳትን ሁሉ ማርኮ ወደ ገነት በመውሰድ 'ባለጠጎች' አጋንንትን 'ባዶ እጃቸውን ሰደዳቸው' ማር. ፫፥፳፯ ፤ ቆላ. ፪፥፲፬-፲፭

## ➢ ለአባቶቻችን ለአብርሃምና ለዘሩ

ድንግል ማርያም 'ለአባቶቻችን ለአብርሃምና ለዘሩ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ የተናገረውን ቃልኪዳኑን አስበ ፤ እስራኤል ባሪያውንም

ተተብለ' በማለት ጸሎትዋን አሳረገች:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ ተምራ ያደገችው ፡ ሰውነትዋን የሥላሴ ማደሪያ እንዲሆን ድንኳን አድርጋ የሠጠችው እመ ብዙኃን ማርያም ሥላሴን በቤቱ ተቀብሎ ያስተናገደውን አበ ብዙኃን አብርሃምን በጸሎትዋ ማሳረጊያ ላይ ጠራችው:: ልጅዋ 'የአብርሃም ልጅ' ተብሎ የሚጠራ የአብርሃም ቃልኪዳን መፈጸሚያ ነውና ድንግሊቱ 'ለአብርሃምና ለዘሩ የተናገረውን ቃልኪዳን አሰበ' አለች::

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃልኪዳን 'በእውነት በረከትን አባርክሃለሁ፣ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ፤ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ' የሚል ነበር:: ዘፍ. ፳፪፡፲፯-፲፰ ይህ አምላካዊ ቃልኪዳንም ተፈጽሞ የአብርሃም ዘሩ በዝቶ ዐሥራ ሁለት ነገድ ሆኖ ፡ በይስሐቅም በእስማኤልም በኩል አብርሃምን አባታችን የሚሉ ብዙኃን ተፈጠረው ለአብርሃም የተገባው ቃልኪዳን ተፈጽሞአል::

ድንግል ማርያም በጸሎትዋ 'ለአብርሃምና ለዘሩ የተናገረውን ቃልኪዳን አሰበ' ብላ መናገርዋ ለአብርሃም ከዘሩ መብዛት ሌላ የተፈጸመለት አንዳች ቃልኪዳን እንዳለ ያሳያል:: በእውነትም እግዚአብሔር ለአብርሃም የሠጠው ትልቅ ቃልኪዳን እንደ ከዋክብት

ለማያውያን ፡ እንደ አሸዋ ምድራውያን ከሆኑ ጻድቃንና ኃጢአተኛ ዘሮቹ በላይ ክርስቶስ ከእርሱ ዘር መወለዱና 'የአብርሃም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ' ተብሎ መጠራቱ ነው፡፡ ማቴ.፩፡፩

ድንግሊቱ ለአብርሃምና ለዘሩ አለች እንጂ 'ለአብርሃምና ለዘሮቹ' አላለችም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል:-

> ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር። ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን። ለዘርህም ይላል፣ እርሱም ክርስቶስ።
> ገላ. ፫፡፲፮

ለአብርሃም 'በዘርህ አሕዛብ ይባረካሉ' ተብሎ የተገባለት ቃልኪዳን የተፈጸመውም አሕዛብ በአብርሃም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በረከት በተኅበኙ ጊዜ ነው፡፡ አብርሃም በሥጋ አባት የሆነው 'አብርሃም አባት አለን' እያሉ ለሚመኩ ለተገረዙት እስራኤላውያን 'የኪዳን ልጆች' ብቻ ነበር፡፡ ሉቃ. ፫፡፱ ፤ ሐዋ. ፫፡፳፭ እነርሱን ግን 'የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር' የሚያሰኝ ሕይወት ነበራቸው፡፡

ክርስቶስ እንዲህ ብሏቸዋል :-

'የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ አይኖርምና ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም' ዮሐ. ፰፥፴፯-፵

በእርግጥም አብርሃም በዘመኑ የተገለጠለትን የእግዚአብሔር ሰው መልከ ጼዴቅን ሲያገኝ በአክብሮት አነጋግሮ ከእንጀራና ወይን ጋር ቡራኬን በትሕትና አጎንብሶ ተቀበለ ፡ አሥራትንም ከፈለው እንጂ ሊገድለው አልፈለገም ነበር፡፡ የአብርሃም ልጆች ነን የሚሉት አይሁድ ግን 'እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው' ኢየሱስ ክርስቶስ ከእንጀራና ወይን በላይ የገዛ ሥጋና ደሙን እንካችሁ ብሎ ሲመጣ ሊገድሉት ፈለጉ፡፡ ዘፍ. ፲፬፥፲፯-፳ ፤ ዮሐ. ፮፥፶፪

አብርሃም ለመልከጼዴቅ በከፈለው አሥራት በወገቡ ያሉትን ከእርሱ የሚወለዱትን እነሌዊን ወክሎ አሥራትን ሲሠጥ የአብርሃም ልጆች ነን ባዮቹ አይሁድ ግን ለክርስቶስ በአሥራት ፈንታ እስራትን ከፍለው በወገባቸው ያሉትን ልጆቻቸውንም በግድያቸው ለማሳተፍ 'ደሙ

በእኛና በልጅ ልጆቻችን ላይ ይሁን' አሉ፡፡ ስለዚህ ጌታችን 'አብርሃም እንዲህ አላደረገም' አላቸው፡፡ ማቴ. ፰፺፥፰፳

'ከእነዚህ ድንጋዮች እግዚአብሔር ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል' እንዲል በዘሩ በክርስቶስ ምክንያት ግን ድንጋይ ልብ የነበራቸውና በክርስቶስ አዲስ ልብ ያገኙ የአሕዛብም ሁሉ አባት ሆኗል፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ የተመረጠው፡-

'ለተገረዙትም አባት እንዲሆን ነው፤ ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው' 'እርሱም፦ ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በእምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው' ሮሜ. ፬፥፲፩፥፲፮

ድንግሊቱ 'ወተወክፎ፡ ለእ͞ኤል፡ ቍልዒሁ' 'ልጁን እስራኤልን ተቀበለ' ብላ መናገርዋ እግዚብሔር 'የበኵር ልጄ' ብሎ የጠራውን 'ልጁን እስራኤልን' ከእርሱ ሰው ሆና በመወለድ የቀደመ ቃልኪዳኑን እንዳልረሳና እስራኤል የተባለ 'የያዕቆብን ውበት ወደደ' የተባለው ቃል መፈጸሙን የሚያስረዳ ነው፡፡ ዘጸ. ፬፥፳፫ ፡ መዝ. ፵፯፥፬

እርሱ እስራኤልን ልጆቼ ብሎ 'የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም' እነርሱ ይመጣል ብለው ባሰቡት መንገድ አልመጣምና አልተቀበሉትም፡፡ ሆኖም እርሱ ለአብርሃምና ለዘሩ የተናገረውን ቃል አልረሳም፡፡ 'የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለምና፡፡ እነዚህ ከእስራኤል የሚወለዱ ሁሉ እስራኤል አይደሉምና ፤ የአብርሃምም ዘር ስለሆኑ ሁላቸው ልጆች አይደሉም' ሮሜ ፱፡፮

ድንግል ማርያም በኤልሳቤጥ ቤት ውስጥ ያደረገችውን ጸሎትዋን 'ለአብርሃምና ለዘሩ የተናገረውን ቃልኪዳኑን አሰበ' ብላ አሳረገች፡፡ እውነት ነው ፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃልኪዳን አልረሳምና የተናገረውን ፈጸመ፡፡ እኛ ደግሞ ለአንቺ እና በልጅሽ ክርስቲያን ተብለን ለተጠራን ለዘሮችሽ የተናገረውን ቃልኪዳን አስቦ እንዲምረን እንማጸናለን፡፡

ጌታ ሆይ ለአብርሃም ከገባህለት ቃልኪዳን ለእናትህ የማልከው ቃልኪዳን አይበልጥምን? 'ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ' ብለህ ከጠራኸው ከአብርሃም ይልቅ 'ወገንሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ' ብለህ የመረጥሃትና ከወላጆችዋ እቅፍ ተነጥላ በቤተ መቅደስህ ያደገችው የሦስት ዓመትዋ መናኝ ድንግል ማርያም አትበልጥምን? ዘፍ. ፲፪፡፩ ፣ መዝ. ፵፬፡፲ አብርሃም የተቀበለህ

በድንጓኣ ነበር ፥ እርስዋ ግን የተቀበለችህ ሰውነትዋን ድንኳን አድርጋ ነበር፡፡ አብርሃም ከልጁ ፍቅር ለአንተ ያለው ፍቅር በልጦበት ልጁን ሊሠዋልህ ፈቅዶ ሳለ አስቁመኸው ነበር፡፡ ይህች ድንግል የእግዚአብሔር በግ የሆንህ አንተ በመስቀል ላይ መሥዋዕት ስትሆን በኀዘን ዕንባ የቆሰለች ናትና ለእርስዋ የገባኸውን ኪዳነ፡ምሕረት (የምሕረት ቃልኪዳን) አስበህ እኛንም ይቅር በለን፡፡ 'በእንተ፡ማርያም፡መሐረነ፡ክርስቶስ' 'ክርስቶስ ሆይ ስለ ድንግል ማርያም ብለህ ማረን'

'ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለእምላክ ምስጋና ይሁን'
፪ቆር. ፪፥፲፬

ስለ የብርሃን እናት

የቤተ ክርስቲያኒቱ አበው

ሊቃውንትና መምህራን አስተያየቶች

'የአምላክ ሰው መሆን ለምንድነው? ካልን ዓለምን ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ማውጣት ነው:: ዜና ሥጋዌን የተናገረ ዐቢይ ነቢይ ኢሳይያስ "በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው" ኢሳ. ፱፥፪ የተባሉት ሕዝቦች እኛ መሆናችን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ታውቋል ፩ጴጥ.፪፥፱ በኃጢአት ላይ ሞት ተጨምሮብን በመቃብር ላይ ሲኦል መውረድ ተከትሎን እንጨነቅ ለነበርን ሕዝቦች ብርሃንን ይዛ የተገኘች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: ነቢያት "ፈኑ ብርሃነከ፤ ብርሃንህን ላክ" መዝ. ፵፪፥፫ ብለው ደጅ ሲጠኑት የነበረው ብርሃን በዕለተ ረቡዕ የተፈጠረውን ወይም ለመላእክት በዕለተ ፍጥረት የተገለጠላቸውን ብርሃን አልነበረም፤ ቅዱስ ያሬድ "ብርሃነ ሕይወት" ብሎ የሚጠራውን የማይጠፋ የዘለዓለም ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው እንጅ::

አባ ጊዮርጊስ ኆኅተ ብርሃን ሙጻአ ፀሐይ፤ የብርሃን መስኮት የፀሐይ መውጫ" ሲላት መስማት ነፍስን ከእንቅልፍ የሚያነቃ ምስጋና ነው:: በውዳሴ ማርያም "እመ ብርሃን አንቲ" የሚለውን ቃል ስደገም የሚሰማኝ ደስታ በቃል ልነግራችሁ አልችልም:: ጸሎቱን አቁሜ ፀሐይን እያታለሁ፤ ይች ፀሐይ ከሰጠችን ብርሃን ይልቅ ያገኘ ብርሃን ይበልጣል ብየ እመቤታችንን አደንቃታለሁ:: በትምህርት ቤት ሕይወቴም "በእንተ ስማ ለማርያም ስለ እመብርሃን" የሚለውን ቃል እወድደው ነበር:: እመብርሃን በግለቴ የሕይወቴ መንገድ ፍንትው ብሎ ይታየኛል:: ሊቁ አባ ጊዮርጊስ "ፀሐይ ወወርኅ

ኢቀደሙኪ" ሲላት የተፈጥሮ አይደለም፡ "በጥልቁ ላይ ነበረ" የተባለውን ጨለማ ሳይሆን ለሰው የሚያበራውን ብርሃን ዘበአማን ክርስቶስን በማስገኘት የሚቀድማትም የሚከተላትም የሌለ ስለሆነ ነው እንጅ፡፡

ዛሬ እጅግ የተወደደው የቤተ ክርስቲያናችን መምህር ዲያቆን ሄኖክ "የብርሃን እናት" የሚል መጽሐፍ ጽፎ እንዳነበው ሲጋብዘኝ ደስታዬን አበዛው፡፡ በስሙ የተደሰትሁበትን መጽሐፍ እመቤታችን ምሥጢር ክልቡናው፡ ነገር ከአንደበቱ፡ ብዕር ከእጁ አስማምታለት እንደጣፈጠኝ በተድላ በደስታ ሰነበትሁ፡፡ እርሱ በጻፈው ላይ ማታ ማታ ጣዕመ ነገር በይቅርታዋ የጨመረችለት ይመስለኛል፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ባሰብሁ ጊዜ እግዚአብሔር ሰውን ያከበረበትን ክብር አደንቃለሁ:: የእግዚአብሔርን ሥጦታ በመቀበል ፍጽምት ናትና ለእግዚአብሔር ሥጦታ በማቅረብም ፍጽምት ናት:: ሌላው ለእግዚአብሔር ሥጦታ ላቅርብ ባለ ጊዜ ከባሕርዩ ውጪ የሆነ ወይም የከንፈሩን ፍሬ ያቀርባል:: ድንግል እመቤታችን ግን ነፍስና ሥጋዋን አቀረበች::

ወንድሜ ሆይ! እግዚአብሔር ዋጋህን ያብዛልህና ምስጋናዋ እንደ ወንዝ በሚፈስበት በኤፍሬም ጉባኤ ፡ በሥሩግ መንበረ ጵጵስና ፡ በኤፌሶን ጉባኤ በመንፈስ ተገኝቼ እንድሰማቸው ስላደረግኸኝ አመሰግናለሁ::

ዓለም የተፈጠረው ለአዳምና ለሔዋን ነው:: ብሉይና ሐዲስ የተጻፈውም ለድንግል ማርያምና ለክርስቶስ ነው:: ነቢያት በትንቢታቸው

ለይተው አልተዋትም:: ሙሴ የመገናኛ ድንኳኑን ሲሠራ ያለ እርሱየ አልሠራውም:: ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ እንደገለጥከው መጽሐፍን ማንበብ ለማይችል ዓለም በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈች መጽሐፍ እመቤታችንን ብንሠጠው ማንበብ አልቻለም::

ይህ መጽሐፍ ለብዙ ነፍሳት ጣዕመ ውዳሴዋን የሚያቀምስ ስለመሆኑ አልጠራጠርም:: ስለ ነገረ ማርያም እኔም ጽፌ ነበር:: በአንተ መጽሐፍ ሳየው ዳግም አዲስ ሆነብኝ:: የሊቃውንቱን በመንፈስ እርያም ወጥተው ፡ ኢየሩሳሌም ተሻግረው ያመሰገኗትን ምስጋና አቀመስኸን::

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መልእክ

የአራቱ ጉባኤያት መምህርና በባሕር ዳር ሀገረ ስብከት የሊቃውንት ጉባኤ ኃላፊ

'የብርሃን እናት የሚለውን ቃል ከልጅነቴ ጀምሮ አውቀዋለሁ:: እጅግም እወደዋለሁ አሁን ደግሞ የበለጠ እርሱን የሚያስወድድ ነገር ገጠመኝ:: ምንድነው አትሉኝም ? የማውቀው ቃል ከማውቀው በላይ ትልቅ መጽሐፍ ሆኖ እጁ ከብዕር ፣ አእምሮው ከምስጢር በተስማማለት፡ ዘመኑን በዋጀ፣ ለዚህ ትውልድ ጥያቂ መልስ ለመስጠት በተዘጋጀ ውድ ወንድማችን በዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ ቀረበልኝ ። አነበብኩት ግን ሳልጠግበው አለቀብኝ ።

ገጹ ብዙ ነው ግን እጅግ የሚያጓጓ አቀራረብ ስላለው አይጠገብም። መጽሐፉን የሚገልጥልኝ ቃል ስላጣሁ ። ከሕዝቅኤል ይህን ቃል ተበደርኩ:: 'አፈንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጉረሰኝ። እርሱም፡- የሰው ልጅ ሆይ፡ አፍህ

ይብላ፣ በምስጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ። እኔም በላሁት፣ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ባፈጠ' ብዬ በእንክሮ ልዝጋው ። ግን ታትሞ ደግሜ ለማንበብ ቸኮልኩ። መምህራችን ሄኖክ ኃይሌ እመ ብርሃን እድሜ ትስጥህ ጥላ ከለላ ትሁንህ፡፡

መጋቤ ሐዲስ ምስጢረ ሥላሴ

የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተተረከው የእኔ የአንተና የአንቺ ጥንትና ፍጻሜ፣ መነሻና መድረሻ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ቀድሞ የተሰጠው ክብር ከዚያ ያጋጠመው ጉስቍልናና በድጋሚ ከተጠቀመበት የተሰጠው ለፈተና የማይጋለጥ፣ ውርደትና ኃፍረት የማይጎበኙት ክብር ምን እንደሚመስል በዚህ መጽሐፍ በተረዳ ነገር ቀርቧል፡፡

ይህን መጽሐፍ ሳነብ የመጽሐፉ ዋና ማጠንጠኛ የነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላተ ንባብ ላይ *'ለካስ እንዲህም ተብሎ ይተረጎማል'* እያልኩ የሄድሁበትን ከመናገር ይልቅ የተሰማኝን ስሜት ማጋራት ወደድሁ፡፡

መጽሐፉ በምድረ ፋይድ ካገኘን መከራ አልፎ የአዳምን ይልቁንም የሔዋንን ፀፀት እስከ ሲዖል ይዞን በመጓዝ የሥጋ እናታችን ሔዋን እያንዳንዳቸውን ልጆቿን በሲዖል በእንባና በሰቀቀን መቀበል ግዴታ ሆኖባት መኖሯን ያሳየናል፡፡ ከዚህ የሚልቅ ቅጣትስ ከየት ሊመጣ ይችላል? በዚያ

ሥፍራ ምን ዓይነት የድኅነት ናፍቆት፣ የመውጣት ምኞት፣ የመቢዠት ጥማት እንደ ነበር እነርሱን ሆኖ መረዳት እንኳ ባይቻል መገረሱን ያስቃኘናል፡፡

እንግዲህ የሰው ልጅ በፈጣሪው ትዕዛዝ ላይ በማመፁ የደረሰበት ውድቀትና ያገኘው ጉዳት ጠልቶ የተሰማው ሰው ከጉስቁልናው ለመታደሱ ምክንያት የሆነችው የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ነገር ይገባዋል፡፡

ያን የፀፀትና የኀዘን ጨለማ የሚያስወግደው እውነተኛው ፀሐይ የሚወጣባት ሰማይ ስትዘረጋ ከማየት በላይ ለፍጥረት ምን ደስታ ይኖራል? ለነገደ መላእክትስ ሕልፈት ውላጤ የሌለበት አማናዊው ብርሃን የሚወጣባትን አዲሲቷን ሰማይ ለማብሠር ከመመረጥ በላይ ምን ክብር ይኖራቸዋል? ለገብርኤልስ ለዘመናት የቆጠረውን መወድስ ቅኔ ለማቅረብ በንግሥቲቱ ፊት ከመቆም የሚልቅ ምን ደስታ ይገኛል?

መጽሐፉ እመቤታችን "ይኩነኒ" ብላ ፈቃዷን እስከትሰጥ በፍጥረት ዘንድ የነበረው ልብን ሰቅዞ የሚይዝ እርምጃ የተገለጠበት መንገድ ቃሉ የሰውን ልጅ በሐዲስ ተፈጥሮ ለማከበር በተደረገው አምላካዊ ጉዞ ምን ያህል ወሳኝ እንደ ነበር በጥልቅ ያስገነዝባል፡፡

ጸሐፊውም "ይህን ቃል እንደ ዋዛ ከሌሎች ቃላት ተርታ እንዳት ልጻፍ" ብለው መጨነቃቸው በዚያ ቃል የተገለጸው ፈቃድ ታላቅነትና ለሰው ልጅ ሕይወት መለወጥ የነበረውን በቍዔት ከመረዳት የመነጨ ነው፡፡ በቅድምና የነበረው አካላዊ ቃል በድንግሊቱ ጽሌ ማኅፀን እንዲቀረጽ ምክንያት

ከሆነ ቃል (ፈቃድ) በላይ ምን ኃይል ያለው ቃል ይኖራል? እንደ እኔ እይታ የመጽሐፉ ቅድስተ ቅዱሳን ይህ ርዕስ ጉዳይ ነው!!!

ሀሳቤን ከማጠቃለሌ በፊት ሁለት ነገር ማንሣት ወደድሁ:: የመጀመሪያው መጽሐፉ ስለ "ጌታ እናት" ከመጻፉ አንጻር ልለው የምፈልገው ነው:: እንደ እኔ እምነት ስለ እመ ብርሃን ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ አንድ አስገዳጅ ምክንያት መኖር ይኖርበታል:: እርሱም ለእርሷ ያለን ፍቅር ነው:: ከዚያ ውጪ ለማስመሰልም ሆነ ማንነትን ለማፀደቅ ብለን ለመናገር ብንሞክር "አነጋገርህ ይገልጥሃል" ከመባል አናመልጥም:: የበሰሉ የሙዚቃ ባለሞያዎች የ 'opera music' ን ማስመሰል አይቻልም ይላሉ:: ሕግጋቱን፣ ቅላጼውን፣ ይትበሃሉን፣ ወዘተ . . . ካላወቅህ ለዚያ ዓይነት ሙዚቃም ጥልቅ ፍቅር ከሌለህ ድምጽ መረዋ ስለሆንህ ብቻ የምትጫወተው ነገር አይደለም:: ስለ ብርሃን እናትም እንዲሁ ነው:: ስለ እርሷ ለመጻፍ የመጽሐፍ ሊቅና ደግሞ ብዕረኛ መሆን ብቻውን በቂ አይደለም:: ፍቅሯ በልብህ ውስጥ ካላደረ አይከናወንልህም::

ሌላው ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ በቤተክርስቲያን ሊቃውንት የሚጻፉ መጻሕፍት እውቀት ተኮር ከመሆናቸው ባሻገር የጸሐፊውን ስሜትና መንፈስ በጽሑፉ ውስጥ ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ የተነሣ አብዛኞቹ መጻሕፍት በእውቀት ቢያንፁንም ከተጻፈለት አካል ጋር በመንፈስ የማገናኘት ኃይላቸው ግን እምብዛም ነው:: እንደውም ምሥጢር ለለዩና የንባብ ትዕግሥትን ላዳበሩ እንጂ ወደዚያ ዐውድ ለመምጣት ለሚፈልጉ ፈታኝ ናቸው:: በቤተክርስቲያን የሚፈጸም ማንኛውም አገልግሎት ደግሞ ሰውን ለድኅነት ካላበቃ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ነው:: የሚጽፍም የሚያስተምርም ሰውን ከማቅናት ይልቅ የምሥጢር ሰው መሆኑን ለማሳየት ከሆነ

ጥቅም አይገኝበትም፡፡ ከዚህ በተለየ ቀደም ባሉት ዘመናት ከውጪ አባቶች እነ ቅዱስ ኤፍሬምና የያዕቆብ ዘሥሩግ ከሀገራችን ሊቃውንት ደግሞ እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ርቱዐ ሃይማኖት የአጻጻፍ ዘይቢ ግን ከፈጣሪያቸው፣ ከእመቤታችን ወይም ከሚጽፉለት አንድ ቅዱስ ጋር በመንፈስ የሚያደርጉት ንግግር (dialogue) እንጂ ደረቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ብቻ ስላልነበር በውስጡ ማመስጠር ብቻ ሳይሆን ነፍስን ማናሰስን እናይበት ነበር፡፡ መምህር ሄኖክ በዚህም ሆነ ከዚህ ቀደም በጻፉቸው መጻሕፍት (ሕማማት፣ ቃና ዘገሊላ . . .) ላይ የተከተሉት የአጻጻፍ ዘይቢ ይህኛው በመሆኑ ከአበው ጋር ያላቸውን የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ኅብረት እንዲሁም አንባቢውን እንደ ሰው ከብርና ውርደቱ፣ ውድቀትና ትንሣኤው እንዴት እንደ ነበር እንዲያውቅ ብቻ ሳይሆን እንዲሰማው የማድረግ ጉልበት አለው፡፡ ለሁሉ በሚረዳ ደረጃም "ምክንያተ ድኂኑ" ማን እንደሆነች በምር ያውቅ ዘንድ መጽሐፉ ተገልጦ እነሆ በፊቱ ይነበባል፡፡

ይህን መጽሐፍ ለማንበብ ባገኘሁት ዕድል ከገነት እስከ ሲዖል ከነ አዳም ጋር ተጉገር፣ በዓይናቸው አልቅሼ ትካዜያቸውን ተከፍር፣ ተስፋቸውንም ይዤ "ፈኑ እዴከ እምአርያም ወነአ አድኅነነ" በማለት ከነቢያት ጋር አማጥሁ፡፡ ከቃላት በላይ የሆነች የአሥራ አምስት ዓመት ብላቴና የሰማይ ሠራዊትን አለቃ በቀላል ተያቋ ስትፈትን አብሬ ታዘብኩ፡፡ "ይኩነኒ" በምትለዋ ቃለ ተአዝዞ አዲስ ሥርዓት ሲተከል ዘለዓለማዊ ኪዳን ሲቆም ሲወጠን አይቼ ከዚህ ቃል በቀር ምን ተስፋ ይኖረን ነበር? በሚል የደስታን ዕንባ አፈሰስሁ፡፡ ከዚያ ወደ ኋላ ይመለስ ዘንድ ለማን ይቻለዋል? እከስቷን ስትጎበኝ አብሬ ሄጄ ዝምተኛዋ ወፍ ስትዘምር ሰማሁ፣ የአረጋዊው ዮሴፍን ጽድቅም በቤቱ ተገኝቼ ተመለከትሁ፡፡ በዚያ ደሳሳ ጎጆ ሁሉ በፍቅር የሚናጠቀው

ሕጻን አለ፡፡ በዚያ ለሰው ሁሉ የተሰጠውን ወንድ ልጅ በስስት የሚመለከት፣ ሁሉን በከሃሊነቱ የሚጠብቀውንም በንቃት የሚጠብቅ የእናት ዓይን አለ፡፡ በዚያ በሁሉ ዘንድ ትሑት የሆነች ስሟ ግን ከሁሉ በላይ በልዑሉ ዘንድ የሠለጠነ ብላቴና አለች፡፡ በዚያ ከሀገሯ በስደት ለመንከራተት የተገፉት ለስዱዳን ሁሉ ግን በሰማይም ሆነ በምድር ርስት የሆነች ሀገር አለች፡፡

እነሆ ዛሬም ደግሞ እንደገና ይህ መጽሐፍ ምክንያት አድርገሽ ወደ ልቤ መጣሽ፣ የሰላምታሽንም ድምጽ ሰማሁ "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?"

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀት ከብርሃን እናት ጋር ያለንን ዝምድና በደንብ እንድናስተውል የተደረገልንንም እንድናውቅ በብዙ ለደከመ ወንድማችን መምህር ሄኖክ ያስተማሩ የሐዋርያት ማኅበር ወዳሉበት ያግባህ አኃዝ እግዚአ መዋግደ ጸጋከ እስከትል ጸጋውን ያብዛልህ፣ አሜን!

ቀሲስ ታምራት ውቤ

የነገረ መለኮት ምሩቅና የሥነ ልቡና ባለሙያ

በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረች ስትሆን መልሳ አምላኳን በሥጋ በመልኳ እና በምሳሌዋ ስለ ወለደችው ድንግል፣ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ ላለው የዓለም እረኛ ቀድሞ የድንግልናዋን ወተት ስላጠጣችው እመቤት፣ የጽድቅ ፀሐይ ክርስቶስ ስለ ወጣባት የምሥራቅ ደጅ፣ የብርሃናት አባት ስለ ፈነጠቀባት ብርሀት አዘቅት ምን እንላለን? እንደበት ሁሉ በገናንነቷ ፊት ዲዳ ይሆናል፡፡ ቀለም

ይነጥፋል፤ ብዕርም ይዶለዱማል:: ባሕር ሊቀዝፍ ገብቶ እንደ ዛለ የዋናተኛ ክንድ ጎሊና ይደከማል:: ነገር ግን ለስም አጠራሯ ምስጋና ይግባትና ስለ እርሷ በመናገር የሚገኘው በረከት እንዳይቀርብን ከበዛው እና መጠኑ ከማይታወቀው ምሥጋናዋ ጥቂት ጥቂት የሚነግሩን የታደሉ ምስክሮችን ደግሞ ትሰጠናለች:: ከእነዚህም አንዱ 'የብርሃን እናት' እነሆ!

'የብርሃን እናት' የመናገር እና ያለመናገር ፤ የመቻል እና ያለመቻልን ውጤት ነው:: ቃላት ተጠቅሞ ክብሯን በልብህ ስሌዳ እየሳለ ደስ ያሰኝሃል:: ቃላት ተጠቅሞ የድንግል ገናንነት ጎሊና ከሚደርስበት፤ ልብም ከሚወስነው በላይ መሆኑን እየነገረህ በአግራሞት ዝም ያሰኝሃል::

ቃልነት በውስጡ ቢኖርም ለመናገር እንደሚቸግረው አፍ ያልፈታ ሕፃን፤ ፍቅሯ በልባቸው ቢኖርም አውጥተው እንዳይናገሩት ግን እንደበታቸው ለሚተሳሰፍ ምዕመናን 'የብርሃን እናት' የምሥጋናዋን ፊደል ሀ...ለ እያለ የሚያስተምር እና እንደበታቸውን የሚያረታ መጽሐፍ ነው::

መጽሐፋ ቀዳሚት ሔዋን በእባብ ባደረ ሰይጣን ተታልላ ሕግ በማፍረስ ሞት ብታመጣ፤ ሳይደግስ የማይጣላ እግዚአብሔር በሁለተኛይቱ ሔዋን ድንግል ማርያም ምክንያት ሕይወትን እንደ ሰጠን ይናገራል:: እመጸኛ በሆነችው በሔዋን ጆር እባቡ መርዙን ስለረጨ ያ በጆሮዋ የገባው የኃጢአት ጽንስ ተግባር ሆኖ እድጎ ሞትን ቢያመጣ፤ ታዛዥ በሆነችው በድንግል ጆር ለራሱ ሕያው መቅደስን ይሠራ ዘንድ የገባው የእግዚአብሔር ቃል ከእርሷ ተወልዶ እርግማናችንን በማንግት እንደ ተቤዠን ይተርካል::

'የብርሃን እናት' እኛ እና እግዚአብሔርን ስለገናኘችን ታላቋ መሰላል ድንግል ማርያም በሰፊው ይተርካል፡፡ ነገር ግን ይህች መሰላል ያዕቆብካያት መሰላል ይልቅ ትበልጣለች፡፡ ያዕቆብ በቤቴል ያያት መሰላል መላእክት ይወጡና ይወርዱባት እንደ ነበር እንጂ ሰው እንደ ወጣባት አይናገርም፡፡ ድንግል ማርያም ግን ለሰው ልጆች ሁሉ ወደ ሰማይ ማረግ ድልድይ ስለሆነች እርሷ ከያዕቆብ መሰላልም ትበልጣለች፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም 'ከምድር ወደ ሰማይ ለማረግ መሰላል ሆንሽ፤ ብርሃንሽም ከፀሐይ ብርሃን ይበልጣል' – 'ኮንኪ ተንከተመ ለዕርገት ውስተ ሰማይ ብርሃንኪ የዐቢ እምብርሃነ ፀሐይ' እንዲል!

ዲያቆን አቤል ካሣሁን
ሰባኪ ወንጌልና ደራሲ

## ለመጻፍ የተነበቡ


1. Kurt Wendt (1962) ዘርዐ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ሚላድ ሐዲስ ፤ Scriptores Ethiopici, Louvain

2. Il Libro Della Luce (1964) ዘርዐ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ብርሃን ፤ Scriptores Ethiopici, Louvain

3. Enrico Cerulli, (1960) ዐሥርቱ ተስእሎታት Vatican

4. Kurt Wendt (1962) ዘርዐ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ሥላሴ ፤ Scriptores Ethiopici, Louvain

5. መጽሐፈ ምሥጢር (2001), ቅዱስ አባ ጊዮርጊስና አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፤ ደሴ

6. መጽሐፍተ ብሉያት ክልኤቱ (1999) ኦሪት ዘፍጥረት ፤ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ

7. መጋቤ ሐዲስ ፍቅረ ማርያም ባዘዘው (2010) ሃይማኖተ አበው ንባቡና ትርጓሜው ፤ አዲስ አበባ

8. ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ ፤ (2007) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፤ አዲስ አበባ

9. መጽሐፈ ቅዳሴ ፤ ንባቡና ትርጓሜው (1988) ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፤ አዲስ አበባ

10. ወንጌል ቅዱስ ፤ ንባቡና ትርጓሜው (1997) ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ

11. ድርሳነ ሚካኤል ፤ (1999) ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ

12. መዝሙራት ዘዳዊት _(1987) ፤ ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ፤ አሥመራ

13. ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (1968) ፤ መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ፤ አሥመራ

14. መልክአ ጉባዔ ልሳነ ግእዝ (1959) ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ

15. ዘይቤ ሚካኤል ዘብሔረ ሸዋ ፤ መልክአ ጉባዔ ባለ ፻፲፬ ፤ አዲስ አበባ

16. አድማሱ ጀንበሬ (2012) ፤ ኩኮሐ ሃይማኖት ፤ ዝጎራ መጻሕፍት ፤ ጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ አዲስ አበባ

17. ሄኖክ ኃይሌ (2010) ፤ ሕማማት ፤ ጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ አዲስ አበባ

18. ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው (2009) ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፤ አዲስ አበባ

19. ማኅሌተ ጽጌ (2013) ፤ አባ ጽጌ ድንግል ፤ ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት ፤ አዲስ አበባ

20. ርቱዐ ሃይማኖት (2013) ፤ መምህር ተስፉ ሚካኤል ታከለ ፤ ማኅበረ ቅዱሳን ፤ አዲስ አበባ

21. Basil the Great, Nonna Verna Harrison (2005) (trans) , On The Human Condition, Second Homily 3, St. Vladimir's Seminary Press New York

22. Gregory, and Manson A.J. (1899) The Five theological orations of Gregory of Nazianzus, Cambridge University Press .

23. Anthony M. Coniaris (1982), Introducing the Orthodox Church: Its Faith and Life , Light & Life Pub Co. Minneapolis

24. John Chrysostom (trans.)Robert Hill (1986) Homilies On Genesis 1-17,The fathers of the Church series Volume 74 Catholic University of AmericaWashington

25. Gregory of Nyssa Tran. Richard A. Norris Jr. 2012 *Homilies on the Song of Songs* , Society of Biblical Literature , Atlanta

26. Kallistos Ware (2000) The Inner Kingdom: The Collected Works, St Vladimir's Seminary Pres, New York .

27. Rachel Jones, (2021) A Brief Theology of Periods, The Good Book Company Epsom

28. Louis Ginzberg (1913) The Legends of the Jews From Creation to Jacob: From the Creation to Jacob Volume 1 Jewish

Publication Society of America, Philadelphia

29. Anthony M. Coniaris, (2011) Knowing God, Life's Highest purpose & Joy. Light & Life Pub Minneapolis

30. Boris Bobrinskoy, (1999) The Mystery of The Trinity, Trinitarian Experince and Vision in the Biblical and Patristic Tradition, SVS Press, New York

31. Panteleimon Lampadarios, (2006) Orthodox Teachings, The Catechism of The One, Holy, Catholic and Apostolic Orthodox Church, According to Holy Scriptures and Sacred Apostolic Tradition, Port Said, Egypt

32. Sabastian Brock, (1998) Hymns on Paradise, St. Ephrem the Syrian, New York

33. Mary B. Cunningham,( 2008) Wider Than Heaven, Eihgth-Century Homilies on the Mother of God, SVS Press, New York

34. Mary Hansbury, (1998) St. Jacob of Serug, On The Mother of God, SVS Press, New York

35. John Behr (2011) St. Athanasius the Great of Alexandria, On The Incarnation, SVS Press, New York

36. E.B. Pusey, (2006) The Confessions of St. Augstine, Watkins Publising, London

37. Christoher A. Beeley, (2008) Gregory of Nazianzus on the Trinity and the Knowledge of God, Oxford University Press, New York

38. Holy Apostles Convent, (1989), The Life of The Virgin Mary, The Theotokos, in the Framework of Sacred Scriptures, Holy Tradition, Patristics and Liturgical and Iconographic Traditions, Colorado

39. Kathleen E. McVey, (1989) Ephrem the Syrian, Hymns, The Classics of Western Sprituality, Paulist Press, New York

40. David Winston, (1981) Philo of Alexandria, The Classics of Western Sprituality, Paulist Press, New York

41. Robert Charles Hill, (1998) St. John Chrysostom, Commentary on the Psalms Volume 1, Holy Cross Orthodox Press, Massachusetts

42. Edward G. Mathews Jr. (2021), Jacob of Sarug's Homilies on the Six Days of Creation : The Seventh Day, Gorgias Press, USA

43. Sebastian P. Brock, (2011) Mary and Joseph, and other Dialogue Poems on Mary, Gorgias Press, USA

44. Dana Miller, (2021) Jacob of Serug's Homily on Samson, Gorgias Press, USA

45. Thomas Kollamarampil, (2010) Jacob of Serug's Homilies on the Nativity, Gorgias Press, USA

46. Chris Maunder, (2019) The Oxford Handbook of Mary, Oxford University Press, Oxford

47. Arthur A. Just Jr. (2003) Ancient Christian Commentary on Scrpture, NT II, Luck, InterVarsity Press, Illinois

48. Sebastian P. Brock, (2020), Singer of The Word of God, Ephrem the Syrian and His Significance in Late Antiquity, Gorgias Press,

USA

49. James Puthuparampil, (2012), Mariological Thought of Mar Jacob of Serugh, Gorgias Press, New Jearsy

50. Nikolas P. Vassiliads, (1997), The Mystery of Death, The Orthodox Brotherhood of Theologians, Athens Greece

51. Seraphim Rose, (2000), Genesis, Creation and Early Man, The Orthodox Christian Vision, St. Herman of Alaska Brotherhood, California

52. Jaroslav Pelikan, (1996), Mary through Centuries, Yale University Press, London

53. Luigi Gambero, (1991) Mary and Fathers of The Chuch, Ignatius Press, San Fransisco

54. Sebastian Brock, (1994), Bride of Light, St. Ephrem Ecumenical Research Institute, Kerla

55. St. Athanasius of Antioch, (2013), The Life of St. Severus of Antioch, St. Shenoda Monastery, Sydney

56. John J. Savage, (1961), St. Ambrose, Hexameron, Paradise, And Cain and Abel, The Catholic University of America Press, Washington D.C.

57. Kristen E. Kvam, (1999), Eve and Adam, Jewish, Christian and Muslim Readings on Genesis and Gender, Indiana Unversity Press, Indiana

አዳምና ሔዋን ጥፋታቸው ምንድን ነው? የአንድን ዛፍ ፍሬ መብላት የሰውን ልጅ ይኼንን ያህል ዋጋ ማስከፈል ነበረበት? እግዚአብሔርስ ከመጀመሪያው ዛፉን ለምን ፈጠረው? ከፈጠረው በኋላስ ለምን እንዳይበሉ መከልከል ፈለገ? ከሚከለክላቸው ዛፉን ለምን አያጠፋውም? ዛፉ መልካምና ክፉን የሚያሳውቅ ዛፍ ከሆነ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ክፉውንና መልካሙን እንዳያውቁ ይፈልጋል ማለት ነው?

አዳምና ሔዋን የዛፉን ፍሬ ሲበሉ ዓይናቸው ለምን ተከፈተ? የዕባብ ሃሳብ ልክ ነበረ ማለት ነው? እግዚአብሔር 'ከዛፉ ፍሬ በበላህ ቀን ትሞታለህ' ብሎ ተናግሮ እያለ በበሉበት ቀን ለምን ሁለቱም አልሞቱም? ሔዋን ያጠፋችው ጥፋቷ ምን ነበረ? አዳምስ ጥፋቱ ምንድን ነው? ሔዋን አሳሳች ተደርጋ ብዙ ትወቀሳለች። አዳምስ ንጹሕ ሰው ነበረ?

በሰው ልጅ ውድቀት ላይ እባብስ ድርሻው ምንድን ነው? በእባብ ያደረው ሰይጣንስ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ቢጣላ የሚጠቀመው ምንድን ነው? እግዚአብሔርስ ሰይጣንን ለምን ፈጠረው? ሰይጣንን ለምን ይቅር አይለውም?

አለዚያም ዓለምን ከሚረብሽ ለምን ሰይጣንን ጨርሶ አያጠፋውም? እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ሰው መሆን ለምን አስፈለገው? ሰው ሳይሆን ማዳን አይችልምን?

ISBN 978-99944-3-518-0
9 789999 435180 >

ዋጋ. 350
$ 25

ኅትመት· ጃጃው አታሚዎች
011-157-70-31/0929-17-31-32/33